ስዕላዊ መረጃ

# ለአዲስ
## ሰለምቴዎች መመሪያ

ሁሉንም የህይወት ዘርፎች የሚያካትቱ አስፈላጊ የሆኑ ሸሪዓዊ
ማብራሪያዎችና ቀለል ያሉ ህግጋት ለአዲስ ሰለምቴዎች

ፈህድ ቢንሣሊም ባህማም



NEW MUSLIM GUIDE

# ለአዲስ ሰለምቴ መመሪያ

ሁሉንም የህይወት ዘርፎች የሚያካትቱ አስፈላጊ የሆኑ ሸሪዓዊ ማብራሪያዎችና
ቀለል ያሉ ህግጋት ለአዲስ ሰለምቴዎች

ፈህድ ሣሊም ባህማም

Ⓒ **Fahd Salim Bahmmam , 1433**

***King Fahd National Library Cataloging-in-Publication Data***

Bahammam, Fahd Salim

The new muslim guide. / Fahd Salim Bahammam ; Larabi

Ben Rezzouk - Riyadh , 1433

246 p ; 16.7X23.7 cm

ISBN: 978-603-00-9103-4

(Amharc Language text)

1-Islamic preaching I-Larab Ben

Rezzouk(translator) Il-Title

210.7 dc 1433/853

**L.D. no. 1433/853**

**ISBN: 978-603-00-9103-4**

**Second Edition**

1440/2019

All rights reserved for

**Modern Guide**

For charitable printing and distribution of the book
Please contact

**Modern Guide**

Kingdom of Saudi Arabia-Riyadh
Tel: + 966112922240
Fax: + 966112922205

بسم الله الرحمن الرحيم

| | |
|---|---|
| AUTHOR | FAHD SALEM BAHAMMAM |
| TRANSLATOR | MUSTAFA HAMID YOUSSEF |
| PROJECT MANAGER | KHALED AHMED AL-AHMADI |
| EDITOR | HUSSEN KEDIR MOHAMMED<br>ABDULRAHEEM MUSA HUSSAN |
| DESIGN AND PRODUCTION | MODERN GUIDE |
| PHOTOGRAPHY | DPI STUDIO<br>ET AL. |
| PUBLISHING AND DISTRIBUTION | DAAR SAMAA' AL-KUTUB<br>PUBLISHING AND DISTRIBUTION |
| ELECTRONIC PUBLISHING | MODERN GUIDE IT |

# ያሳታሚው መቅድም

የእስልምና ሃይማኖት እጅግ በፍጥነት በመስፋፋቱ ረገድ ከሁሉም ሃይማኖቶች እንደሚበልጥ ስታትስቲካዊ መረጃዎች ሁሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ በየዕለቱ ወደ እምነቱ የሚገቡት ሰዎች ቁጥር በአግድሞሽ ከፍ እያለ ነው፡፡ እነዚህ
ሰዎች ይህን የሚያደርጉት ሐይማኖቱ በራሱ ስለሚያሳምናቸውና አዲስ የሰለሙ ሰዎችን ሕይወት ሰር ነቀል በሆነ መልኩ ሲለውጥ ስለሚመለከቱ ነው፡፡

በእርግጥ የዚህ ሁሉ ዋንኛው ምክንያት የእስልምና ሃይማኖት ዘላለማዊ የሆነ የአላህ ሃይማኖት በመሆኑ እንዲሁም ከአዕምሮ፣ ከነፍስና ከሰው አፈጣጠር ጋር ተስማምቶ የሚጓዝ ሃይማኖት በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዘመኑ ያፈራቸው የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተጠቅመው ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ወደ
ኢስላም የሚጋብዙ የተለያዩ የዳዕዋ ማዕከሎች የሚያደርጉት የተባረከና የተቀደሰ ትግልም የራሱን አስተዋፅዖ እያበረከተ
ነው፡፡

ሆኖም ግን ይህ የተባረከና የተቀደሰ የዳዕዋ ትግል አዳዲስ ሰዎች ወደ እስልምና እንዲገቡ በማድረጉ ተግባር ላይ ብቻ
ተገድቧል፡፡ የምስክርነትን ቃል በአንደበታቸው ገልፀው ወደ ኢስላም ለገቡት አዳዲስ ሰዎች እጃቸውን ይዞ በቀጥተኛው
ጎዳና ላይ እስከ መጨረሻው ሊያስጉዛቸው የሚችል ግልፅ የሆነ መንገድ፣ መዳረሻና ግብ በወጉ አያቀርብላቸውም፡፡ ወደ እስልምና የገባ አዲስ ሰው ደግሞ በሁሉም የህይወት ዘርፍ አምኖ ሊቀበለው፣ ሊማረውና ሊተገብረው የሚገባ በርካታ ነገር ከፊት ለፊቱ ይጠብቀዋል፡፡

ዳሩ ስማእ የመፅሐፍት ማዕከል የተጠቀሰውን ክፍተት ሊሞላ በሚችል መልኩ በሁሉም የዓለም ሃገራት ላይ ለሚገኙ አዲስ ሰለምቴዎች በሁሉም ዓይነት ቋንቋ ይህን የመመሪያ መፅሐፍ
ሲያቀርቡ ከፍተኛ ክብር ይሰማቸዋል፡፡ መፅሐፉ አስተማማኝ የሆነ ዕውቀትንና ብቃት ያላቸው ባለሞያዎችን መሠረት ያደረገ ልዩ ሥራ ነው፡፡




ለክቡራትና ለክቡራን አንባቢያን የምናቀርበው ይህ መፅሐፍ ዋንኛው መነሻና መሠረት ከመሆኑ በተጓዳኝ በሁሉም ሃገራት ውስጥ ለሚኖሩ አዳዲስ ሰለምቴዎች ሁሉ የአላህን
ሐይማኖት በማስተዋወቁ ረገድ አገልግሎቱን ለማዳረስ በሚል ፕሮግራሙን በኢንተርኔት፣ በማህበራዊ ድረ-ገፆች፣ በማስተማሪያ ቪዲዮዎችና በመሳሰሉት አሰራጭቷል፡፡

በንግግርና በተግባራችን ቀናዒነትን የእንዲለግሰን አላህን (ሱ.ወ.) እንጠይቃለን፡፡

አሳታሚው

# የማንዋሉ ማውጫ

## መቅድሞች




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የዚህ ዓለም ታላቅ ፀጋ | 24 |
| ይህን ፀጋ ማመስገን የሚቻለው እንዴት ነው? | 25 |
| በህይወት የመኖራችን ዓላማ፡- | 25 |
| ኢስላም ዓለም አቀፍ ሃይማኖት፡- | 26 |
| ለዚህ ነው የእስልምና ሃይማኖት የማንኛውንም ሕዝብ ባህልና ልምድ የሚያከብረው፡፡ | 26 |
| መሬት ሁሉ አላህን የማምለኪያ ቦታ ነው፡- | 26 |
| በእስልምና ሃይማኖት በጌታና በባሪያው መሃል አማላጅ የለም፡- | 27 |
| ነገርግን ኢስላም ብርሃኑን ፈነጠቀና ለሰው ልጅ ክብርን አጎናፀፈው፣ | 27 |
| የእስልምና ሃይማኖት የሙስሊም አዕምሮ ነፃ እንዲሆን አድርጓል፡፡ | 28 |
| ኢስላም የህይወት ሃይማኖት | 29 |
| ምድርን ማልማት | 29 |
| ከሰዎች ጋር መኗኗር | 29 |
| የዕውቀት ሃይማኖት | 29 |
| ኢስላማዊ ሕግጋትን ተማር | 30 |
| የሸሪዓ ሕግጋት፡- | 31 |
| አልዋጂብ (ግዴታ) - ሐራም (ክልክል) - አስሱና ወአል ሙስተሐብ (ተወዳጅ ተግባር) - የሚጠላ (ከርሃ) ነገር ማለት - የተፈቀደ (ሙባሕ) ማለት ደግሞ | 31 |
| አምስቱ የእስልምና መሠረቶች፡- | 31 |
| የሃይማኖቱን ሕግጋት እንዴት አውቃለሁ? | 33 |
| የእስልምና ሃይማኖት ዕውታዎችን በማብራራቱ ረገድ ታማኝ የሆነውን ተጨማሪ ድረ | 33 |
| እስልምና ሚዛናዊ ሃይማኖት ነው፡- | 34 |
| የእስልምና ሃይማኖት ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ያካትታል፡- | 35 |
| እስልምና ሁሉንም የህይወት ዘርፍ የሚመለከት የተሟላ መመሪያ ነው | 35 |
| እስልምና የሚለካው፥ በአንዳንድ ሙስሊሞች ተግባር ሳይሆን በሃይማኖቱ ምንነትና ምንጭ ነው፡፡ | 36 |
| አምስቱ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች፡- | 37 |
| ሃይማኖት | 37 |
| አካል | 37 |
| አዕምሮ | 38 |
| ዘር | 38 |
| ገንዘብ | 39 |

# 1 እምነትህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ሁለቱ ምስክርነቶች፤ ትርጉማቸውና ዓላማቸው | 42 |
| “ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም” የምንለው ለምንድ ነው? | 42 |
| “ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም” የሚለው ቃል ትርጉም | 42 |
| “ከአላህ በስተቀር በእውነተ የሚመለክ አምላክ የለም” የሚለው ቃል መሠረቶች | 43 |
| ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር | 44 |
| ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ማወቅ፡- | 44 |
| ልደታቸው፡- | 44 |
| ህይወታቸውና እድገታቸው፡- | 44 |
| ተልዕኳቸው፡- | 44 |
| የዳዕዋ (የሰበካ) መጀመር፡- | 44 |
| ስደት፡- | 46 |
| እስልምናን ማሰራጨት፡- | 46 |
| ህልፈታቸው፡- | 47 |
| «ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው» የሚለው ቃል ትርጉም | 48 |
| ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ.) ሁሉንም ነገር አስመልክቶ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ | 48 |
| ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያዘዟቸውን ነገሮች መተግበርና ከከለከሉት ተግባራት መታቀብም ያስፈልጋል፡፡ | 48 |
| አላህን ማምለክ የሚኖርብን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በደነገጉት መልኩ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ | 49 |
| ስድስቱ የእምነት መሠረቶች | 49 |
| በኃያሉ አላህ የማመን ትርጉም፡- | 49 |
| በአላህ መኖር ማመን፡- | 51 |
| የአላህ ፍጥረት | 51 |
| አላህ መኖሩ እጅግ ግልፅ የሆነ ነገር ነው፡ መረጃዎችን መዘርዘርም አያስፈልግም፡፡ | 51 |
| በኃያሉ አላህ ጌትነት ማመን | 52 |
| በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን የነበሩ አረብ አጋሪዎች በአላህ ጌትነት ያምኑ ነበር፡- | 54 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| በአላህ ጌትነት ማመን ቀልብን ያረጋጋል፡- | 54 |
| በነፍስ ውስጥ የሚላወሱ መሰረት የለሽ ነገሮችን መዋጋት | 55 |
| ድግምትና አስማተኝነትን መዋጋት | 55 |
| መጥቀምና መጉዳት በአላህ እጅ ነው፡፡ | 56 |
| ስውርንና የወደፊትን ከአላህ ሌላ ማንም አያውቅም፡፡ | 56 |
| ኢስላም በአዕዋፍ ገድ ማለትንና ማሟረትን እርም አድርጓል፡፡ | 56 |
| በአላህ አምላክነት ማመን | 56 |
| በአላህ አምላክነት የማመን አስፈላጊነት፡- | 57 |
| አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው? | 58 |
| በሁሉም የህይወት ዘርፍ አላህን ስለማምለክ፡- | 58 |
| አምልኮ (ዒባዳ) ሰው የተፈጠረበት ዓላማ ነው፡- | 58 |
| የአምልኮ (ዒባዳ) መሠረቶት | 59 |
| የአምልኮ ቅድመ ሁኔታዎች፡- | 59 |
| የመጀመሪያው አምልኮን ያለ ምንም ተጋሪ ለአላህ ብቻ ማዋል ሲሆን | 59 |
| ሌላው ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከአከናወኑት የአምልኮ ተግባር ጋር የሚጣጣምና የሚስማማ መሆን ይኖርበታል፡፡ | 59 |
| ሺርክ (የአምልኮ ተግባርን ከአላህ ዉጪ) ላለ አካል ማጋራት | 60 |
| ታላቁ ሺርክ፡- | 60 |
| ትንሹ ሺርክ፡- | 60 |
| ከሰው መፈለግና ሰውን አንዳንድ ነገር መጠየቅ የሺርክ ተግባር ነውን? | 61 |
| በአላህ ስሞችና ባህሪያት ማመን፡- | 63 |
| ከአላህ ስሞች ውስጥ የተወሰኑት፡- | 64 |
| በአላህ ስሞችና ባህሪያት የማመን ፍሬዎች፡- | 64 |
| ከፍ ያሉ የእምነት ደረጃዎች፡- | 65 |
| አላህን የማመን ፍሬዎች፡- | 65 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| በመላእክት ማመን | 66 |
| በመላእክት የማመን ትርጓሜ | 66 |
| በመላእክት ማመን ምንን ያካትታል? | 66 |
| በመላእክት የማመን ፍሬ ወይም ጥቅም:: | 67 |
| በመጽሕፍት ማመን | 68 |
| በመጽሐፍት የማመን ትርጓሜ | 68 |
| በመጽሃፍት ማመን ምንን ያካትታል? | 68 |
| የቁርኣን ልዩ መገለጫዎች | 68 |
| ቁርኣንን አስመልክቶ ያለብን ግዴታ ምንድን ነው? | 70 |
| በቀደምት መጽሐፍት ውስጥ ስላለ ነገር ሊኖረን የሚገባ አቋም ምንድን ነው? | 71 |
| በመጽሐፍት የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ | 72 |
| በመልዕክተኞች ማመን | 73 |
| የሰው ልጅ መለኮታዊ መልዕክት ያስፈል ገዋል:: | 73 |
| በመልዕክተኞች ማመን ከኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ነው:: | 73 |
| በመልዕክተኞች የማመን ትርጓሜ | 74 |
| በመልዕክተኞች ማመን ምንን ያካትታል? | 74 |
| የመልዕክተኞች መገለጫ | 75 |
| የመልዕክተኞች ምልክቶችና ታዓምራታቸው | 76 |
| በዒሳ(ዐ.ሰ) ዙሪያ ያለው የሙስሊም እምነት | 76 |
| እርሱ ዒሳ(ዐ.ሰ) ከታላላቅ መልዕክተኞች አንዱና ስብዕናው እጅግ የላቀ ነው:: | 76 |
| ነብዩላህ ዒሳ(ዐ.ሰ) የኣደም ዝርያ ሰው ነው:: | 76 |
| እሱ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው:: | 76 |
| በርሱ በዒሳ(ዐ.ሰ) እና በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መሐከል የተላከ መልዕክተኛ የለም:: | 76 |
| አላህ (ሱ.ወ) በእርሱ እጅ እንዲፈፀሙ ባደረጋቸው ታዓምራት እናምናለን:: | 76 |
| ዒሳ(ዐ.ሰ) የአላህ ባሪያና መልክተኛ ነው ብሎ እስከ ሚያምን ድረስ የአንድም ሰው ኢማን የተሟላ ሊሆን አይችልም:: | 76 |
| አላህ (ሱ.ወ) አይሁዶች ዒሳን(ዐ.ሰ) ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ወደ ሰማይ ከፍ አደረገውና አሳረገው እንጂ እሱ አልተገደለም አልተሰቀለምም:: | 77 |
| በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነብይነትና መል ዕክተኝነት ማመን | 78 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ልዩ ይዘት | 78 |
| የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት የቀደምት መል ዕክቶችን መልዕክት የሚቋጭ መሆኑ:: | 78 |
| የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ቀደምት መልዕ ክቶችን የተካ መሆኑ:: | 78 |
| የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልክት ሁለቱንም ፍጡሮች ማለትም ኢጋንንትንም ሰውንም የሚመለ ከት መሆኑ:: | 78 |
| በመልዕክተኞች የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ | 79 |
| በመጨረሻው ቀን ማመን | 80 |
| በመጨረሻው ቀን የማመን ትርጓሜ | 80 |
| ቁርኣን በመጨረሻው ቀን በማመን ላይ ትኩረት ያደረገው ለምንድን ነው? | 80 |
| በመጨረሻው ቀን ማመን ምንን ያካትታል? | 81 |
| በመቀስቀስና በመሰብሰብ ማመን | 81 |
| በምርመራና በሚዛን ማመን | 81 |
| ጀነትና እሳት | 82 |
| የቀብር ስቃይና ድሎቱ | 82 |
| በመጨረሻው ቀን የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ | 83 |
| በአላህ ውሳኔ (በቀደር) ማመን | 84 |
| በአላህ ውሳኔ የማመን ትርጓሜ | 84 |
| በአላህ ውሳኔ ማመን ምንን ያካትታል? | 84 |
| የሰው ልጅ ምርጫ፣ ችሎታና ፍላጎት አለው:: | 84 |
| በአላህ ውሳኔ ማመካኘት | 86 |
| በአላህ ውሳኔ የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ | 87 |

# 2 ንፅህናህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የንጽህና ትርጉም | 90 |
| ለሠላት አስፈላጊ የሆነው መፀዳዳት እንዴት ዓይነት ነው? | 90 |
| ከነጃሳ(ግልፅ ቆሻሻ) መጥራት | 91 |
| ነገሮች መሰረታቸው የተፈቀደና ንጹህ ነው:: | 91 |
| ነጃሳ ነገሮች | 91 |
| ከነጃሳ መጽዳት | 91 |
| የኢስቲንጃእ(ሀፍረተ ገላንና አካባቢውን ማጠብ) እና የመጸዳዳት ስርዓት | 92 |
| ሐደስ(ምናባዊ ቆሻሻ) | 93 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ትንሹ ሐደስና ውዱ | 93 |
| ውዱእ የማደርገው እንዴት ነው? | 94 |
| ትልቁ ሐደስ(ምናባዊ ቆሻሻ) እና ትጥበቱ | 96 |
| ትጥበትን ግድ የሚያደርጉ ነገሮች | 96 |
| አንድ ሙስሊም ከጀናባ ወይም ከትልቁ ሐደስ የሚጠራው እንዴት ነው? | 97 |
| በካልሲ ላይ ማበስ | 97 |
| ውሃን መጠቀም ያቃተው ወይም ያልቻለ ሰው | 97 |


# 3 ሠላትህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ሠላት | 100 |
| የሠላት መሰረታዊ ትርጉሙ | 100 |
| የሠላት ደረጃና ትሩፋት | 100 |
| የሠላት ትሩፋት | 101 |
| ሠላት ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው? | 101 |
| ለሠላት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? | 102 |
| ከሐደስና ከነጃሳ መጥራት:: | 102 |
| ሀፍረተ ገላን መሸፈን | 102 |
| ለሴት - ለሕፃን - ወንድ | 102 |
| ወደ ቂብላ መቅጣጨት ወይም መዞር | 103 |
| የሠላት ወቅት መግባት | 103 |
| አምስቱ የግዴታ ሠላቶችና ወቅቶቻቸው | 104 |
| የሠላት ቦታ (ሰፍራ) | 105 |
| የሠላት ገጽታ | 107 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ማሰብ (ኒያ) | 107 |
| ለሠላት እንደቆመ አላሁ አክበር (አላህ ትልቅ ነው::) ይላል:: | 107 |
| የመክፈቺያ ዱዓ ቢል የተወደደ ነው:: | 107 |
| የፋቲሓን ምዕራፍ ያነባል:: | 108 |
| ፋቲሐን፣ የሠላት ውስጥ ውዳሴዎችንና ሙገሳዎችን በቃሉ ያልያዘ ወይም ያልሸመደደ ሰው ምን ማድረግ አለበት? | 108 |
| የፋቲሓ ትርጓሜ በሚከተለው መልኩ | 109 |
| በመዳፎቹ ጉልበቶቹን በመያዝ ወደ ቂብላ እንደተቅጣጨ ከወገቡ ጎንበስ በማለት ሩኩዕ ያደርጋል፤ | 110 |
| በማስከተል፣ በሰባት የሰውነት ክፍሎቹ መሬት ላይ በመደፋት ሱጁድ ያደርጋል:: | 111 |
| ከዚህ በኋላ በመጨረሻው ረከዓ፣ በመጨረሻም ወደ ቀኙ በመዞር | 113 |
| የምሰግደው እንዴት ነው? | 114 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የሠላት ማዕዘናት ግዴታዎች | 118 |
| የሠላት ውስጥ ሱናዎች | 118 |
| ሱጁደ ሰህው | 118 |
| ሠላትን የሚያበላሹ ነገሮች | 119 |
| በሠላት ውስጥ የተጠሉ ነገሮች፡፡ | 119 |
| የተወደዱ ሠላቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው? | 120 |
| በፈቃደኝነት የሚሰገዱ ሠላቶች የሚከለከሉበት ወቅት፡ | 121 |
| ሠላተል ጀማዓ (በሕብረት መስገድ) | 122 |
| የመከተል ትርጉም፡ | 122 |
| ለኢማምነት የሚቀደመው ማን ነው? | 122 |
| ኢማሙና ተከታዮቹ የሙቆሙት የት ነው? | 122 |
| ኢማም ተከትሎ ሲሰግድ ያመለጠውን ሠላት እንዴት ይሞላዋል? | 123 |
| ረከዓ በምን ትገኛለች? | 123 |
| አዛን | 124 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የአዛንና የኢቃም መገለጫ | 124 |
| ሙኣዚኑን ተከትሎ መድገም | 125 |
| በሠላት ውስጥ መመሰጥ | 126 |
| በሠላት ውስጥ ለመመሰጥ የሚረዱ መንገዶች | 126 |
| የጁምዓ ሠላት | 128 |
| የጁምዓ ዕለት ትሩፋት | 128 |
| ጁምዓ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው? | 128 |
| የጁምዓ ሠላት አፈፃፀምና ድንጋጌዎች | 130 |
| ከጁምዓ ለመቅረት የሚፈቀድለት ማን ነው? | 130 |
| በስራና ሃላፊነት ላይ ለመገኘት ሲባል ከጁምዓ መቅረት እንደ ህጋዊ ምክንያት ይታያልን? | 130 |
| ስራ፣ ከጁምዓ ሠላት ለመቅረት ህጋዊ ምክንያት የሚሆነው ምን ጊዜ ነው? | 130 |
| የመንገደኛ ሰላት | 131 |
| የታማሚ ሰው ሰላት | 131 |


# 4 ጾምህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የረመዳን ጾም | 134 |
| የጾም ትርጉም | 134 |
| የረመዳን ወር | 134 |
| የረመዳን ወር በላጭነት | 134 |
| የጾም ሚስጥር | 135 |
| የጾም ትሩፋት | 135 |
| ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች | 136 |
| ሙብላትና መጠጣት | 136 |
| ለህመምተኛ የሚሰጥ ደም፡፡ | 136 |
| የፍቶት ጠብታ ቢፈስም ባይፈስም፣ በፍላጎትና በምርጫ በመተሻሸት | 136 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| አውቆ ማስታወክ፡፡ | 136 |
| የወር አበባና የወሊድ ደም መፍሰስ፡፡ | 136 |
| አላህ እንዳይጾሙ ፍቃድ የሰጣቸው ሰዎች | 137 |
| በመጾሙ የሚጎዳ ታማሚ | 137 |
| በሽምግልና ወይም ይድናል ተብሎ በማይከጀል በሽታ ምክንያት መጾም የማይችል ደካማ ማፍጠር ይፈቀድለታል፡፡ | 137 |
| ተጓዥ መንገደኛ በጉዞው ላይ እያለ ከአራት ቀን ለማ ይበልጥ ጊዜ ሲያርፍ ማፍጠር ይችላል፡፡ | 137 |
| የወር አበባና የወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች፡፡ | 137 |
| እርጉዝና አጥቢ፡፡ | 137 |
| በረመዳን ጾሙን ያበላሸ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው? | 138 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የውዱዓታ ጾም | 138 |
| የዐሹራን ቀንና ከርሱ በፊት ወይም በኋላ ያለው ቀን፡፡ | 138 |
| የዐረፋ ቀን፡ | 138 |
| ስድስቱ የሸዋል ቀኖች፡ | 138 |
| የተባረከው የጾም ፍቺ በዓል | 139 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| በኢስላማዊው ሕግ የተደነገጉና በዒዱ ዕለት የሚከናወኑ ነገሮች እንዴት ያሉት ናቸው? | 140 |
| የበዓል ሠላት (የዒድ ሠላት)፡ | 140 |
| የጾም ፍች ምጽዋት(ዘካተል ፊጥር)፡ | 140 |
| በተፈቀዱ መንገዶች ሁሉ በመጠቀም፣ በተቻለ መጠን፣ | 141 |
| በኢድ ዋዜማ ሌሊቱን፣ እንዲሁም ወደ ዒድ ሠላት ሲወጣ፣ | 141 |


# 5 ምጽዋትህ (ዘካህ)




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የምጽዋት ዓላማዎች | 144 |
| ምጽዋት ሊወጣለት ግዴታ የሚሆን ንብረት የትኛው ነው? | 145 |
| ለጌጥነትና ለውበት የማይለበስ የሆነ ወርቅና ብር | 145 |
| ተቀማጭ ገንዘብና የተለያዩ የመገበያያ ኖቶች እንደ | 145 |
| ለንግድ የቀረቡ ዕቃዎች | 146 |
| ከምድር የሚበቅሉ፡ አዝመራ፣ ፍራፍሬዎችና የእህል አይነቶች | 146 |
| እንደ ላም፣ ግመልና ፍየል ያሉ የእንሰሳት ሃብት፡ ባለሃብቱ፣ | 146 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ምጽዋት የሚሰጠው ለነማን ነው? | 147 |
| ዘካ የሚገባቸው ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡ | 147 |
| የእንሰሳት ሃብት ዘካ | 148 |
| የእንሰሳት ዘካ ጥቅላዊ መስፈርቶች | 148 |
| የጋማ ከብቶች የዘካ አወጣጥ | 149 |
| ግመል | 149 |
| ከብት | 150 |
| በግና ፍየል | 150 |
| የአዝርዕትና የጥራጥሬዎች ዘካ | 151 |
| ግዴታ የሚሆነው የዘካ መጠን | 151 |


# 6 ሐጅህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የመካ እና የመስጂዱል ሐራም ትሩፋት | 154 |
| የሐጅ ትርጉም | 156 |
| የሐጅ ወቅት | 156 |
| ሐጅ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው? | 156 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| አንድ ሙስሊም ሐጅ ማድረግ የመቻል መገለጫዎች፡ | 157 |
| አንዲት ሴት ሐጅ ለማድረግ መሕረም (የቅርብ ተጠሪዋ) አብሯት መኖሩ መስፈርት ነው፡፡ | 158 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የሐጅ ትሩፋቶች | 158 |
| የሐጅ ዓላማዎች | 159 |
| ዑምራ | 160 |
| የተባረከው የእርድ በዓል | 161 |
| በእርዱ ቀን(የውመ ነሕር) የሚሠሩ ሥራዎች | 161 |
| እርድ(ኡዱሒያ)፡ | 161 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ለእርድ የሚቀርበው እንሰሳ ማሟላት ያለበት መስፈርት | 161 |
| የበዓል እርዱ ምን ይደርጋል? | 162 |
| የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ከተማ (መዲናን) መጎብኘት | 163 |
| በመዲና ውስጥ ሊጎበኙ የሚገቡ ነገሮች ማናቸው? | 163 |


# 7 የንግድ ግንኙነትህ





| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| አላህ (ሱ.ወ) በምድራዊ የሕይወት ቆይታ ሲሳይን ለመፈለግ መልፋትን ደንግጓል፡ አበረታቷል፡፡ | 168 |
| በማበራዊ ግንኙነትና በመጠቃቀሚያ ነገሮች ዙሪያ ያለው መሰረታዊ መመሪያ | 168 |
| በቀጥታ በራሱ እርም የተደረገ፡ | 168 |
| የሚከተሉት ኢስላም በቀጥታ አካላቸውን እርም ያደረጋቸው ነገሮች ናቸው፡፡ | 168 |
| ከተገኙበት ምንጭ አንጻር እርም የተደረጉ ነገሮች | 169 |
| ወለድ | 169 |
| የእዳ ወለድ | 169 |
| የብድር ወለድ | 169 |
| የወለድ ፍርድ | 170 |
| የወለድ ቅጣት | 170 |
| ወለድ በማህበረሰብና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት | 170 |
| በሀብት መከፋፈል ተግባር ላይ በሀብታሞችና በድሆች መካካል ልዩነትን ይፈጥራል | 170 |
| ገንዘብን አለመቆጠብና የአባካኝነት ልማድ | 170 |
| ወለድ፣ ባለ ሃብቶች ሀገርን በሚጠቅም ነገር ላይ እንዳይሳተፉ የሚከለክል እንቅፋት ነው፡፡ | 171 |
| ወለድ የገንዘብ በረከት እንዲወገድ፣ የኢኮኖሚ ውድቀት እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ | 171 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| አንድ ሰው ቀደም ሲል በወለድ የሚገለገል የነበረ ቢሆንና ኢስላምን ቢቀበል፣ የሚሰጠው ብይን ወይም ፍርድ ምንድን ነው? | 171 |
| ሰውን ማታለልና አለማወቅ | 171 |
| ማታለልና ግልጽ አልባነት ያለበት ሽያጭ ምሳሌ | 172 |
| የአንድ እቃ ምንነት አለመታወቅ በግብይቱ ውስጥ ታሳቢነት የሚያገኘው መቼ ነው? | 172 |
| በደልና የሰዎችን ገንዘብ አላግባብ መውሰድ | 173 |
| ማስገደድ፡ | 173 |
| የሰዎችን ገንዘብ በሐሰት ለመብላት ማታለልና ማጭበርበር፡ | 173 |
| የሰዎችን ገንዘብ ያለ አግባብና በግፍ ለመውሰድ በሕግና ደንብ መቀለድ፡ | 173 |
| ጉቦ፡ | 174 |
| በካሃዲነቱ ዘመን ያለ አግባብ ገንዘብ ይወስድ የነበር ሰው ኢስላምን ሲቀበል ፍርዱ ምንድነው? | 174 |
| ቁማር | 174 |
| ቁማር ማለት ምንድን ነው? | 174 |
| የቁማር ሸሪዓዊ ፍርድ፡ | 174 |
| ቁማር በማህበረሰብና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች፡ | 175 |

| ማውጫ | ገጽ |
| --- | --- |
| በሰዎች መካከል ጠብንና ጥላቻን ይፈጥራል፡፡ | 175 |
| ቁማር ገንዘብ የሚያሟጥጥ፣ ሃብትንም የሚያከስም ነው፡፡ | 175 |
| ቁማርን የሚያዘወትር ሰው በሱሱ ይጠመዳል፡፡ | 175 |
| የቁማር ዓይነቶች | 175 |
| ኢስላም፣ ልዩ ትኩረት የቸራቸው በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ ስነምግባሮች | 176 |
| ታማኝነት፡ | 176 |
| እውነተኝነት | 177 |
| ሥራን፣ኃላፊነትን በጥራትና በብቃት መወጣት | 177 |


# 8 ምግብህና መጠጥህ




| ማውጫ | ገጽ |
| --- | --- |
| በምግብና መጠጥ ዙሪያ ያሉ መሰረታዊ መመሪያዎች | 180 |
| አዝርዕቶችና ፍሬዎች | 180 |
| አስካሪ መጠጥና አልኮል | 181 |
| አዕምሮን መጠበቅ | 181 |
| የኸምር ፍርድ | 181 |
| አደንዛዥ እጽ | 182 |
| የባሕር ምግቦች | 182 |
| የየብስ እንሰሳት | 183 |
| የሚፈቀዱ እንሰሳት የትኞቹ ናቸው? | 183 |
| ከእንሰሳት መካከል ስጋቸውን መብላት የተከለከሉ | 183 |
| ኢስላማዊ አስተራረድ | 184 |
| የስጋ ዓይነቶች በምግብ ቤትና በልኳንዳዎች የሚገኝ ስጋ | 184 |
| ሸሪዓዊው አደን | 185 |
| ለአደን መስፈርቶች አሉት፡፡ | 185 |
| የመብላትና የመጠጣት ስርዓት | 186 |


# 9 ልብስህ




| ማውጫ | ገጽ |
| --- | --- |
| ልብስ በኢስላም | 190 |
| ልብስ ብዙ ጉዳዮች ይፈጸሙበታል፡ | 190 |
| የሙስሊም አለባበስና የተፈቀዱ መቆነጃጃዎች | 191 |
| የተከለከሉ አልባሳት | 191 |
| ሀፍረተ ገላን የሚያጋልጥ | 191 |
| በሁለቱ ጾታዎች መሐል መመሳሰልን የሚፈጥር | 192 |
| ከካሃዲያን ልዩ መገለጫ ጋር የሚመሳሰለል ልብስ | 192 |
| ኩራትና መኮፈስን የሚያንጸባርቅ አለባበስ | 192 |
| ሐርነት ወይም ወርቅነት ያለው ከሆነ ለወንዶች የተከለከለ ነው፡፡ | 195 |
| ማባከንና ማዝረክረክ ያለበት፡ | 195 |

# 10 ቤተሰብህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ቤተሰብ በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ | 196 |
| ኢስላም በጋብቻ ጅማሬና በቤተሰብ ምስረታ ላይ ልዩ እይታ አለው፡፡ | 196 |
| ኢስላም ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ወንድም ሆነ ሴት ልዩ ክብር ሰጥቷል፡፡ | 196 |
| ኢስላም ለአባቶችና ለእናቶች ክብር በመስ ጠትና ደረጃቸውን በመጠበቅ፣ እንዲሁም እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ድረስ እነርሱን መንከባከብና ትዕዛዛቸውን መፈፀምን አስመ ልክቶ ልዩ ትኩረት ቸሯል፡፡ | 196 |
| ኢስላም የወንድም ሆነ የሴት ልጆችን መብት እንድንጠብቅ አዟል፡፡ | 197 |
| ኢስላም በአንድ ሙስሊም ላይ ዘመድናን የመቀጠል ግዴታ ጥሎበታል፡፡ | 197 |
| ሴት በኢስላም ውስጥ ያላት ስፍራ | 197 |
| ከሴት ልጅ ክብር ጋር ተያያዥነት ካላቸው ኢስላማዊ ድንጋጌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ | 197 |
| ኢስላም ልዩ ትኩረት እንዲቸራቸው ያደረ ጋቸው ሴቶች | 198 |
| እናት | 198 |
| ሴት ልጅ | 198 |
| ሚስት | 198 |
| በሁለቱ ፆታዎች መካከል ሽኩቻ የሚፈጥር ነገር የለም፡፡ | 198 |
| ከወንድ አንጻር ሴቶች ያላቸው ስፍራ | 198 |
| ሴቷ ለወንዱ ሚስት መሆኗ | 198 |
| የቅርብ ዘመዱ (መሕረም) ከሆነች | 199 |
| ሴቷ ለርሱ ባዕድ ከሆነች | 201 |
| በወንድና በባዕድ ሴት መካከል የሚኖር ግንኙ ነት ስርዓት | 201 |
| ዓይንን መስበር | 201 |
| በስርዓትና በመልካም ስነምግባር አብሮ መኖር | 201 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የኸልዋ (ለብቻ መነጠል) እርምነት | 202 |
| አል ሒጃብ (የሴቶች ኢስላማዊ አለባበስ) | 202 |
| የሂጃብ ይዘት | 202 |
| የሒጃብ ስርዓተ ደንብ | 202 |
| ጋብቻ በኢስላም | 203 |
| ኢስላም ለሚስትነት ያስቀመጣቸው መስፈ ርቶች፡ | 203 |
| ኢስላም ለባልነት ያስቀመጣቸው መስፈር ቶች፡ | 203 |
| የባልና የሚስት መብቶች | 204 |
| የሚስት መብቶች | 204 |
| ቀለብና መጠለያ | 204 |
| መልካም አኗኗር ወይም ግንኙነት | 204 |
| መቻቻል | 205 |
| አብሮ ማደር ወይም መተኛት | 205 |
| ክብርህና ሞገስህ ስለሆነች ልትከላከላት ይገባል፡፡ | 206 |
| የሚስትን ሚስጥር አለማባከን | 206 |
| በሴት ላይ ድንበር ማለፍ አይፈቀድም | 206 |
| ማስተማርና መምከር | 206 |
| ሚስቱ ያስገባችውን ቃል መጠበቅ | 206 |
| የባል መብቶች | 207 |
| በመልካም ነገር ላይ እሱን የመታዘዝ ግዴታ አለባት | 207 |
| ባሏ እንዲረካባት መዘገጃጀት ወይም መመቻቸት | 207 |
| ባል ወደቤቱ እንዲገቡ የማይፈልጋቸውን ሰዎች እን ዲገቡ አለመፍቀድ | 207 |
| በባል ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ከቤት አለመውጣት | 207 |
| ሚስት ባሏን መንከባከብ | 207 |
| ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት | 208 |
| እንደውም ሴቶች እንዳይበደሉና እንዳይ ገፉ የሚያደርጉ መብታቸውን የሚያስከብሩ የሆኑ ቅድመ መስፈርቶችንና በደልን ከልካይ ነጥቦችን አስቀምጧል፡፡ | 208 |
| ፍትሃዊነት | 208 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የሚስቶችን ወጪ መሸፈን መቻል | 208 |
| ከአራት ሚስቶች በላይ አለመጨመር | 208 |
| ቤተሰባዊ ግንኙነትን ለመጠበቅና ዝምድናን ላለማበላሸት አንዳንድ ሴቶችን በአንድነት በአንድ ጊዜ ማግባትም አይፈቀድም:: | 208 |
| ፍቺ | 209 |
| ኢስላም የጋብቻ ውል ዘላቂና ዘውታሪ መሆን እንዳለበት ይመክራል:: | 209 |
| ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ለመውጣት ሲባል ፍቺ የተፈቀደው ለዚህ ነው:: | 209 |
| ፍቺ እራሱን የቻለ ስርዓት አለው: | 209 |
| የወላጆች መብት | 210 |
| ለወላጆች በጎ መዋል ከመልካም ስራዎች መካከል ከባዱና አላህ ዘንድ ብዙ ምንዳን ከሚያስገኙ ተግባሮች ሲሆን፣ | 210 |
| በወላጆች ላይ የማመፅና ለነርሱ ክፉ የመሆን አደገኝነት | 210 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| በአላህ ላይ ከማመፅ ውጭ ባለ ጉዳይ እነርሱን መታዘዝ | 210 |
| ለነርሱ በጎ መዋል በተለይም ሲሸመግሉ | 210 |
| ከሃዲያን ወላጆች | 210 |
| የልጆች መብት | 211 |
| ጥሩ እናት ልትሆን የምትችል መልካም ሚስት ለጋብቻ | 211 |
| ስም ከነርሱ የማይለይ የሆነ መገለጫቸው በመሆኑ፣ | 211 |
| በመልካም ስነ ምግባር አንጸ ማሳደግ፣ መሰረታዊ የሃማኖት ጉዳዮችን ማስተማርና ሃይማኖታቸውን እንዲወዱ ማድረግ:: | 211 |
| ወጪ | 211 |
| ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በሁሉም ልጆች መካከል ፍትሃዊ መሆን:: | 211 |


# 11 ስነ-ምግባርህ በኢስላም




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ስነ-ምግባር በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ | 214 |
| ስነ-ምግባር፣ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰው ዘር ከተላኩበት ዓላማዎች መካከል ዋነኛው ነው:: | 214 |
| ስነ-ምግባር ዋነኛ የእምነት ክፍል ነው | 214 |
| ስነ-ምግባር ከእያንዳንዱ የአምልኮ ዘርፍ ጋር የተሳሰረና የተቆራኘ ነው | 214 |
| አላህ (ሱ.ወ) ለጥሩ ስነ-ምግባር ያዘጋጀው የላቀ ደረጃና ከባድ ምንዳ | 215 |
| በኢስላም ውስጥ የስነ ምግባር ልዩ መገለጫዎች | 216 |
| የላቀ ስነ-ምግባርን ማሳየት በሰው ልጅ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም:: | 216 |
| ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር የሚኖር ስነምግባር | 216 |

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| የላቁ ስነ ምግባሮች በሰዎች ብቻ የተገደቡ አይደሉም:: | 217 |
| ስነ ምግባር ከእንስሳት ጋር | 217 |
| ስነ ምግባርና የአካባቢ ጥበቃ | 217 |
| መልካም ስነ ምግባር በሕይወት ዘርፎች ሁሉ | 218 |
| በቤተሰብ ውስጥ: | 218 |
| በንግድ ውስጥ: | 218 |
| በሥራ ውስጥ: | 219 |
| በጦርነት ላይ ያለው የኢስላም ስነ ምግባራዊ መመሪያ | 219 |
| ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ታሪክ ስነ ምግባራዊ አስተምህሮት መካከል: | 220 |

# 12 አዲሱ ሕይወትህ




| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| አንድ ሰው ወደ ኢስላም እንዴት ሊገባ ይችላል? | 226 |
| አንድ ሰው ሁለቱን የእምነት የምስክርነት ቃል ትርጉማቸውን አውቆ፣ | 226 |
| አዲስ ሙስሊም ገላውን ይታጠባል | 226 |
| ንሠሐ | 227 |
| የትክክለኛ ንሠሐ መስፈርት ምንድነው? | 227 |
| ወንጀሉን ማቆም | 227 |
| ላሳለፈው ወንጀል መጸጸትና መቆጨት | 227 |
| ዳግም ወደ ወንጀሉ ላለመለስ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ | 227 |
| ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዱ እርምጃ ዎች፡ | 227 |
| ከንሠሐ በኋላስ? | 228 |
| የኢማን ጣዕም ወይም ጥፍጥና | 228 |
| ወደ ቀጥተኛው ጎዳና የመመራትንና የንሠ ሐን ጸጋ ማመስገን | 229 |
| ሃይማኖትን አጥብቆ መያዝና ለሚያጋ ጥሙ ችግሮች ታጋሽ መሆን | 229 |
| በጥበብና በመልካም ግሳፄ ወደ ኢስላም በመጣራት ላይ መታገል | 229 |
| ወደ ኢስላም መጣራት | 230 |
| ወደ አላህ መጣራት ያለው ትሩፋት | 230 |
| ወደ አላህ መጣራት በቅርቢቱ ዓለምም ሆነ በወ ዲያኛው ዓለም የመዳኛና የስኬት መንገድ ነው፡፡ | 230 |
| የአንድ ወደ ኢስላም ጥሪ አድራጊ ሰው ንግግር አላህ ዘንድ በላጭና ተወዳጅ ነው፡፡ | 230 |
| ጥሪ ማድረግ(ዳዕዋ)፣ የአላህን ትዕዛዝ መፈፀምም ነው፡፡ | 230 |
| ወደ አላህ መጣራት የመልክተኞች ሁሉ፣ በተለይ የነቢያችን የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባር ነው፡፡ | 230 |
| ጥሪ ማድረግ ወይም ዳዕዋ የማይዘጋ የመልካም ነገር በር ነው፡፡ | 230 |
| የአንድ ዳዒ ምንዳ ከዱንያና በውስጧ ካሉ መጣቀ ሚያ ነገሮች ሁሉ የተሻለና የበለጠ ነው፡፡ | 230 |
| የትክክለኛ ዳዕዋ(ጥሪ) መገለጫዎች | 231 |
| መረጃና ዕውቀት | 231 |
| በዳዕዋ ውስጥ ብልሃትን መጠቀም | 231 |
| ቤተሰብን መጣራት | 232 |
| አካባቢህና ቤተሰብህ | 233 |
| ወደ ኢስላም ከተገባ በኋላ ያው ቤተሰባዊ ሕይወት | 233 |
| ባልና ሚስት በአንድነት ከሰለሙ | 233 |
| እርሱ ሰልሞ ሚስቱ ባትሰልም የሚኖረው ድንጋጌስ ምንድነው? | 234 |
| የመጽሐፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ የሆኑች ሚስት | 234 |
| የመጽሐፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ ያልሆ ነች ሚስት | 234 |
| የተፈታች ሴት ዒዳ (ፍች የሚፀናበት ጊዜ) | 235 |
| የጋብቻ ውል ፈፅሞ፣ ይዟት ያልገባት- ግብረ ስጋ ግንኙነት አብሯት ያልፈፀመ- | 235 |
| የእርጉዝ ሴት ዒዳ | 235 |
| እርጉዝ ያልሆነችና የወር አበባ የምታይ ሴት ዒዳዋ ከተፈታች | 235 |
| ያልደረሰች ሕፃን በመሆኗ | 235 |
| ሴቷ ሰልማ ባሏ ባይሰልም ፍርዱ ምንድን ነው? | 237 |
| የሕፃናት መስለም | 238 |
| ከሰለሙ በኋላ ስም መቀየር የተወደደ ተግባር ነውን? | 240 |
| በሚከተሉት ሁኔታዎች ስምን መቀየር ግዴታ ይሆናል፡ | 240 |
| ተፈጥሯዊ ፈለጎች | 242 |
| ግርዛት | 242 |
| ኢስቲሕዳድ | 242 |
| ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር | 242 |
| ጺምን ማሳደግ | 243 |
| ጥፍርን ማስተካከል | 243 |
| የብብትን ጸጉር መንጨት | 243 |

## *የመፅሐፉ መቅድም*

ከጨለማ ወደ ብርሃን በመውጣት፣ ቀጥተኛ የሆነውን መንገድ በመምራት እንዲሁም ታላቅ ሃይማኖት የሆነውን እስልምና በማስያዝ አላህ (ሱ.ወ.) ፀጋውን ስላጎናፀፈህና ዕድለኛ ስላደረገህ እንኳን ደስ ያለህ!

ምክንያታዊ በሆነው ጀግንነት እውነትን ስትፈልግ የዚህ ታላቅ ሃይማኖት አባል ለመሆን በህይወትህ ውስጥ ትልቅ ውሣኔ ላይ በመድረስህ በድጋሚ እንኳን ደስ አለህ!

የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ የገዛ አንድ ሰው አሊያም ደግሞ የአንድ ቡድን ወይም ተቋም አባል የሆነ ሰው የመሣሪያውን አጠቃቀም መመሪያ ለማወቅ ወይም አባል የሆነበትን ተቋም መተዳደሪያ ደንብ ለመረዳት መጓጓቱ አይቀርም፡፡ ሙብትና ግዴታው ምን እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል፡፡

ይህ እንዲህ ከሆነ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን በማውጣት፣ ቀጥተኛ መንገድ ወደ ሆነው ኢስላም በመምራት አላህ (ሱ.ወ) ፀጋውን ያጎናፀፈው ሰው ደግሞ ከላይኛው እጅግ በበለጠ ስለ ሃይማኖቱ ለማወቅ መጓጓቱ አይቀርም፡፡ አላህን (ሱ.ወ.) በዕውቀት ላይ ተመስርቶ ለማምለክ ስለ ሃይማኖቱ ህግጋት ለማወቅ ይተጋል፡፡ በዙሪያው ከሚከሰቱት ተለዋዋጭ ነገሮች ጋር ሸሪዓውን መነሻ ባደረገ መልኩ ለመኗኗር የእስልምና ሃይማኖትን ለመረዳት ይጥራል፡፡

ስለ እስልምና በመማርህ የምትቸረውን ነቢያዊ የምስራች ልንገርህ፡፡ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የምታገኛቸው መረጃዎች ከነቢያትና ከመልእክተኞች የተወረሱ ሐብቶች ናቸው፡፡ እርግጥነው፤ ከነቢያት ገንዘብም ሆነ ቁሳቁስ አይወረስም፡፡ ከነቢያት የሚወረሰው የሃይማኖት ትምህርት ነው፡፡ ይህን ትምህርት የቀሰመ ሰው የታላቅ ዕድል ባለቤት ሆኗል፡፡ የነቢያት ውርስ የሆነን ትልቅ በረከት ተችሯል፡፡ (አቡ-ዳውድ፥88)

ይህ በስዕል የተደገፈው መመሪያ፥ መፅሐፍ አዲስ ለሰለምከው ወገን፥ ለሰዎች የተቸረ ፀጋ ስለሆነው ስለታላቁ ሃይማኖት እስልምና መግቢያና የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ዕውቀት ያስጨብጥሃል፡፡ ዘወትር በምትኗኗረውና አስፈላጊ በሆኑ የህይወት ጉዳዮችም ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

ለተለያዩ ጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጥሃል፡፡ በዙሪያህ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዴት መኗኗር እንዳለብህም ግልፅና ቀለል ባለ አኳኋን ያብራራልሃል፡፡ መፅሐፉ የሚያቀርብልህ መረጃዎች ውሱን፣ የሰነድ ማስረጃ ያላቸው ሲሆኑ መሠረታቸውም ቁርዓንና የነብዩ /ሰ.ዐ.ወ./ ሐዲሶች ናቸው፡፡

ይህ መፅሐፍ ዝርዝር የሆኑ ማብራሪያዎችን በማቅረቡ ረገድ ለንባብ ቀላል በሆነ አኳኋን ከመዘጋጀቱ ጎን ለጎን አንዳንድ በዕለቱ የሚገጥሙህ የህይወት ጉዳዮች ሸሪዓዊ ብይናቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለግህም በቂ የሆነ ማመሳከሪያ እንዲሆን ተደርጎም ተዘጋጅቷል፡፡

ተጨማሪ የሆነው ፀጋና መቀናትን እንዲያጎናፅፍህ አላህን እንማፀነዋለን፡፡ ቀልብህን በርሱ ትዕዛዝና ሀይማኖት ላይ እንዲያፀናው እንዲሁም የትም ሆነህ ብሩክ እንዲያደርግህ እንለምነዋለን፡፡ ሁላችንንም የክብር ቤቱ በሆነው ጀነት ከነቢያትና ከፃድቃኖች ጋር ያደርገን... አሚን!



አዘጋጁ



# መቅድሞች



## የመቅድሞች ማውጫ


የዚህ ዓለም ታላቅ ፀጋ

በህይወት የመኖራችን ዓላማ

ኢሥላም ዓለም አቀፍ ሃይማኖት

በጌታና በባሪያው መሀል አማላጅ የለም

ኢስላመ የህይወት ሃይማኖት

የእስልምናን ሕግጋት ተማር

የሸሪዓ ሕግጋት

ሃይማኖታዊ ሕግጋትን እንዴት አውቃለሁ?

ኢስላም ፍትሀዊ ሃይማኖት ነው

ሃይማኖት ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ያካትታል

ሥለ እስልምና በትክክል ማወቅ የምንችለው ሃይማኖቱን በመመር
መር እንጂ ሙስሊሞችን በማየት አይደለም

አምስቱ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች

# > የዚህ ዓለም ታላቅ ፀጋ

ኃያሉ አላህ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፀጋዎችን ለሰው ዘር አጎናፅፏል፡፡ ሁላችንም እነዚህን የአላህ ፀጋና ትሩፋቶች ከማጣጣም ለአፍታም ተቆጥበን አናውቅም፡፡

ከጎደሎ ባህሪያት የጠራው ጌታ ብዙዎች ያጡትን የማየትና የመስማት ታላቅ ፀጋን ችሮናል፡፡ አዕምሮን፣ ጤናን፣ ገንዘብን፣ ቤተሰብን ያለክፍያ ሰጥቶናል፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ ፍጥረተ-ዓለሙ ሁሉ እኛን ያገለግል ዘንድ ገርቶናል፡፡ ፀሐዩ፣ ሰማዩ፣ መሬቱ፣ ፍጥረታቱ ሁሉ የእኛ አገልጋይ ተደርገዋል፡፡ «የአላህንም ፀጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋትም፤ አላህ በእርግጥ መሐሪ አዛኝ ነውና፡፡» /አል-ነሕ፡18/

ይህም ሆኖ አጭሩ የዕድሜ ገደባችን ሲጠናቀቅ እነዚህ ፀጋዎችም አብረው ያከትማሉ፡፡

በዚህ ዓለም /ዱንያ/ ላይ ደስታና ዕርካታን አጎናፅፎ እስከቀጣዩ ዓለም /አኼራ/ ድረስ የሚሸጋገር አንድና ብቸኛ ፀጋ ግን አለ፡፡ እርሱም ወደ ኢስላም ጎዳና የመመራት ፀጋ ነው፡፡ ይህ አላህ ለባሮቹ ያጎናፀፈው ታላቅ ፀጋ ነው፡፡

ይህ በመሆኑም ነው፥ አላህ ከሌሎች ፀጋዎች አስበልጦ ይህንን ፀጋ ወደ ራሱ ያስጠጋው፡፡ እንዲህ ይለናል «... ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤»/አል-ማኢዳህ፡3/

አንድን ሰው ከጨለማዎች ወደ ብርሃን በማውጣትና እርሱ ወደ ወደደው ሃይማኖት ከመምራት የበለጠ ታላቅ ፀጋ አላህ ለሰው ልጅ አጎናፅፎዋልን?! አላህ ለሰው ይህን ፀጋ የቸረው፥ በህይወት የተገኘበት ዋንኛ ዓላማ የሆነውን አላህን የመገዛት ተልዕኮ በአግባቡ ያሳካ ዘንድ ነው፡፡ ሰው ይህን በማድረጉ በዚህ ዓለም ላይ ደስታን ሲያገኝ በቀጣዩ ዓለም ደግሞ የማይቋረጥ ምንዳ ይጠብቀዋል፡፡

አላህ ከሰዎች ሁሉ የበለጥን ምርጥ ህዝቦች እንድንሆን አድርጎ በመምረጥ፥ ሰላም በነርሱ ላይ ይሁንና የነቢያትና የመልእክተኞች ሁሉ ጥሪ የሆነውን «ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም» የሚለውን ኃይለ-ቃል እንድናነግብ ማድረጉ ለእኛ ታላቅ ፀጋ ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ፀጋና በረከትስ ይኖራል?



> ኢስላም የዚህ ዓለም ታላቅ ፀጋ

አንዳንድ አላዋቂ ሰዎች ሙስሊም የሆኑት በፍፁም ፈቃዳቸው ብቻ እንደሆነ አድርገው በመቁጠር በነቢዩ ሙሐመድ /ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን/ ላይ አጉል ለመመፃደቅ ሲዳዳቸው፥ አላህ ተችቷቸዋል፡፡ ወደዚህ ሃይማኖት ጎዳና መመራት የሚቻለው በርሱ ፀጋ ብቻ መሆኑን ገልፆላቸዋል፡፡ እንዲህ ይላል አላህ ...«መስለማቸው በአንተ ላይ ይመጻደቃሉ፤ በእስልምናችሁ በኔ ላይ አትመጻደቁ፤ ይልቁንም አላህ ወደ እምነት ስለመራችሁ ይመጻደቅባችኋል፤ እውነተኞች ብትኾኑ (መመጻደቅ ለአላህ ነው) በላቸው፡፡» (አል-ሐሹራት፡17)

በእርግጥ የኃያሉ አላህ ፀጋዎች ብዙ ናቸው፡፡ እንደዚህም ሆኖ በስም ጠቅሶ ያወሳውና ለእኛ እንዳጎናፀፈን የነገረን አንድና ብቸኛ ፀጋ ወደ ኢስላም ጎዳና መመራት፣ እርሱን መገዛትና አንድነቱን በተግባር ማረጋገጥ ነው፡፡

ይህ ፀጋ ከእኛው ጋር ቋሚና ዘውታሪ ሆኖ እንዲቆይ፥ ምስጋና ያስፈልገዋል፡፡ አላህም እንዲህ ብሏል... «ጌታችሁም ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ፥ በትክዱም /እቀጣችኋለሁ/፤ ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና በማለት ባስታወቀ ጊዜ /አስታውሱ/፡፡»(ኢብራሂም፡7)

ይህን ፀጋ ማመስገን የሚቻለው እንዴት ነው?

ማመስገን የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው፡-

1. በሃይማኖት ላይ በመፅናትና በርሱ ምክንያት ችግር ሲገጥም በመታገስ (ገጽ፣ 229 ተመልከት)

2. ጥበብና ትዕግስት በተሞላው አኳኋን እስልምናን በማስተዋወቅና ወደርሱ በመጣራት ነው፡፡ (ገጽ፣ 230 ተመልከት)

## > በህይወት የመኖራችን ዓላማ፡-

ለምን በህይወት ተገኘን? የመኖር ግቡ ምንድነው? የሚሉትን እጅግ ወሳኝ የሆኑ የዘላለም ጥያቄዎችን በመመለሱ ረገድ ብዙ አሳቢያንና ተመራማሪዎች ተመሳሳይ በሆነ አኳኋን ሲደናገሩ ኖረዋል፡፡

ለምን ተፈጠርን?

ብሕይወት የመኖራችን አላማስ ምንድን ነው?

የተከበረው ቁርዓን የሰውን በህይወት የመኖር ዓላማና ግብ በግልፅና ቁልጭ ባለ አኳኋን አስፍሮታል፡፡ ቁርዓን እንዲህ ይላል ...«ጋኔንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡» (አል-ዛሪያት 56)

በዚህ ምድር ላይ በህይወት የመኖራችን ግንባር ቀደሙ ዓላማ አላህን መግገዛት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ያሉት ነገር ይህንን የሚከተሉና የሚያሟሉ ነገሮች ናቸው፡፡

ነገር ግን አላህን መግገዛት /ዒባዳ/ ማለት በኢስላም ግንዛቤ መሠረት ባህታዊ መሆንና ከዓለማዊ ህይወት ራስን መነጠል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ከሶላት፣ ከፆምና ከዘካ ጎን ለጎን የሚካሄዱ ሥራ፣ ንግግር፣ ፈጠራ፣ የርስ በርስ ግንኙነትና የመሳሰሉት ሌሎች ዓለማዊ ተግባራት ሁሉ ዓላማን /ኒያን/ አስካስተካከሉ ድረስ ዒባዳ /አምልኮ/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እንዲያውም ከዚህም አልፎ ለዓለማዊ ነገሮች መጫወትና መደሰት ጥሩ በሆነ ዓላማና ለመልካም «ኒያ» እስከሆነ ድረስ ከዒባዳ ተግባራት ተርታ ይመደባል፡፡

ለዚህ ነው ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ./ «በህጋዊ መንገድ የሚካሄድ ተራክቦ ምፅዋት ነው፡፡» ያሉት ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ./ ለማለት የፈለጉት ከባለቤታችሁ ጋር የምታደርጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይቀር ምንዳ የሚያስገኝ ዒባዳ ነው፡፡

ዒባዳ /አምልኮ/ በህይወት የመኖር ግብ ከመሆኑ ጋር፥ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ከተከናወነ ሙሉ ህይወት ይሆናል፡፡ ሙስሊም በየህይወት እርከኑ የሚያከናውናቸው ተግባራት በሙሉ ዒባዳ ይሆናሉ፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ...«ስግደቴ መገዛቴም፥ ሕይወቴም፥ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል፡፡» /አል-አንዓም፡162/

## > ኢስላም ዓለም አቀፍ ሃይማኖት፡-

የእስልምና ሃይማኖት የተደነገገው፥ በተለያየ ባህል፣ ዘር፣ ልምድና ሃገር ውስጥ ለሚኖሩ ሁሉም ዓይነት ሕዝቦች ዕዝነትና የህይወት ጎዳና ይሆን ዘንድ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል...«(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም» (አል-አንቢያ፡107)

ለዚህ ነው የእስልምና ሃይማኖት የማንኛውንም ሕዝብ ባህልና ልምድ የሚያከብረው፡፡ የእስልምናን መሠረታዊ ህግጋት የማይጥስ እስከሆነ ድረስ አዲስ ሰለምቴዎች የነበሩበትን ባህልና ልምድ እንዲተው አይገደዱም፡፡

እስልምናን በግልፅ የሚቃረን ልምድና ባህል ከሆነ ግን፥ ከሀይማኖቱ ጋር ተስማሚ በሆነ ባህል መቀጠሩ ግድ ይላል፡፡ ከጉድለታት የጠራው ኃያሉ አላህ አንድን ነገር የሚከለክለውም ሆነ የሚያዘው ጥልቅና ውስጥ ዐዋቂነቱን መነሻ አድርጎ ነው፡፡ ለአላህ ህግጋት ተገዥ መሆናችን፥ በርሱ የማመናችን መገለጫ ነው፡፡

እዚህ ጋር አንድ ማሳሰብ የሚኖርብን ነገር ይኖራል፡፡ ይኸውም አንድ አዲስ ሰለምቴ የሆነ ሰው፥ ከእስልምና እና ከሕግጋቶቹ ጋር አንዳችም ግንኙነት የሌላቸው ባሕላዊ ልምዶችን አንዳንድ ሙስሊሞች ሲያከናውኑ አይቶ ይህንኑ ለመተግበር መፈለጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ይህ መሰሉ ተግባር ሃይማኖት ሳይሆን በልምድ የተያዘና የተፈቀደ የየዕለት ባህል መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል፡፡

መሬት ሁሉ አላህን የማምለኪያ ቦታ ነው፡-

በኢስላም አተያይ የትኛውም የመሬት ክፍል ለመኖርም ሆነ አላህን ለማምለክ የተፈቀደና ምቹ ነው፡፡ ሙስሊሞች ተሰደው ይኖሩበት ዘንድ ግዴታ የተጣለባቸው ውሱን የሆነ ሃገርም ሆነ ቦታ የለም፡፡ ዒባዳ ለማድረግ እስከቻሉ ድረስ በየትኛውም ሃገር መኖር ይችላሉ፡፡

አንድ ሙስሊም ዒባዳ እንዳያደርግ የሚከለክለው ኃይል እስካልገጠመው ድረስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይሰደድ ዘንድ አይገደድም፡፡ አላህን ከማምለክ የሚያግደው ከአቅም በላይ የሆነ ሐይል ካጋጠመው ግን ዒባዳ ማድረግ ወደ ሚችልበት ሌላ ቦታ መሰደድ ይኖርበታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል...«እናንተ ያመናችሁ ባሮች ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ) እኔንም ብቻ ተገዙኝ፡፡» (አል-ዐንከቡት፡56)



## > በእስልምና ሃይማኖት በጌታና በባሪያው መሃል አማላጅ የለም፡-

ብዙ ሃይማኖቶች ለአንዳንድ ግለሰቦች ከሌላው ሰው በተለየ መልኩ ሃይማኖታዊ መለያዎችን ችረዋል፡፡ የሰዎች የአምልኮ ጥንካሬም ሆነ የእምነት ደረጃ የሚለካው በእነዚህ ግለሰቦች ፈላጭ ቆራጭነት እንዲሆን አድርገዋል፡፡

እነዚህ ግለሰቦች በእነዚህ ሃይማኖቶች መሠረት በሰውና በአምላክ መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር የሚያደርጉ አገናኝ ድልድዮች መሆናቸው ነው፡፡ ምህረት የሚለግሱትም እነርሱ ናቸው፡፡ የሩቅ ምስጢር (ገይብ) አዋቂ እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ይህ እነርሱን ግልፅ ኪሳራ ላይ የጣላቸው የሃቅ ተቃራኒ የሆነና የሐሰት ጥሪያቸው ነው፡፡

ነገርግን ኢስላም ብርሃኑን ፈነጠቀና ለሰው ልጅ ክብርን አጎናፀፈው፣ ከፍ ያለ ደረጃም ሰጠው፡፡ የሰው ደስታ፣ ንስሐም ሆነ አምልኮ መወሰን ያለበት የፈለገውን ያህል ክብርና ደረጃ ይኑራቸው በጥቂት ግለሰቦች ፈቃደኝነት ላይ ነው የሚለውን ከንቱ አስተሳሰብ ውድቅ አደረገው፡፡

የአንድ ሙስሊም የአምልኮ ተግባር የሚወሰነው በርሱና በአላህ መካከል ብቻ ነው፡፡ ሌላ በመሃከል ሆና የሚያገናኝ አማላጅ ግለሰብ አያስፈልግም፡፡ አላህ ለባሪያው ቅርብ የሆነ ጌታ ነው፡፡ የባሪያውን ጥሪ ሰምቶ ምላሽ መስጠት ይችላል፡፡ አምልኮውን፣ ሶላቱን በመመልከትም ምንዳ ይሰጠዋል፡፡




> በእስልምና ሃይማኖት በጌታና በባሪያው መሃል አማላጅ የለም፡-

ማንኛውም የሰው ዘር ምህረት የመቸርም ሆነ ንሰሀ የመቀበል መብትም ሆነ ሥልጣን የለውም፡፡ አንድ የአላህ ባሪያ የሆነ ግለሰብ ለአላህ ፍፁም ቅን ሆኖ ንሰሃ እስከገባ ድረስ፥ አላህ ንሰሀውን ይቀበለዋል ምህረትም ይለግሰዋል፡፡ ማንም ግለሰብ በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ ተፅዕኖ የማሳደር መለኮታዊ ኃይል የለውም፡፡ ነገራት ሁሉ የሚከናወኑት በአላህ እጅ ነው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት የሙስሊም አዕምሮ ነፃ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በጥልቅ እንዲያዝና እንዲመራመር ጥሪ አቅርቦለታል፡፡ በአንድ ጉዳይ ሲወዘገብም በቁርዓንና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተረጋገጠ ንግግርና ተግባር እንዲዳኝ አዞታል፡፡

ከአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በስተቀር ለማንኛውም ሰው በሚናገረው ንግግር ሁሉ ሰዎች ለርሱ ፍፁም ታዛዦች እንዲሆኑለት የሚያድረግ ስልጣን የለውም፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ግን ከአላህ በሆነ ወህይ (በራዕይ) እንዝ ካልሆነ ከራሳቸው አፍልቀው የሚናገሩት አንዳችም ነገር ስለሌለ እርሳቸውን ያለምንም ማወላዳት መታዘዙ ተገቢ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ...«ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡ እርሱ (ንግግሩ) የሚወረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡» (አል-ነጅም፡3-4)

አላህ በዚህ ሃይማኖት አማካኝነት ምን ያህል ታላቅ ፀጋ እንዳጎናፀፈን እናስተውል! ሃይማኖቱ ከአፈጣጠራችን ጋር ተስማሚ ነው፡፡ የሰውን ክቡርነት ይጠብቃል፡፡ ሰው ራሱን በራሱ ብቻ የሚገዛና ከአላህ ውጪ የማንም ተገዢና ባሪያ እንዳይሆን ነፃ ያወጣል፡፡



# > ኢስላም የህይወት ሃይማኖት

የእስልምና ሃይማኖት የዚህን ዓለም (ዱንያ) ህይወትና የቀጣዩን ዓለም (አኼራ) ህይወት አመዛዝኖ ጎን ለጎን የሚያስኬድ ሃይማኖት ነው፡፡ ዱንያ ዘር የመዝሪያ ዓለም ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የዘራውን ለማጨድ፥ በሁሉም የህይወት ዘርፍ መልካም የተባሉ ነገሮችን ሁሉ የሚተክለው በዚህ የዱንያ ዓለም ውስጥ ነው፡፡

ይህንን ተክልና ዘር አግባብነት ባለው መልኩ ለመዝራትና ለመትከል፥ ህይወትን በቆራጥ ውሳኔና በፅናት ማስተናገድን ይጠይቃል፡፡ ይህ ሁኔታ እንደሚከተለው ሊገለፅ ይችላል፡፡

## ምድርን ማልማት

አላህ እንዲህ ይላል «... እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፤ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡» (ሁድ፡61)

አላህ የዚህ ምድር ነዋሪዎች እንሆን ዘንድ ፈጥሮናል፡፡ እንድናለማት፣ አንድናሳድጋትና እንድናበለፅጋትም አዞናል፡፡ ገር የሆነውን ኢስላማዊ ሸሪዓ በማይቃረን መልኩ ለሰው ልጅ ግልጋሎት ትውል ዘንድ መገንባት እንዳለብንም አዞናል፡፡

ሌላው ቀርቶ ከባድ ሁኔታ ባጋጠመህ ወቅት እንኳ ምድርን ማልማትና ማሳደግ የአምልኮ ተግባር (ዒባዳ) እንደፈፀምክ ይቆጠርልሃል፡፡


ለዚህ ነው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)፥ አንድ ሰው ችግኝ ለመትከል በእጁ ይዞ ሳለ ቂያማ ብትቆም እንኳ፥ እስከ ቻለ ድረስ ሰደቃ ይሆንለት ዘንድ የያዛትን ችግኝ ይትከላት በማለት ያስገነዘቡት፡፡ (አል-ሙስነድ፡ 2712)

## ከሰዎች ጋር መኗኗር

የእስልምና ሃይማኖት ምድርን በመገንባቱና በማበልፀጉ ረገድ ከሰዎች ጋር እንድንተጋገዝ የበረታታናል፡፡ የየሰው ባህልና ሃይማኖት የተለያየ ቢሆንም መልካም ሥነ-ምግባርና ሰናይ የሆነ ግብረ-ገብነትን በመላበስ ተቀላቅለን እንድንኗኗርና እንድንተባበር ሃይማኖቱ ያዘናል፡፡

ከህብረተሰቡ ተነጥሎ መኖርና መገለል፥ የከሀዲዎችና የለውጥ አራማጆች መንገድ አለመሆኑንም ያስገነዝበናል፡፡

ይህ በመሆኑ ነበር የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሰዎች ጋር አብረው ይኖሩ የነበረውና የሚያደርሱባቸውን ሁከትና ማዋከብም በፀጋ እንዲሁም በትዕግስት ያስተናግዱ የነበረው እንዲህ አይነቱ ሰው ከሚነጠለውና ከሚገለለው ሰው የተሻለ ነውም ይሉ ነበር፡፡ (ኢብን ማጃህ፡ 4032)



> ኢስላም እንደ ሌሎች ሃይማኖቶች በሃይማኖትና በእውቀት መካከል የሚደረግን ጦርነት አያውቅም

### የዕውቀት ሃይማኖት

በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ የወረደው የመጀመሪያው የአላህ ቃል «አንብብ!» የሚለው መሆኑ እንዲሁ እንደዘበት የተከሰተ ክስተት አይደለም፡፡ ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ የዕውቀት ዘርፎች ሁሉ በእስልምና ሃይማኖት የተበረታቱ ናቸው፡፡

ሌላው ቀርቶ አንድ ሙስሊም ዕውቀት ለመቅሰም ሲንቀሳቀስ ወደ ጀነት በሚያደርሰው ጎዳና ላይ እየተጓዘ መሆኑን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ተናግረዋል፡፡ እንዲህ ብለዋል...«እውቀት በሚያስገበይ ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው በዚህ ጥረቱ አላህ ወደ ጀነት የሚያደርሰውን ጎዳና ገር ያደርግለታል፡፡» (ኢብን ሒባን ፡ 84)

ሌሎች ሃይማኖቶች እንደሚያስቡት የእስላም ሃይማኖት በዕውቀትና በሃይማኖት መካከል ግጭት አለ ብሎ አያምንም፡፡ ይልቁንም ከዚህ በተቃራኒው ሃይማኖት ዕውቀትን ማፈላለጊያ ብርሃን ነው ብሎ ያምናል፡፡ ለሰው ልጅ እስከጠቀመ ድረስ ማወቅና ማሳወቅ ተገቢ ተግባር መሆኑን እስልምና ያስገነዝባል፡፡

እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት፥ ለሰዎች መልካም ነገርን የሚያስተምር አዋቂና አስተማሪ ደረጃው እጅግ ከፍ ያለና የተከበረ መሆኑን ይናገራል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ፍጥረታት በጠቅላላ ለሰዎች መልካምን ነገር ለሚያስተምር ግለሰብ እንደሚፀልዩ (ዱዓእ) እንደሚየደርጉ ተናግረዋል፡፡ (ቲርሚዚ ፡ 2685)

## > ኢስላማዊ ሕግጋትን ተማር

አንድ ሙስሊም በሁሉም የህይወት ዘርፍ ዙሪያ ያሉ ኢስላማዊ ሕግጋትን ለማወቅ መጓጓት ይኖርበታል፡፡ የአምልኮ፣ የየዕለት ውሎና ግንኙነት ሥርዓቶችን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ካደረገ የዒባዳ ተግባሩን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ የሚያከናውን ይሆናል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል «አላህ መልካም ነገር ላሰበለት ሰው የሃይማኖት ግንዛቤን ይሰጠዋል፡፡» (አል- ቡኻሪ፡71 ሙስሊም፡1037)

በተለይ ግዴታ የሆኑ እንደ ሰላትና ንፅህና አጠባበቅ (ጠሃራ) የመሳሰሉ ህግጋትን መማር አለበት፡፡ የተከለከሉ የምግብ ዓይነቶችን ማወቅም ይኖርበታል፡፡ ግዴታ ያልሆኑ ሆነው ሃይማኖቱ የሚያበረታታቸው አንዳንድ ነጥቦችን ማወቁም ተገቢ ነው፡፡



> አላህ መልካም ነገር የሻለት ሰው በዲን ላይ ያሳውቀዋል።

## > የሸሪዓ ሕግጋት፡-

በሸሪዓ ሕግጋት መሠረት የአንድ ሰው ንግግርም ሆነ ተግባር ከአምስት ማዕቀፎች ሊወጣ አይችልም፡፡

| | |
|---|---|
| አልዋጂብ (ግዴታ) | የግዴታ ተግባር ማለት አላህ ያዘዘው፣ ተግባሪው ምንዳ የሚያገኝበትና ከመተግበር የታቀበው ደግሞ የሚቀጣበት ተግባር ማለት ነው፡፡ አምስቱ ሶላቶችና የረመዷን ፆምን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ |
| ሐራም (ክልክል) | ክልክል ተግባር ማለት አላህ የከለከለው፣ ከመተግበር የታቀበው ምንዳ የሚያገኝበትና የተገበረው ደግሞ የሚቀጣበት ተግባር ማለት ነው፡፡ ዝሙትና አስካሪ መጠጥን በምሳሌነት ማውሳት ይቻላል፡፡ |
| አስሱና ወአል ሙስተሐብ (ተወዳጅ ተግባር) | ይህ ደግሞ ይተገበር ዘንድ ኢስላም ያበረታታው፣ ተግባሪው ምንዳ የሚያገኝበትና ከመተግበር የታቀበው ደግሞ የማይቀጣበት ተግባር ማለት ነው፡፡ ሰዎች ጥሩ የሆነን ፈገግታ ማሳየት፣ ቀድሞ ሰላምታ ማቅረብና ከመንገድ ላይ ቆሻሻን ማስወገድ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ |
| የሚጠላ (ከርሃ) ነገር ማለት | የእስልምና ሃይማኖት እንዳይደረግ ያበረታታው ተግባር ማለት ሲሆን ይህን ተግባር ከማድረግ በመቆጠብ ምንዳ የሚገኝ ሲሆን መተግበሩ ግን ለቅጣት አይዳርግም፡፡ በሶላት ውስጥ ጣትን እያነቃነቁ መጫወት ከዚህ የተጠላ «መክሩህ» ተግባር ውሰጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ |
| የተፈቀደ (ሙባሕ) ማለት ደግሞ | መተግበሩም ሆነ መቆጠቡ፥ ከልካይና አዛዥ ከሆነ የህግ (ሸሪዓ) መርህ ጋር ግንኙነት የሌለው ክንውን ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ መሠረታዊ በሆነ መልኩ መብላት፣ መጠጣት፣ መናገር ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ |



# > አምስቱ የእስልምና መሠረቶች፡-

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ «እስልምና በአምስት ነገሮች ላይ ተገንብቷል፡፡ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፣ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር፣ ሰላትን መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ሐጅ ማድረግና ረመዷንን መፆም ናቸው፡፡» (አል-ቡኻሪ፡ 8 ሙስሊም፡16)

እነዚህ አምስቱ መሠረቶች ሃይማኖቱ የተገነባባቸው ዋና ዋና ምሰሶዎች ናቸው፡፡ በሚቀጥሉት ክፍሎች ዝርዝር ሕግና ስርዓታቸውን እናብራራለን፡፡

ከዚህ ለጥቆ ደግሞ ሰላት ይከተላል፡፡ ሰላት ከአምልኮዎች (ኢባዳት) ሁሉ የተከበረውና ታላቁ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡፡ «ሶላት (የሃይማኖቱ) ምሰሶ ነው፡፡» (ቲርሚዚ፥2749)

መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ለማለት የፈለጉት ፥ የእስልምና ሃይማኖት ቀጥ ብሎ ሊቆምና ሊገነባ የሚችለው በሶላት ነው፡፡ ያለ ሶላት ሃይማኖቱን መገንባት አይቻልም ነው፡፡

ሶላት ጤናማና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ንፅህና (ጠሃራ) ነው፡፡ ስለዚህ «ከእምነትህ» ቀጥሎ «ንፅህናን» ከዚያም «ሶላትህ» ይከተላል፡፡

| የእስልምና መሠረቶች | |
|---|---|
| 1 | ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር |
| 2 | ሶላትን መስገድ |
| 3 | ዘካን መስጠት |
| 4 | ረመዷንን መፆም |
| 5 | ሐጅ ማድረግ |

1



ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር

2



ሶላትን መስገድ

3



ዘካን መስጠት

4



ረመዷንን መፆም

5



ሐጅ ማድረግ

## > የሃይማኖቱን ሕግጋት እንዴት አውቃለሁ?

አንድ ሰው ህመም ካጋጠመውና ይህን ህመሙን የሚያሽር መፍትሄ ከፈለገ፥ በዘርፉ ብቃት ያላቸው የህክምና ባለሞያዎች ማፈላለጉ የማይቀር ነው፡፡ ህይወቱ እጅግ ውድ ዋጋ ያላት በመሆኗ ሐኪሙ ያዘዘለትን መድሃኒት በታዘዘው መሠረት በአግባቡ ከመውሰድ እንደማይዘናጋ እሙን ነው፡፡

ሃይማኖት ደግሞ ለሰው ከምንም በላይ ውድ ነገር ነው፡፡ ሃይማኖቱን ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ የማያውቀውን ነገር ለመረዳትም ታማኝ የሆኑ የዕውቀት ባለቤቶችን ጠይቆ መረዳት ይኖርበታል፡፡

ይህን መፅሐፍ ማንበብህ ስለ ሃይማኖትህ በትክክል በማወቁ ረገድ እርምጃዎችን እንድትጀምር ያደርግሃል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል«...የማታውቁ ብትሆኑ የዕውቀት ባለቤቶችን ጠይቁ፡፡» (አል-ነሕል፡43)

ይህን መጽሐፍ ከማንበብ ባሻገርም ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድም ይኖርብሃል፡፡ አንዳንድ ከበድ ያሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙህ በአካባቢህ ያሉ መሳጂዶችና ኢስላማዊ ማዕከሎች ጎራ በማለት ጠይቀህ መረዳት ይኖርብሃል፡፡ ተከታዩን ድረ-ገፅ በመጎብኘትም መረጃዎችን ማግኘት ትችላለህ፡፡

www.islamicfinder.org

የእስልምና ሃይማኖት ዕውታዎችን በማብራራቱ ረገድ ታማኝ የሆነውን ተጨማሪ ድረ-ገፅ መጎብኘትም ይኖርብሃል፡፡

www.newmuslimguide.com

www.guide-muslim.com



> አዲስ ሰለምቴ የሆነ ሙስሊም ግለሰብ በአቅራቢያው ከሚገኙ ኢስላማዊ ማዕከላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የተለያዩ ታማኝ መፅሐፍትን ማገላበጥና ድረ-ገፆችን መጎብኘት ይጠበቅበታል፡፡

## > እስልምና ሚዛናዊ ሃይማኖት ነው፡-

እስልምና ከመጠን በላይ አለማክረርና አለማካበድን እንዲሁም ከደረጃ በታች አለመውረድና አለመለስለስን መለያው አድርጎ የተደነገገ ሃይማኖት ነው፡፡ ይህ መለያው በሁሉም ሃይማኖታዊና አምልኮአዊ መርሆቹ ውስጥ ጎልቶ ይንፀባረቃል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ለመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ለሰሀቦችም ሆነ ለምእመናን ሚዛናዊ ይሆኑ ዘንድ በማስገንዘብ አስረግጦ ነግሯቸዋል፡፡ ይህም በሁለት መንገዶች ሊገለፅ ይችላል፡-

1. በሃይማኖት ጎዳና ላይ በመፅናትና በልብ ውስጥ ለአላህ ሕግጋቶች ከፍተኛ ቦታ በመስጠትና፡፡
2. ከአክራሪነት፣ ከድንበር አላፊነትና ከጠርዘኝነት በመከልከል ናቸው፡፡

ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል፡፡ «እንደታዘዝከውም ቀጥ በል፤ ከአንተ ጋር ያመኑትም (ቀጥ ይበሉ)፤ ወሰንንም አትለፉ፤ እርሱ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና፡፡»(ሁድ፡112)

ጌታችን በዚህ አንቀፅ ለማለት የፈለገው በእውነት ላይ በመፅናት ብዙም ሳታካብዱና አላስፈላጊ ነገሮችን በመጨማመር ድንበር አላፊ ሳትሆን ለዚሁ እየታገልክ ኑር ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በአንድ ወቅት የእምነት ባልደረባቸውን (ሰሀባቸውን) ስለ ሐጅ ተግባራት ሲያስተምሩት፥ ያለፉት ህዝቦች ለጥፋት ሊዳረጉ የቻሉት ድንበር በማለፍ መሆኑን በማውሳት፥ ሰሀቢው ከማካበድ ተግባር እንዲቆጠብ አስገንዝበውታል፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት...«አደራችሁን! በሃይማኖት ውስጥ ማካበድን ተጠንቀቁ፥ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ለጥፋት የዳረጋቸው ማካበድ ነው፡፡» (ኢብን ማጃህ፡3029)

ለዚህ ነው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) «አደራችሁን አቅማችሁ በሚፈቅደው ተግባር ላይ ብቻ ተሰማሩ» ያሉት (አል-ቡኻሪ፡1100)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተልዕኮዋቸውን ትክክለኛ ገፅታ ቁልጭ ባለ ቃል ገልፀዋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተላኩት ለሰዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ነገር ለማሸከም ሳይሆን፥ ገራገርና በጥበብ የተሞላ ዕውቀት ለማስጨበጥ ነው፡፡ መልእክተኛው እንዲህ ብለዋል አላህ «አጨናናቂ ወይም አጣባቢ አድርጎ አልላከኝም ነገር ግን አግራሪና አስተማሪ አድርጎ ልኮኛል፡፡» (ሙስሊም፡1478)



## > የእስልምና ሃይማኖት ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ያካትታል፡-

እስልምና በመስጂድ ውስጥ ተወስኖ በዱዓ እና በሶላት ብቻ የሚገለፅ ሙስሊሞች የሚያከናውኑት በመንፈሳዊነት የተገደበ ሃይማኖት አይደለም፡፡

ወይም ደግሞ ተከታዮቹ ግለሰቦች አምነው የሚቀበሉት በልብ ውስጥ ብቻ የሚያድር እምነት አይደለም፡፡

በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩር ሥርዓትም አይደለም፡፡

አሊያም ደግሞ አንድን ማህበረሰብ ለመገንባት ያለመ ንድፈ-ሐሳብ ብቻም አይደለም፡፡

ወይም ደግሞ ከሌሎች ወገኖች ጋር በመኗኗሩ ረገድ ሊኖር ስለሚገባው መልካም ሥነ-ምግባርና ግብረ-ገብ የሚያስተምር የእነፃ ትምህርት ብቻም አይደለም፡፡

ይልቁንም ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ያካተተ የተሟላ አስተምህሮ ነው፡፡ እያንዳንዱን የኑሮ እርከን ያጠቃለለ ነው፡፡

አላህ ይህን የመሰለ ፀጋ ሙስሊሞች እንዲጎናፀፉ አድርጓል፡፡ ይህን ሙሉ ሃይማኖት እንከተለው ዘንድም ወዶልናል፡፡ እንዲህ ይላል ...«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡» (አል-ማኢዳህ፡3)

አንዱ የመካ ሙሽሪክ ለማሾፍ በመፈለግ ሰልማን አል-ፋርሲ ለተባሉት ሰሀቢ እንዲህ አላቸው «ጓደኛችሁ (ረሱልን ለማለት ነው) የመፀዳጃ ቤት ስርዓትን ጨምሮ ሁሉንም ነገር ያስተምራችኋል፡፡» ታላቁ ሰሀቢም «አዎን ያስተምሩናል!» ብለው መለሱና በዚሁ ዙሪያ ያለውን ኢስላማዊ ሕግና ሥርዓት አብራሩለት፡፡



> እስልምና ሁሉንም የህይወት ዘርፍ የሚመለከት የተሟላ መመሪያ ነው

> እስልምና የሚለካው፥ በአንዳንድ ሙስሊሞች ተግባር ሳይሆን በሃይማኖቱ ምንነትና ምንጭ ነው፡፡

ጤናን የሚጎዳ ተግባር የሚፈፅም የጤና ባለሙያ ወይም መልካም ሥነ- ምግባር የሌላው መምህር ቢያጋጥምህ፥ የእነዚህ ሰዎች ተግባር ከተሰማሩበት ሙያ ጋር የማይገጥምና የማይጣጣም በመሆኑ ትገረምና ትደነቅ እንደሆን እንጂ የትምህርትም ሆነ የሕክምና ሙያ ለህብረተሰቡም ሆነ ለብልፅግና የማይጠቅሙ አላስፈላጊ ተግባራት ናቸው ወደሚል ድምዳሜ አትደርስም፡፡

ባይሆን ልትል የምትችለው ይህ ሐኪምም ሆነ መምህር ከተሰማራበት ሙያ ጋር የማይጣጣም ተግባር እየከናወነ ነው፡፡

አንዳንድ ሙስሊም ግለሰቦች ተገቢ ያልሆነ ተግባር ሲፈፅሙ ካየን፥ ተግባራቸው እስልምናን እያንፀባረቀ እንደሆነ አድርገን መቁጠር አይኖርብንም፡፡ ይልቁንም ልክ ሐኪሙና መምህሩ ከሙያቸው ጋር የሚቃረን ተግባር በልምድ እንዳከናወኑት ሁሉ፥ ከእስልምና ጋር በጭራሽ ግንኙነት የሌለው በልምድና በባህል እንዲሁም በሰብዓዊው ፍጡር ድክመት የሚሰሩ መጥፎ ተግባራት መሆናቸውን ማወቅ አለብን፡፡

## > አምስቱ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች፡-

እነዚህ አምስት ነገሮች ሰው ተገቢ በሆነ መልኩ ይኖር ዘንድ የሚያስፈልጉ ወሳኝ የሆኑ ጥቅሞች ናቸው፡፡ ለሁሉም መለኮታዊ ህግጋት የተደነገጉት እነዚህን ነገሮች ለመጠበቅና እነዚህን ተቃርነው የተገኙ ነገሮችን ለመከላከል ነው፡፡

እስልምና የተደነገገው፥ አንድ ሙስሊም ለዱንያዊ ሆነ አኼራዊ ህይወት በዚህ ዓለም ላይ ተረጋግቶ ይሰራ ዘንድ፥ እነዚህን አምስት ነገሮች ለመጠበቅና ለመንከባከብ ነው፡፡

ሙስሊሙ ህብረተሰብ የሚኖረው፥ እርስ በርሱ ተደጋግፎ እንደቆመ ግንብ በመተሳሰር ነው፡፡ አንዱ አካል ሲጎዳ ሌላውም ጉዳቱ በትኩሳትና በእንቅልፍ ማጣት እንደሚሰማው እንደ አንድ የሰውነት አካል ሆነው ይኖራሉ፡፡



> ተግባራችን ተገቢ ወዳልሆነ ተግባር ቢያሰማራንም የሰው ልጅን ነፍስ መጠበቅ እንደ ሚኖርብን አላህ አዞናል፡፡

1 ይህንኑ መጠበቅ የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው፡-

2 በመገንባትና በመንከባከብ

1 ሃይማኖት፡-

ሃይማኖት ማለት አላህ ሰዎችን ለዚሁ ዓላማ ሲል የፈጠረበትና ታላቅ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ መልእክተኞች የላከውም ይህንኑ እንዲጠብቁ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል... “በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖትንም ራቁ በማለት መልእክተኛን በእርግጥ ልከናል...” (አል-ነሕል፡36)

የሃይማኖትን ብፁዕነት የሚያቆሽሹና እንደ ሺርክ፣ ከንቱ እምነት፣ ወንጀልና ኃጢአት የመሳሰሉ ነገሮች ሃይማኖትን ለመጠበቅ ሲባል ኢስላም ተከላክሏቸዋል፡፡

2 አካል፡-

ተግባራችን ተገቢ ወዳልሆነ ነገር ቢያሰማራንም የሰው ልጅን ነፍስ መጠበቅ እንዳለብን አላህ አዞናል፡፡ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እስከ ሆንን ድረስ አላህ ለእኛ ምህረትን ይለግሰናል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል… "… ሺፍታና ወሰን አላፊ ሳይሆን (ለመብላት) የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡" (አል-በቀራህ፡173)

የራስን ነፍስ መግደልና መጉዳትንም ከልክሏል፡፡ እንዲህ ይላል… "በአላህም መንገድ ለግሱ በእጆቻችሁም (ነፍሶቻችሁን) ወደ ጥፋት አትጣሉ…" (አል-በቀራህ፡195)

የእስልምና ሃይማኖት አንድ ሰው የትኛውም ሃይማኖት ይከተል በሱ ላይ ድንበር እንዳይታለፍበትና ወንጀል እንዳንፈፅምበት በሚል ወሰኖችን አበጅቷል መቀጣጫ ህግጋትንም አኑሯል፡፡ እንዲህ ይለናል…«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በተገደሉ ሰዎች ማመሳሰል በናንተ ላይ ተፃፈ….» (አል-በቀራህ፡178)

3 አዕምሮ፡-

አዕምሮ አላህ ከለገሳቸው ታላላቅ ፀጋዎች ውስጥ አንዱ በመሆኑ፥ እርሱን የሚጎዱና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳርፉበትን ነገሮች እስልምና ከልክሎዋል፡፡ የሰው ክብርና ማንነት የሚገለፀው በርሱ ነው፡፡ በዚህ ዓለም (ዱንያ) ሆነ በቀጣዩ ዓለም አኼራ ሂሳቡን የሚያወራርደውና ጥያቄ የሚቀርብለት በርሱ ነው፡፡

ለዚህ ነው አላህ ማንኛውንም ዓይነት አስካሪ መጠጥና አደንዛዥ ዕፅን የከለከለው (ሃሐራም) ያደረገው ከፀያፍና ከሸይጣን ተግባራት ተርታ መድቦታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፣ ቁማርና ጣዖታትም የመጠንቆያ እንጨቶች (አዝላምም) ከሰይጣን ስራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፤ እርኩስን ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡" (አል-ማኢዳህ፡90)

4 ዘር፡-

የእስልምና ሃይማኖት ዘርን ለማስቀጠልና ለቤተሰብ ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠውና ጥበቃ ያደረገለት ነገር መሆኑ በተለያዩ መርሆቹና ህግጋቶቹ ውስጥ ጎልቶ ሲታይ ይስታዋላል፡፡ ከዚህ ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

- የእስልምና ሃይማኖት ለትዳር በጣም ያበረታታል፡፡ ቀለል ባለ አኳኋን እንዲመሰረተም ይገፋፋል፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹ እንዳናካብዳቸውም ያዘናል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "ከናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ፡፡" (አል-ኑር፡32)

- እስልምና ሕገ-ወጥ የሆኑ ማንኛውም ዓይነት የፆታ ግንኙነቶችን ከልክሎዋል፡፡ ወደ እርሱ የሚያደርሱ ጎዳናዎች ሁሉ ዝግ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ እንዲህ ይለናል፡፡ «ዝሙትን አትቅረቡ፤ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፤ መንገድነቱም ከፋ!» (አል-ኢስራእ፡32)

- እስልምና የሰው ዘርና ክብር ማንቋሸሽና ማጥላላትንም በጥብቅ አውግዞዋል፡፡ ይህ መሰሉን ተግባር ከከባባድ ወንጀሎች ውስጥ መድቦታል፡፡ ይህን ወንጀል የፈፀመ ሰው በአኼራ ከሚጠብቀው ቅጣት በተጨማሪ፤ ዱንያ ላይም ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቀው አላህ አስጠንቅቋል፡፡

- የወንድም ሆነ የሴት ልጅ ክብር እንዲጠበቅና እንዳይጣስ አዞዋል፡፡ የራሱንም ሆነ የቤተሰቦቹን ክብር ለማስጠበቅ ሲል የተገደለ ሰው በአላህ መንገድ እንደተሰዋ ሰማዕት ቆጥሮታል፡፡ (ገጽ፣ 196 ተመልከት)

5 ገንዘብ፡-


ገንዘብ ጥበቃ ይደረግለት ዘንድ እስልምና ግዴታ አድርጓል፡፡ የዕለት ጉርስን ፍለጋ መንቀሳቀስንም እንዲሁ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የሚደረግ የንግድ ግብይትና የቢዝነስ ልውውጥንም የተፈቀደ ተግባር አድርጎታል፡፡

ለገንዘብ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል ከሚል እሳቤ በመነሳትም፥ አራጣን፣ ስርቆትን፣ ማታለልን፣ ማጭበርበርንና በሀሰት መንገድ የሰው ገንዘብ መብላትን ሓራም አድርጓል፡፡


እነዚህን የወንጀል ተግባራት የሚፈፅም ሰው፥ በቅዱስ ቁርአን ከፍተኛ የሆነ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል፡፡ (ገጽ፣ 168 ተመልከት)



> የሰውን ክብርና ዘር መጠበቅ ከኢስላማዊ መርህ ታላላቅ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡



# እምነትህ



# 1

ወደ ተለያዩ ህዝቦች የተላኩ ነቢያት በሙሉ ይዘው በተነሱት ተልእኮ ውስጥ "አላህ ያለማንም ተጋሪ በብቸኝነት መመለክ የኖርበታል፡፡ ከርሱ ውጪ ሌላን በማምለክ ሊካድ አይገባውም" የሚል ሙሉ ስምምነት አለ፡፡

ይህ ዕውነታ "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፡፡ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው፡፡" የሚለውን ቃል ያንፀባርቃል፡፡ አንድ ሰው ወደ አላህ ሃይማኖት ሊገባ የሚችለው በዚህ ቃል አማካኝነት ነው፡፡

## የክፍል አንድ ማውጫ

### ሁለቱ ምስክርነቶች፤ ትርጉማቸውና ዓላማቸው

- "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም!" ለምን እንላለን?
- "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም" የሚለው ቃል ትርጉም
- "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም" የሚለው ቃል መሠረቶች

### ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን ስለመመስከር

- የአላህ በረከትና ሠላም በርሳቸው ላይ ይሁንና ነቢዩን ማወቅ
- "ነብዩ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው፡፡" የሚለው ቃል ትርጉም

### የስድስቱ እምነት መሠረቶች

### አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው?

### ሽርክ (ለአላህ ተጋሪ ማበጀት)

### በአላህ ሥሞችና ባህሪያት ማመን

### በመላእክት መኖር ማመን

### በመለኮታዊ መፅሐፍት ማመን

### በመልእክተኞት መላክ ማመን

### በመጨረሻው ቀን ማመን

### በአላህ ውሣኔ ማመን

## ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንና መሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ



### “ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም” የምንለው ለምንድ ነው?

- በሙስሊም ላይ የመጀመሪያው ግዴታ ይህን ቃል ማረጋገጥ ነው:: አንድ ሰው ወደ እስልምና መግባት ከፈለገ በቃሉ ውስጥ ባለው ፅንሰ-ሃሳብ ማመንና ቃሉን መግለፅ ይኖርበታል::
- ቃሉ ባካተተው ዕውነታ ከልቡ አምኖና የአላህን ውዴታ ፈልጎ ቃሉን በንግግር በመግለፅ የመሰከረ ሰው ከእሳት ቅጣት ነፃ ለመውጣት ሰበብ ይሆነዋል:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል… “(የአላህን ውዴታ በመፈለግ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም ብሎ የመሰከረ ሰው አላህ በርሱ ላይ እሳትን እርም አድርጓታል::” (አል-ቡኻሪ:415)
- ይህ ቃል በውስጡ ባካተተው ፅንሰ-ሃሳብ አምኖ የሞተ ሰው የጀነት ነዋሪ ይሆናል:: ነቡዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እነዲህ ብለዋል … “ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን አውቆ የሞተ ሰው ጀነት ገብቷል::” (አህመድ:464)
- ይህ በመሆኑም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን ማወቀ የግዴታዎች ሁሉ ተላቁ ግዴታ ነው::

### “ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም” የሚለው ቃል ትርጉም

ይህ ማለት ብቸኛ ከሆነው አላህ በስተቀር በዕውነት የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው:: ከተቀደሰውና ከፍ ካለው አላህ በስተቀር ከማንም ላይ መለኮታዊነትን መሻር ማለት ሲሆን መለኮታዊ ስልጣንን አንድና አጋር ለሌለው አላህ ብቻ ማረጋገጥ ማለት ነው::

«አል-ኢላህ» (አምላክ)! ማለት የሚመለክ ማለት ነው:: አንድን ነገር ያመለከ ሰው ያንን ነገር ከአላህ ሌላ አምላክ አድርጎ ይዞታል:: ከተቀደሰው፣ ከፍ ካለውና ፈጣሪ ከሆነው አንዱ ጌታ በስተቀር የሚመለኩ ነገሮች በሙሉ ባጢል (ሐሰት) ናቸው::

አምልኮ የሚገባው ከጉድለት የጠራውና ከፍ ያለው አላህ ብቻ ነው:: ቀልቦች በውዴታ፣ በማላቅ፣ በማክበር፣ በመተናነስ፣ በመፍራት፣ በርሱ ላይ በመመካት ያመልኩታል:: ለልመናም እርሱን ይጠሩታል:: ከአላህ ውጪ ለልመና የሚጠራ የለም:: እርዳታ የሚጠየቀው እርሱ ብቻ ነው:: በርሱ ካልሆነ በማንም መመካት አይቻልም:: ለርሱ ካልሆነ ለማንም አይሰገድም:: የአምልኮ እርድ ለርሱ ካልሆነ ለማንም አይታረድም:: አምልኮ የተባለን በሙሉ ለርሱ ብቻ ማጥራት ግዴታ ነው:: አላህ እንዲህ ብሏል:: “አላህን ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት፣ ሶላተንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልተዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)::” (አል-በይናህ:4)

ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም የሚለው ቃል በማረጋገጥ፥ አላህን ጥርት አድርጎ ያመለከ ሰው፥ ታላቅ የሆነ ደስታን ይጎናፀፋል:: እርጋታና ስክነት ያለው መልካም ህይወት ይኖራል:: አላህን በብቸኝነት ከማምለክ ሌላ፥ ለቀልብ ትክክለኛ የሆነ መረጋጋትን፣ እርካታንና ረፍት የሚሰጥ ሌላ ነገር የለም:: አላህ እንዲህ ብሎዋል:: “ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሠራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን…” (አል-ነሕል:97)

## "ከአላህ በስተቀር በእውነተ የሚመለክ አምላክ የለም" የሚለው ቃል መሠረቶች

የዚህ ታላቅ የሆነ ቃል ትርጉምና ዓላማ ግልፅ እንዲሆንልን ከተፈለገ ሁለት መሠረቶችን ማወቁ ግድ ይለናል፡፡

1

የመጀመሪያው መሠረት፡- «ላ ኢላሃ» (አምላክ የለም) የሚለው ነው፡፡ ይህ ከአላህ ውጪ ባሉ ነገሮች ላይ አምልኮን መሻራችንን ማረጋገጫ ቃል ነው፡፡ ማጋራትን ውድቅ ማድረጊያ ቃል ነው፡፡ ከአላህ ሌላ በሚመለኩ ነገሮች ሁሉ መካድ ግዴታ ነው፡፡ ከአላህ ሌላ ሰውም ሆነ እንስሳትም ሆነ መቃብርም ሆነ ከዋክብትም ሆነ ሌላ ማምለክ አይቻልም፡፡

2

ሁለተኛው መሠረት፡- ኢልለ ላህ (ከአላህ በስተቀር) የሚለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ አምልኮን ለአላህ ብቻ የምናረጋግጥበት ቃል ነው፡፡ ሶላትን፣ ዱዓእና መመካትን የመሳሰሉ የአምልኮ ዓይነቶችን ሁሉ ለአላህ ብቻ የምናውልበት ማረጋገጫ ነው፡፡


የአምልኮ ዓይነቶችን በሙሉ ልንሰጥ የሚገባው አንድና አጋር ለሌለው አላህ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን እንኳ ከአላህ ውጪ ላለ ነገር አሳልፎ የሰጠ ከሃዲ ይሆናል፡፡
አላህ እንዲህ ይላል ..."ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለርሱ በርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚግገዛ ሰው ምርመራው ጌታው ዘንድ ብቻ ነው፤ እነሆ ከሀዲዎች አይድኑም፡፡" (አል-ሙእሚን፡117)
ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም የሚለው ቃል ትርጓሜና መሠረቶች እንዲህ በሚለው የአላህ ቃል ውስጥ ተገልጿል... "በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡" (አል-በቀራህ፡256)
በዚህ የአላህ ቃል ውስጥ "በጣዖትም የሚክድ" የሚለው ቃል የመጀመሪያ መሠረት የሆነውን "አምላክ የለም" የሚለውን ቃል ሲሆን ያረጋገጠው "በአላህ የሚያምን" የሚለው የጌታችን ቃል ደግሞ ሁለተኛ መሠረት የሆነውን ከአላህ በስተቀር የሚለውን ቃል የረጋግጥልናል፡፡



> የቀልብ እርጋታና የነፍስ እርካታ የሚገኘው የአላህን አንድነት በማረጋገጥ ነው፡፡

## ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ማወቅ:-

### 1 ልደታቸው:-



የተወለዱት እ.ኤ.አ. በ570 መካ ውስጥ ነው:: ሲወለዱ አባታቸው በህይወት አልነበሩም:: እናታቸውንም ያጡት ገና ልጅ ሆነው ሳለ ነው:: ተንከባክበው ያሳደጓቸው መጀመሪያ አያታቸው ዓብዱል ሙጠሊብ ሲሆኑ በመቀጠል ትንሽ አደግ እንዳሉ ደግሞ አጎታቸው አቢ-ጣሊብ ናቸው

### 2 ህይወታቸውና እድገታቸው:-



ለነቢይነት ማዕረግ ከመብቃታቸው በፊት ለአርባ አመታት ያህል እ.ኤ.አ. (ከ570 -610) ከቁረይሽ ጎሳዎች ጋር ኖሩ:: በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ የታላቅ ሥነ-ምግባርና የፅናት ተምሳሌት እንዲሁም መለያ ሆነው ቆይተዋል:: «ታማኙ» «እውነተኛው» በሚሉ የቅፅል ሥሞች በገሃድ ይታወቁ ነበር:: እረኛ ነበሩ:: ከዚያም በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል:: የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ነብይ ከመሆናቸው በፊትም በኢብራሒም መንገድ በመጓዝ አላህን በብቸኝነት ያመልኩ ነበር:: የጣዖትና የባዕድ አምልኮዎችን ይርቁና ይጠየፉ ነበር::

**የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሙሉ ስም:-**

ሙሐመድ ቢን አብደላህ ቢን ዓብዱል ሙጠሊብ ቢን ሃሺም አል-ቁረይሺ
የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጎሳ በዓረቦች ዘንድ እጅግ የተከበረ ጎሳ ነው::

**ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሰው ዘር ሁሉ የተላኩ መልእክተኛ ናቸው::**

አላህ ነቢያችን ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሁሉም የሰው ዘር በጠቅላላ ልኳቸዋል:: እርሳቸውን መታዘዝ በሁሉም ሰው ላይ የተጣለ ግዴታ ነው:: አላህ እንዲህ ብሏል... "(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልእክተኛ ነኝ::" (አል-ዕራፍ:158)

### 3 ተልዕኳቸው:-



የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አርባ ዓመታትን በዚህ ሁኔታ ካሳለፉ በኋላ፥ በመካ አቅራቢያ ከሚገኙ ተራራዎች አንዱ በሆነው «ኑር» ተራራ ውስጥ በሚገኘው «ሒራእ» ዋሻ ውስጥ በመሆን በጥልቅ ተመስጦ አላህን ያመልኩ ነበር፡፡
ከዚያም ከአላህ ዘንድ የሆነ ወህይ (ራዕይ) ይገለፅላቸው ጀመር፡፡ የአላህ ቃል የሆነው ቁርኣን በእርሳቸው ላይ መውረድ ጀመረ፡፡ በመጀመሪያ በርሳቸው ላይ የወረደው የቁርኣን ቃል..."አንብብ ፥ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም" የሚለው ነበር
ይህ የእርሳቸው ተልዕኮ ዕውቀትን፣ ንባብን፣ ብርሃንና የቀጥተኛ ጎዳናን የማብሰሪያ አዲስ ዘመን ጅማሮ መሆኑን ለመግለፅ ይህ አንቀፅ ወረደ፡፡
ከዚያ በሃያ ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሌሎች የቁርኣን አናቅፅ እየተከታተሉ ወረዱ፡፡

### 4 የዳዕዋ (የሰበካ) መጀመር:-

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለሦስት ዓመታት ያህል ሰበካቸውን በድብቅ አካሄዱ፡፡ ከዚያም ለተከታዮቹ አስር ዓመታት ሰበካቸውን በግልፅና በገሃዱ አደረጉ፡፡ ነቢዩና (ሰ.ዐ.ወ.) የእምነት ባልደረቦቻቸው (ሶሃቦች) ይህን በማድረጋቸው፥ ጎሳዎቻቸው ከሆኑት ቁረይሾች ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ፣ ሁከትና፣ ማዋከብ ገጠማቸው፡፡
ወደ ሐጅ ለሚመላለሱ ጎሳዎች የእስልምና ግብዣ ቀረበላቸው፡፡ የመዲና ነዋሪዎች ዘንድ ጥሪው ተቀባይነትን አገኘ፡፡ ከዚያ ቀስበቀስ ወደ መዲና ከተማ የስደት ጉዞ ተደረገ፡፡

**በርሳቸው ላይ ቁርኣንን አወረደ:-**

አላህ፥ ከፊቱም ሆነ ከኋላው ሃሰት የሌለውን ታላቅ መፅሐፍ ቁርኣን በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ አወረደ፡፡

**የነቢያትና የመልእክተኞች መደምደሚያ:-**

አላህ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) የላከው የመጨረሻና መደምደሚያ ነቢይ አድርጎ ነው፡፡ ከርሳቸው በኋላ የሚነሳ አንድም ነቢይ የለም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "...ግን የአላህ መልእክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡" (አል-አሕዛብ፡40)




## 5 ስደት፡-

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እ.ኤ.አ. በ622 ያኔ «የስሪብ» ትባል ወደ ነበረችው መዲና ከተማ ስደት አደረጉ፡፡ በወቅቱ የሃምሳ ሦስት ዓመት ጎልማሳ ነበሩ፡፡ ዳዕዋቸውን ያወገዙ የቁረይሽ ጎሳ ባላባቶች ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ግድያ ለመፈፀመ አሲረው ነበር፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ኢስላም እየተጣሩ ለአስር አመታት ያህል በመዲና ከተማ ኖሩ፡፡ ሰላት፣ ዘካና ሌሎች የሸሪዓው ህግጋቶች እንዲተገበሩ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡




## 6 እስልምናን ማስራጨት፡-

የአላህ መልእክተኛ ወደ መዲና ከተሰደዱ በኋላ ከ622-632 ባለው ጊዜ ውስጥ የኢስላማዊ ስልጣኔ መሠረት ተክለዋል፡፡ አዲስ ሙስሊም ማህበረሰብ ፈጥረዋል፡፡ ዘረኝነትና ጎሰኝነትን አስቀርተዋል፡፡ ዕውቀትን አሰራጭተዋል፡፡ የፍትህ፣ የፅናት፣ የወንድማማችነት፣ የመረዳዳት መርህን ገንብተዋል፡፡

አንዳንድ ጎሳዎች እስልምናን በአጭሩ በማስቀረት ተነሳስተው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ጦርነቶች ተካሂደዋል፡፡ አላህ ሃይማኖቱንና መልእክተኛውን ረድቷል፡፡ ከዚህ በኋላ በመካ ነዋሪ የሆኑ ብዙ ጎሳዎች ወደ እስልምና ገብተዋል፡፡ በዓረብ ፔንሱላ ከተማዎች የሚኖሩ በርካታ ጎሳዎችም በራሳቸው ምርጫ ፍላጎትና ውዴታ ወደ ዚህ ታላቅ ሃይማኖት እየተግተለተሉ ገብተዋል፡፡



## 7 ህልፈታቸው፡-

የአላህ መልእክተኛ(ሰ.ዐ.ወ.) በሂጅራ የዘመን አቆጣጠር በወርሃ ሠፈር 11፣ መልእክታቸውን አድርሰው ጨረሱ፣ አደራቸውንም ተወጡ፡፡ አላህም ሃይማኖቱን ሙሉ በማድረግ ለሰዎች ፀጋውን አጎናፀፈ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የወባ ህመም አጋጠማቸው፡፡ ያደረባቸው ህመም እየፀና ሄደ በወርሃ ረቢዑል አወል በዕለተ ሰኞ በ11ኛው ዓመተ ሒጅራ ይህን ዓለም ተሰናብተው ወደ ቀጣዩ ዓለም ተሸጋገሩ፡፡ ይህ ማለት እ.ኤ.አ. ሜይ 8¸ 632 መሆኑ ነው፡፡

ከዚህ ዓለም ሲለዩ የስድሳ ሦስት ዓመት አዛውንት ነበሩ፡፡ ግብአተ-መሬታቸው የተፈፀመው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መስጂድ አጠገብ እሜቴ ዓኢሻ ቤት ውስጥ ነው፡፡

### «ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው» የሚለው ቃል ትርጉም

እንዲህ ብሎ መመስከር፥ የተናገሩትን አምኖ መቀበል፣ ትዕዛዛቸውን መፈፀምና ክልከላቸውን መታቀብ ማለት ነው፡፡ አላህንም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በደነገጉትና ባስተማሩን መሠረት ብቻ ማምለክና መገዛት ማለት ነው፡፡

### ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን ማመኔ የሚያጠቃልለው ምንና ምንድ ነው?

**1** ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ.) ሁሉንም ነገር አስመልክቶ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም፡-

- ከህዋስ ስለራቁ ምስጢራዊ ነገሮች፣ ስለመጨረሻው ቀን፣ ስለጀነት ፀጋዎችና ስለ እሳት ቅጣት፣
- በእለተ ቂያማ ስለሚከሰቱ ነገሮችና ምልክቶቻቸው እንዲሁም በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆኑ ነገሮች፡-
- ስላለፉና ስለቀደሙ ህዝቦች፣ በነቢያትና ጥሪ ባደረጉላቸው ህዝቦች መካከል ስለተፈጠሩት ነገሮች

**2** ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያዘዟቸውን ነገሮች መተግበርና ከከለከሉት ተግባራት መታቀብም ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም፡-

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚያዝዙን ትዕዛዛት ከራሳቸው አፍልቀው ሳይሆን ከአላህ በሚገለፅላቸው ራዕይ አማካኝነት መሆኑን በእርግጥኝነት ማመን ይኖርብናል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል... "መልእክተኛውን የሚታዘዝ ሰው፥ በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡" (አል-ኒሳእ:80)
- እርሳቸው ከከለከሏቸው ሐራም ነገሮች፣ መጥፎና ጎጂ የሆኑ ሥነ-ምግባራትና ግብረ ገቦች መታቀብም ይኖርብናል፡፡ እነዚህን ነገሮች እንዳናደርግ የከለከሉንም እውነታው ከእኛ ቢሰወርና ባናውቀውም ለአንዳች ጥበብ አላህ ፈልጎ ያደረገው መሆኑንና ለራሳችን ጥቅም መሆኑን ማመን ይኖርብናል፡፡
- ያዘዙንን መተግበራችን፣ ከከለከሉን መታቀባችን ዞሮ ዞሮ ለእኛ መልካም እንደሆነና በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ደስታን እንደሚያጎናፅፈን በእርግጠኝነት ማመን ይኖርብናል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ..."ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልእክተኛውን ታዘዙ፡፡" (አሊ-ዒምራን:132)
- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ትዕዛዝ ሆን ብሎ መጣስ ለቅጣት የሚዳርግ ተግባር መሆኑ ተገቢ ነገር መሆኑንም ማመን ይኖርብናል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "...እነዚያም ትእዛዙን የሚጥሉ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ፡፡" (አል-ኑር:63)



> በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና (ሐዲስ) ውስጥ የተረጋገጡ እውነታዎችን አንድ ሙስሊም አምኖ የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡

## 3 አላህን ማምለክ የሚኖርብን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በደነገጉት መልኩ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ዕውነታ ብዙ ነገሮችን የሚያካትት በመሆኑ ይህን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ይኸውም፡-

- አርዓያነታቸውን መከተል፡-

የአላህ መልእክተኛን (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና (የየእለት ተግባር) ፣ መመሪያና ህይወት በአጠቃላይ ንግግራቸውን፣ ተግባራቸውንና አፅድቆታቸውን ጨምሮ በሁሉም የህይወት እርከናችን በአርዓያነት ልንከተለው ይገባል፡፡

አንድ የአላህ ባሪያ የአላህ መልእክተኛን ሱንና ይበልጥ በአርዓያነት በተከተለ ቁጥር፥ ይበልጥ ወደ አላህ የተጠጋና ደረጃውም ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል... “በላቸው አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋል፤ ኃጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፤ አላህ መሐሪ አዛኝ ነው፡፡” (አሊ-ዒምራን፡31)

- **የተሟላ ህግ፡-** የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይዘው የመጡት ሃይማኖትና ህግጋት በሁሉም ረገድ ምሉዕና ጉድለት የሌለው ነው፡፡ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ.) ያልደነገጉትን የአመልኮ ተግባር በአዲስ መልክ መፍጠር ለማንም ሰው ቢሆን የተፈቀደ አይደለም፡፡

- **አላህ የደነገገው ህግ** በሁሉም ጊዜና ቦታ ተስማሚ ነው፡- በአላህ መፅሐፍና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና ውስጥ የተደነገገው ህግና ሥርዓት በሙሉ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ሁሉ ተስማሚ ነው፡፡ ሰዎችን ከምንም ካስገኛቸውና ከፈጠራቸው ጌታ በላይ ሰዎችን የሚጠቅም ነገር የሚያውቅም ማንም የለም፡፡



> በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና (ሐዲስ) ውስጥ የተረጋገጡ እውነታዎችን አንድ ሙስሊም አምኖ የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡

- **ከሱንና ጋር ስምሙ መሆን፡-** አንድ የአምልኮ ተግባር አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ የአላህን ውዴታ ብቻ አስቦ (ነይቶ) መስራትና ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና ጋር የተጣጣመ መሆኑ ግድ ይላል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል… “የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ስራን ይስራ በጌታውም መግገዛት አንድንም አያጋራ በላቸው፡፡” (አል-ከህፍ፡110) በዚህ አንቀፅ ውስጥ «መልካም ሥራ» በሚል የተወሳው ከአላህ መልእክተኛ ሱንና ጋር ተጣጥሞ የተገኘ ስራ ማለት ነው፡፡

- **ሃይማኖታዊ ተግባር መፍጠር ሃራም ነው፡-** አላህን ለማምለክ በሚል፥ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ያልደነገጉትንና ሸሪዓዊ ባልሆነ መንገድ አዲስ የአምልኮ ተግባር የፈጠረ ሰው፥ የነቢዩን መንገድ ተፃሮ የተገኘ በመሆኑ ወንጀለኛ ይሆናል፡፡ ስራውም ተመላሽና ተቀባይነት የሌለው ይደረጋል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል… “… እነዚያም ትእዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ፡፡” (አል-ኑር፡63) ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል “በዚህ ጉዳያችን ውስጥ ከርሱ ያልሆነን ነገር የፈጠረ፤ ሥራው ተመላሽ ነው፡፡” (አል-ቡኻሪ፡2550 ሙስሊም 1718)



# > ስድስቱ የእምነት መሠረቶች

## በኃያሉ አላህ የማመን ትርጉም፡-

የኃያሉ አላህ መኖርን እውነት ብሎ አምኖ መቀበል ነው፡፡ ጌትነቱን፣ አምላክነቱን፣ ማረጋገጥ ነው፡፡ በስሞቹንና በባህሪያቱ ማመን ነው።

ስለ እነዚህ አራት ጉዳይ ከዚህ እንደሚከተለው ዘርዘር ባለ መልኩ እንነጋገራለን፡-

## 1 በአላህ መኖር ማመን፡-

### የአላህ ፍጥረት፡-

በአላህ መኖር ማመን ሰው በተፈጥሮው የሚያረጋግጠውና ሌላ ተጨማሪ መረጃ የማያስፈልገው ነገር ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ምንም የተለያየ ሃይማኖትና መንገድ ቢከተሉም በጣም በርካታ ሰዎች አላህ ለመኖሩ ዕውቅና ይሰጣሉ፡፡

የእርሱን መኖር የሚያረጋግጥ ጥልቅ የሆነ ስሜት በቀልባችን ይሰማናል፡፡ በተፈጥሮው አማኝ በሆነው ስሜታችን ገፋፊነት መጥፎና አስቸጋሪ ነገር ሲገጥመን ወደርሱ እንሸሻለን፡፡ አንዳንዶች ለመሸፋፈንና ለመዘናጋት ሙከራ ቢያደርጉም፥ አላህ በእያንዳንዱ ሰው ነፍስ ውስጥ ወደ ሃይማኖተኛነት የመዘንበል ስሜትን ፈጥሯል፡፡

እኛም አላህ ለተጣሪዎች ምላሽን ሲሰጥ፣ ለጠያቂዎች የጠየቁትን ሲቸር፣ ለተለማማኞች ፍላጎታቸውን ሲያሟላ ስለምናይና ስለምንሰማ፥ ይህ ሁኔታ አላህ ለመኖሩ እርግጠኛ መረጃ ይሆነናል፡፡



አትክሮት ላለውና ላስተነተነ ሰው አላህ ለመኖሩ ማስረጃ ከሚሆኑት ታላላቅ ነገሮች ውስጥ አንዱ ሰው እራሱ ነው፡፡ አላህ የአዕምሮን፣ የስሜት ህዋሳትንና፣ ሙሉ የሆነና ስርዓት ያለው አፈጣጠርን በፀጋነት አጎናፅፎታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል... “በነፍሶቻችሁም ውስጥ (ምልክቶች አሉ)፤ ታዲያ አትመለከቱምን?” (አል-ዛሪያት፡21)

### አላህ መኖሩ እጅግ ግልፅ የሆነ ነገር ነው፡ መረጃዎችን መዘርዘርም አያስፈልግም፡፡ ግልፅ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥም፡-

- በሁሉም ሰው ዘንድ እንደሚታወቀው ማንኛውም ድርጊት አድራጊ ሊኖረው ግድ ነው፡፡ በየጊዜው የምንመለከተው ይህ እጅግ በርካታ ፍጥረት አስገኚና ፈጣሪ ሊኖረው ግድ ይላል፡፡ እርሱም ኃያሉና ታላቁ አላህ ነው፡፡ አንድ ፍጡር ያለምንም ፈጣሪ ተገኘ ማለት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ራሱን በራሱ ፈጥሯል ማለትም እንዲሁ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ነገር ራሱን በራሱ ሊፈጥር አይችልም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል “ወይስ ያለ አንዳች ፈጣሪ ተፈጠሩን ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?” (አልጡር፡35)

በዚህ አንቀፅ መተላለፍ የተፈለገው መልእክት “እነርሱ ያለፈጣሪ አልተፈጠሩም፡፡ እነርሱም ራሳቸውን አልፈጠሩም፡፡ ስለዚህ ፈጣሪያቸው ሊሆን የሚችለው የተቀደሰውና ከፍ ያለው አላህ ነው” የሚል ነው፡፡

- ሰማዩ፣ ምድሩ፣ ከዋክብቱ፣ ዛፎቹና ይህ ፍጥረተ-ዓለም በአጠቃላይ የተመሠረተበት ሥርዓት ግልፅ በሆነ ሁኔታ የሚያሳየን ነገር ቢኖር፥ የዚህ ፍጥረተ-ዓለም ፈጣሪ አንድ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ እርሱም ከፍ ያለውና ከጉድለት የጠራው አላህ ነው፡፡ "... የዚያን ነገሩን ሁሉ ያጠነከረውና የአላህን ጥበብ (ተመልከት)፡፡" (አል-ነምል፡88)

ከዋክብቶችን በምሳሌነት እንውሰድ፥ ፅኑ በሆነ አኳኋንና ስርዓት ነው የሚጓዙት፡፡ ሁሉም ኮከብ ያለምንም መሰናክልና መወላገድ በራሱ በሆነ ምህዋር ብቻ ይጓዛል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል "ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፤ ሌሊትም ቀንን (ያለ ጊዜው) ቀዳሚ አይኾንም፤ ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ፡፡" (ያሲን፡40)

## 2 በኃያሉ አላህ ጌትነት ማመን

### በኃያሉ አላህ ጌትነት የማመን ትርጉም፡-

ኃያሉ አላህ የሁሉም ነገር ባለቤት፣ ፈጣሪና ሲሳይን ሰጪ ነው ብሎ አምኖ መቀበልና እውነት ነው ብሎ በቁርጠኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በጌትነቱ ማመን ማለት ህይወት የሚሰጠውና የሚነሳው፣ የሚጠቅመውና የሚጎዳው እርሱ ብቻ ነው ብሎ ማመን ነው፡፡ የሁሉም ትዕዛዝ ባለቤት እርሱ ነው ማለት ነው፡፡ መልካም ነገር ሁሉ በእጁ ነው፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ነገሮችም ተጋሪ የለውም ብሎ ማመን ነው፡፡




ይህ እንግዲህ አላህ በተግባሩ ብቸኛ ነው ብሎ ማረጋገጥ ነው፡፡ ስለዚህ እንደሚከተለው ማመን ያስፈልጋል፡-

በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ያሉትን ነገሮች የፈጠረው አላህ ብቻውን ነው ከርሱ ሌላ ፈጣሪ የለም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል… "አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው፡፡" (አል-ዙመር፡62)
የሰው ተግባር ግን አንድን ነገር ወደ ሌላ ቅርፅ መቀየር ወይም እርስ በእርሱ ማቆራኘትና የመሳሰሉት እንጂ ከባድና ከምንም ተነስቶ የሚፈጥረው ነገር የለም፡፡ ሙት የሆነውን ነገር ወደ ህይወት ማምጣትም አይችልም፡፡

ለፍጥረታት ሁሉ ሲሳይን የሚሰጠው አላህ ነው፡፡ ከርሱ ውጪ ሲሳይን ሰጪ የለም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "በምድር ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ቢሆን እንጂ…" (ሁድ፡6)

አላህ የሁሉም ነገር ባለቤት ነው፡፡ ከርሱ ሌላ የነገሮች እውነተኛ ባለቤት የለም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "የሰማያትና የምድር በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፤ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡» (አል-ማኢዳህ፡120)

የሁሉም ነገር አስተናባሪ እርሱ ነው፡፡ ከርሱ ሌላ ነገሮችን የሚየስተናብር የለም፡፡ እንዲህ ይላል… «ነገሩን ሁሉ ከሰማይ ወደ ምድር ያዘጋጃል፡፡» (አል-ሰጅዳህ፡5)
ሰሰው ህይወቱንና ጉዳዮቹን የሚያስተናብረው በተገደበና በተወሰነ መልኩ ነው፡፡ ባለውና በሚችለው ነገር ብቻ ነው የሚያስተናብረው፡፡ ይህ ማስተናበር ደግሞ ውጤታማ ሊሆንም ላይሆን ይችላል፡፡ ከጉድለት የጠራውና የኃያሉ ፈጣሪ ማስተናበር ግን አጠቃላይ ነው፡፡ ከርሱ ቁጥጥር የሚወጣ አንዳችም ነገር የለም፡፡ ያለማንምና ያለምንም ተቃውሞ ያሻውን ፈፃሚ ነው፡፡ እንዲህ ይላል "ንቁ፤ መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው፤ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) (ላቀ፡፡» (አል-አዕራፍ፡54



"በምድር ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለ ቢሆን እንጂ፤" (ሁድ፡6)

## በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን የነበሩ አረብ አጋሪዎች በአላህ ጌትነት ያምኑ ነበር፡-

በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን የነበሩ ከሃዲያን አላህ፥ ፈጣሪ፣ ንጉሥና አስተናባሪ መሆኑን ያምኑ ነበር፡፡ ይህ እምነታቸው ግን ወደ እስልምና እንዲገቡ አላደረጋቸውም… "ሰማያትንና ምድርንም የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይላሉ፡፡" (ሉቅማን፡25)

አላህ የአለማት ጌታ መሆኑን፣ ፈጣሪ፣ ባለቤትና አስተናባሪ መሆኑን ያረጋገጠ ሰው፣ አላህን በብቸኝነት ሊያመልክ ይገባዋል፡፡ የአምልኮ ተግባራትን ያለማንም ተጋሪ ለርሱ ብቻ ማዋል ይኖርበታል፡፡

አንድ ሰው የፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪ፣ አስተናባሪ፣ ህይወት ሰጪና ነሺ አላህ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የአምልኮ ዓይነቶችን ከርሱ ውጪ ላሉ ነገሮች ማዋል በጣም የማያስገርም ነገር ነው፡፡ ይህ አስጠያፊ በደልና ታላቅ ወንጀል ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ነው ሉቅማን ልጃቸውን ሲመክሩ እንዲህ ያሉት "… ልጄ ሆይ! በአላህ (ጣዖትን) አታጋራ፤ ማጋራት ታላቅ በደል ነውና ያለውን (አስታውስ)፡፡" (ሉቅማን፡13)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህ ዘንድ ታላቅ ወንጀል ምን እንደሆነ ሲጠየቁ "አላህ ፈጥሮህ ሳለ ለርሱ ተጋሪን ማድረግህ ነው፡፡" በማለት መልሰዋል፡፡ (አል-ቡኻሪ፡4207 ሙስሊም፡86)

## በአላህ ጌትነት ማመን ቀልብን ያረጋጋል፡-

አንድ የአላህ ባሪያ በእርግጠኝነት የሚያውቅ ከሆነ፥ ከኃያሉ አላህ ውሳኔ ውጭ ሊሆን የሚችል ፍጡር እንደሌለ ይገነዘባል፡፡ ምክንያቱም የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት አላህ ሲሆን ከጥበቡ ጋር በሚስማማ መልኩ እንዳሻው የሚያደርጋቸው እርሱ ነው፡፡

የሁሉም ፈጣሪ እርሱ ነው፡፡ ከአላህ ውጭ ያለው ፍጥረት ሁሉ የተፈጠረና ፈጣሪው ወደ ሆነው አላህ ፈላጊ ነው፡፡ ነገሮች ሁሉ በአላህ እጅ ናቸው፡፡ ከርሱ ውጭ ፈጣሪ የለም፡፡ ከርሱ ውጭ ሲሳይን ሰጭ የለም፡፡ ከርሱ ሌላ ፍጥረተ-ዓለሙን የሚያስተናብር የለም፡፡ ያለርሱ ፈቃድ የምትንቀሳቀስ ቅንጣት ነገር የለችም፡፡ ያለርሱ ትዕዛዝ የምትቆምም የለችም፡፡

ይህ እምነት ያለው ሰው ቀልቡ በአላህ ላይ ብቻ ይንጠለጠላል፡፡ እርሱን ብቻ ይጠይቃል፣ ከርሱ ብቻ ይፈልጋል፡፡ በሁሉም የህይወት ጉዳዩ የሚመካው በርሱ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ሁሉንም የህይወት ገጠመኝ በፅናት፣ በቁርጠኝነትና በተረጋጋ መንፈስ ይጋፈጣል፡፡ ምክንያቱም ለህይወቱ የሚያስፈልገውን ለማግኘት ሁሉንም ሰበብ ከመምከሩ ጎን ለጎን የአላህን እርዳታም ይጠይቃል፡፡ ቃላፊነቱንም ይወጣል፡፡

ይሄኔ ነፍሱ ትረጋጋለች፡፡ ሰው ዘንድ ያለውን አይከጅልም፡፡ ሁሉም ነገር ያለው በአላህ እጅ ነው፡፡ የሚፈልገውን ይፈጥራል፡፡ ይመርጣልም፡፡



> በአላህ ጌትነት ማመን ቀልብን ያረጋጋል

## በነፍስ ውስጥ የሚላወሱ መሰረት የለሽ ነገሮችን መዋጋት

ከኢስላም በፊት ዐረቦች፣ እንዲሁም የዓለም ሕዝብ በአጠቃላይ የተረት ተረትና መሰረት የለሽ አመለካከቶችና ቅዠቶች ሰለባ ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ ምድርን ከጫፍ እስከ ጫፍ ያጥለቀለቃት፣ አንድ ሕዝብ ከሌላኛው ያልተሻለበት ሁኔታ ነበር፡፡ በመሆኑም፣ ዐረቦች በመጀመሪያ ሰሞን ቁርኣንን ተረት ተረት ወይም ድግምት ነው ብለው ገምተው ነበር፡፡

ኢስላም ብርሃኑን ¨Å ምÉር ይዞ በመጣ ጊዜ አዕምሮን ከመሰረት የለሽ አመለካከት፣ ከተረት ተረትና ቅዠት ቀንበር ነፃ አወጣው፡፡ ይህም የሆነው በሕግጋቱና ጥቅል መመሪያዎቹ ሲሆን፣ እነርሱም የአዕምሮንና የነፍስን ጤናማነት የሚጠብቁ እንዲሁም ከርሱ ሌላ ያለን በመተው ወደ አላህ ብቻ ወደ መንጠልጠል የሚያመላክቱ በመሆናቸው ነው፡፡

### 1 ድግምትና አስማተኝነትን መዋጋት

ኢስላም ድግምትን ሟርትንና ጥንቆላን በሙሉ እርም አድርጓል፡፡ የማጋራትና የፀመት ዓይነት አድርጎ መድቦታል፡፡ ድግምተኛ በቅርቢቱም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ለስኬት እንደማይበቃ ተናግሯል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም፡፡»

በአንድ ሙስሊም ላይ ወደ ድግምተኞች መሄድን፣ እነርሱን መጠየቅን፣ ከነርሱ በሽታ መፈወስን መከጀል፣ ወይም ሕክምና ወይም መፍትሄ መፈለግን እርም አድርጓል፡፡ ይህን ያደረገ ሰው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በተወረደው የካደ መሆኑንም ገልጿል፡፡ ምክንያቱም መጥቀምም መጉዳትም በአላህ እጅ ነው፡፡ የሩቅን ምስጢር ከርሱ ሌላ የሚያውቅ የለም፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድን ጠንቋይ የመጣና የጠየቀው ከዚያም እውነት ብሎ የተቀበለው ሰው በርግጥ እሱ በሙሐመድ ላይ በተወረደው ክዷል፡፡»



> አላህን በአምልኮ አንድ ማድረግ «ከአላህ በስተቀር በእውነተ የሚመለክ አምላክ የለም» የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ነው፡፡

## 2 መጥቀምና መጉዳት በአላህ እጅ ነው፡፡

ኢስላም ፍጡራን በጠቅላላ፣ ሰውም፣ ዛፎችም፣ ድንጋዮችም፣ ከዋክብትም፣ ምንም ያህል ቢገዝፉም፣ የአላህን ኃያልነት የሚያስረዱ ምልክቶች እንጂ ሌላ አለመሆናቸውን ገልጿል፡፡ ከሰው ልጅ አንድም በፍጥረተ-ዓለም ላይ ጫና ሊያሳድር የሚችል፣ አስደናቂ ኃይል ያለው የለም፡፡ መፍጠር፣ ማዘዝና ማዘጋጀት በርሱ ትዕዛዝ ስር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ ላቀ፡፡» (አል-አዕራፍ: 54)

የእነዚህን ፍጥረታት ግዝፈትና [ቂቅ አፈጣጠራቸውን ያስተዋለ ሰው፣ ፈጣሪያቸው ቻይና አስተናባሪ ጌታ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ ስለሆነም እርሱ የአምልኮ ዓይነቶች በሙሉ ሊፈፀሙለት የሚገባ እንደሆነም ያውቃል፡፡ እርሱ ፈጣሪ ነው፡፡ ከርሱ ሌላ ያለ ሁሉ ፍጡር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው፡፡ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡፡ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፤ እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)፡፡»

## 3 ስውርንና የወደፊትን ከአላህ ሌላ ማንም አያውቅም፡፡

ኢስላም ከአላህ ሌላ ስውርንና የወደፊትን የሚያውቅ እንደሌለ ተናግሯል፡፡ ከጠንቋይም ሆነ ከሟርተኞች መካከል ይህን አውቃለሁ ብሎ የሚል ውሸታም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፡ ከርሱ በስተቀር ማንም አያውቃቸውም፡፡»

ከፍጡራን ሁሉ የተከበሩትና የላቁት ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንኳን ለራሳቸው ጉዳትንም ሆነ ጥቅምን አያስገኙም፡፡ ስውርና የወደፊትንም የሚያውቁ አልነበሩም፡፡ በክብርም ሆነ ደረጃ ከርሳቸው በታች የሆነማ እንዴት (ሊያውቅና ሊኖረው) ይችላል?!! አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «አላህ የሻውን በስተቀር ለራሴ ጥቅምንም ጉዳትንም ማምጣት አልችልም፡፡ ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር፡፡ እኔ ለሚያምኑ ህዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው፡፡» (አል-አዕራፍ: 188)

## 4 ኢስላም በአዕዋፍ ገድ ማለትንና ማሟረትን እርም አድርጓል፡፡

ኢስላም በአዕዋፍ፣ በመልክ፣ በንግግርና በተለያዩ ነገሮች ገድ ማለትን፣ ማሟረትንና መሰል ነገሮችን እርም አድርጓል፡፡ መልካም ምኞትንና ለመጪው ብሩህ ተስፋና አመለካከት ማሳደርን አዟል፡፡

በአዕዋፍ ገድ የማለት ምሳሌ:- አንድ የወፍ ዓይነትን ሲመለከት፣ ከመንገዱ ወይም ከጉዞው በማሟረት የሚስተጓጎል ወይም የሚቀር፣ ወይም የወፉን ድምፅ በጉዞ ላይ ሆኖ ሲሰማ ጉዞውን ሳያጠናቅቅ አቋርጦ መመለስ ገድን በወፍ የመተንበይ ምሳሌ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነኚህ ነገሮች ማጋራት(ሺርክ) እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ «በአዕዋፍ ገድ ማለት ማጋራት ነው፡፡» (አቡዳውድ 3912፣ ኢብኑ ማጃህ 3538)

ምክንያቱም ይህ ነገር አንድ ሙስሊም ውስጥ ከሰረፀ፣ አላህ የፍጥረተ-ዓለም አስተናባሪ ነው፤ የሩቅን የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው፤ ከርሱ ሌላ ማንም አያውቅም ከሚለው እምነቱ ጋር ይቃረናል፡፡ በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ኢስላም መልካም ግምትንና ጥሩን መጠበቅን፣ በአላህ ላይ መልካም ግምት ማሳደርን አዟል፡፡ ይህን የሚጠቁሙ ቃላቶችን ምርጫ ማድረግ እንዳለብንም ነግሯል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልካም ምኞትን ወይም ግምትን ይወዱ ነበር፡፡ እሱም መልካም ቃል ነው፡፡ (አህመድ 8393)

## 3 በአላህ አምላክነት ማመን

### በኃያሉ አላህ የማመን ትርጉም:-

ግልፅም ሆነ ድብቅ የአምልኮ ዓይነቶች ሁሉ የሚገቡት ለኃያሉ አላህ ብቻ ነው ብሎ በቁርጠኝነት አምኖ መቀበል ማለት ነው፡ ሁሉንም የአምልኮ ዓይነቶች ለአላህ ብቻ እናውላለን፡፡ ዱዓእን፣ ፍራቻን፣ መመካትን፣ እርዳታ መፈለግን፣ ሰላትን፣ ዘካንና ፆምን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከአላደህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡፡ "አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እርሱ እጅግ በጣም ርኅሩኅ አዛኝ ነው፡፡" (አል-በቀራህ:163)

አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን አላህ ነግሮናል፡፡ ይህ ማለት የሚመለከው አንድ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ከአላህ ሌላ አምላክ ተደርጎ ሊይያዝ የሚገባው ነገር የለም፡፡ ከርሱ ውጭ ማንም አይመለክም፡፡

## በአላህ አምላክነት የማመን አስፈላጊነት፡-

በአላህ አምላክነት የማመን አስፈላጊነትን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ግልፅ እንዲሆን ማድረግ፡-

1 ሰውም ሆነ ጋኔን የተፈጠረበት ዓላማ ነው፡፡ እነዚህ የተፈጠሩት አላህን በብቸኝነትና ያለምንም ተጋሪ ለመግዛት ነው፡፡ አላህም እንዲህ ብሏል...«ጋኔንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡» (አል-ዛሪያት፡56)

2 የአላህ መልእክተኞች የተላኩት መለኮታዊ መፅሐፍት የወረዱት ለዚሁ ዓላማ ነው፡፡ ዓላማቸው በእውነት መመለክ የሚገባው አላህ መሆኑን ለማፅናት ሲሆን ከርሱ ውጭ በሚመለኩ ነገሮች ደግሞ ለመካድ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል... “በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ በማለት መልእክተኛን በእርግጥ ልከናል፤” (አል-ነሕል፡36)

3 በሰው ልጅ ላይ የመጀመሪያው ግዴታ አላህን በብቸኝነት መገዛት ነው፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሙዓዝ ቢን ጀበልን ወደ የመን ለሰበካ በላኩት ጊዜ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነገር ነግረውት ነበር፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት... “የመፅሐፍቱ ባለቤት የሆኑ ህዝቦች ክርስቲያኖች /አይሁዶች/ ያጋጥሙሃል በመጀመሪያ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም ወደ ሚለው ቃል ጥራቸው፡፡” (አል-ቡኻሪ፡1389 ሙስሊም፡19)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ለማለት የፈለጉት “በሁሉም የአምልኮ ዓይነቶች አላህን ብቻ አምልኩ በላቸው፡፡” ለማለት ነው፡፡

4 “ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም” የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም፥ በአላህ አምላክነት ማመን ነው፡፡ አምላክ ማለት የሚመለክ ማለት ነው፡፡ ከአላህ በቀር በዕውነት የሚመለክ የለም፡፡ ማንኛውም የአምልኮ ዓይነት ከርሱ ውጭ ለማንም አናውልም፡፡

5 በአላህ አምላክነት ማመን፣ አዕምሮ የሚመራው አሳማኝ የሆነ፣ አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ፣ ባለቤትና አዘጋጅ ነው ብሎ የማመን ውጤት ነው፡፡



## > አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው?

አምልኮ (ኢባዳ) ማለት:- አላህ የሚወደውና የሚደሰትበት እንዲሁም ንግግሮችንና ተግባራትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ሲሆን ሰዎች ይተገብሩት ዘንድ አላህ ያዘዘው ተግባር ነው:: ይህ ተግባር እንደ ሶላት፣ ዘካ፣ ሐጅ ግልፅ ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) እንደ መውደድ፣ አላህን እንደ መፍራት፣ በርሱ እንደመመካትና ከርሱ እርዳታን እንደመፈለግ ስውር ተግባር ሊሆን ይችላል:: ሌሎችም እንደዚሁ::



> የአላህን ምንዳ መከጀል ዓላማ ያደረገ (ኒያ ያለው) ማንኛውም ተግባር እንደ አምልኮ (ዒባዳ) የሚቆጠር ሲሆን፣ በዚህ ተግባርም ምንዳ (አጅር) ይገኝበታል::

### በሁሉም የህይወት ዘርፍ አላህን ስለማምለክ:-

ወደ አላህ መቃረብን ዓላማው ያደረገ የማንኛውም አማኝ ሙእሚን ተግባር በአምልኮ ዒባዳ ውስጥ ይካተታል::

በእስልምና ሃይማኖት መሠረት አምልኮ በሶላት፣ በፆምና በመሳሰሉ የፀሎት ስነ-ሥርዓቶች የተገደበ ነገር አይደለም:: ይልቁንም ማንኛውም ዓይነት ጠቃሚ ተግባር መልካም የሆነን ዓላማ (ኒያ) እስካነገበ ድረስ፥ የአምልኮ ተግባር እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን ተግባሪውም አላህ ዘንድ ይመነዳበታል::

የአላህ ትዕዛዝ በአግባቡ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ አካላዊ ጥንካሬ ለማግኘት በሚል ዓላማ አንድ ሙስሊም ቢመገብ፣ ቢጠጣና ቢተኛ አላህ ዘንድ ምንዳ ያገኝበታል::

ስለዚህ ሙስሊም ህይወቱን በሙሉ ለአላህ እያስገዛ ነው ማለት ነው:: አላህን ለመታዘዝ ሰውነቱ ይጠነክር ዘንድ ይመገባል:: በዚህ ዓላማ በመመገቡ አላህን እያመለከ ነው:: ከአመንዝራነት ራሱን ለመጠበቅ በሚል ዓላማ ትዳር ይመሰርታል:: ጋብቻው በራሱ የአምልኮ ተግባር ይሆንለታል:: ልክ እንደዚሁ ዓላማው ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ ንግዱ፣ ሥራው፣ ቢዝነሱ ሁሉ አምልኮ ይሆንለታል:: እውቀት መፈለጉ፣ መመራመሩ፣ መፈላሰፉ፣ መፍጠሩ ሁሉ እንደ አምልኮ ይቆጠርለታል::

አንዲት እንስት ባልዋን፣ ልጆቿንና ቤቷን መንከባከቧ በርሱ የአምልኮ ተግባር ይሆንላታል::

በሁሉም የህይወት ዘርፍ የሚከናወኑ ጠቃሚ ተግባራት በሙሉ መልካም ዓላማና ዕቅድን መነሻ አድርገው እስከተፈፀሙ ድረስ እንደ አምልኮ ተግባር ይቆጠራሉ::

### አምልኮ (ዒባዳ) ሰው የተፈጠረበት ዓላማ ነው:-

አላህ እንዲህ ይላል... "ጋኔንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም:: ከነርሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፤ ሊመግቡኝም አልሻም:: አላህ እርሱ ሲሳይን ሰጪ የብርቱ ኃይል ባለቤት ነው::" (አል-ዛሪያት:56-58)

አላህ ሰውንም ሆነ ጋኔን የፈጠረበት ጥበብ እርሱን ይግገዙ ዘንድ እንደሆነ ተናግሯል:: እነዚህ ፍጥረታት አላህን የሚግገዙት ለራሳቸው ጥቅም እንጂ አላህ ከእነርሱ ጥቅም ፈላጊ ሆኖ አይደለም::

ሰው የተፈጠረበትን መለኮታዊ ይህን ዓላማ ዘንግቶ በዓለማዊ ህይወት ውስጥ ሰጥሞ ከቀረ፥ በዚህ ምድር ላይ ካሉ ሌሎች ፍጥረታት የሚለየው ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው:: እንስሳቶች ከሰው በተቃራኒ በቀጣዩ ዓለም ስለሰሩት ሥራ አይጠየቁም እንጂ እነርሱም ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይፈነጥዛሉ::

አላህ እንዲህ ብሏል... "... እነዚያም የካዱት (በቅርቢቱ ዓለም) ይጠቀማሉ፤ እንስሳዎችም እንደሚበሉ ይበላሉ እሳትም ለነርሱ መኖሪያቸው ናት::" (ሙሐመድ:12)

ተግባርና ዓላማቸው ከእንስሳ ጋር ተመሳስሏል፡፡ ነገርግን ከእንስሳ የሚለያቸው በመጨረሻው ቀን የስራቸውን ውጤት ማግኘታቸው ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ምንም ከማያውቁት እንስሳት በተለየ አዕምሮ ያላቸው፣ የሚገነዘቡና የሚያውቁ በመሆናቸው ነው፡፡

## የአምልኮ (ዒባዳ) መሠረቶት

አላህ እንተገብረው ዘንድ ያዘዘን አምልኮ በሁለት ዋና ዋና መሠረቶች ላይ የተገነባ ነው፡-

አንደኛ፡- ሙሉ የሆነ ፍራቻና መተናነስ፡-

ሁለተኛ፡- ሙሉ የሆነ ውዴታን ለአላህ ማዋል፡-

አላህ በባሮቹ ላይ ግዴታ ያደረገው አምልኮ፥ ለአላህ ብቻ የሚውል ሙሉ የሆነ ፍራቻ፣ መተናነስና ዝቅ ማለትን በውስጡ ያካተተ ከመሆኑ ጎን ለጎን ሙሉ የሆነ ውዴታና ከጃሎትን ለአላህ ብቻ ማዋልን ይጠይቃል፡፡

ስለሆነም ልክ ምግብን ወይም ገንዘብን እንደምንወደው ሁሉ አላህንም ፍራቻና መተናነስን ባላካተተ አኳኋን የምንወደው ከሆነ አምልኮ አይባልም፡፡

ልክ እንደዚሁ አውሬና ጨቋኝ መንግስትን እንደምንፈራው ሁሉ አላህንም ውዴታን ባላጎዳኘ አኳኋን የምንፈራው ከሆነ ከአምልኮ አይቆጠርም፡፡

ሆኖም ግን በስራችን ውስጥ ውዴታንና ፍራቻን ካቆራኘን ትክክለኛ አምልኮን አስገኘተናል፡፡ አምልኮ ደግሞ ሊውል የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው፡፡



## የአምልኮ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

አምልኮ የተስተካከለና አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ከተፈለገ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. የመጀመሪያው አምልኮን ያለ ምንም ተጋሪ ለአላህ ብቻ ማዋል ሲሆን
2. ሌላው ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከአከናወኑት የአምልኮ ተግባር ጋር የሚጣጣምና የሚስማማ መሆን ይኖርበታል፡፡

አላህ እንዲህ ብሏል "አይደለም እርሱ በጎ ሰሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ የሰጠ ሰው ለርሱ በጌታው ዘንድ ምንዳው አለው፤ በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነሱም አያዝኑም፡፡" (አል-በቀራህ፡112)

በዚህ አንቀፅ ውስጥ "ፊቱን ለአላህ የሰጠ ሰው" ማለት፥ የአላህን አንድነት በተግባር ያረጋገጠና አምልኮን ለርሱ ብቻ ያጠራ ማለት ነው፡፡

"በጎ ሰሪ ሆኖ" የሚለው ደግሞ፥ የአላህን ህግና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) አርዓያነት የሚከተል ማለት ነው፡፡

ሥራን ከመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ሱንና (መንገድ) ጋር ማጣጣም ማለት እንደ ሶላት፣ ፆምና አላህን ማውሳት የመሳሰሉት ተግባራትን እርሳቸው ባከናወኑት መሠረት መፈፀም ማለት ነው፡፡

ነገር ግን ሌሎች የዕለት ተዕለት ተግባራትን ለጥሩ ዓላማ (ኒያ) እስካከናወናቸው ድረስ ከአምልኮ ተግባራት ተርታ የሚመደቡ ቢሆንም፥ ከአላህ መልእክተኛ ሱንና ጋር የግድ እንዲጣጣሙ ማድረግ አይጠበቅብንም፡፡ ባይሆን መጠንቀቅ የሚኖርብን ሸሪዓውን የሚቃረን ሐራም ነገር ላይ ላለመውደቅ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የአላህን ትዕዛዝ ለመተግበር ጠንካራ ያደርገው ዘንድ ስፖርት ቢሰራ ወይም የቤተሰቡንና የልጆቹን ወጪ ለመሸፈን ስራ ቢሰራ ኒያውን እስካሳመረ ድረስ እንደ አምልኮ ተግባር ቢቆጠርለትም ከሱንና ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ግዴታ አይደለም፡፡

## > ሺርክ (የአምልኮ ተግባርን ከአላህ ዉጪ) ላለ አካል ማጋራት

- ሺርክ በአላህ አምላክነት ላይ ያለንን እምነት የሚፃረር ነገር ነው፡፡ በአላህ አምላክነት ማመንና የአምልኮ ተግባራትን ለርሱ ብቻ ማዋል ከታላላቅና ወሳኝ ከሆኑ ግዴታዎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ መሆኑ እርግጥ ከሆነ፥ ከዚህ በተመሳሳይ መልኩ ለአላህ ብቻ የሚገባውን የአምልኮ ተግባር ለሌላ አካል ማጋራት ደግሞ አላህ ዘንድ የወንጀሎች ሁሉ ቁንጮ ነው፡፡ ንሰሃ ካልገቡ በቀር አላህ በፍፁም የማይምረው ብቸኛ ወንጀል ነው፡፡

  አላህ እንዲህ ይላል... “አላህ በርሱ ማጋራትን በፍፁም አይምርም፤ ከዚህ ሌላ ያለውንም ኀጢአት ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡ በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ፡፡” (አል-ኒሳእ፡ 48)

  ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህ ዘንድ ከወንጀሎች ሁሉ ታላቁ ምን እንደሆነ ሲጠየቁ “አላህ ፈጥሮህ ሳለ ለርሱ ተጋሪ ማድረግህ ነው” በማለት መልሰዋል፡፡ (አል-ቡኻሪ፡ 4207 / ሙስሊም፡ 86)

- በአላህ ማጋራት ስራን በሙሉ ከንቱና ውድቅ ያደርጋል፡፡ አላህም እንዲህ ብሏል፡፡ ... “...ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ከነርሱ በታበሰ ነበር፡፡” (አል-አንዓም፡88)

  በአላህ አጋርቶ ንሰሃ ሳይገባ የሞተ ሰው ዕጣፈንታው ዘላለም በጀሃነም እሳት መቀጣት ይሆናል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡፡ ...”እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡” (አል-ማኢዳህ፡72)

### ሺርክ ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ ታላቅና ታናሽ

**1** ታላቁ ሺርክ፡- ይህ ማለት አንድን የአምልኮ (ዒባዳ) ዓይነት ከአላህ ውጪ ላለ አካል አሳልፎ መስጠት ማለት ነው፡፡ አንድ አላህ የሚወደውን ንግግርም ሆነ ተግባር ለአላህ ብቻ ካዋልነው አንድነቱን አፀደቅን ወይም አመንበት ማለት ነው፡፡ ይህን ተግባር ከርሱ ሌላ ለሆነ አካል ካዋልነው ደግሞ፥ ከደነዋል አጋርተንበታል፡፡

ለእንዲህ ዓይነቱ የሺርክ ተግባር ምሳሌን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ከአላህ ውጪ ያን አካል ከህመም እንዲያሽረን፣ ሲሳይን እንዲያሰፋልን ከጠየቅነውና ከለመንነው በታላቁ የሺርክ ተግባር ላይ ወድቀናል ማለት ነው፡፡ ከአላህ ውጪ ለሆነ ነገር ብንሰግድ ወይም በርሱ ላይ ብንመካም እንደዚያው ነው፡፡

አላህ እንዲህ ይላል ... “ጌታችሁም አለ፡- ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፤ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሃነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡” (አል-ሙእሚን፡60)

እንዲህም ይላል ... “... ምእምናንም እንደ ሆናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ አሉ፡፡” (አል-ማኢዳህ፡23)

ሌላ ሱራ ላይም እንዲህ ብሏል...”ለአላህም ስገዱ ተገዙትም፡፡” (አል ነጅም፡ 62)

እነዚህን ተግባራት ከአላህ ሌላ ላለ አካል ያዋለ ሰው አጋሪ እንዲሁም ከሃዲ ይሆናል፡፡

**2** ትንሹ ሺርክ፡- ይህ ደግሞ ወደ ታላቁ ሺርክ ሊያደርስ የሚችል ንግግር ወይም ተግባር ነው፡፡ ትንሹ ሺርክ ታላቁ ሺርክ ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

ለዚህኛው የሚሆን ምሳሌ መጥቀስም ይቻላል፡- ሰው እንዲያይለት በማሰብ ሶላትን ማስረዘም ወይም ሰዎች እንዲያደንቁት በማሰብ ቁርኣን ሲያነብ ወይም አላህን ሲዘክር ድምፁን ከፍ ማድረገና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) “እኔ ለእናንተ በጣም ከምፈራላችሁ ነገር ውስጥ አንዱ ትንሹ ሺርክ ነው፡፡” በማለት ሲናገሩ ሰሃቦችም “አንቱ የአላህ መልእክተኛ ትንሹ ሺርክ ምንድ ነው?” በማለት ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም “የይዩልኝ ስራ ነው፡፡” በማለት መልስ ሰጡ (አህመድ፡2363)

ሆኖም ግን ፍፁም ለሰው ተብሎ የሚደረግ የአምልኮ ተግባር ሶላትም ሆነ ፆም የመናፍቅ ሥራ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር ከእስልምና ሃይማኖት ውጪ የሚያደርግ ታላቅ የሺርክ ተግባር ነው፡፡

## ከሰው መፈለግና ሰውን አንዳንድ ነገር መጠየቅ የሺርክ ተግባር ነውን?

የእስልምና ሃይማኖት የተደነገገው የሰውን አዕምሮ ከንቱ ከሆኑ እምነቶች ነፃ ለማውጣት ነው፡፡ የተደነገገው የሰው ልጅ ከአላህ ውጪ ላለ አካል ዝቅ እንዳይል ነው፡፡

ለሙታንም ሆነ ግዑዝ ለሆኑ አካላት ዝቅ ብሎ በመተናነስ ፍላጎትን መጠየቅ ህገ-ወጥ የሆነ ተግባር ነው፡፡ ይህ ከንቱ እምነትና ሺርክ ነው፡፡

ነገር ግን አጠገባችን ያለንና ህይወት ያለውን ሰው አቅሙ የሚችለውን ነገር እንዲያደርግልን ብንጠይቀው ወንጀል አይደለም፡፡ ለምሳሌ ውሃ ውስጥ የሰጠመ ሰው ህይወቱን ያተርፈው ዘንድ ሰውን መጠየቁ፣ ወይም አንድ ሰው ዱዓእ እንዲያደርግልን ብንጠይቅ እስልምና የሚፈቅደው ህጋዊ ተግባር ነው፡፡



> በህይወት ያለና አጠገባችን የሆነን ሰው አቅሙ የሚፈቅደውን ነገር እንዲያደርግልን ብንጠይቀው፥ እንደ የዕለት ውሎ የሚቆጠር ህጋዊ የሆነ ተግባር ነው፡፡

ሙታንን ወይም ግዑዝ አካላትን መከጀልና መማፀን የሺርክ ተግባር ነውን?

አይቻልም(በፍፁም) | አዎን

**አዎን:**

ይህ ›=eLሀንና ኢማንን የሚቃረን ነው፡፡ ምክንያቱም ሙታንና ግዑዛን ነገሮች፣ ጥያቄውን መስማትም ሆነ ምላሽ መስጠት አይችሉም፡፡ ልመና (ዱዓ) አምልኮ ነው። በመሆኑም ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል አሳልፎ መስጠት ማጋራት ነው፡፡ ›=eLሀ በታወጀበት ዘመን የነበሩ ዐረቦች ያጋሩ የነበሩት ግዑዛንንና ሙታንን በመለመን ነበር፡፡

**አይቻልም(በፍፁም):**

ሕያው ሆኖ ጥያቄህንና ልመናህን ሊሰማ የሚችልን አካል መለመንህና መጠየቅህ፡፡ እርሱ በሚችለው ነገር ላይ እንዲረዳህና እንዲያግዝህ በጠየቅከው ዓይነት? ልመናህን ለመመለስና ጥያቄህን ለመስማት ይችላልን?

አይቻልም(በፍፁም) | አዎን

**አዎን:**

ይህ ተገቢ ልመና ነው፡፡ ምንም ችግር የለውም፡፡ በሰዎች ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ከሚከሰቱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡

**አይቻልም(በፍፁም):**

ከሕያው ሰው እርሱ የማይችለውን ነገር ከርሱ መፈለግ ወይም መከጀል ማለት አንድ መውለድ የማይችል መካን፣ ከሕያው ሰው ፃድቅ ልጅ እንዲሰጠው እንደመለመን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከኢስላም ጋር የሚቃረን ትልቁ የማጋራት ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ከአላህ ሌላ ያለን አካል መለመን ነውና፡፡

## > በአላህ ስሞችና ባህሪያት ማመን፡-

ይህ ማለት፥ አላህ በመፅሐፉ ውስጥ ወይም መልእክተኛው በስሱናቸው ያፀደቁትንና አላህ እራሱን የሰየመበትን ስም እንዲሁም ማንነቱን የገለፀበትን ባህሪ ለአላህ በሚገባው መልኩ ማመን ማለት ነው፡፡

ከጉድለት የጠራ የሆነው አላህ ምርጥ የሆኑ ስሞችና ሙሉዕ የሆኑ ባህሪያት አሉት፡፡ በስሙም ሆነ በባህሪያቱ ፍፁም አምሳያ የሌለው ጌታ ነው፡፡ እንዲህ ይለናል "የሚመስለው ምንም ነገር የለም እርሱም ሰሚው ተመልካቱ ነው፡፡" (አል-ሹራ፥11)

አላህ በሁሉም ስሞቹና ባህሪያቱ ከየትኛውም ፍጡር ጋር ፍፁም የማይመሳሰልና የጠራ ነው፡፡

### ከአላህ ስሞች ውስጥ የተወሰኑት፡-

አላህ እንዲህ ይላል "እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ" (አል-ፋቲሐህ፡3)

አላህ እንዲህ ይላል "እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡" (አል ሹራ፡11)(አል ሹራ 11)

አላህ እንዲህ ይላል "እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡" (ሉቅማን፡9)
አላህ እንዲህ ይላል "አላህ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፤" (አል-በቀራህ፡ 255)

አላህ እንዲህ ይላል "ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለሆነው፡፡" (አል-ፋቲሐህ፡2)



## በአላህ ስሞችና ባህሪያት የማመን ፍሬዎች:-

1 ኃያሉ አላህን ያሳውቀናል:- በአላህ ስሞችና ባህሪያት ያመነ ሰው ስለ አላህ ያለው እውቀት ይጨምራል:: በአላህ ላይ ያለው እርግጠኛ እምነትም ይጨምራል:: ስለ አላህ አንድነት ያለው ዕምነት ይጠነክራል:: የአላህን ስሞችና ባህሪያት ያወቀ ሰው፥ ቀልቡ በአላህ ታላቅነት፣ ውዴታና አክብሮት መሞላቱ የግድ ነው::

2 አላህን በስሞቹ ማወደስ እንችላለን:: ይህ ምርጥ ከሆኑ የዚክር (የውዳሴ) ዓይነቶች ውስጥ ይካተታል:: አላህ እንዲህ ይላል... "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት::" (አል-አሕዛብ: 41)

3 ስምና ባህሪውን ካወቅን፥ በስሞቹና በባህሪያቱ ልንማፀነው እንችላለን:: አላህ እንዲህ ይላል "ለአላህም መልካም ስሞች አሉት ስትፀልዩም በርሷም ጥሩት" (አል-አዕራፍ: 180)በምሳሌ ለማስረዳት ያህል:- አንተ ሲሳይን ሰጪ ሆይ! ሲሳይን ስጠኝ:: አንተ ይቅር ባይ ሆይ! ይቅር በለኝ:: አንተ አዛኝ ሆይ! እዘንልኝ... ማለት እንችላለን::


## ከፍ ያሉ የእምነት ደረጃዎች:-

እምነት የተለየዩ ደረጃዎች አሉት:: የአንድ ሙስሊም እምነት መዘንጋቱንና ሐጢአቱን መነሻ አድርጎ ሊቀንስ ይችላል:: ልክ እንደዚሁ ለአላህ ባለው ታዛዥነት፣ አምልኮና ፍራቻ ልክ እምነቱ ይጨምራል::

የእምነት ከፍተኛው ደረጃ ሸሪዓው እንዳለው «ኢህሳን» በሚል ይተወቃል:: ስለ «ኢህሳን» ምንነት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል... "አንተ ባታየው እንኳ እርሱ ያይሃልና፥ አላህን ስትገዛው እያየኸው እንደምትገዛው ሆነህ ተገዛው::" (አል-ቡኻሪ:50 ሙስሊም:8)

ቆመህም ሆነ ተቀምጠህ፣ በደስታም ሆነ በሃዘን ወቅት በአጠቃላይ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ሆነህ አላህን ማስታወስ ይኖርብሃል:: አላህ ምንግዜም በቅርበት ይመለከትሃል:: እየተመለከተህ መሆኑን ካወቅህ ወንጀል አትፈፅምም:: እርሱ ካንተ ጋር መሆኑን የምታውቅ ከሆነ ፍርሃትም ሆነ ተስፋ መቁረጥ አይቆጣጠሩህም:: በእርግጥ አላህን በሶላትህና በዱዓህ እያናገርከው ብቸኝነት ሊሰማህ አይችልም::

የሰወርከውንም ግልፅ ያደረግከውንም አላህ እንደሚያውቅ እየተገነዘብክ ነፍስህ ወደ ኃጢአት ልትገፋፋህ አትችልም::ኃጢአት ላይ ተዳልጠህና ተሳስተህ ከወደቅህ ደግሞ ወደ አላህ በመመለስ ምህረቱን ትማፀነዋለህ እርሱም ይምርሃል::





## አላህን የማመን ፍሬዎች፡-

1 አላህ ክፉ ነገሮችን ሁሉ ለምእመናን ይከላከልላቸዋል፡፡ ከጭንቅ ያድናቸዋል፡፡ ከጠላቶቻቸው ሴራም ይጠብቃቸዋል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል “አላህ ከነዚያ ካመኑት ላይ ይከላከልላቸዋል፡፡” (አል-ሐጅ ፡ 38)

2 በአላህ ላይ የሚኖረን እምነት መልካም የሆነን ህይወት፣ ደስታንና ፍስሃን ያጎናፅፋል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ... “ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሥራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤” (አል-ነሕል፡97)

3 እምነት ነፍስን ከከንቱ እምነቶች ፅዱ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በአላህ የሚያምን ሰው፥ ጉዳዩን ሁሉ ለአንድ አላህ ብቻ ይተዋል፡፡ እርሱ የዓለማት ጌታ ነው፡፡ እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ ከርሱ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም፡፡ በአላህ የሚያምን ሰው ፍጡርን አይፈራም፡፡ ማንንም ሰው በቀልቡ አይከጅልም፡፡ ከዚህም በላይ ከንቱና አላስፈላጊ ከሆኑ እምነቶች ራሱን ነፃ ያደርጋል፡፡

4 የኢማን ከፍተኛ ተፅዕኖ፡- የአላህን ውዴታ ያስገኛል፡፡ ጀነት ያስገባል፡፡ ቋሚና ዘላለማዊ ለሆነ የፀጋ ስኬት ያበቃል፡፡ ሙሉ የአላህ እዝነትን ያስገኛል፡፡

ኢምነትህ

## > በመላእክት ማመን

### በመላእክት የማመን ትርጓሜ

ይህ የመላእክትን መኖር፣ እነርሱ ከሰው ዘርም ከአጋንንትም ዓለም ያልሆኑ የስውር ዓለም ፍጡራን እንደሆኑ በቁርጠኝነት ማጽደቅ ነው፡፡ እነርሱ የተከበሩና አላህን ፈሪዎች ናቸው፡፡ አላህን ትክክለኛ የሆነ መገዛትን ይገዙታል፡፡ እርሱ ያዘዛቸውን በመፈፀም ያስተናብራሉ፡፡ በአላህ ላይ ፈፅሞ አያምጹም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «(መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው፡፡ በንግግር አይቀድሙትም (ያላለውን አይሉም) እነሱም በትዕዛዙ ይሰራሉ፡፡» (አል አንቢያ 26-27)

በእነሱ ማመን ከኢማን ስድስት መሠረቶች አንዱ መረት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «መልክተኛው ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ፡ ምዕመናኖችም (እንደዚሁ) ሁሉም በአላህ በመላእክቱም በመጻሕፍትቱም በመልክተኞቹም.... አመኑ፡፡» (አል በቀራ 285)

ኢማንን አስመልክተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ «በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍት፣ በመልዕክተኞች፣ በመጨረሻው ቀንና በክፉም በደጉም በአላህ ውሳኔ ልታምን ነው፡፡» (ሙስሊም 8)

### በመላእክት ማመን ምንን ያካትታል?

1 **በመኖራቸው ማመን፡** እነርሱ የአላህ ፍጥረታት እንደሆኑ እናምናለን፡፡ በተጨባጭ ያሉ ናቸው፡፡ አላህ የፈጠራቸው ከብርሃን ነው፡፡ እርሱን በመገዛትና በመታዘዝ ላይ አግርቷቸዋል፡፡

2 **ከነርሱ መካከል እንደ ጂብሪል** (ዐ.ሰ) በስሙ ያወቅነውን እስከነስሙ እናምናለን፡ በስማቸው ያላወቅነውናቸውንም በጥቅሉ እናምንባቸዋለን፡፡

3 **ከባህሪያቸው በምናውቀው ማመን፡፡ ከባህሪያቸው መካከል፡**

- እነርሱ የስውር ዓለም ፍጥረታት መሆናቸው፡፡ ለአላህ የሚገዙ ፍጡራን ናቸው፡፡ ከቶም የጌትነትም ሆነ የአምላክነት ባህሪ የላቸውም፡፡ እንደውም እነሱ አላህን ለመታዘዝ ሙሉ በሙሉ የተገሩ የአላህ ባሮች ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «አላህ ያዘዛቸውን በመጣስ አያምጡም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሰራሉ፡፡» (አል ተህሪም 6)

- የተፈጠሩት ከብርሃን ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ «መላእክት ከብርሃን ተፈጠሩ፡፡» ሙስሊም 2996

- ክንፎች አሏቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለመላእክት ክንፍን እንዳደረገ ተናግሯል፡፡ የክንፎቻቸው ብዛት ይበላለጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ምስጋና ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ፣ መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፣ ባለ ሦስት ሦስትም፣ ባለ አራት አራትም ክንፎች የኾኑ መልክተኞች አድራጊ ለኾነው አላህ ይገባው፤ በፍጥረቱ ውስጥ የሚሻውን ይጨምራል፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡» (ፋጢር 1)

4 በአላህ ትዕዛዝ መሰረት እነርሱ ከሚያከናውኗቸው ስራዎቻቸው ባወቅነው ማመን፡፡ ከነርሱ መካከል፡-

- መለኮታዊ ራዕይን ወደ መልክተኞች በማምጣት የተወከለ አለ፡፡ እሱም ጂብሪል (ዐ.ሰ) ነው፡፡
- ነፍስን በማውጣት የተወከለም አለ፡፡ እርሱም የሞት መልአክና ተባባሪዎቹ ናቸው፡፡
- መልካምም ሆነ እኩይ፣ የባሮችን ስራ መዝገቦ በማቆየት ወይም በመጠበቅ የተወከሉ አሉ፡፡ እነሱም የተከበሩ ፀሐፍት መላእክት ናቸው፡፡

### በመላእክት የማመን ፍሬ ወይም ጥቅም፡፡


በመላእክት ማመን በሙእሚን ሕይወት ውስጥ ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ ከነኚህ ጥቅሞች መካከል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፡፡

1 የአላህን ልቅና፣ ኃይል፣ ሙሉዕነትና ችሎታ ያሳውቃል፡፡ የፍጥረታት ትልቅነት የፈጣሪያቸውን ትልቅነት ያሳያል፡፡ በመሆኑም አንድ ሙዕሚን በመላእክት በማመኑ ለአላህ የሚሰጠው ደረጃና ለርሱ ያለው ከበሬታ ይጨምራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ብዙ ክንፎች ያሏቸው መላዕክትን ከብርሃን የፈጠረ ነው፡፡

2 አላህን በመታዘዝ ላይ ጽናትን ያጎናጽፋል፡፡ መላዕክት ስራዎቹን በሙሉ እንደሚፅፉ የሚያምን ሰው፣ ይህ እምነቱ የአላህ ፍራቻ እንዲያድርበት ያደርጋል፡፡ በይፋም ሆነ በድብቅ በአላህ ላይ አያምጽም፡፡

3 አንድ አማኝ በዚህ ሰፊ ዓለም ውስጥ አላህን የሚታዘዙ መላእክት አብረውት በተሟላና ባማረ መልኩ እንዳሉ በእርግጠኝነት በሚረዳ ጊዜ አላህን የመታዘዝ ትዕግስትን ይላበሳል፡፡ መላመድንና መረጋጋትን ያገኛል፡፡

4 ከመላእክት መካከል የሚጠብቋቸውና የሚከላከሉላቸው በማድረግ አላህ ለአደም ልጆች በቸረው ትኩረቱና ክትትሉ ማመስገን፡፡



> ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰማይ በውስጧ ባሉት ፍጥረታት እንደተጨናነቀች ተናግረዋል፡፡ በውስጧ የስንዝር ያክል ቦታ እንኳን ቢሆን የቆመ ወይም ያጎነበሰ፣ ሩኩዕ ያደረገ ወይም በግንባሩ የተደፋ፣ ሱጁድ ያደረገ መልአክ ቢኖር እንጂ ክፍት እንደማይሆን ተናግረዋል፡፡


# > በመጽሕፍት ማመን

## በመጽሐፍት የማመን ትርጓሜ

አላህ (ሱ.ወ) በመልከተኞቹ ላይ ወደ ባሮቹ ያወረዳቸው መጽሐፍት እንዳለው፣ እነኚህ መጽሐፍት በሙሉ የአላህ ቃልና ንግግር እንደሆኑ ማመን ነው:: ለክብርና ልቅናው ተገቢ በሆነ መልኩ በርግጥ ተናግሯል:: እነኚህ መጽሐፍት በውስጣቸው ለሰው ልጅ፣ ለሁለቱም ዓለም የሚሆን መመሪያና ብርሃን የያዙ እውነቶች ናቸው ማለትን በቁርጠኝነት ማረጋገጥ::

በመጽሐፍት ማመን ከኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ማዕዘን ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው፣ በዚያም በመልከተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፣ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ::» (አል ኒሳእ 136)

አላህ (ሱ.ወ) በርሱ በመልዕክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፣ በቁርአን እንድናምን አዟል:: ከቁርአን በፊት በተወረዱ መጽሐፍት ማመንን አዟል::



> የተከበረውን ቁርአን መፃፍ የሚከናወነው ረቀቅ ባሉ ስርዓቶች መሰረት፣ በብቃትና በጥራት ነው::

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢማንን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡ - «በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልዕክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና በክፉም በደጉም በአላህ ውሳኔ ልታምን ነው::» (ሙስሊም 8)

### በመጽሕፍት ማመን ምንን ያካትታል?

1. ከአላህ በትክክል የተወረዱ በመሆናቸው ማመን
2. የአላህ ቃል (ንግግር) መሆናቸውን ማመን
3. በነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ላይ እንደተወረደው ቁርኣን፣ በሙሳ(ዐ.ሰ) ላይ እንተወረደው ተውራት፣ በዒሳ(ዐ.ሰ) ላይ እንደተወረደው ኢንጂል ዓይነት አላህ በስም የጠራቸውን በስማቸው ማመን::
4. ከዜናዎቻቸው፣ በትክክለኛ ዘገባ የደረሱንን በእውነተኝነታቸው ማመን::

## የቁርአን ልዩ መገለጫዎች

የተከበረው ቁርአን በነብያችንና በአርአያችን በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የተወረደ የአላህ ቃል ነው:: በመሆኑም ሙእሚን ይህን" መጽሐፍ በእጅጉ ያልቀዋል:: ድንጋጌዎቹን ለመተግበርና አንቀፆቹን እያስተነተነ ለማንበብ ይጥራል::

ይህ ቁርአን በቅርቢቱ ዓለም መመሪያችን፣ በመጨረሻው ዓለም የስኬታችን ሰበብ መሆኑ ብቻ ልዩ ለመሆን ይበቃዋል::

የተከበረው ቁርአን በርካታ መለያዎች አሉት:: ከቀደሙት መለኮታዊ መጽሐፍት የሚነጥሉት የርሱ ብቻ የሆኑ የተለያዩ መገለጫዎችም አሉት:: ከነኚህም መካከል:-

1. የተከበረው ቁርአን የአምላከን ድንጋጌ ማጠቃለያ የያዘ መሆኑ:: በቀደምት መጽሐፍት ውስጥ ያለውን፣ አላህን በብቸኝነት የመገዛት ትዕዛዝን የሚያጠናክር ኾኖ ነው የመጣው::

   አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አወረድን» (አል ማኢዳ 48)


«ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭ» ማለት በቀደምት መጽሐፍት ውስጥ ከተነገሩ ዜናዎች፣ ከተላለፉ የእምነት አመለካከቶችና ጉዳዮች ጋር የሚስማማና የማይቃረን ማለት ነው፡፡ «በርሱ ላይ ተጠባባቂ» የሚለው ደግሞ ከርሱ በፊት የነበሩ መጽሐት ላይ የሚመሰክርና በአደራ የሚጠብቅ ማለት ነው፡፡

2 እነሆ  የሰው ልጆች በሙሉ በቋንቋና በጎሳ መለያየታቸው እንዳለ ሆኖ፣ ዘመናቸው ምንም እንኳ ከቁርኣን መወረድ በኋላ የመጣ  ቢሆንም እርሱን የመከተል፣ እርሱ ያቀፈውን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ቀደምት መጽሐፍት ግን የተወረዱት ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ለተወሰኑ ሕዝቦችና በተወሰነ ዘመን ላይ ነበር፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ይህም ቁርኣን እናንተንና የደረሰውን ሰው ሁሉ በርሱ ላስፈራራበት ወደኔ ተወረደ (በል)፡፡» (አል አንዓም 19)

3 አላህ (ሱ.ወ) የተከበረውን ቁርኣን የመጠበቁን ኃላፊነት ለራሱ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም የመቀየር፣ የመደለዝ፣ የመከለስና የመበረዝ  እጅ አልተሰነዘረበትም፡፡ ወደፊትም ለመቼውም አይዘረጋበትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤ እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡» (አል ሒጅር 9)

ስለሆነም በውስጡ ያሉ ዜናዎች በሙሉ ትክክለኛ ናቸው፡፡ ልንቀበለውም የግድ ይላል፡፡


## ቁርኣንን አስመልክቶ ያለብን ግዴታ ምንድን ነው?



- ቁርኣንን ልንወድ ይገባል፡፡ ደረጃውን ማላቅና እሱን ማክበርም ይገባል፡፡ እርሱ የፈጣሪ ንግግር ነው፡፡ ከንግግሮች ሁሉ ትክክለኛውና በላጩ እርሱ ነው፡፡
- ምዕራፎቹንና አንቀፆቹን በማስተንተን እርሱን ዘወትር ማንበብ አለብን፡፡ የቁርኣንን ተግሳጻት፣ ዜናዎችና ታሪኮች ልናስተነትን ይገባል፡፡ የሕይወታችንን ደካማና ጠንካራ ጎን ለመለየት ሕይወታችንን ለቁርኣን መስጠት አለብን፡፡
- ድንጋጌዎቹን ልንከተል፣ ትዕዛዛቶቹንና ስርዓቶቹን ልንተገብር፣ እንዲሁም የሕይወታችን መመሪያ ልናደርገው ይገባል፡፡

እመት ዓኢሻ(ረ.ዐ)፣ ስለ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባህሪ በተጠየቁ ጊዜ፣ «ባህሪያቸው ቁርዓን ነበር፡፡ « በማለት መልሰዋል፡፡ (አህመድ 24601/ሙስሊም 746)

የሐዲሱ መልክት፣ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፣ በኑሯቸውና በተግባራቸው የቁርዓንን ድንጋጌና ሕግጋት በመፈፀም የሚያሳዩ እንደነበሩ ይገልጻል፡፡ በርግጥም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለቁርኣን መመሪያ ሙሉዕ ተከታይነታቸውን አስመስክረዋል፡ ፡ እሳቸው ለእያንዳንዳችን ዓይነተኛ ተምሳሌታችን ናቸው፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣ በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፡፡» (አል አህዛብ 21)




> አንድ ሙስሊም ተውራትና ኢንጂል ከአላህ ዘንድ የተወረዱ እንደነበሩ ያምናል፡፡ ነገር ግን በርካታ ቅየራዎችና ድለዛዎች የተካሄደባቸው በመሆኑ ከቁርአንና ከሱና ጋር የሚጣጣመውን እንጂ በውስጣቸው ያለውን አንዱንም እውነት ብሎ አይቀበልም፡፡

## በቀደምት መጽሐፍት ውስጥ ስላለ ነገር ሊኖረን የሚገባ አቋም ምንድን ነው?

አንድ ሙስሊም፣ በነብዩላህ ሙሳ(ዐ.ሰ) ላይ የተወረደው ተውራት፣ በነብዩላህ ዒሳ(ዐ.ሰ) ላይ የተወረደው ኢንጂል፣ በትክክል ከአላህ ዘንድ የተወረዱ እንደነበሩ ያምናል፡፡ ሁለቱም በውስጣቸው ለሰው ልጆች ለዚች ዓለምና ለወዲያኛው ዓለም ሕይወታቸው መመሪያና ብርሃን የያዙ፣ ተግሳጻትን እንዲሁም ድንጋጌዎችንና ዜናዎችን አቅፈው የነበሩ መሆናቸውን ያምናል፡፡

ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) በቁርኣን ውስጥ የመጽሐፍት ባለቤት የሆኑት አይሁዶችና ክርስቲያኖች፣ መጽሐፍታቸውን እንደበረዙና እንዳበላሹ፣ ከመጽሐፍ ያልሆነን ነገር በውስጡ እንደጨመሩ፣ ከነበረውም እንደቀነሱ ነግሮናል፡፡ በመሆኑም በወረዱበት ይዘት ላይ አልቆዩም፡፡

አሁን ያለው ተውራት፣ በሙሳ(ዐ.ሰ) ላይ የተወረደው ተውራት አይደለም፡፡ ምክንያቱም አይሁዶች አጣመውታል፤ ለውጠውታል፡፡ በርካታ ድንጋጌዎቹን ተጫውተውበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከነዚያ አይሁዳውያን ከሆኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አሉ፡፡» (አል ኒሳእ 46)

አሁን ያለው ኢንጂልም ቢሆን በዒሳ(ዐ.ሰ) ላይ የተወረደው ኢንጂል አይደለም፡፡ ክርስቲያኖችም ኢንጂልን አጣመውታል፡፡ በርካታ በውስጡ የነበሩ ድንጋጌዎችን ለውጠዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ክርስቲያኖችን በማስመለከት እንዲህ ብሏል፡- «ከነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያላደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ፡፡ እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልኾነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ፡፡ እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ፡፡» (አለ ዒምራን 78)

«ከነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን፡፡ በርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታን ተዉ፤ ስለዚህ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው አላህም ይሰሩት የነበሩትን ሁሉ በእርግጥ ይነግራቸዋል፡፡» (አል ማኢዳ 14)

ዛሬ በመጽሐፍት ባለቤቶች እጅ የሚገኘው፣ ተውራትንና ኢንጂልን አካቷል ብለው የሚያምኑበት መጽሐፍ ቅዱስ፣ በውስጡ በርካታ ብለሹ የእምነት አመለካከቶችንና ትክክለኛ ያልሆኑ ዜናዎችን፣ እንዲሁም የውሸት ትረካዎችን ይዟል፡፡ ስለሆነም ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቁርኣን ወይም ትክክለኛ የሐዲስ ዘገባ እውነትነቱን ያጸደቀውን በስተቀር እውነት ብለን አናምንበትም፡ ፡ ቁርኣንና ሀዲስ ያስተባበሉትን

ደግሞ እናስተባብላለን፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነውን በዝምታ እናልፋለን፡፡ እውነት ብለን አናጸድቅም ውሸት ነው ብለንም አናስተባብልም፡፡

እንዲህ ከመሆኑም ጋራ፣ አንድ ሙስሊም እነኚህን መጽሐፍት አያንኳስስም፤ አያራክስም፣ ምክንያቱም ምናልባት በውስጣቸው ያልተበረዘና ያልተለወጠ የአላህ ንግግር ቅሪት ሊኖር ይችላል፡፡

## በመጽሐፍት የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ

በመጽሐፍት ማመን በርካታ ጥቅሞች ወይም ፍሬዎች አሉት፡፡ ከነዚህ ጥቅሞች መካከል፡

1. አላህ (ሱ.ወ) ከምእመናን ላይ አደጋን በጠቅላላ ይመክታል፡፡ ከመከራና ስቃይ ውስጥ ያወጣቸዋል፡፡ ከጠላቶቻቸው ሴራም ይጠብቃቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «አላህ ከነዚያ ካመኑት ላይ ይከላከልላቸዋል፡፡» (አል-ሐጅ፡ 38)

2. አላህ በድንጋጌዎቹ ውስጥ ያለውን ጥበብ ወይም ምክንያታዊነት ማወቅ፡፡ ይኸውም ለያንዳንዱ ሕዝብ ተጨባጭ ሁኔታውን የሚመጥንና ከባህሪው የሚስማማ የሆነ የራሱ ልዩ ድንጋጌ የደነገገለት መሆኑ ነው፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፡» (አል ማኢዳ 48)

3. እነኚህን መጽሐፍት በማውረድ ለተከሰተው የአላህ ጸጋ ምስጋና ማቅረብ፡፡ እነኚህ መጽሐፍት በዱንያም በአኺራም ብርሃንና መመሪያ ናቸው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዳችን ለዚህ ታላቅ የአላህ ጸጋ ምስጋና ማቅረብ ይጠበቅብናል፡፡



## > በመልዕክተኞች ማመን

### የሰው ልጅ መለኮታዊ መልዕክት ያስፈልገዋል፡፡



ለሰው ልጆች ሕግጋትን የሚያብራራላቸውና ወደ ትክክለኛው ጎዳና የሚመራቸው ከጌታ የሆነ መልዕክተኛ ሊኖራቸው የግድ ይላል፡፡ መለኮታዊ መልዕክት የዓለም እስትንፋስና የሕይወት ብርሃን ነው፡፡ መንፈስ፣ ሕይወትና ብርሃን የሌለው ዓለም እንዴት ዓይነት ሕልውና ሊኖረው ይችላል?

አላህ (ሱ.ወ) መልክቱን ሩሕ ሲል የሰየመው ለዚህ ነው ፡፡ ሩሕ ከሌለ ሕይወት የለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦ «እንደዚሁም ወደ አንተ ከትዕዛዛችን ሲኾን መንፈስን (ቁርኣንን) አወረድን፡፡ መጽሐፉም እምነቱም ምን እንደሆነ የምታውቅ አልነበርክም፡፡ ግን (መንፈሱን) ከባሮቻችን የምንሻውን ሰው በርሱ የምንመራበት ብርሃን አደረግነው፡፡ አንተም ወደ ቀጥተኛው መንገድ በርግጥ ትመራለህ፡፡» (አል ሹራ 52)

ይኸውም የሰው ልጅ አዕምሮ በጥቅሉ ጠቃሚና ጎጂ ነገሮችን መለየት የሚችል ቢሆንም፣ በመልዕክተኞች አማካይነት ካልሆነ በስተቀር በረቀቀ መልኩ መጥፎውንና መልካሙን የሚለይበት መንገድ አይኖረውም፡፡

በሁለቱም ዓለም ደስታም ሆነ ስኬት ሊገኝ የሚችልበት መንገድ በመልዕክተኞች እጅ የሚገኘው ብቻ ነው፡፡ ክፉና ደጉንም በረቀቀ መልኩ የሚለየው መንገድ የነርሱ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ፣ መልዕክተኞች ካስተላለፉት መልዕክት ጀርባውን የሰጠ ሰው ለመልዕክቱ ተቃራኒ በሆነበትና ጀርባውን በሰጠበት ልክ አለመረጋጋት፣ ጭንቀትና መረበሽ ያገኘዋል፡፡

### በመልዕክተኞች ማመን ከኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ነው፡፡

በመልዕክተኞች ማመን ከስድስቱ የኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦ «መልዕክተኛው ከጌታው ወደ እርሱ በተወረደው አመነ፡፡ ምእመናንም (እንደዚሁ)፤ ሁሉም በአላህ፤ በመላዕክቱም፤ በመጽሐፍቱም፣ ከመልዕክተኞቹ በአንድም መካከል አንለያይም (የሚሉ ሲሆኑ ) አመኑ፡፡» (አልበቀራ 285)

አንቀጹ፣ በመልዕክተኞች መካከል ምንም ሳይለያዩ በሁሉም ማመን ግዴታ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ አይሁዶችና ክርስቲያኖች እንዳደረጉት በከፊሎቹ አምነን በከፊሎቹ አንክድም፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የኢማን ማዕዘናትን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፦ «በአላህ በመላበአላህ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና በክፉም በደጉም በአላህ ውሳኔ ልታምን ነው፡፡» (ሙስሊም 8)

## በመልዕክተኞች የማመን ትርጓሜ

አላህ (ሱ.ወ) በእያንዳንዱ ሕዝብ ውስጥ ከነርሱው የሆኑ፣ አላህን በብቸኝነት ወደ መገዛት የሚጣሩና ለርሱ ተጋሪ እንደሌለው የሚያስተምሩ መልዕክተኞችን የላከ መሆኑን በቁርጠኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡ መልዕክተኞች ሁሉም እውነተኞችና እውነተኝነታቸው በአምላክ የተረጋገጠ ነው፡፡ አላህን በእጅጉ የሚፈሩና ታማኞች ናቸው፡፡ ወደ ትክክለኛው ጎዳና የተመሩና የሚመሩ ናቸው፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እነርሱን የላከበትን ነገር በሙሉ አድርሰዋል፡፡ ከርሱ ምንም የደበቁትም ሆነ የቀየሩት ነገር የለም፡፡ ከራሳቸው ዘንድ አንዲትም ፊደል በውስጡ አልጨመሩም አልቀነሱምም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በመልዕክተኞቹም ላይ ግልጽ ማድረስ ብቻ እንጂ ሌላ የለባቸውም፡፡» (አል ነሕል 35)



## በመልዕክተኞች ማመን ምንን ያካትታል?

1 መልዕክታቸው በትክክልና በቀጥታ ከአላህ ዘንድ ነው የተላለፈው ብሎ ማመን፡፡ የመልዕክተኞች ሁሉ ጥሪ፣ አላህን ያለአጋር በብቸኝነት ወደ ማምለክ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በየ ሕዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖትንም ራቁ በማለት መልዕክተኛን በእርግጥ ልከናል፡፡» (አል ነህል 36)

በርግጥ የየነብያቱ ደንብና ስርዓት ንዑስ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሊለያይ ይችላል፡፡ ከነኚያ ከተላኩባቸው ሕዝቦች አንጻር የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከናንተ ለሁሉም ህሕግና መንገድን አደረግን፡፡» (አል ማኢዳ 48)

2 በነብያትና በመልክተኞች በሙሉ ማመን፡፡

አላህ በስማቸው የነገረንን ከነስማቸው እናምንባቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ሙሐመድ፣ ኢብራሒም፣ ሙሳ፣ ዒሳ፣ ኑሕ (ዐለይሂሙ ሰላም) .... ከነሱ መካከል ስማቸውን የማናውቃቸውን ደግሞ በጥቁሉ እናምንባቸዋለን፡፡ ከነሱ መካከል አንዱን የካደ ሁሉንም ከዷል፡፡

3 በቁርኣንና በሐዲስ የተጠቀሱ የመልዕክተኞችን ገድልና ተዓምራት እውነት ነው ብሎ መቀበል፡፡ ለምሳሌ ለነብዩላህ ሙሳ (ዐ.ሰ) ባሕሩ የተሰነጠቀላቸው መሆኑን ማመን፡፡

4 ወደ እኛ የተላኩትን መልዕክተኛ ህግና ስርዓት መተግበር፡፡ እሳቸውም ከሁሉም በላጩና መቋጫ የሆኑት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው፡፡

## የመልዕክተኞች መገለጫ

| | |
|---|---|
| 1 | መልዕክተኞች የሰው ዘር ናቸው:: <br> በነሱና በሌላው ሰው መሐከል ያለው ልዩነት፣ አላህ (ሱ.ወ) በመለኮታዊ ራዕይና መልዕክት የመረጣቸው መሆኑ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ከአንተም በፊት ወደ እነሱ የምናወርድላቸው የኾኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም::» (አል አንቢያእ 7) <br> የጌትነትም ሆነ የአምላክነት ደረጃ የላቸውም:: <br> ነገር ግን በውጫዊ ተክለ ሰውነታቸው ምንም እንከን የሌላቸው፣ የሙሉዕነትን ደረጃ የደረሱ ሲሆን በስ-ነምግባራቸውም በሙሉዕነት የመጨረሻውን ጣራ የነኩ ናቸው:: በተጨማሪም በጎሳቸውም የተከበረ ጎሳ አባል ናቸው:: እንዲሁም ብሩህ አዕምሮና ማራኪ ልሳን የተቸሩ ናቸው:: ይህም የመልዕክቱን ውጣ ውረድ በአግባቡ እንዲሸከሙ አድርጓቸዋል:: የነብይነትን ፈተናም በብቃት እንዲወጡ አግዟቸዋል:: <br> አላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኞችን ከሰው ዘር ያደረገበት ምክንያቱ የሰዎች ተምሳሌቶች ከራሳቸው እንዲሆን ነው:: በመሆኑም መልዕክተኞችን መከተልና እነርሱን በተምሳሌትነት መያዝ በሰዎች ሊከናወን የሚችልና በችሎታቸው ስር ያለ ጉዳይ ነው:: |
| 2 | አላህ (ሱ.ወ) መልዕክቱን በማስተላለፉ ለይቷቸዋል:: <br> ከሌላው ሰው ነጥሎ እነርሱን መለኮታዊ ራዕዩን እንዲረከቡ መርጧቸዋል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደ እኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ::» (አል ካሕፍ 110) <br> የነብይነት ማዕረግም ሆነ መለኮታዊ መልዕክት፣ በመንፈሳዊ ምጥቀት ወይም በጮሌነት ወይም በአዕምሮ ብስለት የሚያገኙ ነገር አይደለም:: <br> እሱ የአላህ መምረጥና ማጨት ነው:: አላህ (ሱ.ወ) ከሰዎች መካከል መልዕክተኞችን መርጦ አጭቷቸዋል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «አላህ መልክቱን የሚያደርግበትን ስፍራ ዐዋቂ ነው::» (አል አንዓም 124) |
| 3 | እነርሱ ከአላህ በሚያስተላልፉት መልዕክት ከስህተትና ከመርሳት የተጠበቁ ናቸው:: ከአላህ በሚያስተላልፉት መልዕክት አይሳሳቱም:: አላህ ወደ እርነሱ የላከውንም በማስፈፀም አይሳሳቱም:: |
| 4 | እውነተኝነት: <br> መልዕክተኞች በንግግራቸውም በተግባራቸውም እውነተኞች ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ይህ አዛኙ ጌታ የቀጠረን፣ መልዕክተኞቹም እውነትን የነገሩን ነው::» (ያሲን 52) |
| 5 | ትዕግስት: <br> መል፡ክተኞች ወደ አላህ ሃይማኖት አብሳሪና አስጠንቃቂ በመሆን በርግጥ ተጣርተዋል:: በዚህም የተለያዩ ስቃዮችና መከራዎች ደርሰውባቸዋል:: ሁሉንም የሚደርስባቸውን መከራና ስቃይ የአላህን ቃል የበላይ በማድረግ ጉዞ ላይ በትዕግስት ተሸክመው አልፈዋል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ከመልዕክተኞችም የቆራጥነት ባለቤት የነበሩት እንደታገሱ ሁሉ ታገስ::» (አል አሕቃፍ 35) |

### የመልዕክተኞች ምልክቶችና ታዓምራታቸው

አላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኞቹን በማስረጃና ተያያዥነት ባላቸው የተለያዩ ነገሮች እውነተኝነታቸውንና ነብይነታቸውን በማረጋገጥ ረድቷቸዋል:: ከዚህም መካከል በሰው ልጅ ችሎታ የማይከሰቱ በሆኑ ታዓምራትና ግልጽ በሆኑ ምልክቶች ያደረገላቸው እገዛ ወይም ድጋፍ አንዱ ነው:: ይህም የሆነው እውነተኝነታቸውን ለማጽደቅና ነብይነታቸውን ለማጽናት ነው::

ታዓምራት የሚባለው ተለምዶን ጥሰው የሚከሰቱ ነገሮችን ነው:: ይኸውም አላህ (ሱ.ወ) በነብያቱና በመል፡ክተኞቹ አማካይነት ይፋ የሚያደርገው ሲሆን ሰዎች መሰሉን ሊያመጡ ወይም ሊያስከስቱ የማይችሉት እንደሆነ በመፎካከር መልክ የሚከሰት ነው::

## ከነብያት ተዓምራት መካከል:

- የነብዩላህ ሙሳ(ዐ.ሰ) በትር ወደ እባብነት መቀየር:

* ነብዩላህ ዒሳ(ዐ.ሰ) ሕዝቦቻቸው በቤቶቻቸው ውስጥ ስለሚመገቡትና ስለሚያከማቹት ምግብ መናገራቸው፡
* ለነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጨረቃ መሰንጠቅ፡

## በዒሳ(ዐ.ሰ) ዙሪያ ያለው የሙስሊም እምነት

1 **እርሱ ዒሳ(ዐ.ሰ) ከታላላቅ መልዕክተኞች አንዱና ስብዕናው እጅግ የላቀ ነው፡፡** እነኚህ ከመልዕክተኞች መካከል ስብዕናቸው እጅግ የላቀ ነቢያት የቆራጥነት ባለተቤት በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነርሱም ሙሐመድ' ኢብራሒም' ኑሕ' ሙሳና ዒሳ ናቸው (አለይሂሙ ሰላም)፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) በሚከተለው ቃሉ ዘክሯቸዋል፡- «ከነብዮችም የጠበቀ ቃልኪዳናቸውን በያዝን ጊዜ (አስታውስ)፤ ከአንተም፣ ከኑሕም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም፣ ከመርየም ልጅ ዒሳም(በያዝን ጊዜ አስታውስ)» (አል አሕዛብ 7) ይላል፡፡

2 **ነብዩላህ ዒሳ(ዐ.ሰ) የኣደም ዝርያ ሰው ነው፡፡**

አላህ (ሱ.ወ) ወደ ነገደ ኢስራኢል የላከው ሲሆን የተለያዩ ተዓምራት በርሱ እጅ እንዲፈፀሙ አድርጓል፡፡ ምንም ዓይነት የጌትነትም ሆነ የአምላክነት ደረጃ የለውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት ለኢስራኢልም ልጆች ታምር ያደረግነው የሆነ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ » (አል ዙኽሩፍ 59)

ነብዩላህ ዒሳ(ዐ.ሰ) ሕዝቦቹን፣ እሱንም ሆነ እናቱን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው እንዲይዟቸው ፈፅሞ አላዘዘም፡፡ ለነርሱ ያላቸው አላህ ያዘዘውን ብቻ ነበር፡፡ «ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ» (አል ማኢዳ 117)

3 **እሱ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፡፡**

እናቱ መርየም፣ ፃድቅ፣ እውነተኛ፣ ለጌታዋ ፍፁም ታዛዥና ተገዢ፣ ጥብቅ፣ ጨዋና ድንግል ሴት ነች፡፡ ዒሳን(ዐ.ሰ) የፀነሰችው ያለአባት በአላህ (ሱ.ወ) ችሎታ ነው፡፡ የእርሱ አፈጣጠር ዘልዓለማዊ ተዓምር ነው፡፡ ልክ ኣደምን ያለአባት እና ያለእናት እንደፈጠረው ሁሉ እርሱንም ያለ አባት ፈጠረው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ ኣደም ብጤ ነው፡፡ ከዐፈር ፈጠረው ከዚያም ለርሱ (ሰው) ሁን አለው ሆነም፡፡» (አል ዒምራን 59)

4 **በርሱ በዒሳ(ዐ.ሰ) እና በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መሐከል የተላከ መልዕክተኛ የለም፡፡** ስለ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ትንቢት ተናግሮ አብስሯል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የመርየም ልጅ ዒሳም፡ የኢስራኢል ልጆች ሆይ! እኔ ከበፊቴ ያለውን ተውራትን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደ እናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ) በግልጽ ታዕምራት በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ፡፡» (አሥ ሦፍ 6)

5 **አላህ (ሱ.ወ) በእርሱ እጅ እንዲፈፀሙ ባደረጋቸው ታዓምራት እናምናለን፡፡** ለምፃምን ማዳኑን፣ አይነ ስዉራን ማብራቱን፣ ሙታንን ማስነሳቱን፣ ሰዎች በቤታቸው ውስጥ ስለሚበሉትና ስለሚያከማቹት መናገሩን እናምናለን፡፡ ሁሉም በአላህ ፍቃድ የተፈፀሙ ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ለነብይነቱና ለመልዕክተኝነቱ ትክክል ለመሆኑ ግልጽ የሆነ ማስረጃ አድርጎታል፡፡

6 **ዒሳ(ዐ.ሰ) የአላህ ባሪያና መልክተኛ ነው ብሎ እስከሚያምን ድረስ የአንድም ሰው ኢማን የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡** አይሁዶች እርሱን ከገለጹበት የቅጥፈትና ፀያፍ ነገሮች ሁሉ የጸዳና የጠራ እንደሆነም እናምናለን፡፡

በዒሳ እውነተኛ ማንነት ዙሪያ የተሳሳቱትን የክርስቲያኖች አመለካከትም እናወግዛለን፡፡ ይኸውም እሱና እናቱን ከአላህ ሌላ አማልክት ማድረጋቸው ነው፡፡ ከፊላቸው እርሱ የአላህ ልጅ ነው ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ ከስላሴዎች አንዱ ነው ብለዋል፡፡ አላህ እነርሱ ከሚሉት ሁሉ የላቀ ነው፡፡

7 **አላህ (ሱ.ወ) አይሁዶች ዒሳን(ዐ.ሰ) ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ወደ ሰማይ ከፍ አደረገውና አሳረገው እንጂ እሱ አልተገደለም አልተሰቀለምም፡፡** አላህ (ሱ.ወ) የእርሱ ምስል በሌላ ሰው ላይ እንዲሆን አደረገ እናም ያንን ሰው ዒሳ መስሏቸው ገደሉት ሰቀሉትም፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው) አልገደሉትም አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፡፡ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም በእርግጥም አልገደሉትም፡፡ ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡ ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት በርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጅ (አንድም) የለም በትንሳኤም ቀን በነሱ ላይ መስካሪ ይኾናል፡፡ » (አል ኒሳእ 157-159)

አላህ (ሱ.ወ) እርሱ ዘንድ ወደ ሰማይ እንዲያርግ በማድረግ ጥበቃ አድርጎለታል፡፡ በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ይወርዳል፡፡ በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ሕግና ስርዓት ይዳኛል፡፡ ከዚያም በዚ‹ ምድር ይሞታል፤ በሷም ውስጥ ይቀበራል፡ ፡ ሌሎች ሰዎች እንደሚቀሰቀሱት የትንሳኤ ቀን ይቀሰቀሳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ በርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን ከርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን፡፡» (ጧሃ 55)

## በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነብይነትና መልዕክተኝነት ማመን

❖ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እናምናለን:: እርሳቸው የመጀመሪያዎችም የኋለኞችም አለቃና የነብያት መቋጫ ናቸው:: ከርሳቸው ብኋላ የሚነሳ ነብይ የለም:: መልዕክታቸውን አድርሰዋል:: አደራቸውን ተወጥተዋል:: ሕዝባቸውን መክረዋል:: በአላህ መንገድ መታገል የሚገባቸውን ያክል ታግለዋል::

❖ እርሳቸው የተናገሩትን በሙሉ እንቀበላለን:: ያዘዙትን እንተገብራለን:: ከከለከሉትና ካስጠነቀቁት ነገር እንርቃለን:: እርሳቸው በዘረጉልን መስመር መሰረት አላህን እንገዛለን:: ከርሳቸው ባሻገር ማንንም በአርዓያነት አንከተልም:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ::» (አል አሕዛብ 21)

❖ ለወላጅ፣ ለልጅ፣ በአጠቃላይ ለሰዎች ካለን ውዴታ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ውዴታ ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «አንዳችሁም እኔ እርሱ ዘንድ ከወላጆቹ፣ ከልጆቹና ከሰዎች በሙሉ የበለጠ ተወዳጅ እስካልሆንኩ ድረስ አያምንም::» (አል ቡኻሪ 15/ ሙስሊም 44) እርሳቸውን በትክክል መውደድ ማለት ፈለጋቸውን መከተል፣ መመሪያቸውን መንገድ ማድረግ ነው:: ትክክለኛ ደስታም ሆነ ሙሉዕ መመራት ሊረጋገጥ የሚችለው እርሳቸውን በመታዘዝ ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ብትታዘዙትም ትመራላችሁ፤ በመልክተኛውም ላይ ግልጽ ማድረስ እንጂ ሌላ የለበትም::» (አል ኑር 54)

❖ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያስተላለፉትን በሙሉ መቀበል አለብን:: ለፈለጋቸውም ታዛዦች መሆን ይኖርብናል:: የእርሳቸውን መመሪያ ትልቅ ስፍራና ክብር ልንቸረው ያስፈልጋል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ፣ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍፁም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም::» (አል ኒሳእ 65)

❖ የእርሳቸውን ትዕዛዝ ከመጻረርና ከመቃረን ልንጠቀቅ ይገባል:: ምክንያቱም የርሳቸውን ትዕዛዝ መቃረን ለፈተና፣ ለጥመትና ለአሳማሚ ቅጣት ይዳርጋል:: አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «እነዚያም ትዕዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ» (አል ኑር 63)

## የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ልዩ ይዘት

የነብዩ ሙሐመድ መልክት ከቀደምት መልዕክቶች ለየት የሚያደርጉት በርካታ ይዘቶች አሉት:: ከነዚህም መካከል:-

❖ **የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት የቀደምት መልዕክቶችን መልዕክት የሚቋጭ መሆኑ::** አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም:: ግን የአላህ መልዕክተኛና የነብዮች መደምደሚያ ነው::» (አል አሕዛብ 40)

❖ **የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ቀደምት መልዕክቶችን የተካ መሆኑ::** ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ከተላኩ ብኋላ አላህ (ሱ.ወ) እርሳቸውን ከመከተል ውጭ ምንም ዓይነት ሃይማኖትን አይቀበልም:: በርሳቸው ጎዳና እንጂ አንድም ሰው ወደ ጀነት ጸጋ መድረስ አይችልም:: እርሳቸው ከመልዕክተኞች ሁሉ የተከበሩ ናቸው:: ሕዝባቸውም ከሕዝቦች ሁሉ ምርጥና በላጭ ሕዝብ ነው:: ሕግጋታቸውም ከሕግጋት ሁሉ የተሻለና የተሟላ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው::» (አል ዒምራን 85)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል: «የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ: ከዚህ ሕዝብ ውስጥ የሁድም ሆነ ክርስቲያን አንድም ሰው ስለኔ ሰምቶ በተላኩበት የማያምን አይኖርም ከእሳት ጓዶች ቢሆን እንጂ» (ሙስሊም 153 / አህመድ 8609)

❖ **የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መልክት ሁለቱንም ፍጡሮች ማለትም አጋንንትንም ሰውንም የሚመለከት መሆኑ::** አላህ (ሱ.ወ) ጅኖች ያሉትን ሲያወሳ እንዲህ ብሏል:- «ወገኖቻችን ሆይ የአላህን ጠሪ ተቀበሉ::»

(አል አሕቃፍ 31) « አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢኾን እንጂ አልላክንህም ::» (ሰበእ 28)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል: «በስድስት ነገሮች ከነብያት ተልቄያለሁ: ጥቅላዊ የንግግር ስልትን ተሰጥቻለሁ፤ ጠላትን በማስፈራት ታግዥለሁ፣ ምርኮ ተፈቅዶልኛል፣ ምድር ንፁሕና የጸሎት ስፍራ ተደርጋልኛለች፣ ወደ ፍጡራን በመሉ ተልኬያለሁ፣ ነብያት በእኔ ተደምድመዋል::» (አል ቡኻሪ 2815 / ሙስሊም 523)

## በመልዕክተኞች የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ

በመልዕክተኞች ማመን ከባድ ጥቅም አለው ከነዚህም መካከል

1 አላህ(ሱ.ወ) ለባሮቹ ያለውን ርህራሄና እንክብካቤ ማወቅ፡

ይኸውም መልዕክተኞቹን ወደ ነርሱ በመላክ ወደ ቀጥተኛው ጎዳና እንዲመሯቸውና በምን መልኩ አላህን ማምለክ እንዳለባቸው እንዲያብራሩላቸው በማድረጉ ነው፡፡ የሰው ልጅ አዕምሮ ይህን የማወቅ ችሎታ የለውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ስለ ነብያችን ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፡- «(ሙሐመድ ሆይ) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡» (አል አንቢያእ 117)

2 በዚህ ታላቅ ጸጋው ላይ አላህን ማመስገን

3 መልዕክተኞችን መውደድ፣ ማላቅና ለነሱ በሚገባ መልኩ እነሱን ማድነቅና ማሞገስ፡፡ ምክንያቱም እነሱ አላህን በመገዛት፣ መልዕክቱን በማድረስና ለባሮቹ መልካምን በማስተማር ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋልና ነው፡፡

4 መልዕክተኞች ከአላህ ዘንድ የተላኩበትንና ይዘው የመጡትን መልዕክት መከተል፡

እሱም አላህን በብቸኝነት ማምለክና ለርሱ ተጋሪ አለማድረግ ነው፡፡ እርሱንም በተግባር መተርጎም ነው፡፡ በዚህም ምእመናን በሁለቱም ዓለም መመራትን ስኬትንና መልካሙን ሁሉ ያገኛሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከኔም የኾነ መሪ ቢመጣላችሁ መሪየን የተከተለ አይሳሳትም አይቸገረምም፡፡ ከግሳጼዬም የዞረ ሰው ለርሱ ጠባብ ኑሮ አለለው፡፡» (ጧሃ 123-124)



> የአቅሷ መስጂድ ሙስሊሞች ልብ ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው፡፡ በምድር ላይ ከሐረም መስጂድ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የተሰራ መስጂድ ነው፡፡ ነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) እና የተቀሩት ነብያትም በውስጡ ሰግደዋል፡፡

# > በመጨረሻው ቀን ማመን

## በመጨረሻው ቀን የማመን ትርጓሜ

አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን ከቀብር ይቀሰቅሳል ከዚያም በስራዎቻቸው ይተሳሰባቸዋል በዚያም ይመነዳቸዋል፤ በዚህም የጀነት ነዋሪዎች በማረፊያቸው ይረጋሉ፤ የእሳት ነዋሪዎችም በማረፊያቸው ይረጋሉ፤

ብሎ በቁርጠኝነት ማመን ነው፡፡

በመጨረሻው ቀን ማመን ከኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ነው፡፡ በርሱ ሳያምኑ ኢማን ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ግን መልካም ስራ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ሰው ነው»» (አል በቀራ 177)

## ቁርኣን በመጨረሻው ቀን በማመን ላይ ትኩረት ያደረገው ለምንድን ነው?

ቁርኣን በመጨረሻው ቀን በማመን ላይ ለየት ያለ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በየአጋጣሚው ሁሉ ስለሱ አሳስቧል፡፡ በተለያየ የዐረበኛ አገላለጾች የርሱን ተከሳችነት አጽንኦት ሰጥቶታል፡፡ በበርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመጨረሻው ቀን ማመንን በአላህ ከማመን ጋር አስተሳስሮታል፡፡

ምክንያቱም በአላህና በፍትሃዊነቱ ማመን በመጨረሻው ቀን ማመንን ያስገድዳል፡፡ የዚህ ማብራሪያም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

አላህ (ሱ.ወ) በደልን አይቀበልም፡፡ በዳይን ሳይቀጣ፣ ተበዳይንም ሳይክስ አይተውም፡፡ መልካም ሰሪን ሳይመነዳና ሳይከፍለው አይቀርም፡፡ ሁሉንም ባለ መብት የሚገባውን መብት ይሰጠዋል፡፡ በዚች ዓለም ላይ በዳይ ሆኖ የሚኖር፣ በዳይ ሆኖ የሚሞት፣ ነገር ግን ምንም የማይቀጣ ሰው እንመለከታለን፡፡ በተቃራኒው ተበዳይ ሆኖ የሚኖር ተበዳይ ሆኖ የሚሞት ግን አንድም መብቱ የማይመለስለት ሰው እናያለን፡፡ ታዲያ አላህ በደልን አይቀበልም የሚለው ትርጓሜ ምንድነው? ትርጓሜው ከዚህ ሕይወት ሌላ እኛ ዳግም የምንኖርበት ሌላ ሕይወት አለ ማለት ነው፡፡ የግድ ሌላ የምላሽ ሕይወት ይኖራል፡፡ መልካም ሰሪ የሚመነዳበት፣ መጥፎ የሰራም የሚቀጣበት፣ ሁሉም ባለ መብት የሚገባውን መብት የሚያገኝበት ዓለም ይኖራል፡፡



> ኢስላም ግማሽ የቴምር ፍሬን በመለገስ እንኳን ቢሆን ለሌሎች መልካም በመዋል ከእሳት እንድንርቅ ያዘናል፡፡

## በመጨረሻው ቀን ማመን ምንን ያካትታል?

አንድ ሙስሊም በመጨረሻው ቀን ማመኑ በርካታ ጉዳዮችን በውስጡ ያካትታል፡፡ ከነዚህ ጉዳዮች መካከል፡-

1 በመቀስቀስና በመሰብሰብ ማመን፡- ሙታን ከመቃብራቸው ወጥተው ሕያው እንዲሆኑ ይደረጋሉ ፡፡ ሩሐቸውም ወደየገላዎቻቸው ይመለሳሉ፡፡ ሰዎች የዓለማት ጌታ ፊት ይቆማሉ፡፡ ከዚያም ጫማ ሳይጫሙ እርቃናቸውን ልክ መጀመሪያ ሲፈጠሩ እንደነበሩት ሆነው በአንድ ስፍራ ይሰበሰባሉ፡፡

በመቀስቀስ ማመን በቁርኣንና በሐዲስ የተነገረ ጉዳይ ነው፡፡ ጤናማ አዕምሮና የተፈጥሮ ባህሪም ያጸደቁት ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጠኝነት አላህ (ሱ.ወ) በቀብሮች ውስጥ ያለን እንደሚቀሰቅስ፣ ነፍሶች ወደየገላዎቻቸው እንደሚመለሱ፣ ሰዎች በጠቅላላ የዓለማት ጌታ ፊት እንደሚቆሙ እናምናለን፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ፡፡ ከዚያም እናንተ በትንሳኤ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ፡፡» (አልሙዕሚኑን 15-16)

መለኮታዊ መጽሐፍት በሙሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ይስማማሉ፡፡ የአላህ (ሱ.ወ) ጥበበኝነት በውስጡ ያዘለውም ይህንኑ ነው፡፡ ይኸውም አላህ (ሱ.ወ) በተጣለባቸው በእያንዳንዱ ኃላፍነት ፍጡራን የሚመነዱበት የሆነ መመለሻ ዓለም እንዳዘጋጀ በመልክተኞቹ ልሳን መናገሩ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን፣ እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን? (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን?)» (አል ሙዕሚኑን 115)

### መቀስቀስን የሚያረጋግጡ የቁርኣን ማስረጃዎች

- የሰው ልጅን ያለ አንዳች ቀዳሚ ምሳሌ የፈጠረው አላህ ነው፡፡ ያለ አንዳች ቀዳሚ ምሳሌ የፈጠረ ደግሞ መልሶ ማስገኘት፣ ወደነበረበት መመለስ አይሳነውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እርሱም ያ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ነው፡፡» (አል ሩም 27)

አላህ (ሱ.ወ) አጥንቶች ከበሰበሱ በኋላ እንደነበሩ መመለሳቸውን ለሚያስተባብል ሰው ምላሽ እንዲሰጥበት ሲያዝ እንዲህ ብሏል፡- « ያ በመጀመሪያ ጊዜ ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፤ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ(ኹኔታ) ዐዋቂ ነው በለው፡፡» (ያሲን 79)

- ምድር ምንም ዓይነት ዛፍም ሆነ አረንጓዴ ተክል የማይታይባት ኾና ከደረቀችና ከሞተች በኋላ፣ አላህ (ሱ.ወ) ዝናብ ያወርድባታል፡፡ እንደ አዲስ በአረንጓዴ ትሸፈናለች፡፡ ከእያይነቱ ቡቃያን ታበቅላለች፡፡ እናም ምድርን በዚህ መልኩ ሕያው ማድረግ የቻለ ጌታ ሙታንንም ሕያው ማድረግ ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን፤ በርሱም አትክልቶችንና የሚታጨድን (አዝመራ) ፍሬ አበቀልን፡ ፡ ዘምባባንም ረዣዥም ለርሷ የተደራረበ እንቡጥ ያላት ስትሆን (አበቀልን) ለባሮቹ ሲሳይ ትኾን ዘንድ (አዘጋጀናት) በርሱም የሞተችን አገር ሕያው አደረግንበት (ከመቃብር) መውጣትም እንደዚሁ ነው፡፡» (ቃፍ 9-11)

- ማንኛውም ማገናዘብ የሚችል ሰው የሚረዳው ነገር ቢኖር አንድ ትልቅና ከባድን ነገር መከወን የቻለ ከሱ በታች የሆነን ነገር በሚገባ መከወን እንደሚችል ጥርጥር የሌለው መሆኑን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እጅግ በጣም ግዙፍ፣ ሰፋፊ፣ ውስብስብና ድንቅ ፍጥረቶች ከመሆናቸው ጋር ሰማያትን፣ ምድርንና ከዋክብትን ያለ አንዳች ቀዳሚ ናሙና ፈጥሯቸዋል፡፡ በመሆኑም የበሰበሱ አጥንቶችን ሕያው በማድረግ ቻይ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ አይደለምን? ነው እንጅ እርሱም በብዙ ፈጣሪና ዐዋቂው ነው፡፡» (ያሲን 81)

2 በምርመራና በሚዛን ማመን፡ አላህ (ሱ.ወ) ፍጡራኑን በዱንያ ሕይወት ሲሰሩት በነበረው ስራቸው ይመረምራቸዋል፤ ይተሳሰባቸዋል፡፡ የአሃዳዊነት፣ የተውሂድ አራማጆች የሆኑ፣ አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዙ፣ ምርመራቸው እጅግ በጣም ገር ነው፡፡ ከአጋሪያን የሆነ አመጸኛ ደግሞ ምርመራው እጅግ በጣም ብርቱ ነው፡፡

ስራዎች ትልቅና ከባድ በሆነ ሚዛን ይመዘናሉ፡ ፡ መልካም ስራዎች በአንድ ጎን፣ ክፉ ስራዎች ደግሞ በሌላኛው ጎን ይደረጋሉ፡፡ የመልካም ስራው ክብደት ከመጥፎው ስራው የበለጠና ሚዛን የደፋለት ከጀነት ሰዎች ይሆናል፡፡ የመጥፎ ስራው ክብደት ከመልካም ስራው የበለጠና ሚዛን የደፋበት ደግሞ ከእሳት ሰዎች ይሆናል፡፡ ጌታህ ማንንም አይበድልም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ስራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ፡፡» (አል አንቢያእ 47)

3

**ጀነትና እሳት:** ጀነት የዘልዓለማዊ ጸጋዎች ዓለም ናት፡፡ ጀነት አላህ (ሱ.ወ) እርሱን ለሚፈሩ፣ እሱና መልክተኛውን ለሚታዘዙ ምዕመናን ያዘጋጃት ናት፡፡ በውስጧ ነፍሶች የሚፈልጉት ዘውታሪ የሆኑ የጸጋ ዓይነቶች በሙሉ አሉ፡፡ በሷ ውስጥ የሚወደዱ ነገሮች ሁሉ የዓይን መርጊያዎች ሲሆኑ ይገኛሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) የጎን ስፋቷ ብቻ የሰማያትና የምድርን ያክል የሆነችውን ጀነት ለመግባት በታዛዥነት ላይ ባሮቹ እንዲሽቀዳደሙ ሲያነሳሳና ሲያበረታታ እንዲህ ብሏል፡- «ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡» (አለ ዒምራን 133)

እሳት ደግሞ ዘልዓለማዊ መቀጫ ዓለም ናት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለካሃዲያን፤ ለነዚያ በአላህ ለካዱና መልክተኞች ላይ ላመጹት መቀጫ ትሆን ዘንድ ያዘጋጃት ናት፡፡ በውስጧ በአዕምሮ ውልብ ብሎ የማያውቅ፣ እጅግ በጣም አሳማሚ ቅጣት፣ ስቃይ፣ ሰቆቃና መከራ አለ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን ከዚች ለከሃዲያን መቀጫ ካዘጋጃት እሳት በማስጠንቀቅ መልክ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «ያችን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጊያዎች የኾነችውን እሳት ተጠበቁ፡ ለከሃዲዎች ተደግሳለች፡፡ » (አል በቀራ 24)

አምላካችን ሆይ ጀነትንና ከንግግርም ከስራም ወደርሷ የሚያቃርበውን እንድትለግሰን እንጠይቅሃለን፡፡ ከእሳትና ወደርሷ ከሚያቃርብ ንግግርና ስራም ባንተ እንጠበቃለን፡፡

4

**4.የቀብር ስቃይና ድሎቱ፡** ሞት እውነት መሆኑን እናምናለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በናንተ የተወከለው መልአከ ሞት ይገድላችኋል ከዚያም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ፡፡» (አል ሰጅዳ 11)

ይህ በተጨባጭ የሚመለከቱት፣ ጥርጥር የሌለው እውነታ ነው፡፡ የሞተ ወይም የተገደለ ብቻ በማንኛውም ሁኔታ ሕይወቱ ያለፈ ሰው፣ ይህ ቀነ ገደቡ እንደሆነና የሞተበት ሁኔታ ከዕድሜው ላይ ምንም እንደማያጎድል እናምናለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ለሕዝብም ሁሉ የተሰነ ጊዜ አላቸው፡፡ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰዓት አይቆዩም (ከጊዜያቱም) አይቀድሙም፡፡» (አል አዕራፍ 34)

❖ አንድ የሞተ ሰው ቂያማው ቆማበታለች፡፡ ወደ ወዲያኛው ዓለምም ተሸጋግሯል፡፡

❖ ለከሃዲያንና ለአማጽያን በቀብር ውስጥ ቅጣት እንደተዘጋጀ፣ ለምእመናንና ለጻድቅ ባሮች ደግሞ የድሎት ጸጋዎች እንደተደገሱ የሚያረጋግጡ በርካታ ሐዲሶች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተዘግበዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ እናምናለን፡፡ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ አንፈላፈልም፡፡ ምክንያቱም ይህ የስውሩ ዓለም ክስተትና አዕምሮ ተጨባጭ ሁኔቴውንና በምን ዓይነት እንደሚከሰት ሊደርስበት ስለማይችል ነው፡፡ ልክ እንደ ጀነትና እሳት የስዉሩ ዓለም ክስተት እንጂ የይፋዊ ዓለም ክስተት አይደለም፡፡ አዕምሮ ሊቀይስ፣ ሊመረምርና ሊወስን የሚችለው በነባራዊው ዓለም ተመሳሳይ ያለውንና የርሱን ስርዓት የሚከተልን ነገር ብቻ ነው፡፡

❖ የቀብር ሕይወት በስሜት ሕዋሳት የሚደረስበት አይደለም፡፡ ስውር ወይም ገይብ ሕይወት ነው፡፡ በሕዋስ የሚደረስበት ቢሆን ኖሮ በስውር ወይም ከሕዋስ በራቀ ነገር ማመንን ጥቅም አልባ ያደርገው ነበር፡፡ ኃላፊነት የተጣለበትንም ሚስጥር ፉርሽ ያደርጋል፡፡ ሰዎችም ባልተቀበሩ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አትቀባበሩም ማለትን ባልሰጋ ኖሮ አላህን እኔ የምሰማወን የቀብር ቅጣት እንዲያሰማችሁ እለምነው ነበር፡፡» (ሙስሊም 2868 /አል ነሳኢ 2958)

ከላይ የጠቀስነው ምክንያቶች በእንሳሳት ላይ ሰለሌሉ እነሱ ይህን እንዲሰሙ ተደርገዋል፡፡



## በመጨረሻው ቀን የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ

1 በመጨረሻው ቀን ማመን ሰዎችን በመልካም ስራ ላይ ስርዓት ይዘው እንዲዘወትሩ አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ እንዲሁም አላህን እንዲፈሩና ከሁሉ ለኔ ባህሪና ከይዩልኝ እንዲርቁ በማድረግ የጎላ ሚና አለው፡፡
አብዛኛውን ጊዜ መልካም ስራ በመጨረሻው ቀን ከማመን ጋር ተያይዞ የሚቀርበውም ለዚህ ነው ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የአላህን መስጂዶች የሚሰራው በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ነው፡፡»
(አል ተውባ 18) «እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የሚያምኑት እነርሱ በሶላታቸው ላይ የሚጠባበቁ ሲኾኑ በርሱ ያምናሉ፡፡ » (አል አንዓም 92)

2 በሕይወት ውጣውረድ እራሳቸውን በመወጠር አላህን በመታዘዝ ላይ ከመሸቀዳደም ለተዘናጉ፣ ወደ አላህ በመቃረብ ጊዜን ከመሻማት፣ እርሱን ከመታዘዝ፣ የዚችን ዓለም እውነተኛ ገጽታና አጭርነት ከማስተንተን፣ የወዲያኛውን ዓለም መርጊያነት ዘልዓለማዊነት ከማሰብ ለተዘናጉና ለረሱ ማሳሳቢያና ማስጠንቀቂያ አለበት፡፡
አላህ (ሱ.ወ)በቁርአን ውስጥ መልዕክተኞችን ስራቸውን በመጥቀስ ሲያወሳ፣ እነዚያን ስራዎችና የላቁ ገድሎች እንዲፈጽሙ ሰበብ የሆናቸውን ጉዳይ በማሞገስ ነበር ያወሳው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እኛ ጥሩ በኾነች ጠባይ መረጥናቸው (እርሷም) የመጨረሻይቱን አገር ማስታወስ ናት፡፡» ማለትም የነኚያ የተከበሩ ስራዎቻቸው መንስኤ እነርሱ የመጨረሻይቱን አገር በማስታወስ ለየት ያሉ መሆናቸው ሲሆን ይህም ማስታወሳቸው እነዚያን ስራዎችና አቋሞች እንዲኖራቸው ገፋፍቷቸዋል፡፡
እነርሱን ለማሳሰብና ለማስጠንቀቅ እንዲህ አለ፡- «የቅርቢቱን ሕይወት ከመጨረሻይቱ ይበልጥ ወደዳችሁን? የቅርቢቱ ሕይወት በመጨረሻይቱ (አንጻር) ጥቂት እንጂ አይደለም፡፡» (አል ተውባ 38)
የሰው ልጅ በመጨረሻው ቀን በትክክል በሚያምን ጊዜ ማንኛውም የዚች ዓለም ጸጋ ከመጨረሻው ዓለም ጸጋ ጋር ሊነጻጸር እንደማይችል እርግጠኛ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በወዲያኛው ዓለም ለአንዲት ቅጽበት የሚያገኘውን ቅጣት ምንም ሊያክለው አይችልም፡፡ በዚህም በዱንያ ላይ ያለ የቅጣት ዓይነትም ከመጨረሻው ዓለም ቅጣት ጋር ሊነጻጸር እንደማይችል ይገነዘባል፡፡ በሌላ በኩል እዚህ ያለ ተድላና ደስታ በወዲያኛው ዓለም ከሚያጋጥም የቅጽበት ጸጋ ወይም ድሎትና ደስታ ጋር አይስተካከልም፡፡

3 የሰው ልጅ በመጨረሻው ቀን ካመነ የስራውን ምንዳ ማግኘቱ አይቀሬ እንደሆነ እርግጠኛ ስለሚሆን ይረጋጋል፡፡ ስለሆነም የሆነ የዚህች ዓለም ጥቅም ቢያመልጠው ወይም ቢያጣው ተስፋ በመቁረጥና በመበሳጨት ነፍሱን በሐዘን አይገድልም፡፡ እንዳውም ታታሪ ሊሆንና አላህ (ሱ.ወ) የመልካም ሰሪን ምንዳ በከንቱ እንደማያስቀር እርግጠኛ ሊሆን ይገባል፡፡ የጎመን ዘር ቅንጣትን የሚያህል ነገር ከርሱ በግፍ ወይም ያለ አግባብ ቢወሰድበት ወይም ቢጭበረበር የትንሳኤ ቀን እሷ እጅግ በምታስፈልገው ወቅት ላይ ያገኛታል፡፡ ፈንታው ያለምንም ጥርጥር በጣም በሚያስፈልገው ወቅት ላይ እንደሚሰጠው ያወቀ ሰው እንዴትስ ያዝናል? በእርሱና በሞጋቹ መሐከል የሚዳኘውና የሚፈርደው የፍትሃውያን ሁሉ ፍትሃዊ የሆነው ጥበበኛው ዳኛ አላህ(ሰ.ወ) እንደሆነ ያወቀ እንዴትስ ይተክዛል?



# > በአላህ ውሳኔ (በቀደር) ማመን

## በአላህ ውሳኔ የማመን ትርጓሜ

ማንኛውም መልካምም ሆነ መጥፎ ነገር የሚከሰተው በአላህ ውሳኔና ፍርድ እንደሆነ በቁርጠኝነት ማረጋገጥ ነው:: እርሱ ያሻውን ሰሪ ነው:: በእርሱ ፍላጎት እንጂ የሚሆን አንድም ነገር የለም:: ከሱ መሻት የሚወጣ ነገርም የለም:: በዓለም ውስጥ ከርሱ ውሳኔ የሚወጣ ነገር የለም:: ከርሱ ማዘጋጀት ወይም ማስተናበር ባሻገር የሚከሰትም ነገር የለም:: ከዚህም ጋር ትዕዛዛትን እንዲፈፅሙ ባሮቹን አዟል:: ክልከላዎችንም ከልክሏቸዋል:: ለሚሰሯቸው ስራዎቻቸውም የመምረጥ ነጻነት ሰጥቷቸዋል:: አይገደዱም:: ስራቸው የሚከሰተው እንደ ችሎታቸውና እንደ ፍላጎታቸው ነው:: አላህ እነሱንም ችሎታቸውንም የፈጠረ እሱ ነው:: በእዝነቱ ያሻውን ያቀናል:: በጥበቡ ያሻውን ያጠማል:: እርሱ በሚሰራው አይጠየቅም እነርሱ ተጠያቂ ናቸው::

በአላህ ውሳኔ ማመን ከኢማን ማዕዘናት መካከል አንዱ ማዕዘን ነው:: ይኸው እውነታ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጂብሪል ስለ ኢማን ጠይቋቸው በሰጡት ምላሽ ላይ ተዘክሯል:- « በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልዕክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና በአላህ ውሳኔ በክፉውም በደጉም ልታምን ነው::» (ሙስሊም 8)



> በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ አንድም ነገር ከአላህ ውሳኔ ውጭ አይሆንም::

## በአላህ ውሳኔ ማመን ምንን ያካትታል?

በአላህ ውሳኔ ማመን አራት ዋና ዋና ጉዳዮችን ያካትታል

- አላህ (ሱ.ወ) በጥቅሉም ሆነ በዝርዝር ስለ ሁሉ ነገር ያውቃል ብሎ ማመን:: እነሆ እርሱ ፍጡራን በሙሉ በርግጥ ከመፈጠራቸው በፊት ያውቃቸዋል:: ሲሳያቸውን፣ ቆይታቸውን፣ ንግግራቸውንና ስራዎቻቸውን አስቀድሞ አውቆታል:: ሁሉንም እንቅስቃሲያቸውንና መርጊያቸውን፣ ሚስጥራቸውንና ይፋቸውን ያውቃል:: ከነርሱ ውስጥ ማናቸው የጀነት ጓዶች እንደሆኑና ማናቸው የእሳት ጓዶች እንደሆኑ አስቀድሞ ያውቃል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «እርሱ አላህ ነው:: ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የኾነ ነው::» (አል ሐሽር 22)

- አላህ(ሱ.ወ) ተግባራትን ሁሉ አስቀድሞ በለውሕ አል-መሕፉዝ ላይ አስፍሯቸዋል። ስለዚህ ማስረጃ የሚሆነው የሚከተለው አላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው።« በምድርም በነፍሳችሁም መከራ(ማንንም) አትነካም ስንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትኾን እንጂ።ይህ በአላህ ላይ ገር ነው (አል ሐዲድ:22) ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-« አላህ የፍጡራንን ችሮታ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ሃምሳ ሺህ አመታት በፊት ጽፏል።»(ሙስሊም 2653)

- እርሷን የሚያስተጓጉላት ምንም ነገር በሌላት፣ ተፈጻሚ በሆነችው በአላህ መሻት እና ምንም በማይሳነው በአላህ ችሎታ ማመን:: ማናቸውም ክስተት የሚከሰተው በአላህ መሻትና ችሎታ ነው:: እርሱ የሻው ይሆናል እርሱ ያልሻው አይሆንም:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- « የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም::» (አል ተክዊር 29)

- ማናቸውንም ነገር የሚያስገኘውና የሚያስከስተው ወይም የሚፈጥረው አላህ (ሱ.ወ) መሆኑን ማመን:: እርሱ ብቸኛ ፈጣሪ ነው:: ከርሱ ሌላ ያለ ነገር ሁሉ ፍጡር ነው:: እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ነገሩንም ሁሉ የፈጠረውና በትክክልም ያዘጋጀው ነው::» (አል ፉርቃን 2)

## የሰው ልጅ ምርጫ፣ ችሎታና ፍላጎት አለው፡፡

በአላህ ውሳኔ ማመን የሰው ልጅ በምርጫው በሚፈጽማቸው ተግባሮቹ ላይ ፍላጎትና ችሎታ አለው ከማለት ጋር አይቃረንም፤ አይጋጭም፡፡ ምክንያቱም የእስላማዊ ድንጋጌና ነባራዊ ተጨባጭ ክስተት ይህንን ለርሱ የሚያረጋግጡና የሚያጸድቁ ናቸው፡፡

ከእስላማዊ ድንጋጌ አንጻር አላህ (ሱ.ወ) መሻትን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፡- «ይህ የተረጋገጠው ቀን ነው፡፡ የሻም ሰው ወደ ጌታው መመለስን ይይዛል፡፡» (አል ነበእ 39)

ችሎታን በማስመልከትም አላህ እንዲህ ብሏል፡- «አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡ ለርስዋ የሰራችው አላት፡፡ በርስዋም ላይ ያፈራቺው (ኀጢአት) አለባት፡፡» (አል በቀራ 286)

ከነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ደግሞ ማንኛውም ሰው ችሎታና መሻት እንዳለውና በነርሱም የሚሰራውን እንደሚሰራ፣ የሚተወውንም እንደሚተው ያውቃል፡፡ እንደመራመድና መሰል እንቅስቃሴዎች ያሉ በፍላጎቱ የሚከሰቱትን፣ እንደመንቀጥቀጥና እንደ ድንገተኛ መውደቅ ያሉ ያለፍላጎቱ ከሚፈጸሙት ለይቶ ያውቃል፡፡ ነገር ግን የፍጡር መሻትና መቻል በአላህ መሻትና ችሎታ የሚከሰቱ ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከናንተ ቀጥተኛ መኾንን ለሻ ሰው (መገሰጫ ነው) ፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም፡፡» (አል ተክዊር 28-29)

በአንቀጹ ላይ እንደምንመለከተው መጀመሪያ የሰው ልጅን መሻት አጸደቀ፤ ከዚያም በአላህ መሻት ውስጥ የሚካተት እንደሆነ አሳሰበ፡፡ ምክንያቱም ፍጥረተ-ዓለሙ በጠቅላላ የአላህ ይዞታ ነው፡፡ በርሱ ይዞታ ውስጥ ደግሞ ከርሱ ዕወቀትና መሻት ውጭ የሚሆን ነገር አይኖርም፡፡




> «እኛ ወይ አመስጋኝ ወይም ከሃዲ ሲኾን መንገዱን መራነው (ገለጽንለት)» (አል ደህር 3)

## በአላህ ውሳኔ ማመካኘት

የግዳጅና ኃላፊነት፣ የትዕዛዝን የክልከላ ተያያዥነታቸው ከሰው ልጅ ችሎታና ምርጫው ጋር ነው። አንድ መልካም ሰሪ ቀናውን ጎዳና የመረጠ በመሆኑ ይመነዳል። መጥፎ ሰሪ ደግሞ እኩይ የሆነን የጥመት መንገድ በመምረጡ ይቀጣል።

አላህ (ሱ.ወ) የምንችለውን እንጂ አላስገደደንም። በመሆኑም አላህ በርሱ ውሳኔ በማመካኘት እርሱን ማምለክ መተውን ከአንድም ሰው አይቀበልም።

ከዚህም በተጨማሪ የሰው ልጅ ከማመጹ በፊት አላህ አውቆ የወሰነው ምን እንደሆነ አያውቅም። አላህ ደግሞ ችሎታና የመምረጥ ነጻነት ሰጥቶታል። የመልካምና የመጥፎን ጎዳና ነጣጥሎ አብራርቶለታል። በመሆኑም ካመጸ፣ አመጽን ለአላህ ታዛዥ ከመሆን በላጭ አድርጎ የመረጠው እራሱ ነው። በአመጸኛነቱ የሚያገኘውን ቅጣት የመሸከም ግዴታ አለበት።



> አንድ ሰው በአንተ ላይ ድንበር በማለፍ ንብረትህን ቢውስድብህና ቢያሰቃይህ፣ ከዚያም ለዚህ እኩይ ተግባሩ በርሱ ላይ አላህ የወሰነበት መሆኑን እንደ ምክንያት ቢያቀርብ ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖራትም። በፈጸመው በደል ትቀጣዋለህ፤ ንብረትህንም ታስመልሳለህ። ምክንያቱም ሰውየው ይህን የፈጸመው በምርጫውና በፍላጎቱ ስለሆነ ነው።

## በአላህ ውሳኔ የማመን ጥቅም ወይም ፍሬ

በአላህ ውሳኔ ማመን በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

1 በአላህ ውሳኔ ማመን በዚህ የሕይወት ቆይታ ንቁ ሆኖ፣ አላህ የሚወደውን በመፈፀሙ እንዲጥርና እንዲተጋ ከሚያደርጉ ነገሮች ዋነኛውና ትልቁ ነገር ነው፡፡

ምእመናን በአላህ ላይ ከመመካታቸው ጎን ለጎን የክስተት ሰበቦችን እንዲጠቀሙ ታዞዋል፡፡ ኢማን ማለት ደግሞ በአላህ ፍቃድ እንጂ የክስተት ሰበቦች ውጤት ሊያስገኙ እንደማይችሉ እርግጠኛ መሆን ነው፡፡ ምክንያቱም የክስተት ሰበቦችን የፈጠረው አላህ ነው፡፡ ውጤታቸውንም የፈጠረውም እሱ ነው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በሚጠቅምህ ነገር ላይ ታታሪ ሁን፡፡ በአላህ ታገዝ፡፡ አትሳነፍ፡፡ የሆነ (መሰናከል) ነገር ቢገጥምህ እንዲህ እንዲህ ባደረግ ኖሮ እንዲህ እንዲህ ይሆን ነበር አትበል፡፡ ነገር ግን አላህ ወሰነ ያሻውንም ፈፀመ በል፡፡ እንዲህ ቢሆን ኖሮ ማለት የሸይጣንን በር ትከፍታለች፡፡» (ሙስሊም 2664)

2 የሰው ልጅ የነፍሱን ልክ ማወቅ አለበት፡፡ ሊኮራም ሊኮፈስም አይገባም፡፡ ምክንያቱም እሱ በአላህ የተወሰነውን ነገርና ወደፊት የሚከሰተውን ክስተት ማወቅ የማይችል ደካማ ፍጡር ነው፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ምንጊዜም በደካማነቱና ወደ ፈጣሪው ከጃይ መሆኑን ማመን አለበት፡፡

የሰው ልጅ በተፈጥሮው መልካም ነገር ሲገጥመው ይኮራል በርሱም ይታለላል፡፡ መጥፎ ነገርና አደጋ ሲያጋጥመው ደግሞ ይበሳጫል፤ ይተክዛል፡፡ እናም የሰው ልጅን በአላህ ውሳኔ ከማመን በስተቀር መልካም ነገር ሲገጥመው ከመኮፈስና ድንበር ከማለፍ፣ እንዲሁም መጥፎ ነገር ሲገጥመው ከማዘንና ከመተከዝ ሊታደገው የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡ ማናቸውም የተከሰቱና የሚከሰቱ ነገሮች የአላህ ውሳኔ የተላለፈባቸውና አላህ አስቀድሞ ያወቃቸው ናቸው፡፡

3 በአላህ ውሳኔ ማመን ውግዝ ለሆነው ምቀኝነት እልባት ይሰጣል፡፡ አንድ ሙእሚን አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ሰዎችን አይመቀኝም፡፡ ለነርሱ የለገሳቸውና ይህንን ነገር የወሰነላቸው አላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡ እናም ሙእሚን ሌሎችን ሲመቀኝ በአላህ ውሳኔና ፍርድ ላይ እያመጸ መሆኑን ወይም ውሳኔውን እየተቃወመ እንደሆነ ያውቃል፤ ስለሆነም አይመቀኝም፡፡


4 በአላህ ውሳኔ ማመን በልብ ውስጥ ችግሮችን ለመጋፈጥ ጀግንነትን ይፈጥራል፡፡ ቁርጠኝነትንም ያጠናክራል፡፡ ምክንያቱ፣ በአላህ ውሳኔ ማመን የዱንያ ቆይታ (አጀል) ሲሳይ በአላህ የተወሰነ እንደሆነና የሰው ልጅን የሚያጋጥመው የተጻፈው ነገር ብቻ መሆኑን እርግጠኛ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ነው፡፡

5 በአላህ ውሳኔ ማመን በሙእሚን ነፍስ ውስጥ የተለያዩ የኢማን ጭብጦችን ይተክላል፡፡ እርሱ ምንጊዜም እገዛ የሚሻው ከአላህ ብቻ ነው፡፡ የክስተት ሰበቦችን ከመፈፀሙም ጋር የሚንተራሰውና የሚመካው በአላህ ላይ ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም ምንጊዜም ጌታውን ከጃይ ይሆናል፡፡ በጽናት ላይ እንዲያበረታው ከርሱ እገዛን ይፈልጋል፡፡

6 በአላህ ውሳኔ ማመን የመንፈስ እርጋታን ይፈጥራል፡፡ ሙእሚን፣፣ የደረሰበት ነገር መጀመሪያውኑ ሊስተው እንዳልነበረ፣ የሳተውም ነገር መጀመሪያውኑ ሊያገኘው እንዳልነበረ ያውቃል፡፡



# ንፅህና



# 2

አላህ (ሱ.ወ) አንድ ሙስሊም ውስጣዊ አካሉን-ልቦናውን ከማጋራትና እንደ ምቀኝነት፣ ኩራትና ተንኮል ካሉ የልብ በሽታዎች፣ውጫዊ አካሉን ደግሞ ከነጃሳና ቆሻሻ ከሆኑ ነገሮች እንዲያፀዳ አዟል፡፡ ይህን ከፈፀመ የአላህን ውዴታ ይጎናጸፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡-«አላህ (ከኀጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፡፡ ተጥራሪዎችንም ይወዳል፡፡» ይላል፡፡ (አል በቀራ 222)

## የምዕራፉ ማውጫ

የንጽህና ትርጉም

ከነጃሳ(ቆሻሻ) መጽዳት

- ከነጃሳ መጥራት
- የኢስቲንጃና የመጻዳዳት ስርዓቶች

ሐደስ (ምናባዊ ቆሻሻ)

- ትንሹ ሐደስና ለርሱ ውዱእ ማድረግ

ውዱዕ የማደርገው እንዴት ነው?

- ትንሹን ሐደስ(ምናባዊ ቆሻሻ) ማስወገድ
- ትልቁ ሐደስና ትጥበት
- ሙስሊም ከጀናባ ወይም ከትልቁ ሐደስ የሚጠራው እንዴት ነው?
- ውሃን መጠቀም ያቃተው ወይም ያልቻለ ሰው

# > የንጽህና ትርጉም

የንጽህና መሰረታዊ ትርጉም፡- መጥራት፣ መጽዳት ወይም መወልወል ነው፡፡

አላህ(ሱ.ወ) አንድ ሙስሊም ላዩንም ውስጡንም እንዲያጠራ አዞታል፡፡

ላዩን ግልጽ ከሆኑ እርም ነገሮች፣እንዲሁም ከቆሻሻና ፀያፍ ነገሮች፣ ውስጡን ደግሞ ከማጋራት(ሺርክ) እና፣ እንደ ምቀኝነት፣ ኩራትና ቂም ከመሳሰሉ የቀልብ በሽታዎች እንዲያጸዳ አዞታል፡፡ ይህን ከፈፀመ፣ የአላህን ውዴታ ይጎናጸፋል፡፡ አላህ(ሱ.ወ)፡-«አላህ (ከኀጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፡፡ ተጥራሪዎችንም ይወዳል፡፡» ይላል፡፡ (አል በቀራ 222)

አላህ(ሱ.ወ) ሠላት ከመስገድ በፊት ከቆሻሻዎች መጥራትን አዟል፡፡ ይህ፣ ሠላት ከአላህ ጋር የመገነኛና የመነጋገሪያ መንገድ በመሆኗ ነው፡፡ በተለምዶ እንደሚታወቀው አንድ ሰው ከአንድ ንጉሥ ወይም መሪ ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ጸዱዕ ሆኖና የሚያምር ልብሱን ለብሶ ነው፡፡ ታዲያ የንጉሦች ንጉሥ የሆነው ኃያሉ አምላክ ጋር የሚገናኝስ እንዴት ሊሆን ይገባል?

## ለሠላት አስፈላጊ የሆነው መፀዳዳት እንዴት ዓይነት ነው?

አላህ(ሱ.ወ) አንድ ሙስሊም ሠላት ለመስገድ፣ ቁርኣን ለመንካት ወይም በተከበረው ካዕባ ዙሪያ ለመዞር በሚፈልግበት ጊዜ በኢስላማዊው ሕግ የተደነገገን ልዩና እራሱን የቻለ የመፀዳዳት ዓይነትን በቅድሚያ እንዲያከናውን ግዴታ አዘል ትእዛዝን አዞታል፡፡ በበርካታ ስፍራዎች ላይ ደግሞ ይህንኑ እንዲፈፅም በውዴታ ግዴታ (ሙስተሐብ) መልኩ አበረታቷል፡፡ ከነኚህ ስፍራዎች መካከል፣ በእጅ ሳይነካ በቃል ቁርኣንን በሚያነብ ጊዜ፣ ዱዓ ሲያደርግ፣ ሲተኛ፣ እና ወዘተ...

አንድ ሙስሊም ለመስገድ ሲፈልግ ከሁለት ነገሮች መጥራት ይገባዋል፡፡

1. ከነጃሳ (ከግልፅ ቆሻሻ)
2. ከሐደስ (ምናባዊ ቆሻሻ)



> አላህ(ሱ.ወ)፣ ሙስሊም ወስጡን ከማጋራትና ከቀልብ በሽታዎች ላዩን ደግሞ ከእርምና ቆሻሻ ነገሮች እንዲያጸዳ አዟል፡፡

## > ከነጃሳ(ግልፅ ቆሻሻ) መጥራት

- ❈ **ነጃሳ ማለት፣**አምልኮ ስንፈፅም ኢስላላማዊው ድንጋጌ በቆሻሻነት የፈረጃቸውንና ከነርሱ እንድንጠራ ትዕዛዝ የሰጠበትን ተጨባጭ ነገሮች የሚገልፅ ነው፡፡

- ❈ **ነገሮች መሰረታቸው የተፈቀደና ንጹህ ነው፡፡** ነጃሳ ባዕድና በአጋጣሚ የሚከሰት ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፡ የአንድን ልብስ ንጹህነት ከተጠራጠርንና ነጃሳ እንደተገኘበት እርግጠኞች መሆን ካልቻልን፣ በመሰረቱ ንጹህ ነው እንላለን፡፡

- ❈ **ሠላት ለመስገድ ስንፈልግ** ሰውነታችንን፣ ልብሳችንና የምንሰግድበትን ስፍራ ከነጃሳ ነገሮች የማጽዳት ግዴታ አለብን፡፡

### ነጃሳ ነገሮች

| | |
|---|---|
| 1 | የሰው ልጅ ሽንትና ዓይነ ምድሩ |
| 2 | ደም፤ ትንሽ ጠብታ ደም ግን ችግር የለውም |
| 3 | ስጋቸው የማይበላ የማንኛውም እንሰሳት ሽንትና ፋንድያ (ገጽ 183 ተመልከት) |
| 4 | ውሻና አሳማ |
| 5 | ሙት እንሰሳት (የሞቱ እንሰሳትን ሁሉ የሚመለከት ሲሆን ስጋቸው የሚበላና በሸሪዓዊ መንገድ የታረዱትን ግን አይመለከትም፡፡ ገጽ 184 ይመልከቱ ) የሞተ ሰው አካል ፤አሳና ነፍሳቶች ቢሞቱም ንጹህ ናቸው፡፡ |

### ከነጃሳ መጽዳት

ነጃሳ(ግልፅ ቆሻሻ) ከሰውነት፣ ከልብስ ወይም ከአንድ ቦታ፣ ወዘተ. ላይ ሲታጠብ፣አወጋገዱ፣ ውሃን ወይም ሌላን ነገር በመጠቀም፣ አለያም በሌላ መንገድ ቢሆንም፣ የነጃሳው ነገር መልኩናና አካሉ ከቆሸሸው ቦታ ላይ መወገዱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢስላማዊው ድንጋጌ ነጃሳን ማስወገድን እንጂ ከውሻ ነጃሳ በስተቀር ነጃሳን ለማስወገድ በተወሰነ ቁጥር ማጠብን መስፈርት አላደረገም፡፡ የውሻ ነጃሳም ቢሆን ልጋጉን፣ሽንቱንና ዓይነ-ምድሩን እንጂ አካሉን አያካትትም፡፡ የውሻን ቆሻሻ በተመለከተ፣የመጀመሪያውን በአፈር አድርጎ፣ ሰባት ጊዜ ማጠብን አዟል፡፡ የተቀሩትን ነጃሳዎች ግን መልካቸውና አካላቸው መወገዱ ብቻ በቂ ነው፡፡ የመልኩ ፋና እና ሽታው መቅረቱ ችግር አይኖረውም፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ የወር አበባ ደምን በማጠብ ዙሪያ ለአንዲትን ሠሓቢት፡ - «ደሙን ማጠብሽ ይበቃሻል ፋናው መቅረቱ ችግር የለውም፡፡» ብለዋታል፡፡ (አቡ ዳውድ 365)



> ነጃሳ ማስወገድን በተመለከተ በማናኛውም ንጹህ የማስወገጃ ነገር ተጠቅሞ አካሉን ማስወገድ በቂ ነው፡፡

## የኢስቲንጃእ(ሀፍረተ ገላንና አካባቢውን ማጠብ) እና የመጸዳዳት ስርዓት

- አንድ ሰው ሽንት ቤት ሲገባ፣ ግራ እግሩን ማስቀደምና «ቢስሚላህ፣አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኹቡሲ ወል ኸባኢስ» - በአላህ ስም፣ አምላኬ ሆይ ከእርኩሱና ከእርኩሲቷ (ሰይጣን) በአንተ እጠበቃለሁ- ማለቱ ይወደዳል፡፡
- በሚወጣ ጊዜ ደግሞ ቀኝ እግርን በማስቀደም «ጉፍራነከ» -ምህረትህን ለግሰን- ማለት ይወደዳል፡፡
- በሚጸዳዳበት ጊዜ ሀፍረተ ገላውን ከሰዎች እይታ የመከለል ግዴታ አለበት፡፡
- ሰዎች በቆሻሻው በሚጎዱበት ስፍራ መጸዳዳት ክልክል ነው፡፡
- የሚጸዳዳው ከቤት ውጭ ባለ መስክ ውስጥ ከሆነ፣ እርሱ ሊጎዳቸው፣ እነሱም ሊጎዱት የሚችሉ እንስሳት አለያም አውሬዎች የሚኖሩበት በሆነ ጎሬ ውስጥ መጸዳዳቱም ክልክል ነው፡፡
- የሚጸዳዳው በሜዳ ላይ ከሆነና የሚከልለው ግርዶሽ የሌለ ከሆነ፣ ፊቱን ወደ ቂብላ ማዞር ወይም ለቂብላ ጀርባውን መስጠት አይገባውም፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡- «በምትጸዳዱበት ጊዜ፣ ስትሸኑም ሆነ ዓይነምድር ስታስወግዱ፣ፊታችሁን ወደ ቂብላ አታዙሩ ጀርባችሁንም ለቂብላ አትስጡ፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 386/ ሙስሊም 264)
- የሚፈናጠሩና የሚረጩ ነጃሳዎች ልብሱና ሰውነቱን እንዳይነኩት ጥንቃቄ ማድረግ፣ከነኩት ደግሞ የማጠብ ግዴታ አለበት፡፡
- ተጸዳድቶ ሲያበቃ ከሁለት አንድ ነገር መፈፀም አለበት

**ከ**

የሽንትና የዓይነምድር መውጫ አካሎቹን በውሃ ማጠብ (ኢስቲንጃእ)

**ወይም**

በሶስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ደንጋዮች ፣ለስላሳ የመጸዳጃ ወረቀቶች፣ ወይም ሰውነቱን ከነጃሳ ሊያጸዳለት በሚችል መሰል ነገር ማጽዳት ነው፡፡

## > ሐደስ(ምናባዊ ቆሻሻ)

- ሐደስ፡ ማለት ምናባዊ የሆነ፣ ሰው ከርሱ ከመጥራቱ በፊት ሠላት መስገድን የሚከለክል ነገር ነው፡፡ እንደ ነጃሳ በግልፅ የሚነካ ነግር አይደለም፡፡

- ሐደስ ከአንድ ሙስሊም ላይ የሚወገደው ሊያጠራ በሚችል ውሃ ወዱእ ሲያደርግ ወይም ገላውን ሲታጠብ ነው፡፡ ሊያጠራ የሚችል ውሃ የሚባለው፣ ነጃሳ ያልተቀላቀለበት ውሃ፣ ወይም ነጃሳ ነክቶት፣ መልኩን ወይም ጣዕሙን ወይም ሽታውን ያልቀየረው ውሃ ነው፡፡

ሐደስ በሁለት ይከፈላል፡፡

- አንድ ሰው እርሱን ከላዩ ላይ ለማስወገድ የግድ ውዱእ ሊያደርግ የሚገባው ዓይነት ሲሆን እሱም ትንሹ ሐደስ ይባላል፡፡
- አንድ ሰው እርሱን ከላዩ ላይ ለማስወገድ የግድ በውሃ ገላውን ሙሉ በሙሉ በማደረስ መታጠብ ያለበት ዓይነት ሲሆን ትልቁ ሐደስ በመባል ይጠራል፡፡

### ትንሹ ሐደስና ውዱ

አንድ ሙስሊም ምናባዊ ጸዱዕነቱን አጥቶ ውዱእ ማድረግ የግድ የሚሆንበት ከሚከተሉት ነገሮች አንዱ በሚከሰበት ጊዜ ነው፡፡

1 ሽንት፣ ዓይነምድርና ማንኛውም ከሁለቱ መጸዳጃ ብልቶች የሚወጣ ንፋስና መሰል ነገሮች ከወጡ፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) ጽዱዕነትን የሚያፈርሱ ነገሮችን ሲዘክር፡- «ወይንም ከናንተ አንዱ ከዓይነምድር ቢመጣ» ብሏል፡፡ (ኒሳእ 43) ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሠላት ውስጥ ሆኖ ሐደስ እንደተከሰተበት የተጠራጠረን ሰው በማስመልከት፡- «ድምጽ እስካልሰማ ወይም ሽታ እስካለገኘ ድረስ አቋርጦ አይሂድ!» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 175/ ሙስሊም 361)

2 ያለግርዶ በስሜት ብልትን መንካት፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡- «ብልቱን የነካ ሰው ወዱእ ያድርግ» ብለዋል፡፡ (አቡ ዳውድ 181)

3 የግመል ስጋ መብላት፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፣ «የግመል ስጋን በመብላቴ ውዱእ ላድርግን?» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ «አዎን» በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ (ሙስሊም 360)

4 አእምሮ በእቅልፍ ወይም በአእምሮ ህመም ወይም በስካር መሳት

ቢሃራ

## > ውዱእ የማደርገው እንዴት ነው?

ውዱእና ከቆሻሻ መጸዳዳት፣ ትሩፋት የሚያስገኙና የላቁ ተግባራት ናቸው:: አንድ ባሪያ ዓላማውን ካሳመረና ለአላህ ካጠራ፣ እንዲሁም ከአላህ ምንዳን ከከጀለበት፣ አላህ በርሱ ወንጀሉንና ስህተቱን ያብስለታል:: ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡ -«አንድ ሙስሊም ባሪያ ውዱእ በሚያደርግበት ጊዜ፡ ፊቱን ሲታጠብ፣ በዓይኑ በመመልከት የሰራው የእይታ ወንጀል ከውሃው ጋር ከፊቱ ይወገዳል:: እጁን ሲታጠብ፣ በእጁ የፈፀመው ወንጀል ከውሃው ጋር ይወገዳል:: እግሮቹን ሲያጥብ፣ በእግሮቹ በመጓዝ የፈፀመው ወንጀል ከውሃው ጋር ከእግሮቹ ይወገዳል:: በዚህ መልኩ ከወንጀል ጽዱዕ ሆኖ ይወጣል::» ብለዋል:: (ሙስሊም 244)

### ውዱዕ የማደርገው እንዴት ነው? ትንሹን ሐደስ የማስወግደውስ?



አንድ ሙሰሊም ውዱእ ማድረግ በሚፈልግ ጊዜ ውዱዕ ማድረጉን ሊያስብ ይገባል:: ይኸውም በልቦናው ሐደስን እንደሚያስወግድ ማሰብ ነው:: በልብ ማሰብ (ኒያ) ለማንኛውም ተግባር ተቀባይነት መስፈርት ነው:: ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡ - «ስራዎች የሚለኩት እንደ ታሰበላቸው ዓላማ ነው::» ብለዋል:: (አል ቡኻሪ 1/ ሙስሊም 1907) ከዚያም በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት እንዲሁም በማዕዘናቱ መሐከል ረዥም ቆይታ ሳይኖር ወዱእ ማድረግ ይጀምራል::

**1**

በአላህ ስም (ቢስሚላህ) ይላል::




**2**

መዳፎቹን ሶስት ጊዜ ይታጠባል:: ይህ የተወደደ ተግባር(ሙስተሐብ) ነው::



**3**

በውሃ ይጉመጠመጣል:: ይኸውም በአፉ ውስጥ ውሃን በማስገባትና ተግሞጥሙጦ በመትፋት ይሆናል:: ይህን ሶስት ጊዜ ቢያደርግ የተወደደ ነው:: ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ማድረግ ነው::



**4**

ይሰረነቃል:: ይኸውም ውሃን በአፍንጫው በመሳብ ከዚያም በአፍንጫ ገፈቶ ማውጣት ነው:: ውሃውን የሚያስወጣው በአፍንጫው በሚያስወጣው አየር ነው:: በርሱ ላይ ጉዳት ከሌለው በስተቀር ውሃን በሚገባ ወደ ውስጥ መሳብ (መሰርነቅ) የተወደደ ነው:: ሶስት ጊዜ ይህን ማድረግ ምስተሐብ ነው:: ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው::



5

ፊቱን ይታጠባል፡፡ የግንባሩ፣ ከፀጉር መብቀያው ጫፍ እስከ አገጬ ስር ድረስ፣እንዲሁም ከአንዱ ጆሮ እስከ ሌላኛው ጆሮ ድረስ በመታጠብ የሚፈፀም ነው፡፡ ይህንንም ሶስት ጊዜ ቢፈፅም የተወደደ ነው፡፡ ግዴታው ግን አንድ ግዜ ብቻ ነው፡፡ ጆሮዎች የፊት አካል አይደሉም፡፡



6

እጆቹን ከጣቶቹ ጫፍ እስከ ክርኑ ድረስ ያጥባል፡፡ ክርኖች በትጥበቱ ውስጥ ይካተታሉ፡፡ ሶስት ጊዜ መደጋገሙ ይወደዳል፡፡ ግዴታው አንድ ግዜ ብቻ ነው፡፡



7

እራሱን(ፀጉሩን) ያብሳል፡፡ ይኸውም መዳፎቹን በውሃ በማራስ፣ ከግንባሩ በመጀመር፣ ከማጅራቱ ቀጥሎ እስከለው የኋለኛው የራስ ጫፍ ድረስ ማባስ ነው፡፡ በመዳፎቹ እያበሰ ወደ ፊትለፊት መመለሱ ይወደዳል፡፡ እንደሌሎቹ የሰውነት ክፍሎች ሶስት ጊዜ መደጋገም የተወደደ አይደለም፡፡



8

ጆሮዎቹን ያብሳል፡፡ ይኸውም ጭንቅላቱን ካበሰ በኋላ ሁለቱን አመልካች ጣቶቹን ጆሮዎቹ ውስጥ በማስገባት በአውራጣቱ ደግሞ የላይኛውን የጆሮው ክፍል ማበስ ነው፡፡



9

እግሮቹን ከነቁርጭምጭሚቶቹ ያጥባል፡፡ ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ማድረጉ የተወደደ ነው፡፡ ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ካልሲ ከለበሰ መስፈርቶቹን ጠብቆ በላዩ ላይ ማበስ ይችላል፡ ፡ (ገጽ፣ 97 ተመልከት)



## ትልቁ ሐደስ(ምናባዊ ቆሻሻ) እና ትጥበቱ

ትጥበትን ግድ የሚያደርጉ ነገሮች

እነኚህ ነገሮች፣ አንድ ሙስሊም ከተገበራቸው ሠላትን ከመስገድና ጠዋፍ ከማድረግ በፊት ገላውን መታጠብ ግዴታ የሚያደርጉ ነገሮች ናቸው:: ይህ ሰው ከመታጠቡ በፊት ትልቁ ሐደስ አለበት ይባላል::

ትጥበትን ግድ የሚያደርጉ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:

1 የፍቶት ፈሳሽ (የዘር ፍሬ - መኒይ)፣ በንቃት ሕሊናውም ሆነ በእንቅልፍ ውስጥ፣ በእርካታ መልክ እየተገፋተረ መውጣት::

የፍቶት ፈሰሽ (መኒይ) የሚባለው በጣም በስሜት ውስጥ ሲገባና እርካታ ሲሰማ ከብልት የሚወጣ ነጭና ትኩስ ፈሳሽ ነው::

2 የግብረ ስጋ ግንኙነት: ይህ የፍቶት ፈሰሽ (መኒይ) ባይፈስም፣ የወንድ ብልት ብቻ የሚጠቁም ድርጊት ነው:: የወንዱ ብልት ጫፍ ሴቷ ብልት ውስጥ መግባቱ ብቻ ትጥበትን ግዴታ ያደርጋል:: አላህ (ሱ.ወ):-«(ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት ጀናባ) ብትኾኑ (ገላችሁን) ታጠቡ::» ይላል:: (አል ማኢዳ 6)

3 የወር አበባና የወሊድ ደም መፍሰስ

- የወር አበባ ደም የሚባለው፣ በየወሩ ሴቶች የሚፈሳቸው ተፈጥሯዊ ደም ነው:: ሰባት ቀን ወይም ከዚያ በላይ ይፈሳል:: እንደሴቶቹ ተፈጥሯዊ ልዩነት ከዚያም ያነሰ ሊሆን ይችላል::

- የወሊድ ደም ደግሞ በመውለዳቸው ምክንያት ከሴቶች የሚወጣ ደም ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ ይቆያል::

የወር አበባና የወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች፣ ደሙ በሚፈስባቸው ቀናት የጾምና የሠላት ግዴታ ይነሳላቸዋል:: ከደሙ ሲጸዱ፣ ጾሙን ይከፍላሉ ሠላቱን ግን አይከፍሉም:: በነኚህ ቀናት ውስጥ ባሎቻቸው ሊገናኟቸው አይፈቀድላቸውም:: ከግንኙነት መለስ ባለ ነገር ግን መጠቃቀምና መደሰት ይችላሉ:: ሴቶቹ ደሙ ከቆመላቸው በኋላ ገላቸውን መታጠባቸው የግድ ይሆናል::



> ለግዴታ ትጥበት ሰውነትን በጠቅላላ በውሃ ማዳረስ በቂ ነው::

አላህ (ሱ.ወ):- «ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው:: ንጹህ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቧቸው:: ንጹህ በኾኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኟቸው::» ይላል:: (አል በቀራ 222) «ንጹህ በኾኑም ጊዜ » ማለት ገላቸውን በታጠቡ ጊዜ ማለት ነው::

ገፅሀናህ

## አንድ ሙስሊም ከጀናባ ወይም ከትልቁ ሐደስ የሚጠራው እንዴት ነው?

አንድ ሙስሊም መጽዳትን በልቡ አስቦ ገላውን በሙሉ በውሃ ከታጠበ፣ ከትልቁ ሐደስ ይጸዳል።

- ይህ ትጥበት የተሟላ የሚኾነው ግን፣ ከተጸዳዳ በኋላ የሚያደርገውን ዓይነት ኢስቲንጃ አድርጎ፣ውዱእን አስከትሎ፣ከዚያም ሰውነቱን በጠቅላላ በውሃ አዳርሶ ሲታጠብ ነው። ይህ ዓይነቱ ትጥበት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአስተጣጠብ ፈለግ ጋር ስለሚገጣጠም ከምንዳ አንፃር ከፍተኛው ነው።

- አንድ ሙስሊም ከጀናባ ሲታጠብ ትጥበቱ ከውዱእ ያብቃቃዋል። ከትጥበቱ በተጨማሪ ውዱእ ማድረግን አይገደድም። በላጩ ግን፣ በነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የአስተጣጠብ ፈለግ መሰረት ወዱእንም ያካተተ ትጥበት መታጠብ ነው።

## በካልሲ ላይ ማበስ

ከኢስላም ገርነት መገለጫዎች መካከል አንድ ሙስሊም ወዱእ ሲያደርግ በውሃ በራስ መዳፉ እግሮቹን ሙሉ ለሙሉ የሸፈነውን የላይኛውን የካልሲውን ወይም የጫማውን ክፍል እግሮቹን በመታጠብ ምትክ ማበስ የሚችል መሆኑ ነው። ይህን ለማድረግ ግን፣ ቀደም ሲል ውዱእ እያለው ያጠለቃቸው ወይም የተጫማቸው መሆን አለበት። ሳያወልቅ ሊያብስ የሚችለው ደግሞ፣ ነዋሪ ከሆነ ከ24 ሰዓታት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን መንገደኛ ከሆነ ደግሞ ለ72 ሰዓታት ያህል ነው።

ከጀናባ ለመጽዳት በሚያደርገው ትጥበት ግን በፈለገው ሁኔታ ላይ ቢሆንም ሁለቱን እግሮችን ማጠብ ግዴታ ነው።



### ውሃን መጠቀም ያቃተው ወይም ያልቻለ ሰው

አንድ ሙስሊም በበሽታ፣ ውሃ በማጣት፣ ወይም ለመጠጥ ብቻ እንጂ ውሃ የማያገኝ በመሆኑ ምክንያት ውዱእ ለማድረግ ወይም ሰውነቱን ለመታጠብ ውሃን መጠቀም ካልቻለ አለያም ካቃተው፣ ውሃ አግኝቶ መጠቀም እስከሚችል ድረስ በአፈር ተየሙም ማድረግ ይፈቀድለታል።

የተየሙም አደራረግ፡ በውስጠኛው መዳፎቹ አፈር ላይ አንድ ምት በመምታት በመዳፎቹ ላይ በቀረው አፈር ፊቱን ማበስ፣ቀጥሎም የቀኝ እጁን የላይኛውን የመዳፍ ክፍል በግራው የውስጠኛ መዳፍ ማበስ፣ እንዲሁም የግራ እጁን የላይኛውን የመዳፍ ክፍል በቀኙ የውስጠኛ መዳፍ በማበስ ይፈፅማል።





# ሠላትህ



# 3

ሠላት የሃይማኖት መሰረት ነው፡፡ ባሪያውን ከጌታው ጋር የሚያገናኝ መስመር ነው፡፡ ስለሆነም ከአምልኮዎች ሁሉ ታላቁና ደረጃውም እጅግ የላቀ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፣ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እርሷን እንዲጠብቅ አዟል፡፡ ነዋሪም ሆነ መንገደኛ፣ ጤነኛም ሆነ ህመምተኛ፣እንዲተገብራት አዟል፡፡

## የምዕራፉ ማውጫ

- የሠላት ደረጃና ትሩፋት
- የሠላት ትሩፋት
- አምስቱ የግዴታ ሠላቶችና ወቅቶቻቸው
- የሠላት ቦታ
- የሠላት አፈፃፀም
- የምሰግደው እንዴት ነው?
- የሸላት ማዕዘናትና ግዴታዎች
  - ሠላትን የሚያበላሹ ነገሮች
  - በሠላት ውስጥ የሚጠሉ ነገሮች
- የመቃረቢያ ስግደቶች የትኞቹ ናቸው?
- የህብረት(ጀመዐህ) ሠላት
- አዛን (ጥሪ)
- በሠላት ውስጥ መመሰጥ
- የጁምዓ ሠላት
- የመንገደኛ ሠላት
- የታማሚ ሰው ሠላት

# ሠላት

የሠላት መሰረታዊ ትርጉሙ፡ መማፀን ወይም መለመን ሲሆን፣ ባሪያን ከፈጣሪው ጋር የምታገናኝ መስመር ነች፡፡ በውስጧ ወሳኝ የሆኑ የባርነት መገለጫዎችን አቅፋለች፡፡ ወደ አላህ መሸሽና በርሱ መታገዝን አዝላለች፡፡ በሠላት ውስጥ ባሪያው ጌታውን ይለምናል፣ በሚስጥር ያወራል፣ ያወሳዋል፣ ነፍሱ ትጸዳለች፣ ባሪያው እውነተኛ ማንነቱን ያስታውስበታል፣በውስጧ እየኖረባት ያለችውን የዱንያን ትክክለኛ ገጽታ ይገነዘባል፡፡ የዚህች ዓይነቷ ሠላት፣ በሪያው በአላህ ህግጋትና ድንጋጌ ላይ ጽናት እንዲኖረው፣ ከግፍ፣ ከዝሙትና ከአመፀኝነት እንዲርቅ ታደርገዋለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡ - «ሠላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፤ ሠላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡» ይላል፡፡ (አል አንከቡት 45)



## >የሠላት ደረጃና ትሩፋት

ሠላት ከአካላዊ አምልኮዎች ታላቋና ደረጂም የላቅ ነው፡፡ ቀልብን፣ አዕምሮንና ምላስን በአንድነት የሚያሳትፍ አምልኮ ነው፡፡ የሠላት አንገብጋቢነትን ከብዙ አቅጣጫ መመልከት ይቻላል፡፡

### ሠላት ከፍ ያሉ ደረጃዎች አሉት

1 ከኢስላም ማዕዘናት መካከል ሁለተኛው ማዕዘን ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡- «ኢስላም በአምስት መሰረታዊ ማዕዘናት ላይ ተገነባ፡፡ -ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም፣ ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር፣ ሠላትን ማቋቋም፣....» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 8 /ሙስሊም 16) የአንድ ግንባታ ማዕዘን ወይም ምሰሶ፣ ያለርሱ ግንባታው የማይቆምበት መሰረቱ ማለት ነው፡፡

2 ሸሪዓዊ መረጃዎች፣ በሙስሊሞችና በካሃዲያን መካከል መለያ ነጥብ ያደረጉት ሠላትን ማቋቋምን ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «በአንድ ሰውና በክህደት መሐከል ያለው ነገር ሠላትን መተው ነው፡፡ » ብለዋል፡፡(ሙስሊም 82) «በእኛና በእነርሱ መሐከል ያለው ኪዳን ሠላት ነው፡፡ እርሷን የተወ በርግጥ ክዷል፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቲርሚዚ 2621/ አል ነሳኢ 463)

3 አላህ (ሱ.ወ) ሠላትን በማንኛውም ሁኔታ ላይ ሆኖ እንዲተገበር አዟል፡፡ በመንገደኛነት፣ በነዋሪነት፣ በሰላም፣ በጦርነት፣ በጤንነት፣ በህመምም ላይ ሆኖም በሚቻለው መጠን ሁሉ ይተገበራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «በሰላቶች ተጠባበቁ» ይላል፡፡ (አልበቀራ 238) ምዕመናን ባሮቹን ደግሞ፡- «እነዚያም እነሱ በስግደቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁ የኾኑት፡፡ »በማለት ይገልጻቸዋል፡ (አል ሙእሚኑን 9)

## የሠላት ትሩፋት

የሠላትን ትሩፋት በማስመልከት በርካታ የቁርኣንና የሐዲስ ማስረጃዎች ተላልፈዋል፡፡ ከነሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1 ሠላት ወንጀሎችን ታብሳለች፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አምስት ሠላቶችና ከጁምዓ እስከ ጁምዓ ትላልቅ ወንጀሎች እስካልተጣሱ ድረስ በመካከላቸው የሚፈፀሙትን ወንጀሎች ያብሳሉ፡፡» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 233/ አል ቲርሚዚ 214)

2 ሠላት፣ለአንድ ሙስሊም በመላው ሕይወቱ የምታበራለት ብርሃኑ ናት፡፡ በመልካም ነገር ላይ ታግዘዋለች፡፡ ከመጥፎ ነገሮች ታርቃዋለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡» ይላል፡፡ (አል አንከቡት 45) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ሠላት ብርሃን ነው፡፡» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 223)

3 ሠላት፣ የትንሳኤ ቀን ባሪያው በመጀመሪያ የሚገመገምባት ጉዳይ ናት፡፡ እርሷ ካማረችና ተቀባይነት ካገኘች፣ የተቀረው ስራ ተቀባይነት ያገኛል፡፡ እርሷ ተመላሽ ከሆነች የተቀሩት ስራዎችም ተመላሽ ይሆናሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «የትንሳኤ ቀን ባሪያው በመጀመሪያ የሚገመገምበት ነገር ሠላት ነው፡፡ እርሷ ካማረች የተቀሩት ስራዎቹ ያምራሉ፡፡ እርሷ ከተበላሸች የተቀሩት ስራዎችም ይበላሻሉ፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ሙዕጀሙል አውሰጥ ሊጠበራኒ 1859)

ሙእሚን በጣም የሚረካበት ቆይታ፣ በሠላት ውስጥ ጌታውን ሲያናግር ነው፡፡

በዚህን ጊዜ፣ መንፈሳዊ እረፍትን፣ መረጋጋትናና አጫዋችን ያገኛል፡፡

ሠላት ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቋ የዓይን ማረፊያ ነበረች፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የሀንኑ ሲገልጹ፡-«የዓይኔ መርጊያ በሰላት ውስጥ ተደርጎልኛል፡፡»ይላሉ፡፡ (አል ነሳኢ 3940)

ወደ ሠላት ለሚጣራው ሙአዚናቸው ቢላል፡- «ቢላል ሆይ በርሷ አሳርፈን» ይሉ ነበር፡፡ (አቡ ዳውድ 4985)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ የሆነ ጉዳይ ካሳሰባቸው ወይም ካጨናነቃቸው ወደ ሰላት ይሸሹ ነበር፡፡ (አቡ ዳውድ 1319)

## ሠላት ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

ሠላት፣ በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች ሲቀሩ በማንኛውም ጤናማ አዕምሮ ባለው፣ ሃላፊነትን ለመሸከም በደረሰ ሙስሊም ሁሉ ላይ ግዴታ ነው፡፡ ሴቶች በወር አበባ ወይም በወሊድ ደም ላይ ሆነው አይሰግዱም፡፡ ከጸዱና ደሙ ከተቋረጠ በኋላም ሠላትን አይከፍሉም፡፡ (ገጽ 96 ተመልከት)

ለአቅመ አዳምና ሄዋን መድረስ የሚወሰነው ከሚከተሉት ምልክቶች አንዱ ሲሟላ ነው፡፡

| |
|---|
| አስራ አምስት ዓመት መድረስ |
| በፊት ለፊት ወይም በኋላ ብልቶች ዙሪያ ከርደድ ያለ ጸጉር ማብቀል |
| በሕልም ወይም በንቃተ ሕሊና የፍቶት ፈሳሽን ማፍሰስ |
| ለሴት፣ የወር አበባ መታየት ወይም ማርገዝ |



> አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅ፣ በጦርነትና በአደጋ ጊዜ እንኳን ቢሆን፣ ብቻ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ሆኖ ሠላትን እንዲተገብር አዟል፡፡

## > ለሠላት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

1 ከሐደስና ከነጃሳ መጥራት፡፡ ዝርዝር ገለፃውን አሳልፈናል (ገጽ፣ 91 ተመልከት)

2 ሀፍረተ ገላን መሸፈን

ሀፍረተ ገላን በአጭርነትና ወይም በስስነት የሰውነት ክፍሎችን የማያጋልጥና የማያሳይ በሆነ ልብስ መሸፈን የግድ ነው፡፡


ሀፍረተ ገላ ሦስት ዓይነት ነው፡፡

ለሴት፡ ሰላት ለመስገድ የደረሰች ሴት ሀፍረተ ገላ ከፊቷና ከመዳፎቿ በስተቀር ሰውነቷ በሙሉ ነው፡፡

ለሕፃን፡ ትንሽ ሕፃን ልጅ ሀፍረተ ገላው ሁለቱ ብልቶቹ ብቻ ናቸው፡፡

ወንድ፡ የደረሰ ወንድ ሀፍረተ ገላ ከእምብርቱ እስከ ጉልበቱ ድረስ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ)፡- «የአደም ልጆች ሆይ (ሀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡» ይላል፡፡ (አል አዕራፍ 31) ሀፍረተ ገላን መሸፈን ከመጌጥ ትንሹ ደረጃ ነው፡፡ ‹‹በመስገጃው ሁሉ›› ማለት በየሠላቱ ማለት ነው፡፡



> ሙስሊም ሴት፣ በሠላት ውስጥ ከፊቷና ከመዳፎቿ በስተቀር ሌላውን ሰውነቷን በሙሉ መሸፈን አለባት፡፡

## 3 ወደ ቂብላ መቅጣጨት ወይም መዞር

አላህ (ሱ.ወ)፡- «ከየትም (ለጉዞ) ከወጣህበት ስፍራ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ አቅጣጫ አዙር፡፡» ብሏል፡፡ (አል በቀራ 149)

- የሙስሊሞች የስግደት አቅጣጫ የተከበረው ካዕባ ነው፡፡ እሷን የገነባት የነብያት አባት የሆነው ኢብራሂም(ዐ.ሰ) ነው ፡፡ ነብያት ወደርሷ የአምልኮ ጉዞ (ሐጅ) አድርገዋል፡፡ እርሷ የማትጠቅም የማትጎዳም ድንጋይ እንደሆነች እናውቃለን፡፡ ግን አላህ (ሱ.ወ) ሙስሊሞች በሙሉ ወደ አንድ አቅጣጫ በመዞር አንድ እንዲሆኑ፣ ስንሰግድ ወደርሷ እንድንዞር ወይም እንድንቅጣጭ አዞናል፡፡ ስለሆነም፣ ወደ ካዕባ በመዞራችን የአላህ ብርነታችንን እንገልፅበታለን፡፡

- አንድ ሙስሊም ሲሰግድ ካዕባን ፊት ለፊት የሚመለከታት ከሆነ ወደርሷ ፊቱን ማዞር ግድ ነው፡፡ ከርሷ በርቀት የሚገኝ ሰው ደግሞ ወደ መካ አቅጣጫ መዞሩ በቂ ነው፡፡ በሚቅጣጭ ጊዜ  ከካዕባ አቅጣጫ ትንሽ ማዘንበሉ ወይም መዞሩ ችግር የለውም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «በምስራቅና በምዕራብ መሐከል ያለ በሙሉ የሠላት አቅጣጫ (ቂብላ) ነው፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቲርሚዚ 342)

- ልክ የተቀሩት ግዴታዎች በመቸገር ምክንያት ግዴታነታቸው እንደሚነሳ ሁሉ፣ በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ካዕባ መዞር ላልቻለም ግዴታነቱ ይነሳለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፡፡» ይላል፡፡ (አል ተጋቡን 16)

## 4 የሠላት ወቅት መግባት


ይህ ለሠላት ትክክለኛነት መስፈርት ነው፡፡ ወቅቷ ከመግባቱ በፊት የተሰገደች ሠላት ትክክለኛ አትሆንም፡፡ ከወቅቷ ማዘግየትም የተከለከለ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «ሶላት በምእመናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና፡፡» ይላል፡፡ (አል ኒሳእ 103)

ወቅት በመግባት ዙሪያ በተወሰኑ ነገሮች ላይ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡

- ሠላትን በመጀመሪያው ወቅት ላይ መስገዱ በላጭ ነው፡፡

- ሠላትን በወቅቷ መስገድ ግዴታ ነው፡፡ በማንኛውም ምክንያት ቢሆንም ሠላትን ማዘግየት ክልክል ነው፡፡

- በእንቅልፍ ወይም በመርሳት ምክንያት ሠላት ያለፈው ሰው ባስታወሰ ጊዜ ፈጥኖ መስገድ አለበት፡፡



> አላህ (ሱ.ወ)፡- «ሶላት በምእመናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና፡፡» ይላል፡፡ (አል ኒሳእ 103)

## > አምስቱ የግዴታ ሠላቶችና ወቅቶቻቸው

አላህ (ሱ.ወ) በሙስሊሞች ላይ በቀንና በሌሊት ውስጥ አምስት ሠላቶችን ግዴታ አደርጓል፡፡ እነኚህ ሠላቶች የሃይማኖት ምሶሶዎች ናቸው፡፡ ግዴታነታቸውም እጅግ አጽንዖት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ለነርሱም የሚከተሉትን ወቅቶች አድርጎላቸዋል፡፡


የፈጅር ሠላት፡ ሁለት ረካዓ ነው፡፡ ወቅቱ የሚጀምረው ጎሕ ከሚወጣበት ጊዜ ሲሆን፣ በአድማስ ላይ ብርሃን ሲፈነጥቅ ወይም ጨለማ መገፈፍ ሲጀምር ይከሰታል፡፡ የሚያበቃው ደግሞ ፀሐይ ስትወጣ ነው፡፡





የዙህር ሰላት፡ አራት ረከዓ ነው፡፡ ወቅቱ የሚጀምረው ፀሐይ ከመሐል አናት በምታዘነብልበት ጊዜ ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ የእያንዳንዱ ነገር ጥላ ከራሱ ቁመት ጋር ሲስተካከል ነው፡፡

የዐሥር ሠላት፡ አራት ረከዓ ነው፡፡ ወቅቱ የሚጀምረው የዙህር ወቅት ካበቃበት ጊዜ ጀምረ ሲሆን ይኸውም የእያንዳንዱ ነገር ጥላ ከራሱ ቁመት ጋር ሲስተካከል ነው፡፡ የሚያበቃው ደግሞ ፀሐይ ስትጠልቅ ነው፡፡ አንድ ሙሰሊም ይህችን ሠላት፣ የፀሐይ ብርሃን ጮራ መድከምና መገርጣት ሳይጀምር ፈጠን ብሎ ሊሰግድ ይገባዋል፡፡





የመግሪብ ሠላት፡ ሦስት ረከዓ ነው፡፡ ወቅቱ የሚጀምረው ፀሐይ ከጠለቀችበትና ፍንጣቂዋ ከአድማስ ላይ ሲወገድ ወይም ሲደበቅ ነው፡፡ የሚያበቃው ደግሞ ከፀሐይ መጥለቅ በኋላ የሚታየው ቀዩ ወጋገን ሲጠፋ ነው፡፡

የዒሻእ ሠላት፡ አራት ረከዓ ነው፡፡ ወቅቱ የሚጀምረው ቀዩ ብርሃን ከጠፋበት ቅጽበት ነው፡፡ የሚያበቃው እኩለ ሌሊት ላይ ነው፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታ በሚገጥምበት ጊዜ ጎህ እስኪ ቀድ ባሉት ሰዓቶችም ውስጥ ሊሰገድ ይችላል፡፡



አንድ ሙስሊም የሰላትን ወቅቶች በተመለከተ በወቅቶች ሰሌዳ መጠቀም ይችላል ነገር ግን ወደ ሰላት ለመግባት እሱን የመመልከት ግዴታ የለበትም

# > የሠላት ቦታ (ስፍራ)

ኢስላም ሠላት በህብረት ወይም በጀመዓ እንዲፈፀም አዟል፡፡ ለሙስሊሞች መገናኛና መሰባሰቢያ መንገድ ይሆን ዘንድም በመስጂድ ውስጥ እንዲፈፀም አበረታቷል፡፡ ይህን በማድረግ፣በመካከላቸው ወንድማማችነትና ፍቅር ይጨምራል፡፡ ኢስላም የጀመዓ ሠላትን አንድ ሰው ለብቻው ከሚሰግደው ሰላት በብዙ ደረጃዎች የሚበልጥ አድርጎታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አንድ ሰው በጀመዓ የሚሰግደው ሠላት በነጠላ ለብቻ ከሚሰገደው ሠላት በሃያ ሰባት ደረጃ ይበልጣል፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 619/ ሙስሊም 650/ አህመድ 5921)



ሠላት በማንኛውም ስፍራ ቢሰገድ ትክክለኛ ነው፡፡ ይህም የአላህ እዝነት መገለጫ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ምድር መስገጃና ንጹህ ተደርጋልኛለች፣ከህዝቦቼ፣ ማንም ሰው ሠላት ከደረሰበት፣ በደረሰበት ስፍራ ይስገድ» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 328/ ሙስሊም 521)

## የሠላት ቦታ ይዘት

ኢስላም፣ ሠላት የሚሰገድበት ቦታ ንጹህ እንዲሆን በመስፈርትነት አስቀምጧል። አላህ (ሱ.ወ)፡- «ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም፣ ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን፡፡» ይላል፡፡ (አል በቀራ 125) የነገሮች መሰረት ንጹህ ነው፤ ነጃሳ ደግሞ ባዕድ/መጤ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ነጃሳ ያለበት መሆኑን እርግጠኛ ባልሆንክበት ነገር ላይ ንጹህነትን ትወስናለህ፡፡ በመስገጃ ወይም ሰሌን ላይ እንጂ አለመስገድ የሚወደድ ተግባር አይደለም፡፡

## ልንከተላቸው የሚገቡ በርካታ ስርዓት ደንቦች አሉ፡፡ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1. በመስገጃ ስፍራ ላይ ሰዎችን አለማስቸገር፡፡ ለምሳሌ፡ የመተላለፊያ መንገድ ላይ መስገድ፣ እንዲሁም ግፊያና መጨናነቅን በሰዎች ላይ የሚፈጥር ስፍራ ላይ መቆም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎችን ማስቸገርና በነሱ ላይ ጉዳት ማድረስን ሲከለክሉ፡- «መጉዳትም መጎዳትም (በኢስላም) ቦታ የለውም፡፡» ብለዋል፡፡ (ኢብኑ ማጀህ 2340/ አህመድ 2865)

2. በመስገጃ ቦታ ላይ፣እንደ ስዕል፣ ከፍ ያለ ድምጽና ሙዚቃ ያለ፣ ሰጋጅን የሚረብሽና ትኩረቱን የሚበትን ነገር መኖር የለበትም፡፡

3. የመስገጃው ስፍራ ለሹፈትና ለፌዝ የሚያጋልጥ መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ፡ ሰካራሞች በተሰበሰቡበት ወይም ጽንፈኞች በሚያዘወትሩበት ስፍራና በመሳሰሉት ቦታዎች፣መስገጃ መሆን የለባቸውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የካሃዲያንን አማልክት መሳደብን የከለከለው እነሱ ባለማወቅ አላህን እንዳይሰድቡ ለመከላከል ሲል ነው፡፡ እንዲህም ይላል፡- «እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚግገዟቸውን (ጣዖታት)አትስደቡ፤ ድንበርን በማለፍ ያለ ዕውቀት አላህን ይሰድባሉና፡፡» (አል አንዓም 108)

4. የመስገጃ ቦታ፣ እንደ ዳንስና ጭፈራ ቤት ያለ፣ አላህን ለማመፅ የተዘጋጀ መሆን የለበትም፡፡ በዚህ መሰሉ ስፍራ ሠላት መስገድ የተጠላ ነው፡፡

## > የሡላት ቦታ



በመስጂድ ውስጥ ከጀመዓ ጋር መስገድ ትችላለህን?

አይቻልም(በፍፁም)

አዎን

አዎ፡ ሡላትን በጀመዓ መስገድ በወንድ ላይ የጠበቀ ግዴታ ነው፡፡ ከስራዎች ሁሉ ትልቁና አላህ ዘንድ እጅግ የላቀ ነው፡፡ በጀመዓ መስገድ ለሴቶችም ይፈቀዳል፡፡

በመስጂድ ውስጥ መስገድ ካልቻልክ ከሱ ሌላ ያሉ ቦታዎች ነጃሳ ናቸውን?

አይቻልም(በፍፁም)

አዎን

በነጃሳ ቦታ ላይ መስገድ የተከለከለ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለሡላት ጽዱዕ እንድንሆን አዞናል፡፡

ቦታው ነጃሳ ባይሆንም ሰዎችን የሚያስቸግር ቦታ ላይ መስገድ ይፈቀዳል? ለምሳሌ መተላለፊያ መንገዳቸው ቢሆን?

አይቻልም(በፍፁም)

አዎን

ሰዎችን ማስቸገርና ለመስገድ እንኳን ቢሆን በነርሱ ላይ መጨናነቅን መፍጠር ክልክል ነው፡፡ ሌላ ቦታ ልትመርጥና ልትቀይር ይገባል፡፡

እንደ ፎቶና ከፍተኛ ድምፅ የመሰሉ ከሡላትህ የሚያስተጓጉሉ ነገሮች ባሉበት ቡታስ?

አይቻልም(በፍፁም)

አዎን

ሰጋጅን ከሚረብሹና ሡላቱን ከሚያስተጓጉሉ ነገሮች ሁሉ መራቅ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ህዝብ (የነቢዩ ኡማህ) ከተቸረው ልዩ ነገር መሐከል በምድር ላይ በየትም ስፍራ ቢሰገድ ሡላቱ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ነው፡፡

## > የሠላት ገጽታ

**1** ማሰብ (ኒያ)

ኒያ ለሠላት ትክክለኛነት መስፈርት ነው፡፡ ለምሰሌ፡ የመግሪብ ወይም የዒሻእ ሠላት መሆኑን ለይቶ፣ በልቦናው በሠላት አላህን መገዛት ማለም፣የሠላት ኒያን ይገልፃል፡፡ ድምፅን ከፍ በማድረግ ሐሳቡን በንግግር መግለጽ አይፈቀድም፡፡ የሚፈለገው በልቦናውና በሕሊናው ማለም ብቻ ነው፡፡ ይህን ድምፅ በማውጣት መግለጽ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ኒያን በንግግር መግለጽ ከነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሆነ ከተከበሩት ባልደረቦቻቸው ስላልተላለፈ ነው፡፡

**2** ለሠላት እንደቆመ አላሁ አክበር (አላህ ትልቅ ነው፡፡) ይላል፡፡ በዚህን ጊዜ፣ የውስጥ መዳፉን ወደ ቂብላ አቅጣጫ በማዞር፣ እጁን በትከሻው ልክ ወይም የበለጠ ከፍ ያደርጋል፡፡

አላሁ አክበር ከሚለው ቃል ውጭ ሌላ ዓይነት ቃልን መጠቀም አይቻልም፡፡ ትርጉሙም፡ ክብር፣ የበላይነትና ኃያልነት ለአላህ የተገባ ነው ማለት ነው፡፡ አላህ ከርሱ ሌላ ካሉ አካሎች ሁሉ ታላቅ ነው፡፡ ከዱንያና በውስጧ ካሉ ፍላጎቶችና መርኪያዎች ሁሉ የበለጠ ነው፡፡ ስለሆነም ስንሰግድ በልቦናችንና በሕሊናችን ተመስጠን ሁሉን ነገር ወደ ጎን በመተው ወደ ታላቁ አላህ እንዙር፡፡

**3** አላሁ አክበር ካለ በኋላ፣ ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ በማነባበር በደረቱ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ምንጊዜም ሲቆም ማድረግ ያለበት ይህንን ነው፡፡



**4** የመክፈቺያ ዱዓ ቢል የተወደደ ነው፡፡ እሱም፡- «ሱብሓነከላሁመ ወቢሐምዲከ፣ ወተባረከስሙከ፣ ወተዓላ ጀዱከ፣ ወላ ኢላሃ ገይሩከ»- የሚለው ሲሆን፣ ትርጉሙ፣ «አምላካችን ሆይ ከምስጋና ጋር ጥራት ይገባህ ፡፡ ስምህ የተባረከ ነው፡፡ ልዕልናህ የላቀ ነው፡፡ ካንተ ሌላ አምላክ የለም፡፡» ማለት ነው፡፡

**5** አዑዙ ቢላሂ ሚነ ሸይጧኒ ረጂም (ከእርጉሙ ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ)



ይላል፡፡ ጥበቃን መፈለግ ይህ ነው ፡፡ ትርጉሙ፣ «ወደ አላህ በመጠጋት ከሴጣን ተንኮል እጠበቃለሁ» ማለት ነው፡፡

**6** በስመላህን፣(ቢስሚላሂ ራሕማኒ ረሒም) -(በአላህ ስም እጅግ ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡ ) የሚለውን ሐረግ ያነባል፡፡ የበስመላህ መልዕክቱ፣ በአላህ ስም የምታገዝና የምባረክ ስሆን እጀምራለሁ ማለት ነው፡፡

**7** የፋቲሓን ምዕራፍ ያነባል፡፡ ፋቲሓ በአላህ መፅሐፍ ውስጥ ባለው ክብርና ደረጃ ታላቁ ምዕራፍ ነው፡፡

- አላህ (ሱ.ወ) ይህን ምዕራፍ ማውረዱን በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ውለታ አድርጎ ቆጥሮታል፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «ከሚደጋገሙ የኾኑን ሰባትንና ታላቁንም ቁርአን (በሙሉ) በርግጥ ሰጠንህ፡፡» ይላል፡፡ (አል ሂጅር 87) «ከሚደጋገሙ የኾኑን ሰባትን» የተባለው ፋቲሓን ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የተሰየመችው የአንቀጾቿ ብዛት ሰባት ስለሆነ ነው፡፡



- ሙስሊም ሁሉ ይህንን ምዕራፍ መማር አለበት፡ ፡ ምክንያቱም፣ ብቻውን ወይም ኢማሙ ድምጹን ከፍ አድርጎ በማያነብባቸው ሠላቶች ውስጥ ተከታይ ሆኖ የሚሰግድ ሰው፣ በሠላቱ ውስጥ እሷን ማነብነቡ ከሠላት ማዕዘናት መካከል አንዱ በመሆኑ ነው፡፡

8 ፋቲሓን ካነበበ ወይም ኢማሙ ሲያነብ እያዳመጠ ከቆየ በኋላ፣ ኣሚን ማለት ይወደድለታል፡፡ ትርጉሙም አምላካችን ሆይ ተቀበለን ማለት ነው፡፡

9 በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዓዎች ላይ ከፋቲሓ አስከትሎ ሌላ ምዕራፍን ወይም አንቀጾችን ያነባል፡፡ ሦስተኛና አራተኛ ረከዓ ላይ ግን ፋቲሓን ብቻ በማንበብ ይገደባል፡፡

- በፈጅር፣ በመግሪብና በዒሻእ ሠላቶች ላይ፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዓዎች፣ ፋቲሓንም ከሱ ቀጥሎ የሚነበበውንም ክፍል፣ ድምጽ ከፍ ተደርጎ ይነበባል፡፡ በዙህርና በዐሥር ሠላት ላይ ግን ድምጽ ከፍ አይደረግም፡፡ የተቀሩት በሠላት ውስጥ የሚባሉ ውዳሴዎችና ሙገሳዎችም ሲነበቡ ድምፅ ከፍ አይደረግም፡፡
- ሌሎች የሶላት ዚክሮች በልቦና ይባላሉ።



### ፋቲሐን፣ የሠላት ውስጥ ውዳሴዎችንና ሙገሳዎችን በቃሉ ያልያዘ ወይም ያልሸመደደ ሰው ምን ማድረግ አለበት?

በቅርቡ የሰለመና ፋቲሐን፣ የሠላት ውስጥ ውዳሴዎችንና ሙገሳዎችን በቃሉ ያልያዘ ወይም ያልሸመደደ ሰው የሚከተለውን መፈፀም ይኖርበታል፡

- ግዴታ የሆኑ የሠላት ውስጥ ውዳሴዎችንና ሙገሳዎችን በቃሉ ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሚከተሉት ውዳሴዎች በዐረብኛ ቋንቋ መሆን አለባቸው፡፡

  ፋቲሐና ተክቢር፤ ሱብሐነ ረቢየል ዐዚም፤ ሰሚዐላሁ ሊመን ሐመዲሁ፤ ረበና ወለከል ሐምድ፤ ሱብሐነ ረቢየል አዕላ፤ ረቢግፊርሊ፤ ተሸሑድ፤ ሠላት ዐለ ነቢይ፤ አሰላሙዐለይኩም ወራሕመቱላህ፡፡

- አንድ ሙስሊም እነኚህን ውዳሴዎችንና ሙገሳዎችን በቃሉ እስከሚይዝ ወይም እስከሚሸመድድ ድረስ በሠላት ውስጥ የሚችለውን ተስቢሕ (ሱብሓነላህ)፣ ተሕሚድ(አልሐምዱሊላህ) እና ተክቢር(አላሁ አክበር) ደጋግሞ ማለት፣ ወይም በቃሉ የያዘውን የቁርኣን አንቀፅ እየደጋገመ ማንበብ አለበት፡፡ ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏልና ነው፡ - «አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፡፡» (አል ተጋቡን 16)
- ይህ ሰው በዚህ ቆይታው ሠላቱን በተሟላ መልኩ ለመካናወን ይረዳው ዘንድ በጀመዓ መስገድን ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡ ፡ ይህም ኢማሙ በተከታዩ ሰው በኩል የሚከሰቱ ክፍተቶችን ስለሚያሟላ ነው፡፡

## ይፋቲሐ ትርጓሜ በሚከተለው መልኩ

«ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው»፡ አላህን በባሕሪያቱ፤በተግባራቱ፣ በግልጽና ስውር ፀጋዎቹ በሙሉ ከውዴታና ከማላቅ በመነጨ መልኩ አመሰግነዋለሁ ማለት ነው፡፡

ጌታ(ረብ)፡ የሁሉ ፈጣሪ፤ ባለቤት፤ አስተናባሪና ባለ ጸጋ የሆነ አካል ማለት ነው፡፡ ዓለማት፡ የሚባለው ደግሞ ማንኛውም ከአላህ ባሻገር ያለ፣ የሰው፣ የጅን፣ የመላእክት፣ የእንስሳትና የተቀሩት ፍጡራንን የሚገልጽ ቃል ነው፡፡

«እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ፡» እነኚህ ከአላህ የተዋቡ ስሞች መካከል ሁለት ስሞቹ ናቸው፡፡ «ርኅሩኅ» ማለት ሁሉን ነገር የሚያዳርስ የሆነ ርኅራኄ ባለቤት ማለት ነው፡፡ «አዛኝ» የሚለው ቃለል ደግሞ ምእመናን ባሮቹን ብቻ የሚደርስ በሆነ የርኅራኄ ባህሪ የሚገለፅ ማለት ነው፡፡

«የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው»፡ የፍርዱና የግምገማው ቀን ባለቤትና አስተናባሪ ማለት ነው፡፡ ይህ አንቀጽ የመጨረሻውን ቀን ያስታውሳል፤ በመልካም ስራ ላይም ያበረታታል፡፡

«አንተን ብቻ እንገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፤» ጌታችን ሆይ! እኛ አምልኮን ላንተ ብቻ እንሰጣለን፤ በየትኛውም የአምልኮ ዓይነት ካንተ ጋር ሌላን አካል አናጋራም፤ በማንኛውም ጉዳያችን ላይ ካንተ ብቻ እርዳታና እገዛን እንፈልጋለን፤ እያንዳንዱ ጉዳያችን በአንተ እጅ ነው፤ ከርሱ የቅንጣት ታክልም ሌላ አካል ባለቤትነት የለውም፡፡ ማለት ነው፡፡

«ቀጥተኛውን መንገድ ምራን»፡ ቀጥተኛውን መንገድ አመላክተን፤ አቅጣጨን፤ ግጠመን፤ ካንተ እስከምንገናኝ ድረስ በርሱ ላይም አጽናን ማለት ነው፡፡ ቀጥተኛው መንገድ ኢስላም ነው፡፡ እርሱም ግልጽ፣ ወደ አላህ ውዴታና ወደ ጀነት የሚያደርስ ወይም የሚወስድ መንገድ ነው፡፡ እርሱ ያ የነብያትና የመልዕክተኞች መደምደሚያ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የጠቆሙት መንገድ ነው፡፡ በርሱ ላይ በመጽናት እንጂ ለሰው ልጅ ስኬትና ደስታ ሊገኝ አይችልም፡፡

«የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን መንገድ»፡ የእነዚያን ቀጥተኛውን መመሪያ ያደልካቸውንና በሱም ላይ ያጸናሃቸውን ሰዎች፣ ማለትም የነብያትንና የፃድቃንን መንገድ ምራን ማለት ነው፡፡ እነሱ በርግጥ እውነትን አውቀው የተከተሉ ናቸው፡፡

«በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ»፡ አንተ ከተቆጣህባቸውና ከተናደድክባቸው ሰዎች መንገድ አርቀን፤ ሰውረን፤ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ሐቅን አውቀው አልተገበሩትም፡፡ እነኚህ የሁዶችና መሰሎቻቸው ናቸው፡፡ ከተሳሳቱት ሰዎችም መንገድ ሰውረን፤ አርቀን፤ ማለት ደግሞ፣ ካለማወቃቸው የተነሳ ወደ እውነት ያልተመሩ ሰዎችን፣ ክርስቲያኖችንና መሰሎቻቸው የሚጠቁም ነው፡፡



ሠላትህ

10 ከዚያም፣ ልክ በመጀመሪያው ተክቢራ ላይ እንዳደረገው እጆቹን በትከሻዎቹ ትክክል ወይም ትንሽ ከፍ አድርጎ በማንሳትና የመዳፎቹን ውስጣዊ ክፍልዳ ቂብላ በማቅጣጨት ለሩኩዕ «አላሁ አክበር» ይላል፡፡



11 በመዳፎቹ ጉልበቶቹን በመያዝ ወደ ቂብላ እንደተቅጣጨ ከወገቡ ጎንበስ በማለት ሩኩዕ ያደርጋል፤ ጭንቅላቱና ወገቡ ወጣ ገባ መሆን የለበትም፤ እንዲህም ይላል፡

- «ሱብሓነ ረቢየል ዐዚም» (ታላቁ ጌታዬ ከእንከንና ከጉድለት ጠራ፡፡) ይህን ውዳሴ ሦስት ጊዜ መደጋገም የተወደደ ነው፤ ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ማለት ነው፡፡ ሩኩዕ አላህን የሚያልቁበትና የሚያወድሱበት ዒባዳ ነው፡፡

«ሱብሓነ ረቢየል ዐዚም» - «ታላቁን አላህ ከእንከንና ከጉድለት አጠረዋለሁ፤ እቀድሰዋለሁ፤» ማለት ሲሆን፣ አንድ ሰጋጅ ይህንን የሚለው ከወገቡ ጎንበስ በማለት ለአላህ ያጎበደደና የተዋረደ ሆኖ ነው፡፡



12 ልክ እንደ ከዚህ በፊቱ እጆቹን በትከሻዎቹ ትክክል ከፍ በማድረግና የመዳፎቹን ውስጠኛ ክፍል ወደ ቂብላ በማቅጣጨት ካጎነበሰበት ቀጥ ብሎ ይቆማል፡፡ ኢማም ወይም ብቻውን የሚሰግድ ከሆነ ደግሞ፣ «ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደሁ» - (አላህ ያመሰገነውን ሰው ሰማው) ይላል፡፡ ከዚያም ሁሉም ፡ «ሐምደን ከሲረን ጠይበን ሙባረከን ፊሂ ሚልኣሰማኢ ወል አርዲ ወሚልአ ማሺእተ ሚን ሸይኢን በዕድ» - (በርካታ፣ መልካምና በውስጡ በረከት ያለው፣ በሰማያት ሙሉ፣ በምድር ሙሉ፣ ከነዚህም ሌላ አንተ በምትሻው ነገሮች ሙሉ የሆነ ምስጋና ይድረስህ) ይላሉ፡፡



13 በማስከተል፣ በሰባት የሰውነት ክፍሎቹ መሬት ላይ በመደፋት ሱጁድ ያደርጋል፡፡ እነኚህም የሰውነት ክፍሎች ግንባር ከአፍንጫ ጋር፤ ሁለት መዳፎች፤ ሁለት ጉልበቶች እና ሁለት እግሮች ናቸው፡፡ ሱጁድ ሲያደርግ እጆቹን ከጎኖቹ ማራራቅ፣ ሆዱንና ጭኖቹን አለማጣበቅና እንዲሁም ጭኖቹንና ባቶቹን አለማገናኘት ይወደድለታል፡፡

14 በሱጁድ ውስጥ፡ «ሱብሐነ ረቢየል አዕላ» - (ከፍ ያለው ጌታዬ ከእንከንና ከጉድለት ጠራ) ይላል፡፡ ) ይህንን አንድ ጊዜ ማለት ግዴታ ሲሆን ሦስት ጊዜ መደጋገም ደግሞ ተወዳጅ ተግባር ነው፡፡

ሱጁድ፣ አላህን ከመለመኛ ስፍራዎች ሁሉ በላጩ ነው፡፡ ሰጋጆች በሱጁድ ውስጥ መባል ያለባቸውን ውዳሴዎችን ካሉ በኋላ የሚፈልጉትን የዱንያም ሆነ የአኺራ ጉዳዮችን መለመን ይችላሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ - «አንድ ባሪያ ለጌታው እጅግ ቅርብ የሚሆንበት ስፍራ ሱጁድ ነው፤ ስለሆነም በርሱ ውስጥ ዱዓን አብዙ፡፡» (ሙስሊም 482)

«ሱብሐነ ረቢየልአዕላ» የሚለው ሐረግ ትርጓሜ፡- «የላቀው አላህ፣ በትልቅነቱና በችሎታው የተቀደሰና ከሰማያት በላይ የላቀ ነው፤ ከማንኛውም ጉድለትና እንከንም የጠራ ነው» ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ቃል እራሱን ዝቅ በማድረግና በመመሰጥ፣ በመሬት ላይ በመደፋት ሱጁድ ለሚያደርግ ሰው ሁሉ፣ በርሱና በጌታው መሐከል ያለን የማይነፃፀር ልዩነት እንዲያስታውስ የሚያደርግ የሆነ ማሳሰቢያ ነው፡፡ በመሆኑም ለጌታው በተመስጦና በመተናነስ ይሰግዳል፡፡

15 ከዚያም «አላሁ አክበር» በማለት ከመጀመሪያው ሱጁድ ቀና ብሎ ይቀመጣል፡፡ አቀማመጡም ግራ እግሩን በማንጠፍና ቀኝ እግሩን በመቸከል ቢሆን ተወዳጅ ነው፡፡ መዳፎቹን ከጉልበቱ ቀጥሎ ባለው የጭኑ ጠረፍ ወይም ጫፍ ላይ ማድረግ ይኖርበታል፡፡



- ሰጋጆች በሠላት ውስጥ በሚቀመጡበት በየትኛውም ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ መቀመጣቸው የተወደደ ነው፡፡ ግን ለመጨረሻው ተሸሁድ በሚቀመጡበት ጊዜ በተጠቀሰው መልኩ ቀኝ እግርን በመቸከል፣ ግራ እግርን በማሾለክ፣ በእግር ላይ ሳይሆን በመሬት ላይ ተመቻችተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- ጉልበቱ ህመም የሚሰማው ወይም ልምድ በማጣት ምክንያት ለመጀመሪያው ተሸሁድ ወይም ለሁለተኛው ተሸሁድ በተነገረው መሰረት መቀመጥ ያልቻለ ሰው ሳይጨናነቅ ለተጠቀሰው አቀማመጥ የቀረበ በሆነ መልኩ መቀመጥ ይችላል፡፡

16 በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ሲቀመጥ፡ «ረቢ ኢግፊር ሊ፣ ወርሓምኒ፣ ወህዲኒ፣ ወርዙቅኒ፣ ወጅቡርኒ፣ ወዓፊኒ፤» - (ጌታዬ ሆይ ምሕረትህን ስጠኝ፤ እዘንልኝ፤ ምራኝ፤ ሲሳይህን ለግሰኝ፤ ጠግነኝ፤ ጤናማ አድርገኝ፡፡) ማለት ይኖርበታል፡፡

17 ከዚያም ልክ በመጀመሪያው ሱጁድ መልኩ ለሁለተኛ ጊዜ ሱጁድ ያደርጋል፡፡

18 በመቀጠልም ከሁለተኛው ሱጁድ ‹‹አላሁ አክበር›› በማለት ተነስቶ ይቆማል፤

19 ልክ እንዲሁ የመጀመሪያውን ረከዓ በሰገደው መልኩ ሁለተኛውንም ረከዓ ይሰግዳል ወይም ያስከትላል፡፡

20 ከዚያም በሁለተኛው ረከዓ፣ ከሁለተኛው ሱጁድ ቀና ካለ በኋላ ለመጀመሪያው ተሸሁድ ይቀመጣል፡፡ ቁጭ ባለበት እንዲህ ይላል፡- ‹‹አትተሒይያቱ ሊልላሂ፣ ወሥሠለዋቱ፣ ወጥጠይባቱ፣ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀ ንነቢይዩ ወረሕመቱልላሂ ወበረካቱሁ፣ አስሰላሙ ዐለይና ወዓላ ዒባዲልላሂ አሣሊሒነ አሽሐዱ አን ላ ኢላሃ ኢልለ ላህ ወአሽሃዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፡››



21 ከዚህ ቡሃላ እንደ ሰላቱ ዓይነት ባለ ሶስት ወይም አራት ረከዓ ሰላት ከሆነ የቀረውን የሰላት ክፍል ለመሙላት ይቆማል፤ ነገር ግን በሶስተኛም ሆነ በአራተኛ ረከዓዎች ላይ የሚነበነበው ፋቲሓ ብቻ መሆን አለበት፡፡

- የሚሰገደው የሰላት ዓይነት እንደ ፈጅር ሰላት ባለ ሁለት ረከዓ ከሆነ ከዚህ በታች በተጠቀሰው መልኩ የመጨረሻውን ተሸሁድ ይከውናል፡፡

22 ከዚህ በኋላ በመጨረሻው ረከዓ፣ ከሁለተኛው ሱጁድ በኋላ፣ ለማጠናቀቂያ ተሸሁድ ይቀመጣል፡፡ በመጀመሪያው ተሸሁድ የሚባለውን በሙሉ ካለ በኋላ በሚከተለው መልኩ ለነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ዱዓ ያደርጋል፡ ‹‹አላሁምመ ሠሊ ዐላ ሙሐመድ ወዓላ ኣሊ ሙሐመድ ከማ ሠልለይተ ዓላ ኢብራሂመ ወዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሐሚዱን መጂድ፤ ወባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዓላ ኣሊ ሙሐመድ ከማ ባረክተ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሐሚዱን መጂድ፡፡››
በማስከተልም፡ ‹‹አዑዙ ቢላሂ ሚን ዐዛቢ ጀሐነመ ወሚን ዐዛቢል ቀብር ወሚን ፊትነቲል ማሕያ ወል መማት ወሚን ፊትነቲል መሲሒ ደጅጃል፡፡›› በማለት ዱዓ ማድረግ ይወደድለታል፡፡ በተጨማሪም የሚሻውን ነገር መለመን ይችላል፡፡

23 በመጨረሻም ወደ ቀኙ በመዞር «አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላህ» ይላል፤ ወደ ግራውም በመዞር ይህንኑ ይደግማል፡፡

አንድ ሰጋጅ በዚህ መልክ በማሰላመት ስግደቱን ያጠናቅቃል፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሠላትን አስመልክተው፡ «በተክቢር ይታሰራል፤ በተስሊም ይፈታል» ብለዋል፡፡ (አቡ ዳውድ 61/ አቲርሚዚ 3)

ከሐዲሱ እንደምንረዳው ወደ ሠላት የሚገባው በመጀመሪው ተክቢራ ሲሆን ከርሱ የሚወጣው ወይም እርሱ የሚጠናቀቀው ደግሞ በተስሊም ወይም በሰላምታ መሆኑን ነው፡፡


24 አንድ ሙስሊም የግዴታን ሠላቶች ከሰገደ በኋላ የሚከተሉትን ውዳሴና የሙገሳ ቃላትን ማለት ይወደድለታል፡፡

1. ሦስት ጊዜ «አስተግፊሩላህ» (የአላህን ምሕረት እማፀናለሁ)

2. «አላሁምመ አንተ ስሰላም ወሚንከ ስሰላም ተባረክተ ያ ዘል ጀላሊ ወል ኢክራም» - (አምላካችን ሆይ አንተ ሰላም ነህ፤ ሰላምም ካንተ ነው፤ አንተ የልቅናና የልግስና ባለቤት ሆይ ከሁሉ በላይ ነህ፡፡)

«አላሁምመ ላ ማኒዐ ሊማ አዕጠይተ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ ወላ የንፈዑ ዘል ጀድዲ ሚንከል ጀድዱ» - (አምላካችን ሆይ! አንተ ለሰጠኸው ከልካይ፣ ለከለከልከውም ሰጪ የለም፤ የዝምድና ባልተቤትም ዝምድናው ካንተ የሚያብቃቃው አይደለም) ይላል፡፡

3. ሰላሳ ሦስት ጊዜ «ሱብሓነላህ»፣ ሰላሳ ሦስት ጊዜ «አልሐምዱሊላሂ»፣ሰላሳ ሦስት ጊዜ «አላሁ አክበር» በማለት ለመቶኛው ማሟያ «ላ ኢላሃ ኢለላሁ፣ ወሕደሁ ላ ሸሪ...ከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓለ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲ...ር» - (ከአላህ ባሻገር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፤ በአምላክነቱ ብቸኛ ነው፤ አጋር የለውም፤ ንግሥና ሁሉ የርሱ ነው፤ ምስጋናም ሁሉ የርሱ ነው፤ እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡) ይላል፡፡



## > የምሰግደው እንዴት ነው? ( ቂያም፤ ሩኩዕ፤ ሱጁድ)



1

ቀጥ ብሎ በመቆም እጆቹን በትከሻውና በጆሮው መካከል ከፍ በማድረግ ‹‹አላሁ አክበር›› ይላል፡፡



2

ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ ደርቦ በማጣመር ደረቱ ላይ ያደርጋል፤ የፋቲሓን ምዕራፍና ከቁርኣን የገራለትን አንቀጽ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ረከዓ ላይ ያነባል፡፡



3

ከዚያም እጆቹን ከፍ በማድረግ ‹‹አላሁ አክበር›› ይላል፤ በቂብላ አቅጣጫ ከወገቡ ጎንበስ በማለት ጉልበቱን በእጁ በመያዝ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ‹‹ሱብሐነ ረቢየል ዐዚም›› ይላል፡፡





4 ከሩኩዕ ቀና በማለት ቀጥ ብሎ ይቆማል፤ በዚህን ጊዜ እጁን በተክቢራ ላይ እንደሚያደርገው ከፍ ያደርጋል፤ ኢማም ሆኖ ወይም ብቻውን የሚሰግድ ሰው ከሆነ ደግሞ «ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደሁ» ይላል፤ ከዚህ በኋላ ሁሉም «ረበና ወለከል ሐምድ» ይላሉ፡፡

5 «አላሁ አክበር» እያለ ወደ ሱጁድ ይወርዳል፤ እጁን ግን ከፍ አያደርግም፤ ሱጁድ የሚያደርገው በሰባት የሰውነት ክፍሎቹ ነው፤ እነርሱም፡ ግንባሩና አፍንጫው፤ እጆቹ፤ ጉልበቶቹና እግሮቹ ናቸው፤ በሱጁድ ላይ ሆኖ ሦስት ጊዜ «ሱብሐነ ረቢየል ዐዚም» ይላል፡፡

6 በሁለቱ ሱጁዶች መካከል፣ ቀኝ እግሩን በመቸከል፣ በግራ እግሩ ላይ ይቀመጣል፤ እጁን በጭኖቹ መጀመሪያ ላይ ያስቀምጣል፤ ከዚያም «ረቢግፊርሊ ወርሐምኒ» ይላል፤ ቀጥሎ ቀደም ሲል እንዳደረገው ለሁለተኛ ጊዜ ሱጁድ ያደርጋል፡፡



## > እንዴት ነው የምሰግደው? (ሁለተኛ ረከዓ፣ ተሸሁድ፣ ሰላምታ)




7

ከሱጁድ ቀና በማለት ወደ ሁለተኛ ረከዓ ይቆማል፤ ከዚያም በመጀመሪያ ረከዓ ላይ ያከናወነውን ደግሞ ያከናውናል፤ ይኸውም መቆም፣ ቁርኣን ማንበብ፣ ሩኩዕ ማድረግ፣ ከሩኩዕ ቀና ማለትና ሱጁድ ማድረግ ነው፡፡



8

ከሁለተኛው ረከዓ ሁለተኛ ሱጁድ ቀና ካለ በኋላ ለመጀመሪያው ተሸሁድ ይቀመጣል፤ አቀማመጡም በሁለቱ ሱጁዶች መካከል በሚቀመጠው መልኩ ነው፤ እንዲህም ይላል፡ «አትተሒይያቱ ሊልላሂ፣ ወሦሠለዋቱ፣ ወጥጠይባቱ፣ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀ ንነቢይዩ ወረሕሙቱልላሂ ወበረካቱሁ፣ አስሰላሙ ዐለይና ወዓላ ዒባዲልላሂ ሠሣሊሒ...ነ አሽሐዱ አን ላ ኢላሃ ኢልለ ላህ ወአሽሃዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፡»



9

የሚሰግደው ሠላት ባለ ሦስት ወይም ባለ አራት ረከዓዎች ከሆነ ወደ ሦስተኛ ረከዓ ይቆማል፤ ከዚያም በመጀመሪያውና በሁለተኛው ረከዓ ላይ የሰራቸውን ስራዎች በሙሉ ደግሞ ይሰራል፡፡ ግን ከፋቲሓ በኋላ ሌላ ምዕራፍ አያነብም፡፡ የተቀሩት ስራዎችና ንግግሮች ካለፉት ረከዓዎች ጋር አንድ ዓይነቶች ናቸው፡፡

10 በመጨረሻው ረከዓ ከሱጁድ በኋላ ቁጭ ብሎ የመጀመሪያውን ተሸሁድ ይላል፤ በተጨማሪም በነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሠለዋት ያወርዳል፤ አባባሉም በሚከተለው መልኩ ቢሆን ይመረጣል፡ ‹‹አላሁምመ ሠሊ ዐላ ሙሐመድ ወዓላ ኣሊ ሙሐመድ ከማ ሠልለይተ ዓላ ኢብራሂመ ወዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሐሚዱን መጂድ፤ ወባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዓላ ኣሊ ሙሐመድ ከማ ባረክተ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሐሚዱን መጂድ፡፡››





11 ከዚያም ‹‹አሰላሙዐለይኩም ወረሕመቱላህ›› በማለት ወደ አንገቱን ቀኝ አቅጣጫ ያዞራል፤ ከዚያም ወደ ግራውም በመዞር ‹‹አሰላሙዐለይኩም ወራሕመቱላህ›› ይላል፡፡ በዚህ መልክ ሠላቱን ያጠናቅቃል፡፡

# > የሠላት ማዕዘናት ግዴታዎች

የሠላት ማዕዘናት የሚባሉት የሠላት ዋና ዋና ክፍሎች ሲሆኑ ታውቆም ሆነ በመርሳት ከተተዉ ሠላት የሚበላሽባቸው ነገሮች ናቸው::

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:

* ተክቢረቱል ኢሕራም (የመግቢያ ተክቢራ ወይም «አላሁ አክበር«) * መቆም ለሚችል ሰው መቆም * ከተከታይ ወይም ማእሙም በስተቀር ፋቲሐን ማንበብ፤ * ሩኩዕ፤ * ከሩኩዕ ቀና ማለት፤ * ሱጁድ፤ * በሁለት ሱጁዶች መሐከል መቀመጥ፤ * የመጨረሻው ተሸሁድ፤ * ለመጨረሻው ተሸሁድ መቀመጥ፤ * መረጋጋት ወይም ጡመእኒና እና ማሰላመት ናቸው

የሰላት ግዴታዎች ማለት በሰላት ውስጥ ግዴታ የሆኑ አካላት ማለት ሲሆን እነዚህ ግዴታዎች ቢሆን ተብሎ ከተተው ሰላቱ ይበላሻል። ነገር ግን አንድ ሰው ረስቶ ወይም ዘንግቶ ከተዋቸው የጎደለውን ለመሙላት የመርሳት ሱጁድ የመውረድ ግዴታ አለበት። ይህም ወደፊት በሚወጣው ርዕስ የምንመለከተው ይሆናል።

የሰላት ግዴታዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው:

* ከተክቢረተል ኢሕራም ውጭ ያሉት ሁሉም ተክቢራዎች፤ * ሩኩዕ ላይ እያሉ አንድ ጊዜ «ሱብሐነረቢየል ዐዚም» ማለት፤ * ብቻውን ለሚሰግድና ኢማም ሆኖ ለሚያሰግድ «ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደሁ» ማለት፤ * ለሁሉም ሰጋጅ «ረበና ወለከልሐምዱ» ማለት፤ * ሱጁድ ውስጥ አንድ ጊዜ «ሱብሐነ ረቢየል አዕላ» ማለት፤ * በሁለቱ ሱጁዶች መሐከል ሲቀመጡ አንድ ጊዜ «ረቢግፊርሊ» ማለት፤ እና * የመጀመሪያው ተሸሁድ፤ ናቸው:: እነኚህ ግዴታዎች በመርሳት ምክንያት ከተተዉ ግዴታነታቸው ይቀራል:: እነርሱም የእርሳና ሱጁድ ወይም ሱጁደ ሰህው በማድረግ ይጠገናሉ::

የሠላት ውስጥ ሱናዎች: ማንኛውም የሠላት ማዕዘን ወይም ግዴታ ውስጥ የማይመደብ ንግግርም ሆነ ተግባር የሠላት ውስጥ ሱና ይባላል:: ሠላትን የሚያስውብና የሚያሟላ ነው:: በመሆኑም እርሱን በዘውታሪነት መፈፀም ተገቢ ነው:: ነገር ግን እርሱን በመተዉ ሠላት አይበላሽም::

ሱጁደ ሰህው

ሱጁደ ሰህው፣ ሁለት ሱጁዶችን ማድረግ ሲሆን በሠላት ውስጥ ለሚከሰቱ ጉድለቶችና ክፍተቶች ማካካሻና መጠገኛነት የተደነገገ ነው::

ሱጁደ ሰህው ማድረግ የሚፈቀደው መቼ ነው?

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ሱጁደ ሰህው ይደረጋል:

1 አንድ ሰጋጅ በመርሳትና በስህተት ምክንያት በሠላቱ ውስጥ ተጨማሪ ሩኩዕን ወይም ሱጁዱን ወይም መቆም ወይም መቀመጥን ከጨመረ ሰጅደተ ሰህው ይሰግዳል::

2 ከሠላት ማዕዘናት መካከል አንዱን ማዕዘን ካጎደለ፣ ያንን ያጎደለውን ማዕዘን ያሟላና በሠላቱ ማብቂያ ላይ ሰጅደተ ሰህው ይሰግዳል::

3 እንደ ተሸሁደል አወል(የመጀመሪያው መቀመጥ) ዓይነት ከሠላት ግዴታዎች መካከል አንዱን ረስቶ ከተወ ሰጅደተ ሰህው ይሰግዳል::

4 የሰገዳቸውን የረከዓት ቁጥር ከተጠራጠረ፣ መጀመሪያ እርግጠኛ የሆነውን፣አነስተኛውን ቁጥር ይይዝና ካሟላ በኋላ ሰጅደተ ሰህው ይሰግዳል::

የአሰጋገዱ ዓይነት: በመደበኛ ሠላቱ ውስጥ እንዳለው ሱጁድና መቀመጥ ዓይነት፣ በሱጁዶቹ መሐከል የሚቀመጥ ሆኖ ሁለት ሱጁዶችን ይሰግዳል::

ሱጁድ የማድረጊያው ጊዜ: ሱጁደ ሰህው ሁለት ጊዜዎች አሉት፤ ሰጋጁ ከሁለቱ በአንዱ በፈለገው ጊዜ ሊሰግደው ይችላል::

* ከመጨረሻው ተሸሁድ በኋላ ይሰግዳትና ከዚያም ያሰላምታል::

* ሠላቱን በሰላምታ ካሰናበተ በኋላ ሁለት ሱጁዶችን ሰግዶ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በሰላምታ ያሰናብታል::

## ሠላትን የሚያበላሹ ነገሮች

1. ሠላት፣ አንድ ሰጋጅ መተግበር የሚችለው ሆኖ፣ ሲታወቀውም ይሁን በስህተት ማዕዘንን ወይም የሠላት መስፈርትን ከተወ ሠላቱ ትበላሻለች::
2. ሲታወቀው ከሠላት ግዴታዎች መካከል አንዱን ግዴታ ከተወ ትበላሻለች::
3. ሲታወቀው ከተናገረ ትበላሻለች::
4. ሠላት ድምጽ ባለው ሳቅ፣ በማሸካከት ትበላሻለች::
5. በማያስገድዱ ሁኔታዎች ውስጥ በሚደረጉ ተከታታይና በርካት በሆኑ እንቅስቃሴዎች ትበላሻለች::



> ሰላት ውስጥ ፊትን ወይም እጅን እያነካኩ መጫወት ይጠላል።



> የአንድ ሰጋጅ ሰላት በሚኖረው የአላህ ፍራቻና ከሰላት ከሚያዘናጉ ነገሮች መራቁ ምንዳውና ደረጃዎቹ ላቀ እንዲሆን ያደርገዋል።

## በሠላት ውስጥ የተጠሉ ነገሮች::

እነኚህ ነገሮች፣ የሠላትን ምንዳ የሚቀንሱ፣ ለሠላት መተናነስን የሚያጠፉ፣ እና የሠላትን ግርማ ሞገስ የሚሰልቡ ናቸው:: እነርሱም እንደሚከተሉት ናቸው::

1. በሰላት ውስጥ መዞር የተጠላ ተግባር ነው ምክንያቱም ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሰላት ውስጥ መዞርን (እየዞረ መመልከትን) አስመልክቶ ጥያቄ ሲቀርብላቸው «እርሱ ሰርቆት ነው(ሸይጧ የአላህ ባሪያ ከሰላቱ ይሰርቀዋል» ብለዋል።(ቡኻሪ፡ 718)
2. በሠላት ውስጥ በእጆች፣ በፊት፣ ጣቶችን በማጣመርና በማንጫጫት መጫወት ይጠላል::
3. አንድ ሰው፣ ልቡ በሽንት ሐሳብና በምግብ ከጃሎት ሐሳብ ልቡ ተጠምዶ ወደ ሠላት መግባቱ ይጠላል:: ነገሩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት ነው:: «ምግብ ቀርቦ፣ ሁለቱ ቆሻሾች እየገፈተሩትም ሠላት የለም» (ሙስሊም 560)

# > የተወደዱ ሠላቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው?

በሙስሊም ላይ፣በቀንና በሌሊት ግዴታ የሚሆኑት ሠላቶች አምስት ናቸው፡

እንዲህ ከመሆኑ ጋር፣ ኢስላማዊው ድንጋጌ ለአንድ ሙስሊም ከነኚህ አምስት ሠላቶች በተጨማሪ የውዴታ ሠላትን እንዲሰግድ ደንግጎለታል፡፡

እነኚህ ሠላቶች የአላህን ውዴታ የማግኚያ ሰበቦች ናቸው፡፡ ከግዴታ ሠላቶችም የጎደለውን የሚያሟሉ ናቸው፡፡

የውዴታ ሠላቶች ብዙ ናቸው፤ ከነርሱ መካከል ዋንኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1 የተዘወተሩ ሱናዎች( አር ረዋቲብ)፤ይሄንን ስያሜ ያገኙት ከግዴታ ሠላቶች ጋር ተቆራኝተው ስለሚመጡ፣ እንዲሁም አንድ ሙስሊም የማይዘነጋቸው በመሆኑ ነው፡፡

ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማንም ሙስሊም ግዴታ ሳይሆን በውዴታ የሆኑ አስራ ሁለት ረከዓዎችን አይሰግድም አላህ በጀነት ቤትን ቢገነባለት እንጂ» (ሙስሊም 728)

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡


| | |
|---|---|
| 1 | ከፈጅር ( ከጎሕ መቅደድ) ሠላት በፊት ሁለት ረከዓ፡ |
| 2 | ከዙሁር ሠላት በፊት አራት ረከዓ፤ በየሁለት ረከዓው ያሰናብታል፡፡ ከዚያን ደግሞ ከዙሁር በኋላ ሁለት ረከዓዎችን ይሰግዳል፡፡ |
| 3 | ከመግሪብ ሠላት በኋላ ሁለት ረከዓ |
| 4 | ከዒሻእ በኋላ ሁለት ረከዓ |

2 የዊትር ሠላት፡ በዚህ ስያሜ የተጠራችው የረከዓዎቿ ቁጥር ኢ-ተጋማሽ ስለሆነ ነው፡፡ ከውዴታ ሠላቶች ሁሉ በላጯ ነች፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- ‹‹እናንተ የቁርአን ባለቤቶች ሆይ ዊትርን ስገዱ›› ብለዋል፡፡ (አቲርሚዚ 453/ ኢብኑ ማጃህ 1170)

የዊትር ሠላት ተመራጩ ጊዜ በሌሊቱ ማብቂያ አካባቢ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም ከዒሻእ ሠላት በኋላ ጎሕ እስኪቀድ ድረስ በየትኛውም የሌሊት ክፍል ሊሰግዳት ይችላል፡፡

የዊትር ሠላት የረከዓዎች ቁጥር ገደብ የለውም፡፡ ትንሹ ቁጥር አንድ ረከዓ ነው፡፡ ተመራጩ ቁጥር ሦስት ረከዓ ነው፡፡ በዚህ ላይ የፈለገውን መጨመር ይችላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አስራ አንድ ረከዓ አድርገው ይሰግዷት ነበር፡፡

የውዴታ ሠላቶች መሰረታዊ ፈለግ ባለ ሁለት ረከዓ ሠላት መሆኗ ነው፡፡ ሁለት ረከዓዎችን ይሰግድና ያሰላምታል፤ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡ የዊትር ሠላትም እንደዚሁ ነች፡፡ ግን ሠላቱን ማገባደድ ሲፈልግ አንድ ረከዓ ይሰግድና በርሷ ያጠናቅቃል፡፡ በዊትር ሠላት ውስጥ፣ ከሩኩዕ ቀና ካለ በኋላ፣ ሱጁድ ከማድረጉ በፊት በሐዲስ የተወረዱትን ውዳሴዎች ማነብነብ ይወደድለታል፡፡ ከዚህም በኋላ፣ ሁለት መዳፎቹን ወደ ላይ በመዘርጋት አላህን ይለምናል፡፡ ይህ ዱዓ፣ ዱዓኡል ቁኑት በመባል ይታወቃል፡፡



### በፈቃደኝነት የሚሰገዱ ሠላቶች የሚከለከሉበት ወቅት፡

ኢስላም ሠላት በውስጣቸው እንዳይሰገድ ነጥሎ ከጠቀሳቸው ወቅቶች በስተቀር የተቀሩት ወቅቶች በሙሉ አንድ ሰው የውዴታ ሠላቶችን ያለ ገደብ ሊሰግድ ይችላል፡፡ እነኚህ የተከለከሉት ወቅቶች የከሃዲያን ማምለኪያ ሰዓታት ስለሆኑ ያለፈን የግዴታ ሠላት አለያም እንደ ተሒየተል መስጂድ ያሉ ሰበብ ያላቸውን ሠላቶች ካልሆነ በስተቀር የውዴታ ሠላቶችን መስገድ አይቻልም፡፡ ይህ ሠላትን በተመለከተ ያለው ፍርድ ሲሆን አላህን ማወደስና(ዚክር) እና አላህን መለመን(ዱዓእ) ግን በየትኛውም ሰዓት ሊተገበር ይችላል፡፡

የተከለከሉት ወቅቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| 1 | ጎሕ ከቀደደበት ጊዜ ጀምሮ ፀሐይ ወጥታ የጦር ዘንግን ያህል ትንሽ ከፍ እስከምትል ድረስ ያለው ወቅት፤ የምድር ወገብ አካባቢ ላሉ አገሮች ከ20 ደቂቃ በኋላ ይህ ወቅት ይደርሳል፡፡ |
| 2 | ፀሐይ በሰማይ መሐከል ሆና ወደ መጥለቂያዋ እስክትዘነበል ድረስ መስገድ አይቻልም፡፡ ይህ የዙሁር ሰላት ወቅት ከመግባቱ በፊት ያለ ትንሽ ጊዜ ነው፡፡ |
| 3 | ከዐሥር ሠላት በኋላ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ያለው ጊዜ፡ |



> ከዐሥር ሠላት በኋላ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ባለው ጊዜ ሠላት መስገድ ሐራም ነው፡፡

## > ሠላተል ጀማዓ (በሕብረት መስገድ)

አላህ(ሱ.ወ) ወንዶችን በሕብረት እንዲሰግዱ አዟቸዋል፡፡ ሠላተል ጀማዓ ትልቅ ምንዳ እንዳለውና ልቅናውን የሚናገሩ ሐዲሶች ወርደዋል፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡- ‹‹የሕብረት ሠላት ከነጠላ ሠላት በሃያ ሰባት ደረጃ ይበልጣል፡፡›› ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 619 / ሙስሊም 650)

የሠላተል ጀማዓ ትንሹ ቁጥር ኢማምና አንድ ተከታይ ነው፡፡ የጀመዓው ቁጥር በበዛው ልክ አላህ ዘንድ ያለውም ተወዳጅነት ይጨምራል፡፡

### የመከተል ትርጉም፡

መከተል ማለት፣ አንድ ተከትሎ የሚሰግድ ሰው ሠላቱን በኢማሙ ማሰሩ ነው፡፡ ተከትሎ የሚሰግደው ሰው ኢማሙን በሩኩዑ፣ በሱጁዱ ይከተለዋል፡፡ የቁርኣን ንባቡን ደግሞ ያዳምጠዋል፡፡ ኢማሙን ሊቀድመው ወይም ከርሱ ወደ ኋላ መቅረት አይገባውም፤ ይልቁንም ኢማሙ የሚሰራውን ነገር በቶሎ እየተከተለ ይተገብራል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ እነሆ ኢማም የተደረገው ሊከተሉት ነው፡፡ አላሁ አክበር ሲል አላሁ አክበር በሉ፤ አላሁ አክበር እስኪልም ቀድማችሁ አላሁ አክበር አትበሉ፤ ሲያጎነብስ አጎንብሱ፣ እስኪያጎነብስ ድረስም አታጎንብሱ፤ ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደሁ ሲል፣ ረበና ወለከል ሐምዱ በሉ፤ ሲሰግድም ስገዱ፤ እስኪሰግድ ድረስም አትስገዱ.....›› (አል ቡኻሪ 701/ ሙስሊም 414 / አቡዳውድ 603)

### ለኢማምነት የሚቀደመው ማን ነው?

የአላህን መጽሐፍ በቃሉ የሸመደደ ሰው ለኢማምነት ይቀደማል፡፡ ከርሱ በመለስ ያለው ይከተለዋል እንዲህም እያለ ይቀጥላል፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የአላህን መጽሐፍ ይበልጥ አሳምሮ የሚያነብ ሰው ለኢማምነት ይቀደማል፡፡ በንባብም የሚስተካከሉ ከሆነ ደግሞ ይበልጥ ፈለጌን(ሱናን) የሚያውቀው ይቀደማል፡፡....›› (ሙስሊም 673)



### ኢማሙና ተከታዮቹ የሙቆሙት የት ነው?

ኢማሙ ከፊታቸው መሆን አለበት፡፡ ተከታዮቹ ደግሞ፣ የመጀመሪያውን ሠፍ ብሎ የሚቀጥለውን እያሟሉ ተስተካክለው መቆም አለባቸው፡፡ ተከታዩ አንድ ከሆነ ደግሞ ከኢማሙ በስተቀኝ በኩል ይቆማል፡፡

## ኢማም ተከትሎ ሲሰግድ ያመለጠውን ሠላት እንዴት ይሞላዋል?

ከሠላት የተወሰነ ክፍል አምልጦት ኢማሙን የተከተለ ሰው፣ ኢማሙ ኢስኪያሰናብት ተከትሎ ይሰግድና ከዚያም ቀሪዉን ይሞላል፡፡

ከኢማሙ ጋር ያገኘውን የሠላት ክፍል እንደ ሠላቱ መጀመሪያ፣ቀጥሎ የሚሰራውን ደግሞ እንደ ሠላቱ መጨረሻ አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡

## ረከዓ በምን ትገኛለች?

ሠላትን የምንቆጥረው በረከዓዎች ቁጥር ነው፡፡ ከኢማሙ ጋር ሩኩዕ ላይ የደረሰ ሰው ሙሉ ረከዓን አግኝቷል፡፡ ሩኩዕ ያመለጠው ሰው ደግሞ ኢማሙን ተከትሎ ወደ ሠላት ይገባል ነግር ግን ከዚያች ረከዓ ያመለጠው ስራና ንግግር ከረከዓዎቹ አይቆጠሩም፡፡



> ተከትሎ የሚሰግድ ሰው (መእሙም)፣ ኢማሙን ባገኘበት በማንኛውም የሠላት ክፍል ውስጥ ተከትሎ መግባት አለበት፡፡

**ከኢማሙ የመጀመሪያው የሠላት ክፍል ያመለጠው ሰው ምሳሌ፡**

ከፈጅር ሠላት፣ ከኢማሙ ጋር ሁለተኛዋን ረከዓ ያገኘ ሰው፣ ኢማሙ ካሰላመተ በኋላ ቆሞ ያለፈችውን አንድ ረከዓ ማሟላት አለበት፡፡ አጠናቆ እስኪሰግድ ድረስ ማሰላመት የለበትም፤ ምክንያቱም የፈጅር ሠላት ረከዓ ቁጥር ሁለት ነው፤ እርሱ ደግሞ ያገኘው አንዷን በመሆኑ የተቀረውን ማሟላት አለበት፡፡

ኢማሙ ከመግሪብ ሠላት በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ ሆኖ ያገኘው ሰው፣ ኢማሙ ካሰላመተ በኋላ ሦስት ሙሉ ረከዓዎችን መስገድ አለበት፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት፣ እርሱ ኢማሙን ያገኘው በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ ነው፤ ረከዓን ማግኘት የሚቻለው ግን ከኢማሙ ጋር ሩኩዕ ላይ በመድረስ ስለሆነ ነው፡፡

የዙሁር ሠላት ላይ፣ በሦስተኛዋ ረከዓ፣ ኢማሙን ሩኩዕ ላይ ያገኘው ሰው፣ ከኢማሙ ጋር ሁለት ረከዓዎችን አግኝቷል፡፡ ይህ ማለት ለተከትሎ ሰጋጁ ከዙሁር ሠላት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ረከዓዎች ሰገደ ማለት ነው፡ ፡ ኢማሙ ካሰናበተ በኋላ ቆሞ የተቀረውን ማሟላት አለበት፡፡ ዙሁር ባለ አራት ረከዓ ስለሆነ፣ ቆሞ የሚሞላቸው ረከዓዎች ሦስተኛዋንና አራተኛዋን ይሆናል ማለት ነው፡፡

# > አዛን



> አዛን በአላህ ዘንድ ከላቁ ተግባራት መካከል እንድ ነው።

አላህ ለሙስሊሞች አዛን ያደረገው ሰዎችን ወደ ሰላት ለመጥራትና የሰላት ወቅት መግባቱን እንዲሁም የሰላቱን መጀመር ማሳወቂያ ይሆን ዘንድ ነው። ሙስሊሞች ለሰላት እየተጠራሩ ይሰባሰቡ ነበር። ግን አንድ ለሁሉ የሚጠራ አልነበረም አንዳንዶች የክርስቲያኖችን መሰል ደውል አድርጉ ሲሉ ተወሰኑት ደግሞ

እንደ አይሁዳዊያን ቀንድ ይሁን አለ ዑመር ወይም ለሰላት የሚጣራ ሰው አድርጉ አሉ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደህ አሉ፦« ቢላል ሆይ! ተነስና ለሰላት ጥሪ አድርግ።»(ቡኻሪ 579 ሙስሊም377)

## የአዛንና የኢቃም መገለጫ

- በአዛንና በኢቃም ስነ- ስርዓት በግለሰብ ሳይሆን በቡድን ላይ ግዴታ ነው። አውቀው የተውት ከሆነ ሃጢአት ኖሮባቸውም ቢሆን ሰላታቸው ትክክል ነው።
- አዛን ለማድረግ በመልካምና በሚሰማ ድምጽ ሆኖ ሰዎች ሰላት እንዲመጡ የሚጣራ መሆን አለበት
- ለአዛንና ለኢቃም የተለያዩና የተረጋገጡ አኳኋኖች ከነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ተዘግበዋል።

አዛን

1. አላ...ሁ አክበር፣ አላ...ሁ አክበር፤ አላ...ሁ አክበር አ...ላሁ አክበር!
2. አሽሐዱ አን ላ..ኢላ..ሃ ኢለላ...ህ፤አሽሐዱ አን ላ..ኢላ..ሃ ኢለላ...ህ!
3. አሽሐዱ አነ ሙሐመደን ረሱ...ሉላ...ህ፤ አሽሐዱ አነ ሙሐመደን ረሱ...ሉላ...ህ!
4. ሐይየ ዐለ ሠላ...ህ፤ ሐይየ ዐለ ሠላ...ህ!
5. ሐይየ ዐለልፈላ...ሕ፤ ሐይየ ዐለልፈላ...ሕ!
6. አላ...ሁ አክበር አላ...ሁ አክበር
7. ላ..ኢላ...ሃ ኢለላ....ህ!

ኢቃም (የሠላት መጀመሪያ ጥሪ)

1 አላ...ሁ አክበር፣ አላ...ሁ አክበር!

2 አሽሐዱ አን ላ..ኢላ..ሃ ኢለላ...ህ!

3 አሽሐዱ አነ ሙሐመደን ረሱ...ሉላ...ህ!

4 ሐይየ ዐለ ሠላ...ህ!

5 ሐይየ ዐለልፈላ...ሕ!

6 ቀድ ቃመቲ ሠላ...ህ ቀድ ቃመቲ ሠላ...ህ!

7 አላ...ሁ አክበር፣ አላ...ሁ አክበር!

8 ላ..ኢላ...ሃ ኢለላ....ህ!

### ሙኣዚኑን ተከትሎ መድገም

አዛን ለሰማ ሰው፣ ሙኣዚኑን ተከትሎ እርሱ የሚለውን በሙሉ መልሶ ማለት ይወደዳል፡፡ ሙኣዚኑ ‹‹ሐይየ ዐለሠላ..ህ›› እና ‹‹ሐይየ ዐለልፈላ...ሕ›› በሚል ጊዜ ግን፣ ‹‹ላሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላሂል ዐሊዪል ዐዚም›› ማለት አለበት፡፡

በመቀጠልም፣ «አላሁም ረበ ሃዚሂ ዳዕወቲታማ ወሠላቲል ቃኢማ ኣቲ ሙሐመደኒል ወሲ...ለተ ወል ፈዲ...ለተ ወብዐስሁል መቃመል መሕሙደኒ ለዚ ወዐድተሁ» ይላል፡፡



> አንድ ሙስሊም ወደ መስጂድ በተራመደው እርምጃ ልክ አላህ (ሱ.ወ) ምንዳን ይከፍለዋል፡፡

## > በሠላት ውስጥ መመሰጥ

በሠላት ውስጥ መመሰጥ የሠላት እውነተኛ መገለጫና አንኳሩ ነው፡፡ መመሰጥ ማለት፡ አንድ ሰጋጅ፣ በሠላት ውስጥ የተናነሰና እራሱን ዝቅ ያደረገ ሆኖ፣ የሚያነበውን የቁርኣን አንቀጽ፣ ጸሎቱንና ውዳሴን በሕሊናው እያስተነተነ አላህ(ሱ.ወ) ፊት መቆሙ ነው፡፡



> ባሪያው ለጌታው በጣም ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሆኖ ነው፡፡

መመሰጥ፣ ከአምልኮዎች ሁሉ በላጩና የላቀ የታዛዥነት መገለጫ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፣ በመፅሐፉ ውስጥ መመሰጥ የምእመናን ባህሪ መሆኑን ትኩረት ሰጥቶ የተናገረው ለዚህ ነው ፡፡አላህ (ሱ.ወ)፡- #ምእመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ) እነዚያ እነሱ በስግደታቸው ውስጥ አላህን ፈሪዎች (የሆኑት); ይላል፡፡ (አል ሙእሚኑን 1-2)

በሠላት ውስጥ መመሰጥ የቻለ ሰው፣ የኢማንና የአምልኮን ጣዕም ማጣጣም ይችላል፡ ፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «የዓይን መርጊያዬ በሠላት ውስጥ ተደርጋልኛለች» ያሉት ለዚህ ነው፡፡ (አል ነሳኢ 3940)

የዐይን መርጊያ ማለት፣ ከዳር የደረሰ ደስታ፣ ስኬትና እርካታን ማግኘት ነው፡፡

### በሠላት ውስጥ ለመመሰጥ የሚረዱ መንገዶች

በሠላት ውስጥ ለመመሰጥ የሚረዱ መንገዶች አሉ፡፡ ከነሱም፡-

#### 1 አስቀድሞ ለሠላት መዘጋጀት

ዝግጅት ማለት፡ ወንዶች፣ የሚያምር ልብስ በመልበስና ወደ ሠላት በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ በመራመድ አስቀድሞ ወደ መስጂድ በመምጣት፣ ከሠላት በፊት የሚከናወኑ ነብያዊ ፈለጎችን በማከናወን የሚረጋገጥ ነው፡፡

#### 2 አዕምሮን የሚያጠምዱ፣ አዘናጊና እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን በቅድሚያ ማስወገድ

አንድ ሰው፣ ከፊት ለፊቱ ሐሳቡን የሚሰርቁ ምስሎች፣ ልብ የሚያንጠለጥሉ ጨዋታዎችና ሐሳቡን የሚሰርቁ ድምፆች ባሉበት መስገድ የለበትም፡፡ እንዲሁም፣ ሽንት ቤት መግባት እያስፈለገው፣ ተርቦ ወይም ተጠምቶ፣ ምግብና መጠጥ በቀረበበት ቅጽበት ሠላት መጀመር የለበትም፡፡ ይህ ሁሉ ያስፈለገው ሰጋጁ አዕምሮው ነፃ እንዲሆንና ከባድ ጉዳይን በማስተናገድ እንዲጠመድ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ከፊት ለፊቱ የሚያገኘው ሠላቱን ይሆናል፡፡ ሠላት ደግሞ ከጌታው ጋር የሚነጋገርበት ወሳኝ ነገር ነው፡፡

## 3 በሠላት ውስጥ መረጋጋት

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሠላትን ሲሰግዱ፣ በሩኩዓቸውም በሱጁዳቸውም ውስጥ፣ እያንዳንዱ መገጣጠሚያቸው ወደ ቦታው እስኪመለስ ድረስ በመረጋጋት ነበር፡፡ ሠላቱን ማሳማር ያልቻለውን ሰውዬ፣ በሠላቱ ውስጥ በሚፈፅማቸው ተግባሮችን በሙሉ በእርጋታና በዝግታ እንዲፈፅም አዘውታል፡፡ መቻኮልን ከልክለዋል፤ችኮላን ከአሞራ ውሃ አጠጣጥ ጋር አመሳስለውታል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- #በስርቆት አደገኛው ሰው ማለት ከሠላቱ ላይ የሚሰርቅ ነው፡፡; ሲሉ፣ ሠሓቦች፡ «ከሰላቱ ላይ የሚሰርቀው እንዴት ነው?» በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም፡ #ሩኩዓንም ሱጁዱንም በማጓደል ነው; በማለት መለሱላቸው (አህመድ 22642)

በሠላት ውስጥ የማይረጋጋ ሰው፣ በሠላቱ ሊመሰጥ አይችልም፡፡ ምክንያቱም መፍጠን መመሰጥን ስለሚጻረር ነው፡፡ እንደ አሞራ ጎንበስ ቀና ማለት ምንዳን ያሳጣል፡፡

## 4 ፊት ለፊቱ የሚቆመውን አካል ኃያልነት ማሰብ

በሠላት ውስጥ ሆኖ የፈጣሪን ኃያልነትና ልቅና፣ የነፍሱን ደካማነትና ወራዳነት፣እንዲሁም ጌታው ፊት በመቆም እየተማፀነውና እያናገረው እንደሆነ ያስብ፣ ለርሱ በመዋደቅና በመዋረድ ፈጣሪውን ይለምን፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ አላህ (ሱ.ወ) በወዲያኛው ዓለም ለምእመናን ያዘጋጀውንና የደገሰውን፣ እንዲሁም አጋሪያን የሚጠብቃቸውን ቅጣትና ውርደት ያስተንትን፡፡ በወዲያኛው ዓለም ጌታው ፊት የሚቆምበትን ጊዜ ያስታውስ፡፡

አንድ ሙእሚን በሠላት ውስጥ ሆኖ ይህን በአዕምሮው መሳል ከቻለ፣ አላህ በመፀሐፉ ውስጥ፣ ‹‹ጌታቸውን እንደሚገናኙ እርግጠኞች ናቸው›› ብሎ ከዘከራቸው ሰዎች ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- #(ሠላት) በፈሪዎች ላይ እንጅ በሌላው ላይ በእርግጥ ከባድ ናት፡፡ እነዚያ እነርሱ ጌታቸውን የሚገናኙ እነሱም ወደርሱ ተመላሾች መኾናቸውን የሚያረጋግጡ በኾኑት ላይ እንጅ ከባድ ናት; ይላል፡፡ (አል በቀራ 45-46)

አንድ ሰጋጅ በሠላቱ ውስጥ መመሰጥን የሚያገኘው፣ አላህ (ሱ.ወ) እንደሚሰማው፣ የጠየቀውን እንደሚሰጠውና ለልመናው ምላሽ እንደማይነፍገው በሕሊናው መሳል በሚችለው ደረጃ ልክ ነው፡፡

## 5 የሚነበቡ አንቀጾችን፣ የሠላት ውዳሴና ሙገሳዎችን ማስተንተንና ከነሱ ጋር በሕሊና መጓዝ

ቁርኣን የተወረደው ሊያስተነትኑት ዘንድ ነው፡፡ #ይህ ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሀፍ ነው አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑና የአዕምሮዎች ባለቤቶችም እንዲገሰጹ አወረድነው፡፡; አንድ ሰው የሚያነባቸውን አንቀጾች፣ የሚላቸውን ውዳሴዎችና ዱዓዎች ትርጉም ካላወቀ ሊያስተነትን አይችልም፡፡ ትርጉሙን መረዳት ሲችል፣ በአንድ በኩል እርሱ ያለበትን ሁኔታና ተጨባጭ ነገር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአንቀጾቹን፣ የውዳሴና ልመናዎቹን ትርጉም ማስተንተን ይችላል፡፡ ከዚህም፡ መመሰጥ፤እንዲሁም ለጌታው መዋረድና መዋደቅ ይገኝለታል፡፡ ጥልቅ ስሜት ይሰማዋል፡፡ ምናልባትም ዓይኖቹ ሊያነቡ ይችላሉ፡፡ አንድም አንቀጽ ጫና ሳያሳድርበት አያልፍም፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- #እነዚያም በጌታቸው አንቀጾች በተገሰጹ ጊዜ (የተረዱ ተቀባዮች ኾነው እንጅ ) ደንቆሮችና ዕውሮች ኾነው በርሷ ላይ የማይደፉት ናቸው፡፡; ይላል፡፡ (አል ፉርቃን 73)



# > የጁምዓ ሠላት

አላህ (ሱ.ወ) በጁምዓ ዕለት፣ በዙህር ሠላት ወቅት እጅግ በጣም የላቀ የኢስላም መገለጫና ከግዴታዎቹ ሁሉ የጠበቀ ሠላትን ደንግጓል፡፡ ይህ ሙስሊሞች በሳምንት አንዴ የሚሰባሰቡበት ዕለት ነው፡፡በዚሁ ዕለት የጁምዐው ኢማም የሚያቀርብላቸውን ምክርና ተግሳጽ ያዳምጣሉ ከዚያም የጁምዐን ሠላት ይሰግዳሉ፡፡



> ሰጋጆች የጁምዓን ኹጥባ በጥሞና ማዳመጥ ከርሱ ከሚያስተጓጉለቸውን ነገር መራቅ አለ ባቸው፡፡

## የጁምዓ ዕለት ትሩፋት

የጁምዓ ዕለት ከሳምንቱ ቀናቶች ትልቁና የላቀ ክብር ያለው ዕለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከቀናቶች መካከል መርጦታል፡፡ ከተቀሩት ወቅቶች በበርካታ ልዩ ነገሮች አብልጦታል፡፡ ከነኚህም መካከል፡-

- አላህ (ሱ.ወ)፡ ይህን ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች ነጥሎ በዚህ ዕለት አልቆታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡ - ‹‹አላህ (ሱ.ወ) ከኛ በፊት ያሉትን የጁምዓን ዕለት አስቷቸዋል፡፡ ለአይሁዶች የቅዳሜን ዕለት፣ ለክርስቲያኖችም የእሁድን ዕለት አደረገላቸው፡፡ አላህ እኛን አመጣንና ለጁምዓ ዕለትም መራን፡፡›› ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 856)

- አደም የተፈጠረው በዚሁ ዕለት ነው፡፡ የምፅዓት ዕለትም የምትከሰተው በጁምዓ ዕለት ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- #ፀሐይ ከምትወጣባቸው ቀናቶች በላጩ የጁምዐ ቀን ነው፡፡አደም የተፈጠረው በሱ ውስጥ ነው፡፡ ጀነት እንዲገባ የተደረገውም በሱ ውስጥ ነው፡፡ ከሷም እንዲወጣ የተደረገው በዚሁ ዕለት ውስጥ ነው፡፡ ሰዓቲቱም በጁምዓ ዕለት እንጂ አትከሰትም፡፡; ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 854)

## ጁምዓ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

የጁምዓ ሠላት የሚከተለውን መገለጫ ባሟላ ሰው ላይ ግዴታ ነች፡፡

1. ወንድ፡ በሴት ላይ ግዴታ አይደለም
2. ለአቅመ አዳም የደረሰ፡ በባሪያና ባልደረሰ ሕፃን ላይ ግዴታ አይደለም፡፡
3. ነዋሪ፡ በመንገደኛ፣ እንዲሁም ከከተማና ከመንደር ርቆ በዱር በሚኖር ሰው ላይ ግዴታ አይደለችም፡፡

## የጁምዓ ሠላት አፈፃፀምና ድንጋጌዎች

1 ከጀሙዓ ሠላት በፊት ገላን መታጠብ፤ኹጥባ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በጊዜ ወደ መስጂድ መምጣትና ጥሩ ልብስ መልበስ የተወደደ ነው፡፡

2 ሙስሊሞች ጁምዓ በሚሰገድበት ትልቅ መስጂድ ወይም መስጂድ ጃሚዕ ውስጥ ይሰባሰቡና፣ ኢማሙ በመድረክ ላይ በመውጣት ፊቱን ወደ ሰጋጆቹ በማዞር በሁለት ክፍል የተከፈለ ኹጥባ/ ዲስኩር ያደርግላቸዋል፡፡ በሁለቱ ኹጥባዎች መሐከል፣ ለመለያ ያክል ትንሽ ጊዜ በመቀመጥ እረፍት ያደርጋል፡፡ በኹጥባው ውስጥ፣ አላህን እንዲፈሩ ያስታውሳል፡፡ የቁርኣን አንቀጾችን እያጣቀሰ የተለያዩ ምክሮችና ተግሳጾችን ያስተላልፉል፡፡

3 ሰጋጆቹ ኹጥባውን በጥሞና ማዳመጥ አለባቸው፡፡ መነጋገር ወይም ከኹጥባው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በሚያደርጉ ነገሮች እራስን ማጥመድ ክልክል ነው፡፡ መስገጃ መነካካት ወይም አሸዋና አፈር እያነሱ መበተን እንኳን ክልክል ነው፡፡

4 ከዚህ ቀጥሎ፣ ኢማሙ ኹጥባውን ሲጨርስ ከመድረኩ ይወርዳል፡፡ ኢቃም ይደረግና በቁርኣን ንባቡ ድምፁን ከፍ በማድረግ ሁለት ረክዐዎችን ያሰግዳቸዋል፡፡

5 የጁምዓ ሠላት የተደነገገው የተወሰነ ያክል ሰው ለሚገኝበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ፣ የጁምዓ ሠላት ያመለጠው ወይም በሆነ ምክንያት ከጁምዓ ሠላት የቀረ ሰው፣ በሱ ምትክ መስገድ ያለበት ዙህርን ነው፡፡ ብቻውን የሚሰግደው ጁምዓ ተቀባይነት የለውም፡፡

6 ከጁምዓ ሠላት የዘገየና ከኢማሙ ጋር ከረከዓ ያነሰውን ክፍል እንጂ ያልደረሰ ወይም ያላገኘ ሰው የሚሞላው ሠላት በዙህር መልክ ነው፡፡

7 ጁምዓ ግዴታ የማይሆንባቸው፣ ሴቶችና መንገደኛ የመሳሰሉት በሙሉ ከሙስሊሞች ጋር በመሆን ቢሰግዱ ሠላታቸው ተቀባይነት ያገኛል፡፡ በዚህም የዙህር ሰላት ግዴታ ይወርድለታል፡፡

## ከጁምዓ ለመቅረት የሚፈቀድለት ማን ነው?

ኢስላማዊው ድንጋጌ፣ የጁምዓ ሠላት ላይ መገኘቱ ግዴታ በሆነባቸው ሰዎች ላይ ሁሉ በቦታው መጣድ ግዴታ መሆኑን አጥብቆ አሳስቧል፡፡ በዓለማዊ ጉዳይ ከርሱ መዘናጋትን አጥብቆ አስጠንቅቋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- #እናንተ ያመናችሁ ሆይ በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ መሸጥንም ተዉ፤ ይሃችሁ የምታውቁ ብትኾኑ ለናንተ በጣም የተሻለ ነው፡፡» ይላል፡፡ (አል ጁምዓ 9)

ያለ ህጋዊ ምክንያት ከርሱ የሚቀርን ሰው በልቦናው ላይ መናፍቅነት መታተምን አስጠንቅቋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡ - «ያለ ምንም ምክንያት በመዘናጋት ሦስት ጁምዓን የተወ ሰው፣ አላህ (ሱ.ወ) በቀልቡ ላይ ያትምበታል፡፡» ብለዋል፡ ፡ (አቡ ዳውድ 1052 አህመድ 15498) «በቀልቡ ላይ ያትምበታል» ማለት ይጋርደዋል፣ ይሸፍነዋል፣ በውስጡ እንደ መናፍቃንና አመጸኞች ልብ መሃይምነትንና ድርቀትን ያበቅልበታል ማለት ነው፡፡

ከጁምዓ ለመቅረት የሚያስችል ምክንያት፡ ድንገተኛና ያልተለመደ፤ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ወይም በኑሮ አለያም በጤና ላይ አስጊና አደገኛ ሁኔታ መከሰት ነው፡፡



ሠላትህ

## በስራና ሃላፊነት ላይ ለመገኘት ሲባል ከጁምዓ መቅረት እንደ ህጋዊ ምክንያት ይታያልን?

በመሰረቱ፣ በስራና ሃላፊነት ላይ ለመገኘት ሲባል ከጁምዓ ሠላት መቅረት ህጋዊነት ወይም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በዚህ ወቅት ስራችንን ትተን ለሠላት ዝግጁ እንድንሆን፣ #እናንተ ያመናችሁ ሆይ በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ መሸጥንም ተዉ ይሃችሁ የምታውቁ ብትኾኑ ለናንተ በጣም የተሻለ ነው፡፡» በማለት አዞናል፡ (አል ጁምዓ 9)

አላህ (ሱ.ወ)፡- «አላህንም የሚፈራ ሰው ለርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡ ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፡ ፡በአላህ ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡» ይላል፡፡ (አጠላቅ 2-3)



> አላህ ዘንድ ያለው ዋጋ ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው፡፡

### ስራ፣ ከጁምዓ ሠላት ለመቅረት ህጋዊ ምክንያት የሚሆነው ምን ጊዜ ነው?

ቀጥለው ከተጠቀሱት፣ ከሁለቱ በአንዱ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ተደጋጋሚና ዘውታሪ ስራ ከጁምዓ ሠላት ለመቅረት እንደ ምክንያት ሊቆጠር አይችልም፡፡

1. እርሱ በቦታው ላይ በመኖሩና ከጁምዓ በመቅረቱ እንጂ ሊከሰት የማይችል ትልቅ ህዝባዊ ጥቅም ካለና ይህን ስራ እርሱ ከተወው ከፍተኛ ጉዳትና አደጋ የሚደርስ ከሆነ እርሱን ሊተካው የሚችል ማንም ከሌለ፡፡

ምሳሌ

- በድንገተኛ ክፍል የሚሰራ ዶክተር ድንገተኛ አደጋ የደረሰባቸው ቁስለኞችንና በሽተኞች የሚያክም ከሆነ
- ዘበኛና ፖሊስ የሰዎች ንብረት በሌቦችና በወሮበሎች እንዳይዘረፍ በመጠብቅና በመከላከል ላይ ከተሰማሩ
- በትላልቅ ኢንዳስትሪ ውስጥ የማሽኖችና መሳሪያዎችን ሂደት የሚከታተልና የሚቆጣር ቴክኒሻን ከሆነ ክትትል ለሴኮንዶች መቋረጥ የማይችል ከሆነ

2. ስራው ብቸኛ የገቢ ምንጩ ከሆነ አስፈላጊ የዕለት ወጪዎቹን ምግቡን መጠጡንና ወሳኝ ጉዳዮችን ለራሱና ለቤተሰቦቹ የሚያስፈፅምበት ከዚያ ስራ ውጭ ምንም ከሌለው ሌላ ስራ እስከሚያገኝና ያለበት ችግር እስኪወገድለት ድረስ በዚያ ስራ ላይ በመቆየት ጁምዓ ሳይሰግድ ቢቀር ይፈቅድለታል፡፡ወይም ምግቡን መጠጡንና አስፈላጊ ጉዳዮችን ለራሱና ለቤተሰቦቹ የሚያስፈጽምበት እስከሚያገኝ ድረስ ይፈቀድለታል፡፡ ይሁን እንጂ ሌላ ስራና የገቢ ምንጭ ማስገኛ መንገድ የማፈላለግ ግዴታ አለበት፡፡

## > የመንገደኛ ሰላት



- መንገደኛ ከቦታ ቦታ በሚዘዋወርበት ወይም ከአራት ቀን ላነሰ ወቅት ጊዚያዊ ቆይታ በሚያደርግበት ስፍራ ሆኖ ባለ አራት ረከዓ ሰላቶቹን ሁለት ረከዓ አድርጎ መስገድ ይወደድለታል፡፡ዙህር ዐሱርና ዒሻን የአገሬ ነዋሪ የሆነ ኢማምን ተከትሎ ካልሰገደ በስተቀር በአራት አራት ረከዓ ምትክ ሁለት ሁለት አድርጎ ይሰግዳል፡፡ እንዲያ ከሆነ ግን ኢማሙን ሊከተልና እንደሱ አራት ረከዓ ሊሰግድ ይገባል፡፡
- ከፈጅር ሱና በስተቀር የተቀሩትን ተቀጥላ ሱና ሰላቶችን ቢተው ወይም ባይሰግድ ይችላል፡፡
- ዙህርና ዐስሩን በአንድነት መግሪብና ዒሻን በአንድነት አቆራኝቶ መስገድ ይችላል፡፡ በተለይ በሚዘዋወርበትና በሚሳፈርበት ወቅትና ሁናቴ ላይ ከሆነ የአላህን ህግ ገራገርነት እዝነትና ማጨናነቅ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

## > የታማሚ ሰው ሰላት

አዕምሮውን እስካልሳተና እራሱን እስካወቀ ድረስ በፈለገው ሁናቴ ላይ ቢሆንም ሰላት በሙስሊም ላይ ግዴታ ነው፡፡ ነገር ግን እስልምና የሰዎችን ሁኔታና ያለባቸውን ጉዳይ ከግምት አስገብቷል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች አንዱ ህመም ነው፡፡

ይህን ለማብራራት ያክል፡

- መቆም የማይችል ወይም መቆም የሚያስቸግረው ወይም ለመቆም የሚያስችለው ፈውሱ የሚዘገይበት የሆነ ህመምተኛ ቆሞ መስገድ ይሻርለታል፡፡ እርሱ የሚሰግደው ቁጭ ብሎ ነው፡፡ቁጭ ማለትም ካልቻለ በጎኑ እንደተጋደመ ይሰግዳል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ ቆመህ ስገድ፡፡ ካልቻልክ ቁጭ ብለህ ስገድ፡፡ ካልቻልክ በጎንህ ተጋድመህ ስገድ አል ቡኻሪ 1066
- ማጎንበስ (ሩኩዕ) ወይም ሱጁድ ማድረግ ያልቻለ ሰው በሚችለው ልክ ምልክት በማድረግ ይሰግዳል፡፡
- በመሬት ላይ ቁጭ ማለት የሚቸገር ሰው በወንበርና በመሰል ነገሮች ላይ ቁጭ ብሎ መስገድ ይችላል፡፡
- በህመም ምክንያት ለእያንዳንዱ ሰላት መጥራራት ወይም ዉዱእ ማድረግ የሚቸገር ሰው ዙህራና ዐሱርን በአንድነት መግሪብና ዒሻን በአንድነት በማቆራኘት መስገድ ይችላል፡፡
- ሰላት ለመስገድ በህመም ምክንያት ውሃን መጠቀም የማይችል ሰው በአፈር ተየሙም ማድረግ ይችላል፡፡



# ጾምህ



# 4

አላህ (ሱ.ወ) ሙስሊሞች በአመት አንድ ወርን እንዲጾሙ ግዳጅ አድርጎ ደንግጓል፡፡ እሱም የተባረከውን የረመዳንን ወር ነው፡ ፡ አራተኛ የኢስላም ማዕዘንና ታላቅ መሰረት አድርጎታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተፃፈ በናንተም ላይ ተፃፈ (ተደነገገ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡›› ይላል፡፡ (አል በቀራ 183)

## የምዕራፉ ማውጫ


የጾም ትርጉም

የረመዳን ወር ትሩፋት

የጾም ሚስጥር

የጾም ትሩፋት

ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች

እንዳይጾሙ አላህ ፍቃድ የሰጣቸው ሰዎች

- ህመምተኛ
- ደካማ
- መንገደኛ
- በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች
- እርጉዝና አጥቢ ሴት

የውዴታ ጾም

የተባረከው የጾም ፍቺ በዓል (ዒዱል ፊጥር)

- በጾም ፍቺ በዓል ቀን የሚፈቀዱ ነገሮች

# የረመዳን ጾም

## የጾም ትርጉም

ጾም በኢስላም ያለው ትርጉም፡ ጎሕ ከቀደደበት ሰዓት ጀምሮ፣ ፀሐይ እስከትጠልቅ (የመግሪብ ሠላት አዛን የሚባልበት ወቅት) ድረስ ከምግብ፣ ከመጠጥ፣ ከግብረ ስጋ ግንኙነትና ከሌሎችም ጾምን ከሚያበላሹ ነገሮች እራስን በመቆጠብና በማገድ አላህን መገዛት ነው፡፡

## > የረመዳን ወር በላጭነት

የረመዳን ወር፣ በኢስላማዊው ቀመር ዘጠነኛው ወር ነው፡፡ ረመዳን ከዓመቱ ወራት ሁሉ በላጩ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከተቀሩት ወራት በበርካታ ነገሮች አልቆታል፡፡ ከነዚህ ብልጫዎች መካከል የሚከለተሉት ይገኙበታል፡፡

1 አላህ (ሱ.ወ) የተከበረውንና እጅግ የላቀውን መጽሐፍ -ቁርአንን- በውስጡ በማውረድ የመረጠው ወር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡፡-«(እንድትጾሙ የተፃፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ፣ ከቅን መንገድና (ውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲሆን ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡» (አል በቀራ 185)

2 ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ረመዳን ሲገባ የጀነት በሮች ይከፈታሉ፤ የጀሀነም በሮች ይዘጋሉ፤ ሰይጣናት ይታሰራሉ፡፡» (አል ቡኻሪ 3103/ ሙስሊም 1079) አላህ (ሱ.ወ) መልካምን በመሥራትና ከመጥፎ በመራቅ ባሮቹ ወደርሱ የሚመለሱበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

3 ቀኑን የጾመና ሌሊቱን በመስገድ ቆሞ ያሳለፈ ሰው ያለፉት ወንጀሎቹ ይማሩለታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ የረመዳንን ወር የጾመ፣ ቀደም ሲል የሠራው ወንጀል ይማርለታል፡፡» (አል ቡኻሪ 1910 /ሙስሊም 760) «በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ በረመዳን ወር (ተራዊሕና ተሃጁድን በመስገድ) የቆመ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል፡፡» (አል ቡኻሪ 1905/ ሙስሊም 759)

4 በረመዳን ውስጥ የዓመቱ ትልቅ ሌሊት ይገኛል፡፡
ይህች ሌሊት አላህ (ሱ.ወ) በመጽሐፉ፣ በዚች በርሷ ውስጥ የሚሠራ መልካም ሥራ፣ ለረዥም ዓመታት ከሚሠራ መልካም ሥራ እንደሚሻልና እንደሚበልጥ የተናገረላት ነች፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት፡፡» ብሏል (አል ቀድር 3) እናም ይህችን ሌሊት በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ በመስገድ ቆሞ ያሳለፈ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል፡፡ እርሷ በረመዳን ወር በመጨረሻዎቹ አስርት ሌሊቶች ውስጥ የምትገኝ ነች፡፡ ይህችን ሌሊት፣ ማንም ሰው በእርግጠኝነት በዚህ ዕለት ትሆናለች ብሎ መወሰንና መናገር አይችልም፡፡



> የረመዳን ወር በኢስላማዊው ቀመር ዘጠነኛው ወር ነው፡፡

## > የጾም ሚስጥር

አላህ ሱ.ወ፣ በበርካታ ዓለማዊና መንፈሳዊ ምክንያቶች ጾምን ግዴታ አድርጓል፡፡ ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል

### 1 የአላህን ፍራቻ ማጽናት

ጾም፣አንድ ባሪያ የሚወዳቸውን ነገሮች ወይም ፍላጎቶቹን በመተው፣ ስሜቱን በመጫን፣ አላህን የሚገዛበት አምልኮ በመሆኑ፣ በሁሉም ስፍራና ወቅት፣ በድብቅም ሆነ በይፋ ነፍሱን በአላህ ፍራቻ እንዲያንጽና የአላህን ምርመራ እንዲያስተነትን ያደርገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡» ብሏል (አል በቀራ 183)

### 2 ከወንጀልና ከሃጢአት በመራቅ ላይ ስልጠና ወይም ልምምድ መስጠት

አንድ ጾመኛ ሐላል ነገሮችን በመከልከል የአላህን ትዕዛዝ ማክበር ከቻለ፣ የወንጀልና የሀጢአት ስሜቱን በመለጎሙና አላህ ከገደበው ወሰን በመጠበቁ፣ በስህተት ላይ ባለመዘወተር የበለጠ ቻይ ይሆናል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሐሰት ንግግርንና በሱም መሥራትን ያልተወ ሰው፣ አላህ (ሱ.ወ) ምግብና መጠጡን ከመተዉ ጉዳይ የለውም፡፡» (አል ቡኻሪ 1804) ውሸት ማውራትና በውሸት መሥራት ያልተወ ሰው፣ ለጾም የተደነገገለትን ዓላማ በስራ ላይ አላዋለም ማለት ነው፡፡

### 3 ችግረኞችን ማስታወስና መደገፍ

ጾም፣ የተራቡና የተቸገሩ ሰዎችን ሕይወት የሚካፈሉበትና ዓመቱን ሙሉ በችግርና በሰቆቃ የሚያሳልፉትን ድሆች ሁኔታ የሚያስታውሱበት የአምልኮ ዘርፍ ነው፡፡ ትክክለኛ የአላህ ባሪያ፣ ድሃ ወንድሞቹ ምን ያህል በረሃብና በጥማት እንደሚቸገሩ ያስታውሳል፤ በመሆኑም ለነርሱ የእርዳታ እጁን በመዘርጋት የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡



> ጾመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት፡- ጾሙን ሲፈታና ፈጣሪውን ሲገናኝ ይደሰታል፡፡

## > የጾም ትሩፋት

ጾም በኢስላማዊው ሕግ የተደነገጉ በርካታ ትሩፋቶች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

1. በአላህ አምኖ፣ ትዕዛዙንም አክብሮ፣ በረመዳን ትሩፋት ዙሪያ የተላለፉ ጉዳዮችን እውነት ብሎ ተቀብሎ እንዲሁም አላህ ዘንድ የሚያገኘውን ምንዳ በመከጀል ረመዳንን የጾመ፣ ቀደም ሲል የሰራው ወንጀሉ ይማርለታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ረመዳንን፣ በአላህ አምኖ የሚያስገኝለትን ምንዳ አስቦና ከጅሎ የጾመ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል፡፡» (አል ቡኻሪ 1910 / ሙስሊም 760)

2. ጾመኛ፣ ከአላህ ጋር ሲገናኝ በመጾሙ ምክንያት በሚያገኘው ላቅ ያለ ምንዳና ጸጋ ይደሰታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ጾመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት፡፡ በሚያፈጥርበት ጊዜ የሚደሰተውና ከጌታው ጋር ሲገናኝ የሚደሰተው ደስታ ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 1805 /ሙስሊም 1151)

3. በጀነት ውስጥ ከጾመኞች በስተቀር ማንም የማይገባበት የሆነ ረያን የሚባል በር አለ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በጀነት ውስጥ ረያን የሚባል በር አለ፡፡ የትንሳኤ ቀን ጾመኞች

ይገቡበታል፡፡ ከነርሱ ሌላ ማንም በርሱ በኩል አይገባም፡፡ የት አሉ ጾመኞች? ይባላል፡፡ ወዲያውም እነሱ ወደርሱ ይነሳሉ፡፡ ከነርሱ ሌላ ማንም በርሱ በኩል አይገባም፡፡ እነሱ ገብተው ሲያበቁ ይዘጋል፡፡ ማንም በሱ በኩል አይገባም፡፡» (አል ቡኻሪ 1797/ ሙስሊም 1152)

4 አላህ (ሱ.ወ) የጾምን ምንዳ ወደራሱ አስጠግቶታል፡፡ እናም ክፍያውና ምንዳው፣ ከቸሩ፣ ከለጋሱና ከኃያሉ ጌታ ዘንድ የሆነለት ሰው ሊደሰት ይገባል፡፡ አላህ ባዘጋጀለትም ሽልማት ይበሰር፡፡ አላህ (ሰ.ወ) በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት ሲነግረን፦ «ፆም ሲቀር ሁሉም የአደም ልጆች ስራ ለራሳቸው ነው፤ እርሱ ግን የኔ ነው ምንዳውን የምከፍለው እኔው ነኝ፡፡» ይላል፡፡ (አል ቡኻሪ 1805 /ሙስሊም 1151)

## > ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች

ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች፣ አንድ ጾመኛ ሊከለከላቸውና ሊቆጠባቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1 መብላትና መጠጣት፦ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦ «ከጎህ የኾነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር (ከሌሊት ጨለማ) ለናንተ እስከሚገለጽላችሁ ድረስ ብሉ ጠጡም ከዚያም ጾምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ፡፡» (አል በቀራ 187)

ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ጾሙ አይበላሽም፤ ወንጀልም የለበትም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፦ «ጾመኛ መኾኑን ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ጾሙን ይቀጥል፡፡ ያበላውና ያጠጣው አላህ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 1831/ሙስሊም 1155)

2 ምግብንና መጠጥን የሚተካ ነገር፡፡

- በሰውነት ውስጥ የተጓደለን የጨውና የምግብ መጠን ለመጠገን የሚወሰዱ ምግብ ነክ የሆኑ መርፌዎችና መድሃኒቶች ጾምን ያፈርሳሉ፡፡ ምክንያቱም የምግብና የመጠጥን ቦታ ስለሚተኩ፣ በምግብና መጠጥ ላይ ያለፈው ሕግ ይመለከታቸዋል፡፡
- ለህመምተኛ የሚሰጥ ደም፡፡ ምክንያቱም ደም የምግብና የመጠጥ የመጨረሻው መዳረሻ በመሆኑ ነው፡፡
- በማንኛውም መልክ ማጨስ፡፡ ጭስን ወደ ሰውነት እያማጉ ማስገባት፣ ሰውነትን በመመረዝ እንዲጠናከር ያደርገዋል፡፡

3 የፍቶት ጠብታ ቢፈስም ባይፈስም፣ የወንዱ ብልት በሴቲቷ ብልት ውስጥ እንዲሰምጥ በማድረግ የተፈፀመ ግብረ ስጋ ግንኙነት

4 በፍላጎትና በምርጫ በመተሻሸት ወይም በእጅ በማባበልና በመሳሰሉት መንገዶች የፍቶት ጠብታን (የዘር ፍሬ ፈሳሽን) ማፍሰስ

በእንቅልፍ ልብ የሚከሰት የዘር ፍሬ መፍሰስ ጾምን አያበላሽም፡፡

አንድ ሰው ጾምን የሚያበላሹ ነገሮችን እንዳይፈጽም መጠንቀቅና ስሜቱን መቆጣጠር የሚችል ከሆነ ሚስቱን መሳም ይችላል፡፡

5 አውቆ ማስታወክ፡፡ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ትውከት በራሱ ከወጣ ጾምን አያፈርስም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «ትውከት ያሸነፈው ጾመኛ፣ ጾሙን መክፈል አይጠበቅበትም፡፡ በፈቃዱ ያስታወከ ሰው ጾሙን ይክፈል፡፡» (አል ቲርሚዚ 720 /አቡ ዳውድ 2380)

6 አበባና የወሊድ ደም መፍሰስ፡፡

የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም በቀኑ የመጨረሻ ክፍል ላይም ቢሆን ከፈሰሰ ሴቷ ጾሟ ይበላሻል፡፡ በሌላም በኩል፣ በወር አበባ ደም ላይ ቆይታ ጎሕ ከፈነጠቀ በኋላ ብትጸዳና የዚያን ቀን ብትጾም፣ ጾሟ ትክክል አይሆንም፡፡ ያንን ቀን መጾም የለባትም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «የወር አበባ ላይ በምትሆንበት ጊዜ አትሰግድም አትጾምም አይደል እንዴ?» (አል ቡኻሪ 1850)

አንዲት ሴት ከተለመደው የወር አበባና የወሊድ ደም ውጭ በበሽታ ምክንያት ደም የሚፈሳት ከሆነ ከመጾም አትከለከልም፡፡

## > አላህ እንዳይጾሙ ፍቃድ የሰጣቸው ሰዎች

አላህ (ሱ.ወ) ከሰዎች መካከል ለተወሰኑ ሰዎች በረመዳን ወር አለመጾም እንዲችሉ ፍቃድ ሰጥቷል፡፡ ይህንንም ያደረገው ለነርሱ ከማዘን፣ ከማግራትና ከማቅለል አንፃር ነው፡፡ እኚህ ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1 በመጾሙ የሚጎዳ ታማሚ፡- ለርሱ ማፍጠር ይፈቀድለታል፡፡ ከረመዳን በኋላ ሲሻለው ያፈጠረውን ይከፍላል፡፡

2 በሽምግልና ወይም ይድናል ተብሎ በማይከጀል በሽታ ምክንያት መጾም የማይችል ደካማ ማፍጠር ይፈቀድለታል፡፡ ለእያንዳንዱ ቀን አንድ ሚስኪን ያበላል፡፡ ይኸውም፣ በሀገሩ ከሚበላ የምግብ ዓይነት አንድ ኪሎ ተኩል በመስጠት ይሆናል፡፡

3 ተጓዥ መንገደኛ በጉዞው ላይ እያለ ከአራት ቀን ለማይበልጥ ጊዜ ሲያርፍ ማፍጠር ይችላል፡፡ ያንን ጾም የፈታበትን ቀን ከረመዳን በኋላ ሀገሩ ሲመለስ ይከፍላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በሺተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በናንተ ገሩን (ይሻል) በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡» (አል በቀራ 185)

4 የወር አበባና የወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች፡፡

በነኚህ ሁለት ሁኔታዎች ላይ ያሉ ሴቶች መጾም በነሱ ላይ እርም ነው፡፡ መጾማቸው ትክክለኛ አይደለም፡፡ ከረመዳን በኋላ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ (ገጽ፣ 96 ተመልከት)

5 እርጉዝና አጥቢ፡፡

በራሳቸው፣ወይም በልጃቸው ላይ ጉዳትን ከሰጉ ወይም ከፈሩ፣ ማፍጠርና ቀኖቹን መክፈል ይችላሉ፡፡



## በረመዳን ጾሙን ያበላሸ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

ማንኛውም ያለ በቂ ምክንያት ጾሙን ያበላሸ ሰው፣ ከባድ ወንጀል ፈጽሟል የፈጣሪውን ትዕዛዝ ጥሷል፡፡ ስለዚህም፣ በተውበት ወደ አላህ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ጾሙን ያበላሸው በግብረ ስጋ ግንኙነት ካልሆነ፣ ከዚህ ከተውበቱ በተጨማሪ ያንን ጾም የፈታበትን ቀን መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ጾሙን የፈታው በግብረ ስጋ ግንኙነት ከሆነ ግን፣ ያንን ቀን መክፈል፣ እንዲሁም ለሠራው ወንጀል ማበሻ፣ ባሪያን ነፃ ማውጣት አለበት፡፡ ይህም፣ ሙስሊም ባሪያን በመግዛትና ከባርነት በማላቀቅ ይተገበራል፡፡ እናስተውል! ኢስላም፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለሰው ልጅ ከባርነት ቀንበር ነፃ መውጣት ትኩረት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ አሁን እንዳለንበት ዘመን ዓይነት ባሪያን ነፃ ማውጣት የማይቻል ከሆነ፣ ሁለት ወሮችን በተከታታይ ይጾማል፡፡ ይህንንም ካልቻለ ስልሳ ሚስኪኖችን ያበላል፡፡

## > የውዴታ ጾም

አላህ (ሱ.ወ) እንዲጾም ግዴታ ያደረገው በዓመት አንድ ወርን ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቻለና ፍላጎት ያለው፣ ከአላህ ተጨማሪ ምንዳን ለማግኘት የሚከጅል ሰው፣ ሌሎች ቀናትንም እንዲጾም ያበረታታል፡፡ ከነኚህ ቀናት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1. የዐሹራን ቀንና ከርሱ በፊት ወይም በኋላ ያለው ቀን፡፡

   የዐሹራ ዕለት የሚባለው በኢሰላማዊው ቀመር መሰረት፣የወርሃ ሙሐረም አስረኛው ቀን ነው፡፡ ይህ ዕለት፣ አላህ(ሰ.ወ) ነብዩላህ ሙሳን(ዐ.ሰ) ከፈርዖን የገላገላቸውና፣ ፈርዖንን በባሕር ውስጥ ያሰጠመበት ዕለት ነው፡፡ ሙስሊሞች አላህ (ሱ.ወ) ነብዩላህ ሙሳን(ዐ.ሰ) ነፃ ስላወጣ፣ እርሱን ለማመስገንና የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ለመከተል ሲሉ ይጾሙታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ቀን ከፊቱ ወይም አንድ ቀን ከኋላው ጹሙ» (አህመድ 2154)

   ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ስለዚህ ዕለት ጾም ተጠይቀው፣ «ያለፈውን ዓመት ወንጀል ያስምራል፡፡» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 1162)

2. የዐረፋ ቀን፡

   ዐረፋ፣ የወርሃ ዙልሒጃ ዘጠነኛው ቀን ነው፡፡ ዙልሒጃ፣ በኢስላማዊ ቀመር መሰረት አስራ ሁለተኛው ወር ነው፡፡ ይህ ቀን ሐጃጆች ዐረፋ በሚባል ቦታ ላይ በመሰብሰብ አላህን ሲለምኑና ሲማጸኑ የሚውሉበት ዕለት ነው፡፡ ከዓመቱ ቀናት ሁሉ የላቀና የበለጠ ቀን ነው፡፡ ሐጅ ላይ ላልተሳተፈ ሰው ይህን ቀን መጾም ይወደድለታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ዐረፋ ዕለት ጾም ተጠይቀው ሲመልሱ፡- «ያለፈውንና የመጪውን ዓመት ወንጀል ያስምራል፡፡» ብለዋል (ሙስሊም 1162)



3. ስድስቱ የሸዋል ቀኖች፡

   ሸዋል አስረኛው ወር ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ረመዳንን የጾመ፣ ከዚያም ከሸዋል ስድስት ቀናትን አስከትሎ የጾመ ሰው፣ አንድ ዓመት ሙሉውን እንደጾመ ይቆጠርለታል፡፡» (ሙስሊም 1164)

ጾምህ

# > የተባረከው የጾም ፍቺ በዓል

በዓላት፣ ከሃይማኖት መገለጫዎች ውስጥ ይመደባሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና በመጡበት ወቅት አንሷሮችን ከዓመቱ ቀናት በሁለት ቀኖች ውስጥ ሲፈነጥዙ፣ ሲጫወቱና ሲደሰቱ አግኝተዋቸው ነበር፡፡ እናም፡ «እነዚህ ሁለት ቀናት የምን ቀኖቻችሁ ናቸው?» በማለት ጠየቋቸው፡፡ እነሱም፡ «ከኢስላም መምጣት በፊት- በጨለማው ዘመን እንደስትባቸው የነበሩ ቀኖች ናቸው፡፡» በማለት መለሱ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አላህ እነዚህን ቀናት ከነርሱ በተሻሉ ሁለት ቀናት ተክቶላችኋል፡፡ የእርድ ዕለትና የፍስክ ዕለት» አሏቸው፡፡ (አቡ ዳውድ 1134) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ በዓላት የሃማኖቶች መገለጫ እንደሆኑ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡- «እያንዳንዱ ሕዝብ በዓል አለው፡፡ ይህ ደግሞ በዓላችን ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 909 /ሙስሊም 892)

## በዓል በኢስላም

በኢስላም ውስጥ፣ በዓል አንድ የአምልኮ ዘርፍን ስላጠናቀቁ ደስታን የሚገልጹበትና አላህ(ሱ.ወ) ለዚህ አምልኮ ስለመራቸውና ስለገጠማቸው እሱን የሚያመሰግኑበት አጋጣሚ ነው፡፡ በዒድ ቀን፣ የሚያማምሩ ልብሶችን በመልበስ፣ ለከጃዮች መልካም በመዋል በሰዎች ልቦና ውስጥ ደስታን መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ ኢስላም ያስተምራል፡፡ በማንኛውም የተፈቀዱ መንገዶች፣ የሁሉም ልቦና የደስታ ስሜት እንዲሰማውና የአላህን ጸጋ የሚያስታውስ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## የሙስሊሞች በዓል


በዓመት ውስጥ ሙስሊሞች የሚያከብሯቸው ሁለት በዓላት አሉ፡፡ ከሁለቱ ቀናት ውጪ ሰዎች እንደ በዓል አድርገው የሚያከብሯቸውን ቀናቶች ማክበር አይፈቀድም፡፡ እነኚህ በዓላት፡ የጾም ፍቺ በዓል ( የወርሃ ሸዋል የመጀመሪያ ቀን) እና የእርድ በዓል (የወርሃ ዙልሒጃ አስረኛ ቀን) ናቸው፡፡



## የጾም ፍቺ በዓል

የጾም ፍቺ በዓል፣ የረመዳን የመጨረሻው ሌሊት ካለፈ በኋላ የሚከተለው የወርሃ ሸዋል የመጀመሪያው ቀን ነው፡፡ የጾም ፍቺ በዓል በመባል የሚጠራውም ለዚህ ነው፡፡ ይህ ቀን፣ ሰዎች ጾማቸውን በማጠናቀቃቸው፣ በጾማቸው አላህን ይገዙበት እንደነበረው፣ በመደሰት አላህን የሚያመሰግኑበት ዕለት ነው፡፡ ሙስሊሞች ይህን በዓል የሚያከብሩት፣ አላህ ጸጋውን ስላሟላላቸውና የረመዳንን ወር በሙሉ ለመጾም ስላደላቸው፣ አላህን እያመሰገኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)» (አል በቀራ 185)

## በኢስላማዊው ሕግ የተደነገጉና በዒዱ ዕለት የሚከናወኑ ነገሮች እንዴት ያሉት ናቸው?



1 **የበዓል ሠላት (የዒድ ሠላት)፡** ኢስላም፣ ሙስሊሞች ከሴቶችና ሕፃናት ጋር በመሆን በአንድነት ወጥተው ይህን ሠላት እንዲሰግዱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡ የመስገጃ ጊዜው፣ ፀሐይ ወጥታ የጦር ዘንግ ያክል ከፍ ካለችበት ቅጽበት ጀምሮ ከሰማይ መሐከል እስከምታዘነብልበት ጊዜ ይረዝማል፡፡

አፈፃፀሙ፡ የዒድ ሠላት ሁለት ረከዓ ነው፡፡ ኢማሙ ሲያሰግድ ቁርኣን የሚያነበው ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲሆን ከሠላቱ በኋላም ሁለት ኹጥባዎችን ያደርጋል፡፡ በዒድ ሠላት «አላሁ አክበር» የሚለውን ቃል በእያንዳንዱ ረከዓ መጀመሪያ ላይ ደጋግሞ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያው ረከዓ ላይ ፋቲሓን ማንበብ ሳይጀምር በፊት፣ ከመጀመሪያው የሠላት መግቢያ ተክቢራ ሌላ ስድስት ጊዜ «አላሁ አክበር» ይላል፡፡ በሁለተኛው ረከዓ ላይ ደግሞ ከመጨረሻው ሱጁድ ሲነሳና ሲቆም ከሚለው ተክቢራ ሌላ አምስት ጊዜ «አላሁ አክበር» ይላል፡፡

2 **የጾም ፍች ምጽዋት(ዘካተል ፊጥር)፡** አላህ (ሱ.ወ) በዒድ ዕለት፣ ቀንና ሌሊቱን ከሚበላው የሚተርፍ ነገር ያለው ሰው አገሬው ከሚመገበው ሩዝ ወይም ስንዴ ወይም ተምር አንድ ቁና ለሙስሊም ድሆችና ችግረኞች እንዲሰጥ ግዴታ አድርጓል፡፡ ይህም ድሆችና ችግረኞች በዒድ ዕለት ተቸግረው እንዳይውሉ ያደርጋቸዋል፡፡

የዘካተል ፊጥር መስጫ ጊዜ፡ የመጨረሻው የረመዳን ቀን ፀሐይ ከጠለቀችበት ሰዓት ጀምሮ፣ የዒድ ሠላት እስከሚሰገድበት ወቅት ድረስ ነው፡፡ ከዒዱ አንድ ወይም ሁለት ሌሊት ቀደም ብሎ መስጠትም ይቻላል፡፡

ዓይነትና መጠኑ፡ ከሀገሬው ምግብ የሆነ አንድ ቁና ሩዝ ወይም ተምርና የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ቁና የመስፈሪያ ልክ ነው፡፡ ነገር ግን በዘመናዊ የሚዛን ልኬት መሆኑ የተሻለ ነው፡፡ በግምት ሦስት ኪሎግራም ይሆናል፡፡

ለራሱ፣ ለሚስቱ ልጆቹ፣ እንዲሁም ቀለብ ለሚሰፍርላቸውና ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ላለ ፅንስ ማውጣትም ይወደዳል፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው ካገሬው ምግብ አንድ ቁና ይወጣለታል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ሲደነግጉ፣ ምጽዋቱ፣ ጾመኛ በማላገጥና በመጫወት ምክንያት የሚያገኘውን ወንጀል እንዲያብስለትና ለችግረኞች ቀለብ ይሆን ዘንድ ነው፡፡ ከሠላት በፊት ላደረሳት፣ ተቀባይነት ያላት ምጽዋት ትሆናለች፡፡ ከሠላት በኋላ ላደረሳት ደግሞ እንደማንኛውም ሠደቃ፣ ሠደቃ ነች ብለን እንወስደዋለን፡፡ (አቡ ዳውድ 1607)

**3** በተፈቀዱ መንገዶች ሁሉ በመጠቀም፣ በተቻለ መጠን፣ በቤተሰብ ውስጥ፣ ትልቁንም፣ ትንሹንም፣ ወንዱንም፣ ሴቱንም፣ እንዲደሰትና እንዲዝናና ማድረግ በኢስላም የተደነገገ ተወዳጅ ተግባር ነው፡፡ የሚያምር ልብስ መልበስም እንዲሁ የተወደደ ነው፡፡ በዒድ ቀን መጾም ክልክል ነው፡፡ በዒድ ቀን የሚወደደው፣ በሙብላትና በማፍጠር አላህን መገዛት ነው፡፡

**4** በኢድ ዋዜማ ሌሊቱን፣ እንዲሁም ወደ ዒድ ሠላት ሲወጣ፣ «አላሁ አክበር» በማለት አላህን ማላቅ ኢስላም የደነገገው ተግባር ነው፡፡ የዒድ አልፊጥር ሠላት ተሰግዶ ሲያበቃ የተክቢራው ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡ ይህ የሚደረገው፣ አላህ(ሱ.ወ) ወደ ጾም በመምራት፣ የተባረከውን የረመዳንን ወር ጾም ለማጠናቀቅ ስላበቃን፣ ለዋለልን ጸጋ እርሱን ለማመስገንና ደስታችንን ለመግለጽ ነው፡፡ አላህ ሱ.ወ እንዲህ ይላል፡- «ቁጥሮችንም ልትሞሉ፣ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህንን ደነገግንላችሁ)» (አል በቀራ 185)

የተክቢራ አባባል፡ «አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር፤ ላኢላሃ ኢለላህ፤ አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር፤ ወሊላሂልሐምድ» የሚል ነው፡፡

እንዲሁም፡ «አላሁ አክበሩ ከቢራ ወልሐምዱሊላሂ ከሲራ ወሱብሓነላሂ ቡክረተን ወአሲላ» ይባላል፡፡

ወንዶች፣ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ፣ ሰዎችን በማይረብሽ ወይም በማያስቸግር መልኩ ተክቢራን መመላለሳቸው የተደነገገ ተግባር ነው፡፡ ሴቶች ግን ድምፃቸውን ዝቅ ማድረግ አለባቸው፡፡



> ሙስሊሞች ከዒድ ሠላት ከወጡ በኋላ የሚያሳይ ምስል



# ምጽዋትህ (ዘካህ)



# 5

አላህ (ሱ.ወ) ምጽዋትን ግዴታ አድርጎ ደንግጓል፡፡ ከኢስላም ማዕዘናት መካከል ሦስተኛ አድርጎታል፡፡ እሷን የማይፈፅም ሰውን ብርቱ በሆነ ቅጣት ዝቶበታል፡፡ ኢስላም፣ ንስሃ መግባትን፣ ሠላት ማቋቋምንና ምጽዋት መስጠትን ከሙስሊሞች የወንድማማችነት ትስስር ጋር አቆራኝቶታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ቢፀፀቱም፣ ሠላትንም ቢሰግዱ፣ ዘካንም ቢሰጡ፣ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው፡፡›› (አል ተውባ 11)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ኢስላም በአምስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ተገነባ፡፡›› ‹‹.....ሠላትን ማቋቋም፣ ምጽዋትን መስጠት›› ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 8 / ሙስሊም 16)

### የምዕራፉ ማውጫ

የምጽዋት ድንጋጌ ዓላማዎች

ምጽዋት ማውጣት ግዴታ የሚሆንባቸው ጉዳዮች

- ወርቅና ብር
- ንብረትና ተቀማጭ ገንዘብ
- ለሽያጭ የቀረቡ ዕቃዎች
- የምድር በቆልቶች
- የእንሰሳት ሀብት

ምጽዋት የሚሰጠው ለነማን ነው?

# ምጽዋት

**ዘካ ማለት አላህ በሙስሊሞች ላይ ግዴታ ያደረገው ቀለል ያለ ገንዘብ መጠን ነው። የድሆችንና የምስኪኖችን ችግር ለማቅለልና ለሌሎች ዓላማዎች ባለሀብቶች የሚሰጡት ነው።**

### የምጽዋት ዓላማዎች

አላህ (ሱ.ወ) ምጽዋትን በሙስሊሞች ላይ ግዴታ ያደረገበት ከባባድ ዓላማዎች አሉት፡፡ ከፊሎቹን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፡

1 ገንዘብን መውደድ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ሲሆን፣ ይህ ባህሪው ገንዘቡን በመያዝና በመጠበቅ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉጉት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ኢስላማዊው ሕግ ነፍስ ከዘቀጡ የስስታምነትና ልክ የለሽ የገንዘብ ጥማት ባህሪዎች እንድትጸዳና እንዲሁም ከቁሳቁስ ፍቅርና እንድትላቀቅ ምጽዋትን በግዴታነት ደነገገ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከገንዘቦቻቸው ስትኾን፣ በርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነች ምጽዋትን ያዝ፡፡» (አልተውባ 103)

2 ምፅዋት መስጠት በማኅበረሰቡ መካከል የመደጋገፍና የመዋደድ መሰረትን ይጥላል፡፡ የሰው ልጅ ነፍስ ውለታ የዋለላትን አካል በመውደድ ላይ የተገራች ናት፡፡ በምጽዋት አማካይነት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ አባላት ልክ እንደ አንድ ግንብ ከፊሉ ከፊሉን የሚደግፍና እርስ በርሳቸው የሚዋደዱና የሚደጋገፉ ሆነው ይኖራሉ፡፡ በመሐከላቸው ስርቆት፣ ዘረፋና ማጭበርበር በብዛት የማይታየውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

3 በምጽዋት፣ ለዓለማት ጌታ ሙሉ ለሙሉ መማረክና ፍጹም ታዛዥ መሆን ይረጋገጣል፡፡ አንድ ባለ ሃብት፣ ከንብረቱ ላይ ምጽዋትን በሚያወጣ ጊዜ የአላህን ሕግጋት በመተግበርና ትዕዛዙን በመፈፀም ላይ ሲሆን በተሰጠው ጸጋ ላይ የጸጋውን ባለቤት እያመሰገነም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «ብታመሰግኑም እጨምርላችኋለሁ፡፡» ይለናን፡፡ (ኢብራሂም 7)

4 ምጽዋትን በመተግበር ማኅበራዊ ዋስትና ይረጋገጣል፣ እንዲሁም በተለያዩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች መካከል አንጻራዊ የሆነ የኢኮኖሚ መመጣጠን ይከሰታል፡፡ በተጨማሪም ምጽዋትን ለሚገባቸው የማኅበረሰቡ ክፍሎች መስጠት፣ ሀብት በተወሰኑ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ውስጥ የተገደበና የተከማቸ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- «ከናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን፡፡» ይላል፡፡




> ገንዘብን መውደድ ከሰው ልጅ የተቀረፀ ተፈጥሮአዊ መለያ ሲሆን ኢስላም ነፍስን ወደ ማንጻትና በገንዘብ ላይ የተንጠለጠሉ ወደ አለመሆን ተጣርቷል።

ምጽዋትህ (ዘካህ)

## ምጽዋት ሊወጣለት ግዴታ የሚሆን ንብረት የትኛው ነው?

አንድ ሰው ለራሱ በሚጠቀምበት ንብረቱ ላይ ምጽዋት የማውጣት ግዳጅ የለበትም፡፡ ለምሳሌ፣ ዋጋው ምንም ያህል ቢወደድም የሚኖሪያ ቤቱ፣ እንዴትም ያለ ዘመናዊና የቅንጦት ቢሆንም ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስበት መኪናው ላይ፣ ምጽዋት የማውጣት ግዴታ የለበትም፡፡ በሚለብሰው፣ በሚበላውና በሚጠጣውም ነገር ላይ እንዲሁ የግዴታ ምጽዋት የለበትም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ምጽዋትን ግዴታ ያደረገው በግል ጉዳይ ላይ ግልጋሎት የማይሰጡ በሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ላይ ሲሆን እነኚህ ንብረቶች በባሕሪያቸው እየጨመሩና እየፋፉ የሚሄዱ ናቸው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው:-




**1** ለጌጥነትና ለውበት የማይለበስ የሆነ ወርቅና ብር

የወርቅና የብር ክምችትም ሆነ ማንኛውም ንብረት፣ ኢስላማዊው ሕግ የገደበውን መጠን (ሂሣብ) ካልሞላ፣ እንዲሁም ሳይቀንስ አንድ የጨረቃ ዓመት ማለትም 354 ቀናቶች ካልዞረበት በስተቀር ምጽዋት(ዘካ) ሊወጣበት ግዳጅ አይሆንም፡፡

በሁለቱ ማዕድናት ምጽዋት የማውጪያ መጠን (ሂሣብ)

ሂሣብ፣ ለወርቅ 85 ግራምና ከዚያ በላይ ለብር ደግሞ 595 ግራምና ከዚያ በላይ ነው፡፡

አንድ ሙስሊም ይህን መጠን የሚደርስ ወርቅ ወይም ብር ካለውና አንድ ዓመት ከዞረበት፣ ከንብረቱ 2.5 ፐርሰንቱን ይመጸውታል(ዘካ ያወጣል)፡፡




**2** ተቀማጭ ገንዘብና የተለያዩ የመገበያያ ኖቶች እንደ ዓይነታቸው በካሽ በእጁ ያለ ወይም በባንክ አካውንት ውስጥ የሚገኝ ገንዘብ ዘካ ይወጣለታል፡፡

የግዴታ ምጽዋት(ዘካ) አወጣጥ፡

የገንዘቡንና የመገበያያውን ነገር ሊገዛ ከሚችለው የወርቅ መጠን ጋር በማስላት፣ መጠኑ ወርቅ ዘካ ከሚወጣበት ሂሣብ ጋር እኩል ከሆነና ከዚያም ከበለጠ ዘካ ያወጣለታል፡፡ ገንዘቡ ከ85 ግራም ወርቅ ጋር ከተስተካከለ ወይም ከበለጠ፣ እንዲሁም በሰውዬው ይዞታ ስር ኾኖ ሳይቀንስ አንድ የጨረቃ ዓመት ካለፈበት፣ የንብረቱን 2.5 ፐርሰንት ዘካ ያወጣል፡፡

የወርቅ ዋጋ ከፍ፣ ዝቅ ሊል፣ ሊወዋወጥ ይችላል፡፡ በአንድ ሰው ላይ ዘካ ማውጣት ግዳጅ በሚሆንበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 25 ዶላር ነው ብለን ብናስብ፣ በዚያ ወቅት የዘካ ማውጫ መጠን ወይም ሂሣብ የሚከተለው ይሆናል፡፡

25 ዶላር/ግ.ም X 85ግ.ም = 2125 ዶላር ይሆናል፡፡ 85ግ.ም- ምጽዋት ማውጣት ግዳጅ የሚሆንበት የወርቅ መጠን ሲሆን ይህ ቋሚና የማይለወጥ ነው፡፡ 2125 ዶላር-በቀረበው ምሳሌ መሰረት ዘካ ግዳጅ የሚሆንበት የገንዘብ መጠን(ሂሣብ) ነው፡፡ ስለዚህ የዘካው መጠን- 2.5% X 2125 ዶላር = 53.125 ዶላር ይሆናል፡፡



### 3 ለንግድ የቀረቡ ዕቃዎች

ለንግድ የተዘጋጁ፣ እንደ ሪል ኢስቴቶች፣ ቤቶች፣ ሕንፃዎች ያሉ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፡ ወይንም ምግብ ነክ እና አላቂ ሸቀጦች በዚህ ስር ይገባሉ፡፡

የዘካው አወጣጥ፡ ነጋዴው ለንግድ ዕቃዎቹን በሙሉ ዓመት ዞሮባቸው ከሆነ ዋጋቸውን ያሰላል፡፡ የሚያሰላበት ዋጋም ዘካውን ሊያወጣ በተነሳበት ዕለት ባለው የገበያ ዋጋ መሰረት ነው፡፡ የቃዎቹ ዋጋ የዘካ ማውጫ መጠን (ኒሳብ) ከደረሰ፣ ከሱ ላይ 2.5 ፐርሰንት ዘካ ያወጣለታል፡፡



### 4 ከምድር የሚበቅሉ፡ አዝመራ፣ ፍራፎሮችና የእህል አይነቶች

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ ካፈራችሁትና ከዚያም ለናንተ ከምድር ካወጣንላችሁ ከመልካሙ ለግሱ፡፡» (አል በቀራ 267)

ዘካ ማውጣት ግዴታ የሚሆነው በተወሰኑ የአዝርዕት ዓይነቶች ላይ እንጂ በሁሉም አይደለም፡፡ ይህም በኢስላማዊው ድንጋጌ መሰረት ዘካ የሚወጣለትን መጠን ከደረሰ ብቻ ነው፡፡

የሰዎችን ልፋትና ድካም ከግምት ውስጥ ከማስገባት አንጻር፣ ዘካ የሚወጣው ብዛት በዝናብና በወንዝ ውሃ በለሙና በሰው ኃይል ወይም መስኖ በለሙት መካከል ልዩነት አለው፡፡



### 5 እንደ ላም፣ ግመልና ፍየል ያሉ የእንስሳት ሃብት፡ ባለሃብቱ፣ እነሱን በመቀለብ የማይቸገርና የማይለፋ ከሆነ እንዲሁም በግጦሽ ላይ ተሰማርተው ውለው የሚገቡ ከሆነ ዘካ ይወጣላቸዋል፡፡

የሚወጣበትን መጠን (ኒሳብ) የሚወጣለትን መጠንና የመሳሰሉትን ዝርዝር መረጃዎች ከፊቂህ መጽሐፍት ላይ የምናገኘው ይሆናል፡፡

## ምጽዋት የሚሰጠው ለነማን ነው?

ኢስላም ዘካ የሚሰጣቸውን ክፍሎች ገድቦ አስቀምጧል፡፡ አንድ ሙስሊም ከነኚህ ክፍሎች መካከል ለአንዱ ብቻ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ አካሎች ዘካውን መስጠት ይችላል፡፡ ለሚገባቸው ክፍሎች ሊያከፋፍሉለት ለሚችሉ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበሮች መስጠትም ይችላል፡፡ ዘካን በሀገር ውስጥ ማከፋፈሉ በላጭ ነው፡፡

ዘካ የሚገባቸው ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡

1 ድሆችና ችግረኞች፡ አንገብጋቢና መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላትና ለመሸፈን በቂ አቅም የሌላቸው ናቸው፡፡

2 ዘካን በመሰብሰብና በማከፋፈል ስራ ላይ የተሰማሩ የዘካ ሰራተኞች

3 ከአሳዳሪው እራሱን በመግዛት ነፃ ለመውጣት ለሚጥር ባሪያ፡፡ ይህ ሰው ዘካን በመውሰድ ነፃነቱን ያውጃል፡፡

4 ብድር ተበድሮ መክፈል ያቃተው ሰው፡ የተበደረው ብድር ለሰዎች በጎ ለመዋልና ለሕዝባዊ ጥቅም ወይም ለግል ጉዳይ ቢሆንም ልዩነት አይኖረውም፡፡

5 በጦር ግንባር በአላህ መንገድ ላይ ለሚፋለም ጀግና፡ እነኚህ ደግሞ ከሃይማኖታቸውና ከአገራቸው ጠላትን በመመከትና በመጋፈጥ ላይ ያሉ ተዋጊዎች ሲሆኑ ማንኛውም ኢስላምን ለማስፋፋትና ለማስራጨት፣ የአላህን ቃል ከፍ ለማድረግ የሚሰራ ስራም በዚሁ ስር የሚካተት ነው፡፡

6 ልቦናቸው ከኢስላም ጋር በመላመድ ላይ ላሉ አዲስ ሙስሊሞች፡ እነኚህ፣ ከሃዲያን የነበሩ፣ በቅርቡ ኢስላምን የተቀበሉ፣ ወይም ይሰልማሉ ተብሎ የሚከጀሉና ተስፋ የሚጣልባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ለእነኚህ ዘካ የሚሰጧቸው ግለሰቦች ሳይሆኑ፣ መንግሳታዊ ክፍሎችና ጠቃሚነቱን ሊያገናዝቡና ሊመረምሩ የሚችሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ናቸው፡፡

7 ስንቅ ያለቀበት መንገደኛ፡ ይህ ሰው በአገሩ ከፍተኛ ካፒታል ወይም ንብረት ያለው ቢሆንም ባለበት ሁኔታ፣ ስንቅ ካለቀበት፣ ከተቋረጠበትና ገንዘብ ካስፈለገው ዘካ ይሰጠዋል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ዘካ የሚገባቻን ክፍሎች ሲያብራራ እንዲህ ብሏል፡- «የግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድሆች፣ ለሚስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በኢስላም) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም ነፃ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሰሩ፣ በመንገደኞችም ብቻ ነው፡፡» (አል ተውባ 60)



> ድሆች ማት ለአስፈላጊና መሠረታዊ ፍላጐቶችን የሚያሟሉበት አቅም የሌላቸው ማለት ነው።

## የእንሰሳት ሃብት ዘካ

የእንሰሳት ሃብት፣ሰዎች የሚገለገሉባቸው የቤት እንሰሳት ማለት ነው፡፡ እነሱም ግመል፣ ላምና ፍየል ወይንም በግ ናቸው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እነኚህን እንሰሳት በመፍጠር ለሰዎች ትልቅ ውለታ ውሎላቸዋል፡፡ ሰዎች ስጋዎቻቸውን ይመገባሉ፤ ከቆዳዎቻቸው ልብስን ይለብሳሉ፤ በመንገድ ሲጓዙና ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ እነሱንና ጓዛቸውን ይሸከሙላቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦ «ግመልን፣ ከብትን፣ ፍየልንም፣ በርሷ (ብርድን መከላከያ) ሙቀት፣ ጥቅሞችም ያሉባት ስትኾን ለናንተ ፈጠረላችሁ ከርሷም ትበላላችሁ፡፡ ለናንተም በርሷ ወደ ማረፊያዋ በምትመልሷት ጊዜ፣ በምታሰማሩዋትም ጊዜ ውበት አላችሁ፡፡ ጓዞቻችሁንም በነፍሶች ችግር እንጂ ወደማትደርሱባት አገር ትሸከማለች ጌታችሁ በእርግጥ ርኅሩኅ አዛኝ ነውና፡፡ (አል ነሕል 5-7)

## የእንሰሳት ዘካ ጥቅላዊ መስፈርቶች

በእነኚህ እንሰሳት ላይ ዘካ ግዴታ የሚሆነው የሚከተሉት መስፈርቶች ሲሟሉ ነው፡

1. ብዛታቸው የኢስላማዊውን ዘካ የማወጫ መጠን(ሂሣብ) መድረስ፡ ምክንያቱም ዘካ በባለሃብቶች ላይ እንጂ በሌላው ላይ ግዴታ አይደለም፡፡ ለግል ጉዳያቸው የሚጠቀሙባቸው ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ እንሰሳት ያሉት ሰው የዘካ ግዴታ የለበትም፡፡ ከግመል ዘካ የሚወጣው ቁጥራቸው አምስት ሲደርስ ነው፡፡ ለፍየል አርባ፣ ለላም ደግሞ ሰላሳ ነው፡፡ ቁጥራቸው ከዚህ ቁጥር በታች ከሆነ የዘካ ግዴታ የለበትም፡፡
2. በይዞታነት ባለሀብቱ ዘንድ አንድ ሙሉዕ የጨረቃ ዓመት ሊዞርባቸው ወይም ሊያስቆጥሩ ይገባል፡፡
3. በግጦሽ ላይ ተሰማርተው የሚበሉ መሆን አለባቸው፡ እንሰሰዎቹ በግጦሽ ላይ የሚኖሩ፣ ድርቆሽና ግጦሽ በማቅረብ ባለንብረቱ ወጪ የማያደርግባቸው መሆን አለበት፡፡
4. እንሰሳቱ በስራ የተጠመዱ መሆን የለበትም፡፡ ባለቤቱ ማሳውን የሚያርስበት ወይም ዕቃ የሚያጓጉዝበት ወይም እራሱ የሚጓጓዝበት መሆን የለበትም፡፡ ይህ ከሆነ ዘካ የማውጣት ግዳጅ የለበትም፡፡



ምጽዋትህ (ዘካህ)

የጋማ ከብቶች የዘካ አወጣጥ

## 1 ግመል

ሁሉም የግመል ዓይነቶች ባለ አንድ ሻኛ ወይም ባለ ሁለት ሻኛ ቢሆኑም ብዛታቸው አምስት ከደረሰ ዘካ ማውጣት ግዴታ ነው፡፡

| ብዛት | | ግዴታ የሚሆንበት መጠን | ብዛት | | ግዴታ የሚሆንበት መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| ከ | እስከ | | ከ | እስከ | |
| 5 | 9 | አንድ ሴት ፍየል | 46 | 60 | ሒቃህ (የሦስት ዓመት እድሜዋን ጨርሳ አራተኛ እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል) |
| 10 | 14 | ሁለት ሴት ፍየሎች | 61 | 75 | ጀዝዐህ (የአራት ዓመት እድሜዋን ጨርሳ አምስተኛ እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል) |
| 15 | 19 | ሦስት ሴት ፍየሎች | 76 | 90 | ሁለት ቢንት ለቡን (የሁለት ዓመት እድሜያቸውን ጨርሰው የሦስተኛ ዓመት እድሜያቸውን የጀመሩ ሴት ግመሎች) |
| 20 | 24 | አራት ሴት ፍየሎች | 91 | 120 | ሁለት ሒቃህ (የሦስተኛ ዓመት እድሜያቸውን ጨርሰው የአራተኛ ዓመት እድሜያቸውን የጀመሩ ሴት ግመሎች) |
| 25 | 35 | ቢንት መኻድ (የአንድ ዓመት እድሜዋን ጨርሳ ሁለተኛ ዓመት እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል) | ብዛታቸው ከ120 በላይ ሲሆን በየ40ዎቹ ተጨማሪ ግመሎች | | አንድ ቢንት ለቡን (የሁለት ዓመት እድሜዋን ጨርሳ የሦስተኛ ዓመት እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል) ከላይ ከተቀመጠው ቁጥር ላይ ይጨመራል፡፡ |
| 36 | 45 | ቢንት ለቡን (የሁለት ዓመት እድሜዋን ጨርሳ ሦስተኛ እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል) | በየ50ዎቹ ተጨማሪ ግመሎች | | አንድ ሒቃህ የሦስተኛ ዓመት እድሜዋን ጨርሳ የአራተኛ ዓመት እድሜዋን የጀመረች ሴት ግመል ከበላይ ከተቀመጠው ቁጥር ላይ ይጨመራል |



## 2 ከብት

ከከብት ላይ ዘካ ግዴታ የሚሆነው የከብቶቹ ቁጥር ከ30 በላይ ሲሆን ነው

| ብዛት | | ግዴታ የሚሆንበት መጠን |
|---|---|---|
| ከ | እስከ | |
| 30 | 39 | አንድ ጥጃ (አንድ ዓመት የሞላው ጥጃ) |
| 40 | 49 | አንድ ሙሲናህ (የሁለት ዓመት እድሜዋን የጨረሰች ላም) |
| 60 | 69 | ሁለት ጥጆች (ሁለት ዓመት የሞላቸው) |
| 70 | 79 | አንድ መሲናህ (ሁለት ዓመት የሞላት ላም) እና ተቢዕ (አንድ ዓመት የሞላው ጥጃ) |
| 80እና ከዚያ በላይ በየ30ዎቹ | | አንድ ተቢዕ (አንድ ዓመት የሞላው ጥጃ) ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር ላይ ይጨመራል። |
| በየ40ዎቹ | | ሙሲናህ (ሁለት ዓመት የሞላት ላም) ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር ላይ ይጨመራል። |



## 3 በግና ፍየል

የበጎችና የፍየሎች ቁጥር ከ40 በላይ ሲሆን ዘካ ማውጣት ግዴታ ይሆናል



| ብዛት | | ግዴታ የሚሆንበት መጠን |
|---|---|---|
| ከ | እስከ | |
| 40 | 120 | አንድ በግ (ፍየል) |
| 121 | 200 | ሁለት በግ (ፍየል) |
| 201 | 399 | ሦስት በግ (ፍየል) |
| 400 | 499 | አራት በግ (ፍየል) |
| 500 | 599 | አምስት በግ (ፍየል) |
| ከ600 በላይ ከሆነ በእያንዳንዱ 100 ተጨማሪ በግና ፍየል አንድ በግ ወይም ፍየል ተጨማሪ ይደረጋል | | |
| 600 | | 6 በግ (ፍየል) |
| 700 | | ሰባት በግ (ፍየል) |

## የአዝርዕትና የጥራጥሬዎች ዘካ

የአዝርዕትና የጥራጥሬዎች ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸው መስፈርቶች:-

1. ምርቱ የዘካ ማውጫ መጠን (ሂሣብ) የደረሰ መሆኑ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘካ ማውጣት ግዳጅ የሚሆንበትንና ከርሱ በታች ከሆነ ዘካ ማውጣት ግዳጅ የማይሆንበትን መጠን (ሂሳብ) ወሰን አበጅተውለታል፡፡ ይህንኑ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል:- «ከአምስት አውሱቅ በታች የሆነ የተምር ምርት፣ የዘካ ግዳጅ የለበትም፡፡» (አል ቡኻሪ 1405 / ሙስሊም 979)

አውሱቅ ማለት የስፍር መለኪያ ሲሆን፣ ከ580 እስከ 600 ኪሎግራም የሚደርስ የስንዴና የሩዝ መጠንን ይመዝናል፡፡ ስለዚህም፣ መጠኑ ከዚህ በታች በሆነ ፍሬ ላይ ዘካ ግዴታ አይሆንም፡፡

2. አዝርዕቶቹ ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸው የአዝርዕት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

የሰው ልጅ እንደምግብነት በምርጫው የሚጠቀምባቸውና በክምችት መልክ ለረዥም ጊዜ ሳይበላሹ ሊቀመጡ የሚችሉ፣ እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ ዘቢብ፣ ተምር፣ ሩዝና በቆሎ የመሳሰሉ አዝርዕቶች ናቸው፡፡

ለመሰረታዊ ምግብነት የማያገለግሉና ሳይበላሹ፣ ሊከማቹ የማይችሉ የሆኑ ፍራፍሬዎችና አትክልቶች ላይ የዘካ ግዴታ የለም፡፡ እንደ ሩማን፣ እቾሎኒና የመሳሰሉትን ማለት ነው፡፡

3. ምርቱ ሙሉ ለሙሉ የተሰበሰበ ወይም የተለቀመ መሆን አለበት

በአዝርዕትና በጥራጥሬዎች ላይ ዘካ ግዴታ የሚሆነው ምርቱ ሙሉ ለሙሉ ከተሰበሰበና ከተለቀመ በኋላ ነው፡፡ ዓመት መቆጠሩ መስፈርት አይሆንም፡፡ ምርቱ በተሰበሰበበት ወቅት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ በዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ ምርቱ የሚሰበሰብ ከሆነም በእያንዳንዱ የምርት ለቃሚ ወቅት ዘካ ማውጣት ግዴታ ይሆናል፡፡ በዚሁ መልክ በየ ምርት ለቃሚ ወቅት ዘካ ይወጣል ማለት ነው፡፡ ዘካ አውጥቶለት ለረዥም ዓመታት ቢያከማቸው በዚያ ክምችቱ ላይ ዘካ የማውጣት ግዴታ የለበትም፡፡


## ግዴታ የሚሆነው የዘካ መጠን

ኢስላም፣ በዝናብና በወንዝ በሚለሙ የአዝርዕት ምርቶችና በሰው ጉልበት ወይም በመስኖ የሚለሙ የአዝርዕት ምርቶች መካከል የሚወጣውን የዘካ መጠን አበላልጧል፡፡ በዝናብና በወንዝ የሚለሙ የአዝርዕት ምርቶች ላይ ዐሥር በመቶ

እንዲወጣ፣እንዲሁም ገበሬው በመዝራቱ፣ በማጠጣቱና ውሃ ወደ ማሳው እንዲደርስ በማድረጉ፣ ከምንጭና ከጉርጓድ ውሃ በማውጣት መስኖ በማዘጋጀት ለፍቶና ደክሞ ያመረታቸውን ደግሞ አምስት በመቶ ዘካ እንዲያወጣ አዟል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «ዝናብና ምንጮች ባጠጧቸው ምርቶች ላይ አንድ አስረኛ፣ በመስኖ በጠጡ ምርቶች ላይ ደግሞ የአንድ አስረኛ ግማሽ ዘካ አለበት፡፡» (አል ቡኻሪ 1483)





# ሐጅህ



# 6

የሐጅ አምልኮን ለመፈፀም ወደ መካ መጓዝ ከኢስላም ማዕዘናት መካከል አምስተኛው ማዕዘን ነው፡፡ ሐጅ፡ በአካል፣ በቀልብና በገንዘብ የሚከናወኑ የአምልኮ ዓይነቶች የሚሰባሰቡበት አምልኮ ዘርፍ ነው፡፡ በአካሉና በገንዘቡ ይህን አምልኮ መፈፀም በቻለ ሰው ላይ ሁሉ በዕድሜው አንድ ጊዜ መፈፀም ግዴታ ነው፡፡
አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡»
(አለ ዒምራን 97)

## የምዕራፉ ማውጫ

የመካ እና የተከበረው መስጂድ(መስጂደል ሐራም) ብልጫ

የሐጅ ትርጉም

አንድ ሙስሊም ሐጅ የመቻሉ ሁኔታ

ለሴት ልጅ ሐጅ መህረም (የቅርብ ተጠሪዋ ወንድ) አብሯት መኖር መስፈርት ስለመሆኑ

የሐጅ ትሩፋት

የሐጅ ዓላማዎች

ዑምራ

የተባረከው የእርድ በዓል

- በበዓል ቀን ምን ምን ይሰራል?
- የሚታረዱ እንስሳት ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች
- የእርድ አፈፃፀም

የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከተማ፣ መዲናን መጎብኘት

# ሐጅ

## የመካ እና የመስጂዱል ሐራም ትሩፋት

መስጂደል ሐራም የሚገኘው በዐረብያ ደሴት፣ በስተምዕራብ በኩል፣ በቅድሲቷ የመካ ከተማ ውስጥ ነው:: በኢስላም፣ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠውና በርካታ ትሩፋት ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል::

**1** በውስጡ የተከበረው ካዕባ የሚገኝ መሆኑ

ካዕባ፡ ማለት ወደ ሬክታንግልነት ያደላ ግንባታ ሲሆን በቅድሲቷ መካ ከተማ ውስጥ በመስጂደል ሐራም መሐል ላይ የሚገኝ ነው:: መካ፣ ሙስሊሞች አላህ ያዘዛቸውን ሠላት ሲሰግዱና ሌሎችንም አምልኮዎች ሲፈፅሙ የሚቅጣጩባት ወይም ፊታቸውን የሚያዞሩባት የአምልኮ አቅጣጫ ነች::

ለመጀመሪያ ጊዜ በአላህ ትዕዛዝ የገነቧት ነብዩ ኢብራሂምና ልጃቸው ነብዩ ኢስማኢል ናቸው:: ከዚያ በኋላ ለበርካታ ጊዜ በተደጋጋሚ እድሳት ተደርጎላታል::

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:- «ኢብራሂምና ኢስማዒልም ጌታችን ሆይ ከኛ ተቀበል አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና የሚሉ ሲኾኑ ከቤቱ መሰረቶቹን ከፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ)::» (አል በቀራ 127)

ነብዩ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) የቅድሲቷ መካ ነዋሪዎች የነበሩ ጎሳዎች አፍርሰው በድጋሚ በሰሯት ጊዜ ጥቁሩን ድንጋይ ወደ ቦታው በመመለሱ ላይ ተሳትፈዋል::

**2** በምድር ላይ የመጀመሪያው መስጂድ መሆኑ

ታላቁ ሠሐብይ አቡ ዘር አልጊፋሪ(ረ.ዐ)፣ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ)፣ «የአላህ መልክተኛ ሆይ በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው መስጂድ የቱ ነው?» ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ፡

«መስጂደል ሐራም ነው::» በማለት መልሰውለታል::

ከዚየስ? ሲላቸው፣ «መስጂደል አቅሷ ነው::» ብለውታል::

«በመካከላቸው ስንት ዓመት አለ?» ሲላቸው ደግሞ፡

«አርባ ዓመት» ካሉት በኋላ፣ «የትም ቢሆን ሠላት ከደረሰብህ ስገድ በሱ ውስጥ ትሩፋቱ አለና» አሉት:: (አል ቡኻሪ 3186/ ሙስሊም 520)



> የካዕባ በር በርካታ የቁርዓን አንቀጾች በላዩ ላይ ተጽፈዋል

**3** በሱ ውስጥ የሚሰገድ ሠላት ምንዳው እጥፍ ድርብ መሆኑ

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «በዚህ መስጂዴ (በመዲና መስጂድ ውስጥ) የሚሰገድ ሠላት፣ ከመስጂደል ሐራም ውጭ ባሉ መስጂዶች ከሚሰገዱ አንድ ሺህ ሠላቶች ይበልጣል:: በመስጂደል ሐራም ውስጥ የሚሰገድ ሠላት ደግሞ ከርሱ ውጭ ባሉ መስጂዶች ከሚሰገድ አንድ መቶ ሺህ ሠላቶች ይበልጣል::» (ኢብኑ ማጀህ 1406/ አህመድ 14694)

4 አላህና መልክተኛው የከለሏት መሆኗ

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የታዘዝኩት የዚህችን አገር ጌታ ያንን ክልል ያደረጋትን እንድገዛ ብቻ ነው፡፡ ነገሩም ሁሉ የርሱ ነው፡፡ ከሙስሊሞችም እንድኾን ታዝዣለሁ (በል)፡፡» (አል ነምል 91)

አላህ (ሱ.ወ)፣ መካን ሰዎች በውስጧ ደም እንዳይፋሰሱባት፣ ማንንም እንዳይበድሉባት፣ አደን እንዳያድኑባት፣ ዛፎቿንና ተክሎቿን እንዳይቆርጡ እርም አድርጓታል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ (ሱ.ወ) መካን እርም አድርጓታል፤ እርም ያደረጓት ሰዎች አይደሉም ፤ እናም በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው በውስጧ ደም ሊያፈስም ሆነ ዛፎቿን ሊቆርጥ አይፈቀድለትም፡፡» (አል ቡኻሪ 104/ ሙስሊም 1354)


5 አላህና መልክተኛው ዘንድ ከሀገራት ሁሉ በጣም ተወዳጅ መሆኗ

ከሡሐቦች መካከል አንዱ እንዲህ ብሏል፡- «ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በመጓጓዣቸው ላይ ሆነው በሃዝዋ መንደር (በመካ ውስጥ ያለች መንደር ናት) እንዲህ እያሉ ተመልክቻቸዋለሁ፡ «ወላሂ አንቺ በላጭ የአላህ መሬት ነሽ፤ አላህ ዘንድም ተወዳጇ የአላህ መሬት ነሽ፡፡ ካንቺ እንድወጣ ባልደረግ ኖሮ አልወጣም ነበር፡፡»» (አል ቲርሚዚ 3925 / አል ነሳኢ ፊል ኩብራ 4252)

6 አላህ (ሱ.ወ)፣ በይተል ሐራምን መጎብኘት በቻለ ሰው ላይ መጎብኘትን ግዴታ ያደረገ መሆኑ

ነብዩ ኢብራሂም(ዐ.ሰ)፣ ሰዎች ሐጅ እንዲያደርጉ ተጣርቷል፡፡ ሰዎችም ከየስፍራው ወደተከበረው የአላህ ቤት መጡ፡፡ ነብያት ወደረሱ በመምጣት ጅሐ እንዳደረጉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነግረውናል፡፡ አላህም ኢብራሂምን በዚህ አዟቸው እንደነበረ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «(አልነውም) በሰዎችም ውስጥ በሐጅ ትዕዛዝ ጥራ፤ እግረኞች፣ ከየሩቅ መንገድ በሚመጡ ከሲታ ግመሎችም ሁሉ ላይ ኾነው ይመጡሃልና፡፡» (አል ሐጅ 27)





> በካዕባ ዙሪያ ሰባት ጊዜ መዞር ወይም ጠዋፍ ማድረግ፣ ከሐጅና ዑምራ ማዕዘናት መካከል አንዱ ነው፡፡

## > የሐጅ ትርጉም

ሐጅ ማለት የተወሰኑ አምልኮት ተግባራትን ለመፈፀም ወደተከበረው አላህን ማምለኪያ ቤት- በይቱላሂል ሐራም(ካዕባ) በማሰብ መጓዝ ነው፡፡ ከዚያም፣ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላለፉ ተግባሮችና ንግግሮችን ማከናወን ነው፡፡ ኢሕራም መታጠቅ፤ በካዕባ ዙሪያ ሰባት ጊዜ መዞር፤ በሦፋና በመርዋ ኮረብታዎች መሐል ሰባት ጊዜ መመላለስ፤ በዐረፋ መቆም፤ በሚና ጠጠሮችን መወርወርና ሌሎችንም ተግባራት መፈፀምን ያጠቃልላል፡፡

ሐጅ በውስጡ ለአላህ ባሮች ከበባድ ጥቅሞችን ይዟል፡፡ ከነኚህም ጥቀሞች መካከል፤ የአላህን አሃዳዊነት በይፋ ማሳየት፣ ሐጃጆች የሚጎናጸፉት ላቅ ያለ ምህረት፣ የሙስሊሞች መተዋወቅ፣ የሃይማኖት ድንጋጌዎችን በተግባር መማርና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

የሐጅ ወቅት፡ የሐጅ ተግባራት የሚፈፀሙት ከዙልሒጃ ወር ስምንተኛው ቀን አንስቶ እስከ አስራ ሶስተኛው ቀን ድረስ ነው፡፡ ዙልሒጃ፣ በጨረቃ ቀመር (ኢስላማዊ አቆጣጠር) መሰረት አስራ ሁለተኛው ወር ነው፡፡

### ሐጅ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

ሐጅ ግዴታ የሚሆነው፣ በአንድ ለኃላፊነት በደረሰ ሙስሊም ላይ ሲሆን እርሱም የሚችል ከሆነ ነው፡፡

የመቻል ትርጉም

መቻል ስንል፡ ሕጋዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ወደ በይተል ሐራም መድረስ መቻልና የሐጅን ሥርዓት ከተለመደው በጉዞ ላይ ከሚያጋጥም መንገላታት ውጭ ምንም ዓይነት መንገላታትም ሆነ ችግር ሳይገጥመው መፈፀም መቻል ነው፡፡ በተጨማሪም ለነፍሱና ለንብረቱ ዋስትና የሚኖረው መሆን፤ ለሐጅ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት ወጪ የሚያደርገው ገንዘብ፣ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ከሚሸፍንበትና በርሱ ስር ከሚተዳደሩ ሰዎች ወጪ የተረፈ ሲሆን ነው፡፡

## > አንድ ሙስሊም ሐጅ ማድረግ የመቻል መገለጫዎች፡

1. በራሱ ሐጅ ማድረግ መቻሉ፡ አንድ ሙስሊም፣ በቂ ገንዘብ ያለው ከሆነና ከተለመደው የጉዞ እንግልት በተጨማሪ ምንም ዓይነት እንግልት ሳይደርስበት በራሱ ወደ በይተል ሐራም መድረስ ከቻለ የግዴታን ሐጅ በራሱ የማድረግ ግዳጅ አለበት፡፡

2. በራሱ ሳይሆን በሌላ ሰው ሐጅን ማስፈፀም የሚችል መሆኑ፡ ዕድሜው የገፉ አዛውንት በመሆኑ ወይም ህመምተኛ በመሆኑ ምክንያት ሐጅ ማድረግ የማይችል፣ ነገር ግን እርሱን ወክሎ ሐጅ ሊያደርግለት የሚችልን ሰው የሚያገኝ ከሆነና እርሱን ወክሎ ሐጅ እንዲያደርግለት ወጪውን መሸፈን ከቻለ፣ የወኪሉን ወጭ ሸፍኖ ሐጅ የማስደረግ ግዴታ አለበት፡፡

3. በራሱም ሆነ በሌላ ሰው አማካይነት ሐጅ ማድረግ የማይችል፡ ይህ ዓይነቱ ሰው የማይችል እስከሆነ ድረስ ሐጅ የማድረግ ግዴታ የለበትም፡፡

ፍላጎቱን ከሚያሟላበትና የቤተሰቡን ወጪ ከሚሸፍንበት የሚተርፈው ሐጅ ሊያደርግበት የሚችል ምንም ዓይነት ገንዘብ የሌለው ሰው በምሳሌነት ይጠቀሳል፡፡

ሐጅ ማድረግ የሚያስችለው ገንዘብ ለማግኘት ገንዘብ የማሰባሰብ ግዴታ የለበትም፡፡ በቻለ ጊዜ ግን ሐጅ ግዳጅ ይሆንበታል፡፡

ሐጅ ለማድረግ የሚያበቃህ የሆነ በቂ ገንዘብና አካላዊ ብቃት አለህን?

- አዎን → በራስህ ሐጅ ልታከናውን ግዴታ ይሆንብሃል፡፡
- አይቻልም(በፍፁም) ↓

ሐጅ ለማድረግ በቂ ገንዘብ አለህ ነገር ግን ይድናል ተብሎ በማይከጀል ሕመም ምክንያት ሐጅ ለማድረግ የሚያስችል የአካል ብቃት የለህም፣አለያም በጣም ሸምግለሃል፡፡

- አዎን → በዚህን ጊዜ አንተን ወክሎ ሐጅ ለሚያደርግ ሰው ወጪውን የመሸፈን ግዴታ አለብህ፡፡
- አይቻልም(በፍፁም) ↓

ከመሰረታዊ ፍላጎቶችህና በአንተ ስር ከሚተዳደሩ ሰዎች መሰረታዊ ወጪ የሚተርፍ የሆነና ሐጅ ለማድረግ የሚያስችልህ በቂ ገንዘብ ከሌለህ ሐጅ የማድረግ ግዳጅ የለብህም፡፡ ሐጅ ለማድረግ ገንዘብ ማሰባሰብም አይጠበቅብህም፡፡

## > አንዲት ሴት ሐጅ ለማድረግ መሕረም (የቅርብ ተጠሪዋ) አብሯት መኖሩ መስፈርት ነው፡፡

በሴት ላይ ሐጅ ግዴታ ሊሆን የሚችለው መሕረሟ (የቅርብ ተጠሪዋ) ካለ ብቻ ነው፡፡ መሕረሟ አብሯት ከሌለ በሴት ልጅ ላይ ሐጅ ግዴታ አይሆንም፡፡ ለአንዲት ሴት መሕረም የሚሆኗት ባለቤቷ ወይም እርሷን ፈፅሞ ማግባት የማይፈቀድላቸው፣ እንደ አባት፣እያት፣ልጅ፣የልጅ ልጅ፣ ወንድሞችና የወንድም ልጆች፣ አጎቶች፣ ..... (ገጽ 200 ተመልከቱ) ናቸው፡፡

በራሱዋ የምትተማመን ሁና ያለሙህረም ሐጅ ካደረገች ሐጁዋ ትክክል ነው፤ ምንዳም ያስገኛታል፡፡

## > የሐጅ ትሩፋቶች

ሐጅ የሚያስገኘውን ትሩፋቶችና መልካም ነገሮች በማስመልከት ብዙ ተነግሯል፡፡ ከዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡



> ሐጅና ዑምራ ማድረግ የፈለገ ሰው፣ ሐጅና ዑምራን የሚ መለከቱ ኢስላማዊ ሕግጋትን መማርና ማወቅ አለበት፡፡

1. ጅሐ ከሥራዎች ሁሉ በላጭ ሥራ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሥራዎች በላጩ ሥራ የትኛው ነው? ተብለው በተጠየቁ ጊዜ፡
   «በአላህና በመልክተኛው ማመን ነው» አሉ፡፡
   ከዚያስ? ተባሉ
   «በአላህ መንገድ ላይ መታገል» አሉ፡፡
   በድጋሚ ከዚያስ? ተባሉ
   «ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ» ብለው መለሱ (አል ቡኻሪ 1447 / ሙስሊም 83)

2. ሐጅ ሰፊ ምህረት የሚገኝበት አጋጣሚ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሐጅ ያደረገ፣ በሐጁም ውስጥ ከማላገጥና ከማፈንገጥ የራቀ ሰው፣ ልክ እናቱ እንደወለደችው ዕለት ከወነወጀል የጸዳ ሆኖ ይመለሳል፡፡» (አል ቡኻሪ 1449 / ሙስሊም 1350)

3. ከእሳት ነፃ ለመውጣት ታላቅ አጋጣሚ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከዐረፋ ዕለት የበለጠ አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን ከእሳት ነፃ የሚያወጣበት ዕለት የለም፡፡» (ሙስሊም 1348)

4. የሐጅ ምንዳ ጀነት ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ተቀባይነትን ያገኘ ሐጅ ከጀነት ሌላ ለርሱ ምንዳ የለውም፡፡» (አል ቡኻሪ 1683 / ሙስሊም 1349)

እነኚህና ሌሎች ትሩፋቶች የሚሰጡት ሃሳቡ(ኒያው) ላማረ፣ ከልቡ ለሚሰራ፣ ውስጡ ጽዱዕ ለሆነና የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ላልሳተ ሰው ብቻ ነው፡፡

ሐጅህ

# > የሐጅ ዓላማዎች

ሐጅ በግለሰብም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ የሚረጋገጡ ላቅ ያሉ ዓላማዎችና ግቦች አሉት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በእርድ ቀን ሐጅ አድራጊ ሊሰዋው ስለሚገባው እርድ ካወሳ በኋላ፡- «አላህን ስጋዎቿም ደሞቿም ፈጽሞ አይደርሰውም፡፡ግን ከናንተ የኾነው ፍራቻ ይደርሰዋል፡፡» ይላል፡፡ (አል ሃጅ 37) ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፡- «በካዕባ ዙሪያ መዞር፣በሠፋና በመርዋ መካከል መመላለስ፤ ጠጠር መወርወርም የተደረገው አላህን ለማውሳት ብቻ ነው፡፡» (አቡ ዳውድ 1888)

ከነኚህ ዓላማዎችና ግቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

## 1 ለአላህ መዋረድና እራስን ዝቅ ማድረግን መግለጽ

ሐጅ ላይ ያለ ሰው የድሎትና የመንፈላሰስ ገጽታዎች አይንጸባረቁበትም፡፡ የኢሕራም ትጥቁን በመልበስ የፈጣሪውን ደጅ የሚጠና መሆኑን ይገልጻል፡፡ ጥርት ባለ ልብ ወደ ፈጣሪው መጠቃለልን ከሚከለክሉትና ከሚያጠምዱት ዓለማዊ ስንክሳሮች እራሱን ያጸዳል፡፡ በዚህም የፈጣሪውን ምህረትና እዝነት ያገኛል፡፡ ከዚያም፣ በዐረፋ የፈጣሪውን ጸጋና ውለታ አመስጋኝ፣ ጌታውን አሞጋሽ፣ ለወንጀሉና ለስህተቱ ምህረትን ለማኘ ኾኖ ፈጣሪውን እየተማጸነ ይቆማል፡፡

## 2 የጸጋ ምስጋና

አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን ካጎናጸፋቸው ጸጋዎች መካከል፣ በሐጅ የሁለት ጸጋዎች ምስጋና ይረጋገጣል፡፡ እነሱም የሀብት እና ለጤናማነት ጸጋ ምስጋና ናቸው፡፡ ሁለቱም የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ውስጥ ከሚጣቀምባቸው ጸጋዎች ሁሉ በላጮቹ ናቸው፡፡ በሐጅ ላይ ለነዚህ ሁለት ታላላቅ ጸጋዎች ምስጋና ይቀርባል፡፡ ሰዎች ነፍሳቸውን ታግለው አላህን ለመታዘዝና ወደርሱ ለመቃረብ ገንዘባቸውን ያወጣሉ፡፡ ለተጣቀሙበት ጸጋ ምስጋና ማቅረብ ደግሞ አዕምሮ የሚያጸድቀው፣ እንዲሁም የሃይማኖት ሕግና መመሪያ የሚያዘው ግዳጅ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡



## 3 :የሙስሊሞች መሰባሰብና መገናኘት

ከተለያየ የዓለም ክፍል የመጡ ሙስሊሞች በሐጅ ላይ ይገናኛሉ፣ ይተዋወቃሉ፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ በሰዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች ይወገዳሉ፡፡ የሀብት፣ የፆታና የቀለም፣ እንዲሁም የቋንቋ ልዩነቶች ይወገዳሉ፡፡ የሙስሊሞች ቃል አንድ ይሆናል፡ ፡ በዚህ የሰው ዘር በተሰበሰበበት ታላቅ ስብሰባ ፡ በመልካም ማዘዝ፣ አላህን በመፍራትና በሐቅ ላይ በመመካከር እና በትዕግስት ላይ በሙተዋወስ ላይ ያለው የታዳሚዎች አጀንዳ አንድ ይዋሃዳል፡፡ ትልቁ ዓላማውና ግቡ የሕይወት ግቦችን ከመለኮታዊ ግቦች ጋር ማቆራኘትና ማስተሳሰር ነው፡፡

## 4 የመጨረሻውን ቀን ማስታወስ

ሐጅ፣ አንድን ሙስሊም የመገናኛውን ዕለት ያስታውሰዋል፡፡ ሐጅ የሚያደርግ ሰው፣ ልብሶቹን አውልቆ፣ ለሐጅ በመታጠቅ አቤት(ለበይክ) እያለ በዐረፋ ሜዳ ላይ ቆሞ የሰዎችን ብዛትና የልብሳቸው አንድ መሆንን ሲያይ ከከፈን ጋር እንደሚመሳሰል ያስተውላል፡ ፡ በዚህን ጊዜ አዕምሮው፣ አንድ ሙስሊም ከሞተ በኋላ ስለሚያጋጥመው የቀብር ሕይወት ያስባል፡፡ ይህም ከአላህ ጋር ከመገናኘቱ በፊት ዝግጅት እንዲያደርግና ስንቅ እንዲቋጥር ይጋብዘዋል፡፡

## 5 በንግግርም በስራም አላህን በብቸኝነት በመገዛት የአላህን አሃዳዊነት ይፋ ማድረግ

የሐጃጆች መለያቸው ተልቢያ ነው፡፡ (ለበይከላሁመ ለበይክ፤ ለበይከ ላ ሸሪ..ከ ለከ ለበይክ ኢነል ሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪ..ከለክ) «አላህ ሆይ! ጥሪህን አክብረን መጥተናል፤ አንተ አጋር የለህም፣ አቤት ብለናል፤ ምስጋናም፣ ጸጋም፣ ንግሥናም ያንተ ነው፤ አንተ አጋር የለህም፡፡» ይላሉ፡ ፡ ታላቁ ሠሐቢይ፣ የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ተልቢያ በማስመልከት፣ «አሐዳዊነት ገላጭ ነው፡፡» ያለው ለዚህ ነው፡፡ (ሙስሊም 1218) ግልጽ በሆነ መልኩ በተግባር፣ በንግግርና እንዲሁም በየሐጅ ሥራዎች ሁሉ የአላህ አሐዳዊነት ይረጋገጣል ማለት ነው፡፡

## > ዑምራ

ዑምራ፣ የኢሕራም ልብስ በመልበስ በካዕባ ዙሪያ ሰባት ጊዜ በመዞር፣ በሠፋና መርዋ መሐከል ሰባት ጊዜ በመመላለስ እና ከዚያም ጸጉርን በመላጨት ወይም በማሳጠር የሚጠናቀቅ የአምልኮ ተግባር ነው፡፡

ኢስላማዊ ፍርዱ፡ ማድረግ በሚችል ሰው ላይ በዕድሜ አንድ ጊዜ መስራቱ ግዴታ ነው፡፡ ደጋግሞ መስራቱ ይወደዳል፡፡

ጊዜው፡ ዓመቱን ሙሉ ዑምራ ማድረግ ይቻላል፡ ፡ ነገር ግን በረመዳን ወር ውስጥ የሚደረግ ዑምራ እጥፍ ድርብ የሆነ ምንዳ አለው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በረመዳን ውስጥ የሚደረግ ዑምራ (በምንዳ) ከሐጅ ጋር ይስተካከላል፡፡» (አል ቡኻሪ 1764/ሙስሊም 1256)



> በሚችል ሰው ላይ በዕድሜው አንድ ጊዜ ዑምራ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

# የተባረከው የእርድ በዓል

ዒድ አልአድሓ፣ በወርሃ ዙልሒጃ አስረኛ ቀን ላይ የሚከበር ሁለተኛው የሙስሊሞች በዓል ነው። ይህ ወር በኢስላማዊው ቀመር አስራ ሁለተኛው ወር ነው። በዚህ ዕለት በርካታ ትሩፋቶች ይገኛሉ። ከነኚህም ትሩፋቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1 የዒድ አልአድሓ ቀን ከዓመቱ ቀናት ሁሉ በላጩ ቀን ነው። ከዓመቱ ቀናት በሙሉ በላጮቹ ቀናት የወርሃ ዙልሂጃ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናቶች ናቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-«ከነዚህ አስርት ቀናት ይበልጥ አላህ ዘንድ በውስጣቸው የሚሠሩ መልካም ሥራዎች ተወዳጅ የሚሆኑበት ቀን የለም።» ብለው ሲናገሩ ባልደረቦቻቸው፣

«በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግልም ቢሆን?» በማለት ጠየቁ፤ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አዎን! ነፍሱንና ንብረቱን ይዞ የወጣ፣ ከዚያም አንዱንም ይዞ ያልተመለሰ ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግልም ቢሆን (አይበልጥም) አሉ። (አል ቡኻሪ 926 / አት ቲርሚዚ 757)

2 የታላቁ ሐጅ ዕለት ነው፡ በውስጡ ከሐጅ ሥራዎች እጅግ የላቀው፣ አንገብጋቢውና የተከበረው ሥራ ይገኛል። ያም፣ በካዕባ ዙሪያ መዞር፤ እርድን መፈፀም፤ ጀምረተል ዐቀባ ላይ ጠጠር መወርወርና ሌሎች ተግባራት የከናወኑበታል።

## በእርዱ ቀን(የውመ ነሕር) የሚሠሩ ሥራዎች

ሐጅ ላይ ላልሆነ ሰው፣ በዒድ አልአድሓ ዕለት ከዘካተል ፊጥር ውጭ በጾም ፍች በዓል ላይ የሚተገበሩ ነገሮችን በሙሉ መተግበር ይፈቀድለታል። ዘካተል ፊጥር(የጾም ፍች ምጽዋት)፣ በጾም ፍቺ በዓል ላይ ብቻ የሚተገበር ነው። እነኚህን ተግባራት ከዚህ በፊት ጠቅሰናቸዋል።

የእርድ በዓል (ዒድ አልአድሓ)፣ ወደ አላህ መቃረቢያ እርድ (ቁርባን) የሚቀርብበት ዕለት መሆኑ ለየት ያደርገዋል።

እርድ(ኡዱሒያ)፡

እርድ(ኡዱሒያ)፣ በእርድ ቀን ከዒድ ሠላት መልስ ወደ አላህ ለመቃረብ የሚሰዋ ወይም የሚታረድ ግመል፣ ከብት፣ ወይም ፍየልና በግ ሲሆን የወርሃ ዙል ሒጃ አስራ ሦስተኛ ቀን ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ሊተገበር ይችላል። አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ስለዚህ ለጌታህ ስገድ (በስሙ) ሰዋም።» (አል ከውሰር 2) አንቀጹ በዒድ ሠላትና በዒድ ዕለት በሚፈፀሙ እርዶች ተተርጉሟል።

ኢስላማዊ ፍርዱ፡ እርድ፣ በሚችል ሰው ላይ ጠበቅ ያለ ሱና ነው። አንድ ሙስሊም ለራሱና ለቤተሰቦቹ ማረድ አለበት።

ለማረድ ያቀደ ሰው ከወርሃ ዙልሒጃ የመጀመሪያ ዕለት ጀምሮ እርዱን እስኪፈጽም ድረስ፣ ፀጉሩን መላጨት፣ ጥፍሩንም መቁረጥ የለበትም።



> በህንድ አገር የሚገኙ ሙስሊሞች የተባረከውን የእርድ በዓል ሠላት ሲሰግዱ

## ለእርድ የሚቀርበው እንሰሳ ማሟላት ያለበት መስፈርት

1 ከቤት እንሰሳት መሆን አለበት፡፡ እነሱም፡- ፍየል፣ በግ፣ ከብትና ግመል ናቸው፡፡ ከነዚህ ሌላ ያሉ እንሰሳት ወይም በራሪ አዕዋፋት ለእርድ አይቀርቡም፡፡

አንድ ፍየል ወይም በግ ለአንድ አባወራ ከነቤተሰቡ ይበቃዋል፡፡ በአንድ በሬ (ላም) ወይም ግመል ላይ ሰባት አባወራ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

2 የሚፈለግበት የዕድሜ ገደብ ላይ የደረሰ መሆን አለበት፡፡ የሚፈለገው የዕድሜ ገደብ፡- ለበግ ስድስት ወር፤ ለፍየል አንድ ዓመት፤ ለበሬ(ላም) ሁለት ዓመት፤ እና ለግመል አምስት ዓመት ነው፡፡

3 እንሰሳው ግልጽ ከወጣ ነውርና ጉድለት የጸዳ መሆን አለበት፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አራት ዓየነት እንሰሳት ለእርድ ብቁ አይደሉም፡- ጠንጋራነቷ ግልጽ የሆነ እንሰሳ፤ ህመሟ ይፋ የሆነ እንሰሳ፤ አንካሳነቷ ግልጽ የሆነ እንሰሳ እና መረቅ የማይወጣት በጣም የከሳች እንሰሳ » (አል ነሳኢ 4371 አት ቲርሚዚ 1497)

## የበዓል እርዱ ምን ይደርጋል?

- ከእርድ ስጋ ላይ መሸጥ አይፈቀድም፡፡
- እርድ የሚፈጽም ሰው፣ ስጋውን ሦስት ቦታ ከፍሎ፣ አንድ ሦስተኛውን ራሱንና ቤተሰቡን ይመግብበታል፤ ሌላኛውን አንድ ሦስተኛ (ለጓደኛና ቤተ ዘመድ) ስጦታ ያደርገዋል፤ የተቀረውን አንድ ሦስተኛ ደግሞ ለድሆች ይመጸውታል፡፡
- አንድ ሰው፣ ለእርድ ሌላ ግለሰብን ቢወክል፣አለያም እርድ በመፈፀምና ስጋውን ለችገረኞች በማከፋፈል ሥራ ላይ ለተሰማሩ ታማኝ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእርድ ገንዘቡን ሊሰጥ ይችላል፡፡

> ኢስላም፣ የሚታረደው እንሰሳ ከነውርና ጉድለት የጸዳ መሆኑን ለእርድ ትክክለኛነት መስፈርት አድርጎታል፡፡



ሐጅህ

# የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ከተማ (መዲናን) መጎብኘት

መዲና፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመካ ጣዖታዊያን ሲያንገላቷቸው ከመካ ወጥተው የተሰደዱበት ከተማ ነች፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና እንደደረሱ መጀመሪያ ያከናወኑት ሥራ የተከበረውን መስጂዳቸውን መገንባት ነበር፡፡ ይህ መስጂድ የዕውቀትና የኢስላማዊ ጥሪ ማዕከልና በሰዎች መሐከል መልካም ነገርን ማሰራጪያ ጣቢያ ሆኗል፡፡

በሐጅ ስነሥርዓትም ሆነ በሌላ አጋጣሚ የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ መጎብኘት እጅግ የተወደደ ነው፡፡

ይህ ጉብኘት ከሐጅ ሥርዓት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ ለሱ ብቻ የተለየ ወቅትም የለውም፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ወደ ሦስቱ መስጂዶች ካልሆነ በስተቀር ጓዝ ተጭኖ ጉዞ አይደረግም፤ መስጂደል ሐራም፤ይህ መስጂዴና መስጂደል አቅሷ፡፡» (አል ቡኻሪ 1139 /ሙስሊም 1397 /አቡዳውድ 2033)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከመስጂደል ሐራም በስተቀር በዚህ መስጂዴ ውስጥ የሚሰገድ ሠላት ከሱ ባሻገር ባሉ መስጂዶች ውስጥ ከሚሰገዱ ሠላቶች በአንድ ሺህ ይበልጣል፡፡» (አል ቡኻሪ 1133/ ሙስሊም 1394)



## በመዲና ውስጥ ሊጎበኙ የሚገቡ ነገሮች ማናቸው?

አንድ ሙስሊም መዲናን ሲጎበኝ፣ዓላማው አድርጎ መነሳት ያለበት፣ የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ መጎብኘትና በውስጡም ሠላት መስገድን ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መዲና መምጣቱ ካልቀረ የሚከተሉትን ጉዳዮች መፈፀም ይፈቀድለታል፡፡

1 በተከበረው ረውዳ ውስጥ ሠላት መስገድ፡ ይህ ስፍራ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ውስጥ የሚገኝ ውስን ቦታ ሲሆን፣ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤትና በሚንበራቸው መሐከል የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ በሱ ውስጥ መስገድ ታላቅ ትሩፋት አለው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በቤቴና በሚንበሬ መሐከል ያለው ስፍራ ከጀነት ጨፌዎች አንዱ ጨፌ ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 1137 /ሙስሊም 1390)

2 ለነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ ማቅረብ፡ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካነ መቃብር በመሄድ፣ ከቀብሩ ፊት ፊት በመቆም፣ ፊትን ወደ ቀብሩ በማዞር፣ ለቂብላ ጀርባን በመስጠት፣ በስርዓትና ድምጽን ዝቅ በማድገረግ፣ «አሰላሙ ዐለይከ ያ ረሱ..ለላህ ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ አሽሃዱ አነከ በለግተ ርሪሳላ ወአደይተል አማና ወነሥሕተል ኡማ ወጃሃድተ ፊላሂ ሐቀ ጂሃዲሂ ፈጀዛከላሁ ዐን ኡመቲከ አፍደለ ማጀዛ ነቢየን አን ኡመቲሂ» - (አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሰላምና የአላህ እዝነት እንዲሁም በረከቱ በርስዎ ላይ፡፡ እርሶ መልክትዎን እንዳስተላለፉ፣ አደራዎን እንደተወጡ፣ ለሕዝብዎ መልካሙን ሁሉ እንደመከሩ፣ በአላህ መንገድ ላይ እውነተኛውን ትግል እንደታገሉ እመሰክራለሁ፡፡ አላህ አንድ ነብይ ለሕዝቦቹ በዋለው ውለታ ከሚከፍለው ምንዳ በላጭ የሆነውን ምንዳ ለሕዝብዎ በዋሉት ውለታ ይከፈልዎት፡፡) ይላል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ (ሱ.ወ) እስትንፋሴን መልሶልኝ እኔ ለሰላምታው አጸፋውን ብመለስለት እንጂ አንድም ሰው በኔ ላይ ሰላምታን አያቀርብም፡፡» ( አቡ ዳውድ 2041)

ከዚያም በቀኝ አቅጣጫ ትንሽ ፈቀቅ ይልና የረሱል ሰ.ዐ.ወ ተቀዳሚ ምትክ በሆኑት ከሰሃቦች ሁሉ በላጭ በሆኑት አቡበክር ላይ ሰላምታ ያቀርባል፡፡



ከዚያም ጥቂት ወደ ቀኙ ፈቀቅ ይልና በሁለተኛው የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋ(ምትክ)፣ በአቡበክር አሲዲቅ(ረ.ዐ) ላይ፣ በመቀጠልም ከአቡ በክር ቀጥሎ ከሡሓቦች ሁሉ በላጭ በሆኑት በዑመር አልፋሩቅ(ረ.ዐ) ላይ ሰላምታን ያቀርባል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰው ልጅ ሁሉ በላጩ ሰው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት ጥቅምም ሆነ ጉዳትን ማስከሰት አይችሉም፡፡ ስለሆነም እርሳቸውን መለመን ወይም ድረሱልኝ ብሎ መጣራት ፈፅሞ አይፈቀድም፡፡ ሁሉም የአምልኮ ዘርፎች መፈፀም ያለባቸው፣ ለርሱ ምንም አጋር ለሌለው ለአላህ(ሱ.ወ) ብቻ ነው፡፡

3

የቁባእ መስጂድ ጉብኝት፡ በኢስላም ታሪክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂዳቸውን ከመስራታቸው በፊት የተሰራ የመጀመሪያው መስጂድ ነው፡፡ መዲና የመጣ ሰው የቁባን መስጂድ መጎብኘት ይወደድለታል፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ይጎበኙት ነበር፡፡ እንዲህም ብለዋል፦ «ከቤቱ ተጸዳድቶ በመውጣት፣ ከዚያም ወደ ቁባእ መስጂድ በመምጣት ሠላትን የሰገደ ሰው የዑምራን ምንዳ ያገኛል፡፡» (ኢብኑ ማጃህ 1412)



> መዲና አል -መ -ነወራህ የሚገኘውን የቁባእ መስጂድ መጎብኘትና በውስጡም መስገድ ነቢያዊ ፈለግ(ሱንና) ነው።




# የንግድ ግንኙነትህ



# 7

ኢስላም፣ አንድ ግለሰብ ሃብታምም ቢሆን ድሃ፣ ንብረቱን፣ ገንዘቡንና ሞያዊ መብቱን የሚያስከብሩና የሚያስጠብቁ ሕግጋትና ሥርዓቶችን አስቀምጧል፡፡ እንዲሁም ማኅበረሰቡ እርሱ በርሱ በሚተሳሰርበትን፣ ተደጋግፎ የሚያድግበትንና የሚበለጽግበትን የሕይወት ዘርፍን በማመቻቸትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## የምዕራፉ ማውጫ፡

መጠቃቀሚያ ነገሮች መሰረታቸው የተፈቀደ( ሐላል) ነው፡፡

በራሱ እርም የተደረገ ወይም እርም የሆነ

ከተገኘበት ምንጭ አንጻር እርም የተደረገ

አራጣ ወይም ወለድ

- የእዳ አገድ ወለድ
- የብድር ወለድ
- የወለድ ፍርድ
- የወለድ አደገኛነት

ማታለልና አለማሳወቅ

የሰዎችን ገንዘብ ያለ አግባብ መውሰድና መበደል

ቁማር

- ቁማር በማኅበረሰብና በግለሰብ ደረጃ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

ኢስላም ገንዘብ ነክ በሆኑ ግንኙነቶች ላይ ትክረት የሰጠባቸው ስነ ምግባራዊ ስርዓቶች አደራን መጠበቅ

- ታማኝነት፡
- እውነተኝነት
- ሥራን፣ኃላፊነትን በጥራትና በብቃት መወጣት

# ገንዘብ ነክ ትስስር

አላህ (ሱ.ወ) በምድራዊ የሕይወት ቆይታ ሲሳይን ለመፈለግ መልፋትን ደንግጓል፣ አበረታቷል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

- አንድ ግለሰብ፣ ስራ የመስራትና በአቅሙ የመንቀሳቀስ ብቃት ካለው ሰዎችን መለመንን ኢስላም ከልክሎታል፡፡ መስራት እየቻለ፣ የመንቀሳቀስ ብቃት እያለው ሰዎችን የሚለምን ሰው፣ ልመናው አላህ ዘንድም ሆነ ሰዎች ዘንድ ያለውን ክብርና ደረጃ እንደሚያሳጣው አስተምሯል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በፍርዱ ዕለት በፊቱ ላይ ቁራጭ ስጋ የሌለ ሆኖ አላህን እስከሚገናኝ ድረስ አንዳችሁ ሰዎችን ከመለመን አይወገድም፡፡» (አል ቡኻሪ 1405 ሙስሊም 1040)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ችግር ገጥሞት፣ ችግሩን እንዲቀርፉለት ለሰዎች ያቀረበ፣ ችግሩ አትወገድም፤ ችግሩን ለአላህ ያቀረበ ግን አላህ ሊያከብረው ይከጀላል፡፡» (አህመድ 3869 / አቡ ዳውድ 1645)

- ኢስላም በፈቀደው ክልል ውስጥ የሚከናወኑ እስከሆኑ ድረስ፣ ኢንዱስትሪያዊ፣ የልማትና የአገልግሎት መስጠት ስራዎች በሙሉ ነውር የለባቸውም፡፡ ነብያት፣ በሕዝቦቻቸው ውስጥ ይታወቁ የነበሩት፣ የተፈቀዱ ወይም ሐላል ስራዎችን የሚሰሩ በመሆናቸው ነበር፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ፍየል የጠበቀ ቢሆን እንጂ አንድም ነብይ አልተላከም፡፡» (አል ቡኻሪ 2143)

«ነብዩላህ ዘከሪያ አናጺ ነበሩ፡፡» (ሙስሊም 2379) የተቀሩት ነብያትም እንዲሁ በመሰል ሙያዎች ላይ ተሰማርተው ይሰሩ ነበር፡፡

- በስራው ላይ ኒያውን አሳምሮ፣ ራሱን እንዲሁም ቤተሰቡን የሰው እጅ እንዳይከጅሉ ለማድረግ እና ችግረኞችን ለመርዳት ያቀደ ሰው፣ በሚሰራው ስራና በልፋቱ ምንዳን ያገኛል፡፡



> የተፈቀዱ ወይም ሐላል ስራዎች በሙሉ ነውር የሌለባቸው እና የተከበሩ ናቸው፡፡

## በማበራዊ ግንኙነትና በመጠቃቀሚያ ነገሮች ዙሪያ ያለው መሰረታዊ መመሪያ

ሰዎችን አንዱን ከሌላው በሚያገናኙና ከባለጉዳይ ጋር በሚከናወኑ ማናቸውም ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ፡ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማካራየትና፣ ሌሎችንም ስራዎች አስመልክቶ ኢስላም ያስቀመጠው መሰረታዊ መመሪያ የሚከተለው ነው፡፡

አንድ ነገር በራሱ እርም(ሐራም) መሆኑ፣ አለያም ከመጣበት ምንጭ አንጻር እርም(ሐራም) መሆኑ ተነጥሎ ከተነገረው ውጭ፣ ነገሮች ሁሉ የተፈቀዱ ናቸው፡፡ እና እነርሱን ማከናወንም ይቻላል፡፡

### በቀጥታ በራሱ እርም የተደረገ፡

ይህ፣ አላህ (ሱ.ወ) አካሉን እርም ያደረገው ነገር ሲሆን፣ እርሱን መነገድ፣ መግዛትም ሆነ መሸጥ፣ ማከራየት፣ በማምረትና ለሰዎች ማከፋፈልና ማሰራጨት አይፈቀድም፡፡

የሚከተሉት ኢስላም በቀጥታ አካላቸውን እርም ያደረጋቸው ነገሮች ናቸው፡፡

- ውሻና አሳማ
- የሞቱ እንስሳት ወይም የአካላቸው ክፋይ
- አስካሪና አልኮል መጠጦች
- አደንዛዥ እጽና ማንኛውም በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትል ነገር
- በሰዎች መካከል ዝሙትና መሰል እኩይ ተግባራትን የሚያስፋፉ መሳሪያዎች፣ ካሴቶች፣ የኢንተርኔት ድህረ ገጾች፣ የዝሙት ማስፋፊያ መፅሔቶች
- ጣኦታትና ማንኛውም ከአላህ ሌላ የሚገዙት ነገር

## ከተገኙበት ምንጭ አንጻር እርም የተደረጉ ነገሮች

እነኚህ፣ መሰረታቸው የተፈቀደ ገንዘብና ንብረቶች ሆኖ እርምነታቸው ከተገኙበት ምንጭ አንጻር የሆነ ነገሮች ናቸው:: ምንጫቸው ማህበረሰቡንና ግለሰቦችን የሚጎዱ በመሆነቸው ምክንያት እርም የተደረጉ ናቸው:: በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ነገሮችን እርም የሚያደርጉ ምክንያቶች:

ወለድ፤ ማጭበርበር፤ አለመታወቅ፤ በደል፤ ቁማር

እነኚህን ጉዳዮች በሚከተለው መልኩ እናብራራቸዋለን

## > ወለድ

በወለድ ውስጥ በደልና በሌላው ላይ ጉዳት ማድረስ የሚገኝበት በመሆኑ በኢስላማዊው ሕግ እርም የተደረገ ጭማሪ ገንዘብ ነው::

የወለድ ዓይነቶች ብዙ ናቸው:: ታዋቂዎቹና እርምነታቸው በጣም የጠበቀው፡ የብድርና የእዳ ወለድ ነው:: ይህ በአንድ ገንዘብ ላይ ያለ ሽያጭ ወይም በሁለቱ ጠረፎች መካከል የእቃ ልውውጥ ሳይኖር የሚገኝ ጭማሪ ሲሆን ሁለት መልክ አለው::

- የእዳ ወለድ

የብድሩ መክፈያ ወቅት ደርሶ ተበዳሪው በቃሉ መሰረት መክፈል ሳይችል ሲቀር በብድሩ መጠን ላይ የሚደረግ ጭማሪ ነው::

ለምሳሌ፡ አቶ ሰዒድ ከአቶ ኻሊድ ከአንድ ወር በኋላ ለመክፈል 1000 ዶላር ተበደሩ እንበል:: ወሩ ሲያልቅና የመክፈያው ወቅት ሲደርስ፣ አቶ ሰዒድ መክፈል ባይችሉና በቃላቸው መገኘት ቢያቅታቸው፣ አቶ ኻሊድ በተስማሙበት ወቅት ላይ ማለትም ወሩ እንዳለቀ የሚከፍሉት ከሆነ ያለምንም ጭማሪ ገንዘቡን ሊከፍሉት፣ ከተጨማሪ አንድ ወር በኋላ የሚከፍሉት ከሆነ ደግሞ 1100 ዶላር እንዲከፍሉት፣ ደግሞም መክፈል ካልቻሉ ከሁለት ወር በኋላ ደግሞ 1200 ዶላር አድርገው ይከፍሉት ዘንድ እንደ ቅድመ ሁኔታ ቢያስቀምጡ፣ እነኚህ ጭማሪዎች የእዳ ወለድ ይባላሉ::




> ማንኛውም ብድር ወይም ዕዳ ለአባዳሪው ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ወለድ ነው::

- የብድር ወለድ

ይህ ደግሞ ከአንድ ግለሰብ ወይም ባንክ የሆነ ያክል ገንዘብ ሲበደር በስምምነታቸው መሰረት ብድሩን እስኪከፍል ድረስ በየዓመቱ ወይም ከዚያ በታች ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ወቅት በስምምነቱ መሰረት (ለምሳሌ 5 ፐርሰንት) እየተጨመረ ታስቦበት የሚከፍለው ጭማሬ ገንዘብ ነው::

ለምሳሌ፡ አንድ ሰው የሆነን የመኖሪያ ቤት በመቶ ሺህ መግዛት ይፈልግና በቂ ገንዘብ አይኖረውም:: ከዚያም ወደ ባንክ ያመራና ለቤቱ መግዢያ ከባንኩ አንድ መቶ ሺህ ይበደራል:: ይኸውም ለአምስት ዓመታት በየወሩ እየተቆራረጠ የሚከፈል ሲሆን መጠኑም አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር በሚል ስምምነት ነው::

ይህ ዓይነቱ ወለድ የብድር ወለድ ይባላል::

ወለድ ከከባድ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው:: አባዳሪ በማበደሩ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ከሆነም በዚሁ ስር የሚካተት ነው:: ብድሩ የንግዱን ዘርፍ ለማጠናከር፣ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት፣ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት፣ ቤት ለመግዛት፣ ወይም የዕለት ተዕለት ፍጆታዎችን ለመግዢያ የሚውል ቢሆንም ወለድ ካለው የተከለከለ ነው::

ዕቃዎችን ዋጋቸውን ከተመናቸው በላይ በየጊዜው በካሽ በመክፈል መግዛት ግን ወለድ አይደለም::

ለምሳሌ፣ አንድ መገልገያ መሣሪያን ወዲያው በሚከፈል አንድ ሺህ ዶላር መግዛት ወይም ይህንኑ መሣሪያ ለዕቃው ባለቤት፣ ለሻጩ በየወሩ መቶ ዶላር በመክፈል በአንድ ሺህ ሁለት መቶ ዶላር መግዛት ዓይነት ነው::

## የወለድ ፍርድ

ወለድ በጥብቅ የተከለከለ እርም(ሐራም) ነው፡፡ እርምነቱም በግልጽ የቁርኣን አንቀጾችና ሐዲሶች ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ወለድ ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከወንጀለኞች መካከል ጦርነትን እንዳወጀበት የዛተው ወለድን በሚበላና በርሱ በሚገለግል ሰው ላይ ብቻ ነው፡፡ የወለድ እርምነት በኢስላም ብቻ ሳይሆን በቀደምት መለኮታዊ መመሪያዎችም ጭምር የተደነገገ ነው፡፡ ነገር ግን ከቁርኣን ውጭ ባሉ መመሪያዎች ውስጥ ያሉት ሕግጋት ድለዛና ክለሳ እንደተደረገባቸው ሁሉ የወለድ ሕግም ተመሳሳይ ነገር ኢጋጥሞታል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) የመጽሐፍቱ ባለቤት የሆኑትን ሕዝቦች የቀጣበትንና በነርሱ ላይ የተቆጠበትን ምክንያት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡- «ከርሱ በርግጥ የተከለከሉ ሲሆኑ አራጣንም በመያዛቸውና የሰዎችን ገንዘቦች ያለ አግባብ በመብላታቸው ምክንያት (ረገምናቸው)፡፡» (አል ኒሳእ 161)

## የወለድ ቅጣት

1 በወለድ የሚገለገል ሰው ከአላህና ከመልክተኛው ጋር ጦርነት በማወጅ እራሱን ኢጋፍጧል፡፡ በዚህም የአላህ እና የመልክተኛው ተዋጊ ጠላት ይሆናል፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) አራጣን የሚበሉ ሰዎችን እንዲህ ይላል፡- «(የታዘዛችሁትን) ባትሰሩም ከአላህና ከመልክተኛው በኾነች ጦር (መወጋታችሁን) ዕወቁ፡፡ ብትጸጸቱም ለናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ አትበደሉም አትበድሉምም፡፡» (አል በቀራ 279)

ይህ ጦርነት መንፈሳዊና አካላዊ ጫናዎች አሉት፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሰዎችን ያጋጠማቸው አለመረጋጋት፣ ጭንቀት፣ የሃሳብና የትካዜ ፈተና፣ በዚህ ጦርነት ምክንያት የመጣ እንጂ በሌላ አይደለም፡፡ የአላህን ትዕዛዝ በጣሰ ወይም ወለድ በበላ ወይም በወለድ ላይ በተባበረ ሰው ምክንያት የመጣ ጣጣ ነው፡፡ ይህ የዱንያ ወጤቱ ሲሆን ታዲያ የአኺራው የጦርነት ውጤትስ ምን ይሆን?

2 በወለድ የሚገለገልና ወለድን የሚበላ፣ እንዲሁም በዚህ ላይ እገዛ የሚያደርግ ሰው ከአላህ እዝነት የተባረረና የተረገመ ነው፡፡ ጃቢር(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- «የአላህ መልክተኛ ወለድ የሚበላን፣ ወኪሉን፣ ጸሐፊውን፣ ምስክሩንም ጭምር ረግመዋል፡፡» «ሁላቸውም እነሱ (በወንጀሉ) እኩል ናቸው፡፡» ሲሉም ተናግረዋል፡፡ (ሙስሊም 1598)

3 ወለድ የሚበላ ሰው የትንሳኤ ቀን የሚቀሰቀሰው እጅግ ዘግናኝና አስከፊ በሆነ ሁኔታ ነው፡፡ የአውድቅ በሽታ እንዳለበት፣ በጅን እንደተለከፈ ሰው እየተወላከፈና እየወደቀ ይነሳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ቢጤ እንጂ (ከመቃብራቸው) አይነሱም፡፡» (አል በቀራ 275)

4 የወለድ ገንዘብ ምን ቢበዛ ከበረከት የተሟጠጠ ነው፡፡ በወለድ እረፍትን፣ ስኬትንም፣ እርካታና እርጋታንም ማግኘት አይቻልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «አላህ አራጣን (በረከቱን) ያጠፋል ምጽዋቶችንም ያፋፋል፡፡» (አል በቀራ 276)

## ወለድ በማህበረሰብና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት

ኢስላም በማህበረሰብና በግለሰብ ደረጃ በሚያስከትለው ጉዳትና ክስረት የተነሳ በወለድ ዙሪያ ጠበቅ ያለ አቋም ይዟል፡፡

1 በሀብት መከፋፈል ተግባር ላይ በሀብታሞችና በድሆች መካከል ልዩነትን ይፈጥራል

ወለድ፣ ገንዘብ ከማህበረሰቡ ውስጥ በተወሰኑ ሰዎች እጅ ብቻ እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን በርካቶችን የገንዘብ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ በገንዘብ ክፍፍል ላይ ትልቅ ክፍተት የሚፈጥር ነገር ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ማህበረሰብ ድንበር ባለፈ መልኩ ሃብትን ያከበቱ የጥቂት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መፈንጪያ ይሆናል፡፡ የተቀሩት ስራ አጦች፣ ድሆችና ችግረኞች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ቂምን፣ ምቀኝነትንና ወንጀልን ከሚያስፋፉ ምክንያቶች ዋነኛው ነው፡፡

**2** ገንዘብን አለመቆጠብና የአባካኝነት ልማድ

ለአበዳሪ በሚገኝ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የብድር ስርዓት እንዲስፋፋ ነገሮችን ማግራራት፣ ብዙዎች ገንዘብን እንዳይቆጥቡና የአባካኝነት ልማድን እንዲያዳብሩ ያበረታታል፡፡ ምክንያቱም ተበዳሪ ባስፈለገው ጊዜ ገንዘብን በቀላሉ ያገኛል፡፡ በመሆኑም ስላለበትና ስለወደፊቱ አያስብም፡፡ የተበደረውን ገንዘብ በመዝናናትና በትርፍ ነገሮች ላይ ወሰን ባለፈ ሁኔታ ያባክናል፡፡ ብሎም፣ ከፍተኛ የሆነ የብድር ዕዳ ይከማችበትና ሕይወቱ ይጨናነቃል፡፡ ዕድሜ ልኩን በወሰደው ብድርና በተሸከመው እዳ እንደተሸማቀቀ ይኖራል፡፡

**3** ወለድ፣ ባለ ሃብቶች ሀገርን በሚጠቅም ነገር ላይ እንዳይሳተፉ የሚከለክል እንቅፋት ነው፡፡

በወለድ ስርዓት ውስጥ አንድ ባለ ሃብት በገንዘቡ ላይ ተጨማሪ የወለድ ገንዘብ የሚያገኝበት አጋጣሚ ይመቻችለታል፡፡ ይህ ደግሞ ለማህበረሰቡ ምን ያክል ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም፣ ገንዘቡን በኢንዱስትሪ፣ በግብርናና በንግዱ ዘርፎች እንዳያውል ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም፣ እነኚህ ስራዎች ልፋትና ድካምን የሚፈልጉና እንዲሁም የተወሰነ ያክል አደጋ ወይም ክስረት ይኖራቸዋል፡፡

ስለዚህ በመስራት ፋንታ ገንዘቡን አበድሮ አራጣን መሰብሰብን ይመርጣል፡፡

**4** ወለድ የገንዘብ በረከት እንዲወገድ፣ የኢኮኖሚ ውድቀት እንዲከሰት ያደርጋል፡፡

ማንኛውም በድርጅቶች ወይም በግለሰቦች ላይ የሚከሰት የኢኮኖሚ ውድቀትም ሆነ ከፍተኛ ኪሳራ መንስኤው በተከለከለው ወለድ ላይ መዘውተር ነው፡፡ ይህ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) የተናገረው የበረከት መወገድ አንዱ ውጤት ነው፡፡ ምጽዋትና ለሰዎች መልካም መዋል ግን ገንዘብ እንዲባረክና እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «አላህ አራጣን (በረከቱን) ያጠፋል ምጽዋቶችንም ያፋፋል፡፡» (አል በቀራ 276)

አንድ ሰው ቀደም ሲል በወለድ የሚገለገል የነበረ ቢሆንና ኢስላምን ቢቀበል፣ የሚሰጠው ብይን ወይም ፍርድ ምንድን ነው?

አንድ በወለድ ውል በመገልገል ላይ የነበረ ሰው ኢስላምን ከተቀበለ፣ ፍርዱ ሁለት መልክ የኖረዋል፡፡

1- እርሱ ጭማሪውንና የሚገኘውን ጥቅም የሚወስድ አበዳሪ የነበረ ከሆነ፣ ኢስላምን ሲቀበል፣ ዋናውን ብቻ ነጥሎ በመውሰድ ጭማሪውን ይተዋል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡- «ብትጸጸቱም ለናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ፡፡ አትበድሉም አትበደሉምም፡፡» (አል በቀራ 279)

2- ጭማሪውን የሚከፍል (ተበዳሪ) ከነበረ ደግሞ፡-

- ከባድ የሆነ ጉዳት የማያደርስበት ከሆነ ውሉን በማፍረስ ከዚህ ፅልመት መውጣት አለበት፡፡
- ውሉን ማፍረሱ ትልቅ ኪሳራን የሚያደርስበት ከሆነ ግን፣ ደግሞ ላይመለስበት ቁርጥ ውሳኔ በማድረግ ውሉን እስከተዋዋለበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ከጌታውም ግሳጼ የመጣለትና የተከለከለ ሰው ለርሱ (ከመከልከሉ በፊት) ያለፈው አለው፡፡ ነገሩም ወደ አላህ ነው (አራጣ ወደ መብላት) የተመለሰው ሰው እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡» (አል በቀራ 275)



> ወለድ፣ የገንዘብ በረከት እንዲታጣና የኢኮኖሚ ውድቀት እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል፡፡

## > ሰውን ማታለልና አለማወቅ

ይህ ሐረግ ማንኛውንም በውስጡ የተወሰነ የማይታወቅ ክፍተት ያለው ነገርን ያዘለ፣ በሁለቱ ውል ፈፃሚዎች (ሻጭና ገዥ) መሐከል ጭቅጭቅና ሙግት እንዲከሰት፣ አለያም አንዱ ሌላኛውን እንዲበድል ምክንያት የሚሆን ተግባርን የሚገልጽ ነገር ነው፡፡

ኢስላም፣ ሙግትን ወይም በደልና ጉዳትን አስቀድሞ ለመከላከል ሲል ማታለልንና ግልጽ አልባነትን እርም አድርጓል፡፡ ይህ ነገር ሰዎች ቢስማሙበትና ቢወዱትም ክልክል ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማታለል ያለበትን ሽያጭ ከልክለዋል፡፡ (ሙስሊም 1513)

### ማታለልና ግልጽ አልባነት ያለበት ሽያጭ ምሳሌ

1. አንድን ፍሬ ጥሩና መጥፎነቱ ሳይለይ፣ በዛፍ ላይ እያለ ለመቆረጥ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ላይ ሳለ መሸጥ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመብሰሉ በፊት የመበላሸት አደጋ ሊደርስበት ስለሚችል ይህ ዓይነቱን ሽያጭ ከልክለዋል፡፡
2. በውስጡ ያለው ነገር ውድ ይሁን ርካሽ፣ የሚጠቅም ይሁን አይሁን ከመረጋገጡ በፊት አንድ ሳጥንን ወይም እሽግ ዕቃን ለመግዛት የሆነ ያክል ገንዘብ አስቀድሞ መክፈል ክልክል ነው፡፡

### የአንድ እቃ ምንነት አለመታወቅ በግብይቱ ውስጥ ታሳቢነት የሚያገኘው መቼ ነው?

ከውሉ ጋር ብዙ ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮችና በውሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በስተቀር ሸንገላና ምንነቱን አለማሳወቅ የአንድን ውል ፍፃሜ የተከለከለ ለማድረግ አይችሉም፡፡

ለምሳሌ፣ ለአንድ ሙስሊም አንድን ቤት ለመገንባትና ለማሳመር የተጠቀመውን የዕቃ ዓይነት ሳይገልጽ ቤቱን መሸጥ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ምንንቱን አለማሳወቅ ዋናው ነገር ባለመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የተከሰተው በውሉ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ሳይሆን ከውሉ ጋር ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ዙሪያ በመሆኑ ነው፡፡



አንተ ጭማሪ የምትቀበል አበዳሪ ነህን (ወለድ በዪ) ?

- አይቻልም(በፍፁም)
- አዎን → **እንግዲውስ** ያለምንም ጭማሪ ገንዘብህን ዋናውን ብቻ መውሰድ ይኖርብሃል፡፡

ተበዳሪ ነህ፤ ግን ያለ አንዳች ከባድ ኪሳራ ውሉን ማፍረስ ትችላለህን?

- አይቻልም(በፍፁም)
- አዎን → **ምንም ኪሳራ** የማያስከትልብህ ከሆነና የምትችል ከሆነ ውሉን ማፍረስ አለብህ፡፡

ውሉን ማፍረስ የማትችል ከሆነ፣ ወይም በማፍረስህ ምክንያት ትልቅ ጉዳት የሚደርስብህ ከሆነ፣ ደግመህ ላትመለስበት ቁርጠኛ ውሳኔ አድርገህ ውሉን ትጨርሳለህ፡፡

## > በደልና የሰዎችን ገንዘብ አላግባብ መውሰድ

በደል ኢስላም ካስጠነቀቃቸው እኩይ ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ - «በደል የትንሳኤ ቀን ጽልመት ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 23215 / ሙሲሊም 2579)

ትንሽ ቢሆንም፣ የሰዎችን ገንዘብ ያለ አግባብ መውሰድ ክልክል ነው፡፡ ይህ አላህ(ሱ.ወ) ፈፃሚዎቹን በመጨረሻው ዓለም ላይ ጠንካራ ቅጣት እንደሚገጥማቸው ከወዲሁ በመንገር ከዛተባቸው ከከባባድ ሃጢአቶችና ወንጀሎች መካከል ነው፡፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ስንዝር ያክል መሬት የበደለ ሰው በትንሳኤ ቀን ከሰባቱ ምድር (በአንገቱ) ይጠለቅለታል፡፡» (አልቡኻሪ 2321 /ሙስሊም 1610)

### በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ከሚከሰቱ የበደል ምሳሌዎች፡

1 ማስገደድ፡ በየትኛውም የማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ፣ ማስገደድና በኃይል ማንበርከክ አይፈቀድም፡፡ በነፃ ምርጫና በስምምነት ካልሆነ በስተቀር በማስገደድ የሚፈፀም ማንኛውም ውል ተቀባይነት የለውም፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሽያጭ (የሚፀድቀው) በስምምነት ነው፡፡» (ኢብኑ ማጃህ 2185)

2 የሰዎችን ገንዘብ በሐሰት ለመብላት ማታለልና ማጭበርበር፡ ይህም ከከባባድ ወንጀሎች መካከል ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኛን ያታለል ከኛ አይደለም፡፡» (ሙስሊም 101)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ሐዲስ የተናገሩበት ምክንያቱ፡ በአንድ ወቅት ወደገበያ ወጣ ባሉበት፣ እህል የያዘ ከረጢት ተመለከቱ፤ ከዚያም እጃቸውን ወደታች ዘለቅ አድርገው በከረጢቱ ውስጥ ሲሰዱት ከታች እርጥበትን አገኙ፤ ወዲያውም ለሻጩ «አንተ ባለ እህል ይህ ምንድነው?» አሉት፤ እሱም፡ «ዝናብ አግኝቶት ነው የአላህ መልክተኛ» አላቸው፤ እሳቸውም፡ - «ሰዎች እንዲያዩት ከላይ አታደርገውም ነበር? እኛን ያታለለ ከእኛ አይደለም፡፡» አሉት፡፡ (አል ቲርሚዚ 1315)

3 የሰዎችን ገንዘብ ያለ አግባብና በግፍ ለመውሰድ በሕግና ደንብ መቀለድ፡ አንድ ሰው የርሱ ያልሆነ ገንዘብን በሕጋዊ መንገድና በፍርድቤት አስወስኖ የመውሰድ ጮሌነትና ፍጥነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን የአንድ ዳኛ ፍርድ ስህተትን እውነት ሊያደርገው አይችልም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ የሰው ልጅ ነኝ፤ እናንተ ደግሞ እኔ ዘንድ በመምጣት ትካሰሳላችሁ፤ ምናልባት አንዳችሁ ማስረጃ ከማቅረብ አኳያ ከሌላኛው የበለጠ ይሆንና በሰማሁት መሰረት ለርሱ ልፈርድለት እችላለሁ፡፡ እናም ከወንድሙ መብት ለርሱ የፈረድኩለት ሰው እንዳይወስድ፤ እኔ ለርሱ የቆረጥኩለት ከእሳት የሆነ ቁራጭን ነውና፡፡» (አል ቡኻሪ 6748 / ሙስሊም 1713)



> መጠኑ ቢያንስም የሰዎችን ገንዘብ በግፍ መውሰድ ከከባባድ ሃጢአቶችና ወንጀሎች መካከል ነው፡፡

4 ጉቦ፡

ጉቦ ማለት፣አንድ ሰው የርሱ ያልሆነን ንብረት ለማግኘት ሲል ገንዘብ ወይም የሆነ አገልግሎት መስጠቱ ሲሆን፣ ይህ ተግባር ከበደል ዓይነቶች ሁሉ አደገኛው በደልና ከባዱ ወንጀል ነው:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጉቦ ሰጪውንም ተቀባዩንም ረግመዋል:: (አል ቲርሚዚ 1337)



> ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጉቦን የሚሰጠውንም የሚቀበለውንም ረግመዋል::

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ጉቦ ከተስፋፋ፣ ስርዓት የለሽነት ይሰፍናል፤ ስርዓት ይንኮታኮታል:: እድገቱና ስልጣኔውም ይቆማል::

### በካሃዲነቱ ዘመን ያለ አግባብ ገንዘብ ይወስድ የነበር ሰው ኢስላምን ሲቀበል ፍርዱ ምንድነው?

አንድ ሰው አግባብ ባለሆኑ መንገዶች በግፍ ድንበር በማለፍ በስርቆት ወይም በመሸወድና ወዘተ ከሰዎች የወሰደው ገንዘብ እሱ ዘንድ እያለ ከሰለመ የሚያውቃቸው ከሆነና ምንም ዓይነት አደጋ ሳይከሰት ለነርሱ ማስረከብ የሚችል ከሆነ ለባለቤቶቹ የመመለስ ግዴታ አለበት::

ይህን ገንዘብ፣ ምንም እንኳን ኢስላምን ከመቀበሉ በፊት ያገኘው ቢሆንም ይህ በግፍ ድንበር በመተላለፍ የተወሰደ ገንዘብ በእጁ ያለ ገንዘብ ነው:: እናም ከቻለ ይህን ገንዘብ መመለስ ይገባዋል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዘችኋል::» (አል ኒሳእ 58)

ባለቤቱን ለማወቅና ለማግኘት የሚችለውን ያክል ከጣረ በኋላ ማወቅ ካልቻለ ገንዘቡን በመልካም ስራዎች ላይ በማዋል መጽዳት አለበት::

## > ቁማር

### ቁማር ማለት ምንድን ነው?

ቁማር ሁለት ተጫዎቾች ወይም ተወዳዳሪዎች ወይም ተወራራጆች አንዳቸው ካተረፈ (ካሸነፈ) ከከሰረው (ከተሸነፈው) ላይ ገንዘብ እንዲወስድ ቅድመ መስፈርት በሚቀመጥለት ውድድርና ጫወታ ላይ ይከሰታል::በዚህ ላይ የሚሳተፉት ሁለቱም ወገኖች ገንዘቡን ከሌላው ወገን በሚያገኙበት ወይም ለሌላው በማስረከብ በሚከስርበት መሀል የሚሽከረከሩ ናቸው::

### የቁማር ሸሪዓዊ ፍርድ፡

ቁማር እርም ነው:: በቁርአንና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ውስጥ እርምነቱ በግልፅ ተነግሯል::

1 አላህ (ሱ.ወ) በቁማር ምክንያት የሚከሰት ወንጀልና ጉዳት በርሱ ከሚገኝ ጥቅም እጅግ የገዘፈ መሆኑን አስቀምጧል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:- «ስለ ሐዕምርና ከሚያቃውም (አስካሪ) መጠጥና ከቁማር ይጠይቁሃል፤ በሁለቱም ውስጥ ጥቅሞች አሉባቸው ግን ሃጢአታቸው ከጥቅማቸው በጣም ትልቅ ነው በላቸው::» (አል በቀራ 219)

2 አላህ (ሱ.ወ) በግለሰቦችና በማህበረሰብ ላይ ከሚያስከትሉት መጥፎ ጉዳቶች አንጻር ቁማርን ስውር ወይም ረቂቅ እርኩስ በሚል ፍርድ ሰጥቶበታል:: ከርሱ በመራቅም አዟል:: የልዩነትና የጥላቻ መንስኤ፣ ከሠላትና አላህ ከማውሳት የመዘናጊያ ምክንያት መሆኑንም ተናግሯል:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣኦታትም አዝላምም(የመጠንቆያ እንጨቶች) ከሰይጣን ስራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው::(እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና:: ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ ጠብንና ጥላቻን ሊጥል አላህን ከማውሳትና ከስግደትም ሊያግዳችሁ ብቻ ነው ታዲያ እናንተ (ከነዚህ) ተከልካዮች ናችሁን? (ተከልከሉ)» (አል ማኢዳ 90-91)

## ቁማር በማህበረሰብና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች፡

ቁማር በማህበረሰቡና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች እጅግ በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹም፡

1 በሰዎች መካከል ጠብንና ጥላቻን ይፈጥራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቁማር ተጫዎቹች ጓደኛሞችና ወዳጆች የነበሩ ይሆናሉ፡፡ ከዚያ በኋላ፣አንደኛቸው አሸናፊ ሆኖ ገንዘቡን በሚወስድ ጊዜ፣ ሌሎቹ እንደሚጠሉትና ቂም እንደሚይዙበት፣ በነፍሳቸው ውስጥም ለርሱ ጥላቻንና ምቀኝነትን እንደሚያበቅሉ ጥርጥር የለውም፡፡ እርሱ በነሱ ላይ ኪሳራን እንዳደረሰባቸው ሁሉ እነሱም እርሱን ለመጉዳትና ለመተናኮል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀማቸው አይቀርም፡፡ ይህ፣ ሁሉም የሚያውቀውና የሚያስተውለው ተጨባጭ እውነታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፦ «ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ ጠብንና ጥላቻን ሊጥል ነው፡፡» ይላል፡፡

በተጨማሪም ኃላፊነትን ከመወጣት፣ ሠላትን ከመስገድ፣ እንዲሁም አላህን ከማውሳት የሚያዘናጋ ነገር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሰይጣን ሰዎች ቁማርን እንዲጫወቱ የሚያሰማምርበትና የሚገፋፋበትን ሁኔታ ሲጠቅስ እንዲህ ብሏል፦ «አላህን ከማውሳትና ከስግደትም ሊያግዳችሁ ብቻ ነው»

2 ቁማር ገንዘብ የሚሟጥጥ፣ ሃብትንም የሚያከስም ነው፡፡ በቁማርተኞች ላይ በርካታና ከፍተኛ ክስረቶችን ያደርስባቸዋል፡፡

3 ቁማርን የሚያዘወትር ሰው በሱሱ ይጠመዳል፡፡ ቁማርተኛ ሲያሸንፍ በቁማር ላይ ያለው ጉጉትና ምኞት ይጨምራል፡፡ በመሆኑም ይህን የሐራም ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ይቀጥላል፡፡ ሲሸነፍም፣ ምናልባት ያጣሁትን ገንዘቤን አስመልሳለሁ በሚል ጉጉትና ምኞት መጫወቱን ይቀጥላል፡፡ ሁለቱም የስራና የልማት ጸሮች፣

### የቁማር ዓይነቶች

በቀደምት ዘመናትም ሆነ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የቁማር ዓይነቶች በርካታና የተለያዩ ናቸው፡፡ በዘመናችን ከሚገኙ የቁማር ዓይነቶች መካከል የሚከተሉት አሉበት፡

1. ማንኛውም አሸናፊው በማሸነፉ ከተሸናፊው ገንዘብ ሊወስድ ቅድመ መስፈርት የሚቀመጥበት ጫወታ፡፡ ለምሳሌ፡ የሆኑ ሰዎች ተሰባስበው ካርታ ሲጫወቱ በቅድሚያ ሁላቸውም የሆነ ያክል ገንዘብ ያስይዛሉ ወይም ያስቀምጣሉ፡፡ ከነሱ መካከል አሸናፊው የሁሉንም ገንዘብ ይወስዳል፡፡
2. የሆነ ክለብ፣ ወይም ቡድን፣ ወይም ተጫዋች ያሸንፋል አያሸንፍም በሚል መወራረድ፡፡ የሚወራረዱት ሁላቸውም ቅድሚያ ገንዘብ በማስያዝ ሲሆን እያንዳንዳቸው ያሸንፋል ብለው በሚገምቱትና በሚያምኑበት ቡድን ወይም ተጫዋች ስም ገንዘብ ያስይዛሉ፡፡ ከዚያም የተወራረደበት ቡድን ካሸነፈ የተወራራጆቹን ገንዘብ ይወስዳል፡፡ የተወራረደበት ቡድን ከተሸነፈ ገንዘቡን ይከስራል፡፡
3. ዕድልና ዕጣ፡ ለምሳሌ ዕጣው ሲወጣ የአንድ ሺህ ዶላር አሸናፊ ልሆን እችላለሁ በሚል እሳቤ በእጣው ላይ ለመሳተፍ የሆነ ካርድ በሆነ ያክል ዶላር ይገዛል፡፡
4. ተንቀሳቃሽ የሆኑ በኤክትሮኒክስ መሳሪያ የሚሰሩ ወይም በኢንተርኔት ድህረ ገጾች ላይ የሚለቀቁ የቁማር ጨዋታዎች፡፡ በነዚህ ጨዋታዎች ላይ ተጫዋቹ ሁለት ግምቶች ይኖሩታል፡፡ እሱም ገንዘብ ማግኘት ወይም መክሰር ነው፡፡



> በኤለክትሮኒክስ መሳሪያዎች ተንቀሳቃሽም ይሁኑ በማንኛውም መልኩ የሚዘጋጁ የቁማር ጫዋታ ዓይነቶች ሁሉ ክልክል (ሐራም) ናቸው፡፡ ከከባባድ ወንጀሎችም መካከል ናቸው፡፡

## ኢስላም፣ ልዩ ትኩረት የቸራቸው በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ ስነምግባሮች

ኢስላም፣ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ መመሪያና ደንብ እንደዘረጋ ሁሉ፣ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎችም ሊላበሷቸው የሚገቡትን በርካታ ስነምግባሮችና ስርዓቶችን በመዘርዘር ልዩ ትኩረት ችሯቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1



### ታማኝነት፡

ታማኝነት፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን የንግድ ግንኙነት ወሳኝ ስነ ምግባር ነው፡፡ አንድ ሙስሊም፣ ለሙስሊሞችም ሆነ ለካሃዲያን ያለልዩነት ታማኝ መሆን አለበት፡፡ ታማኝነት፣ የአላህን ድንጋጌ ለሚከተል ሙስሊም ዋነኛ መገለጫ ባሕሪው ወይም ስነምግባሩ ነው፡፡ በዚህ ላይ ኢስላም ልዩ ትኩረት እንዳደረገ የሚከተሉትን መረጃዎች መመልከት እንችላለን፡፡

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል፡፡» (አል ኒሳእ 58)
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአንድ ሰውን አደራ አለመጠበቅንና በታመነበት ነገር ላይ ማጭበርበርን ከመናፍቅነት ባህሪ ቆጥረውታል፡፡ «የመናፍቅ መገለጫ ወይም ምልክቶች ሦስት ናቸው፤ ሲናገር ይዋሻል፤ ሲቀጥር ያፈርሳል፤ ሲታመን ይከዳል፡፡» (አል ቡኻሪ 33 /ሙስሊም 59)
- ታማኝነት የሙእሚኖች ዋነኛ መገለጫቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ምእመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ(ዳኑ)»....... «እነዚያ እነርሱ ለአደራዎቻቸውና ለቃል ኪዳናቸው ጠባቂዎች (የኾኑት)» (አልሙዕሚኑን 1-8) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አደራን የሚከዳን ወይም የሚያጭበረብርን ሰው ኢማኑን ውድቅ ያደረጉት ለዚህ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ «አማና የሌለው ሰው ኢማን የለውም፡፡» (አሕመድ 12567)
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነብይነት ከመሾማቸው በፊት በመካ ሳሉ፣ «እውነተኛው፣ ታማኙ» በሚል ቅፅል ስም ይታወቁ ነበር፡፡ ይህም ከሰዎች ጋር በነበራቸው ግንኙነትና ትስስር የታማኝነት ተምሳሌት ስለነበሩ ነው፡፡





እውነተኝነት

እውነተኝነትና ግልጽነት፣ ኢስላም ልዩ ትኩረት ከቸራቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኞቹ ናቸው፡፡

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሻጭና ገዢ በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፡- «እውነተኞች ከሆኑና ግልጽ ካደረጉ ግብይታቸው ይባረክላቸዋል፡፡ ከሸሸጉና ከዋሹ ደግሞ የግብይታቸው በረከት ይነሳል፡፡» (አልቡኻሪ 1973 / ሙስሊም 1532)
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እውነተኝነትን አደራ! እውነተኝነት ወደ መልካም ነገር ይመራል፤ መልካም ነገር ደግሞ ወደ ጀነት ይወስዳል፤ አላህ ዘንድ እውነተኛው ተብሎ እስኪመዘገብ ድረስ አንድ ሰው እውነት ከመናገርና እውነትን ከመጠበቅ አይወገድም፡፡» (ሙስሊም 2607)
- ኢስላም፣ ዕቃውን ለማዳነቅና ለማሻሻጥ ሲል በሐሰት የሚምል ሰው ከባድ ወንጀል ውስጥ እንደተዘፈቀ ያስተምራል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ሦስት ዓይነት ሰዎችን የትንሳኤ ቀን አላህ አያናግራቸውም፡፤ወደነርሱም አይመለከትም፤ አያጠራቸውምም፤ አሳማሚ ቅጣትም አለላቸው፤» ካሏቸው መካከል «በሐሰት መሐላ ዕቃውን የሚያሻሽጥ» ብለው ጠቅሰዋል፡፡ (ሙስሊም 106)

ሥራን፣ኃላፊነትን በጥራትና በብቃት መወጣት

ማንኛውም ፋብሪካ ወይም ሰራተኛ ሙስሊም፣ ስራውን በጥራትና በብቃት፣ እንዲሁም ባማረ መልኩ የመስራት ግዴጅ አለበት፡፡ ይህ የሙስሊም ቋሚና የማይለወጥ መገለጫው ነው፡፡

- አላህ (ሱ.ወ) በማንኛቸውም ጉዳይ ላይ ጥራትና ማሳመርን ደንግጓል፡፡ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ላይም ተግባራዊ እንዲሆን አዟል፡፡ እንደ አደንና እርድ ያለ መጀመሪያ ሲመለከቱት በብቃትና በጥራት ለመስራት አስቸጋሪና የማይቻል በሚመስል ጉዳይ ላይ ሳይቀር ይህንኑ አስቀምጧል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ በሁሉም ነገር ላይ በጥራት መስራትን ወይም ማሳመርን ደንግጓል፡፡ ስትገድሉ አገዳደልን አሳምሩ፡፡ ስታርዱም አስተራረድን አሳምሩ፡፡ አንዳችሁ ማረጃ ካራውን ይሳለው፡፡ እርዱንም በቶሎ ያሳርፈው» (ሙስሊም 1955)
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ የአንድ ሰው አስክሬን ላይ ለመስገድ በተገኙበት ሊጋጣሚ ባልደረቦቻቸውን የአስክሬኑን ማረፊያ ጉድጓድ አስተካክለው እንዲያዘጋጁና አቀባበሩን እንዲያሳምሩ መመሪያ ይሰጧቸው ነበር፡፡ ከዚያም ወደነሱ በመዞር እንዲህ አሉ፡- «ይህ እናንተ የሰራችሁት የሞተውን ሰው የሚጠቅመው ወይም የሚጎዳው ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን አላህ አንድ ሥራ ሲተገበር በሚያምር መልክ መሰራቱን ይወዳልና ነው፡፡» (አል በይሃቂ ፊ ሸዕቢል ኢማን 5315) በሌላ ዘገባ ደግሞ፣ «አላህ (ሱ.ወ)፣ አንዳችሁ አንድን ነገር ሲሰራ በብቃት እንዲሰራው ይወዳል፡፡» ብለዋል፡፡ (አቡ ያዕላ ሸዕበል ኢማን 4386)

(ገጽ፣ 213 ተመልከት)



# ምግብህና መጠጥህ



# 8

ሐላል ምግብ በኢስላም ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል። ዱዓ ተቀባይነት እንዲያገኝ፤ ገንዘብና ቤተሰብ የተባረኩ እንዲሆኑ ሐላል መመገብ የግድ ነው።

ሐላል ምግብ በሚለው ቃል የተፈለገው ትርጓሜ፣ የተፈቀደ፣ በተፈቀደ መንገድ የተዘጋጀ፣ በሌሎች መብት ላይ ድንበር ሳይታለፍ፣ ግፍ ሳይፈፀም የተገኘና በንፁሕ ገንዘብ የተዘጋጀ ምግብ ለማለት ነው።

## የምዕራፉ ማውጫ


በምግብና መጠጥ ዙሪያ ያሉ መሰረታዊ መመሪያዎች

አዝርዕቶችና ፍሬዎች

አስካሪ መጠጦችና አልኮል

አደንዛዥ እጽ

የባሕር ምግቦች

የየብስ እንሰሳት

- ኢስላማዊ አስተራረድ
- በካሃዲያን ምግብ ቤትና ማዘጋጃያ የሚገኝ ስጋ ብያኔ

ኢስላማዊ አደን

የምግብና የመጠጥ ስነ ስርዓቶች

# ምግብህና መጠጥህ

## በምግብና መጠጥ ዙሪያ ያሉ መሰረታዊ መመሪያዎች

ምግቦችንና መጠጦችን በተመለከት ያለው መሰረታዊ መመሪያ፡ የሰው ልጅን በጤናው፣ በስነ ምግባሩና በሃይማኖቱ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የሆኑ፣ በክልክለነታቸው ለብቻ ተነጥለው የተጠቀሱት ነገሮች ሲቀሩ ሌሎቹ ሁሉ የተፈቀዱ መሆናቸውን የሚናገር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እርም ካደረጋቸው ነገሮች በስተቀር በምድር ላይ ያሉ ነገሮችን ሁሉ ለሰው ልጆች የፈጠረላቸው መሆኑ አላህ በሰው ልጅ ላይ ከዋለው ውለታ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለናንተ የፈጠረ ነው፡፡» (አል በቀራ 29)

## >አዝርዕቶችና ፍሬዎች

እንደ አስካሪ መጠጥ ወይም አደንዛዥ ዕጽ ዓይነት አካልና ጤንነት ላይ አደጋ የሚያደርሱ ወይም አዕምሮን የሚሸፍኑና የሚያስቱ ካለሆኑ በስተቀር፣ ከበረሃና ከጫካ ዛፎች፣ ስራ ስሮችና በተፈጥሮ የበቀሉ፣ እንዲሁም ሰዎች የሚዘሯቸው ተክሎች ሁሉም በዓይነታቸው ሊበሉ የሚፈቀዱ ናቸው፡፡ አስካሪ መጠጥ ወይም አደንዛዥ ዕጽ ግን ለአደጋና ለአዕምሮ መመረዝ ሰበብ ስለሆኑ እርም ናቸው፡፡



# > አስካሪ መጠጥና አልኮል

ማንኛውም አዕምሮን የጋረደ ወይም ከርሱ ተቀላቅሎ ያሸነፈው ወይም ሸፍኖት ተጽእኖ ያሳደረበት ነገር በሙሉ ኸምር ወይም አስካሪ መጠጥ ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም አስካሪ ነገር ኸምር ነው፡፡ ማንኛውም ኸምር ደግሞ ሐራም ነው፡፡» (ሙስሊም 2003) አስካሪ መጠጡ፣ እንደ ወይን፣ የቴምር እሸት፣ በለስና ዘቢብ ባሉ ፍራፍሬዎች፣ አለያም እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ ወይም ሩዝ ባሉ አዝርዕቶች፣ ወይም እንደ ማር ባሉ ጣፋጭ ነገሮች የተሰራ ቢሆንም ፍርዱ አንድ ዓይነት ነው፡፡

ማንኛውም አዕምሮን የጋረደ ነገር፣ በየትኛውም ስም ቢጠራም በየትኛውም መንገድ ቢዘጋጅም ኸምር ነው፡፡ ከጭማቂዎች ጋር ወይም ከጣፋጮችና ቸኮሌቶች ጋር ተቀላቅሎ የተዘጋጀ ቢሆንም እንኳ ኸምር ነው፡፡



> ኢስላም አዕምሮን ከሚረብሹትና ከሚጎዱት ነገሮች ሁሉ ጠብቆታል፡፡

## አዕምሮን መጠበቅ

ይህ ታላቅ ሃይማኖት፣ በቅርቢቱም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የባሮችን ጥቅም በማረጋገጥና በማስጠበቅ ላይ ትኩረት የሰጠ ሃይማኖት ነው፡፡ ከነዚህም ጥቅሞች መካከል እጅግ አንገብጋቢና አስፈላጊ ለሆኑ አምስት ነገሮች ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ አድርጎላቸዋል፡፡ እነሱም ሃይማኖት፤ ነፍስ፤ አዕምሮ፤ንብረትና ዘር ናቸው፡፡

አዕምሮ የኃላፊነት መሰረት ነው፡፡ የሰው ልጅ መለኮታዊ ክብርና ምርጫን የተጎናጸፈበት አካል ነው፡፡ በመሆኑም ኢስላማዊው ድንጋጌ እርሱን ከሚያበላሽና ከሚያዳክም ማናቸውም ነገር ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ አድርጎለታል፡፡

## የኸምር ፍርድ

ኸምር መጠጣት ከከባባድ ወንጀሎች መካከል የሆነ ወንጀል ነው፡፡ በቁርአንና በነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ላይ የኸምርን እርምነት የሚያውጁና የእሷን ጉዳይ አጥብቀው የሚያወግዙ መልክቶች ተላልፈዋል፡፡ ከነኚህም መካከል፡

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ የሚያሰክር መጠጥ፣ ቁማርም፣ ጣኦትም፣ አዝላምም፣ ከሰይጣን ስራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡ ፡» (አልማኢዳ 90)

  አላህ (ሱ.ወ) ኸምርን የገለጸት በነጃሳነቷ ነው፡፡ የሰይጣን ተግባር መሆኗን ከገለጸም በኋላ መዳን የምንፈልግ ከሆነ ከእርሷ እንድንርቅም አዞናል፡፡

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም አስካሪ መጠጥ ኸምር ነው፡፡ ማንኛውም ኸምር ደግሞ ሐራም ነው፡፡ በዱንያ ላይ ኸምርን የጠጣና እሱን አዘውታሪ ሆኖ የሞተ በአኼራ አይጠጣም፡፡» (ሙስሊም 2003)

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸምር መጠጣት ከኢማን ጋር የሚቃረንና እሱን የሚያጓድል እንደሆነ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድም ሰው በሚጠጣበት ቅጽበት ላይ ሙእሚን ኾኖ ኸምርን አይጠጣም፡፡» (አል ቡኻሪ 5256 / ሙስሊም 57)

- ኢስላም ኸምርን በሚጠጣ ሰው ላይ ቅጣትን በይኗል፡፡ ኸምርን የሚጠጣ ሰው ክብሩ ይጎድፋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ታማኝነቱ ይወገዳል፡፡
- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) እስከሚሞት ድረስ ኸምርን በመጠጣት ላይ የዘወተረንና በመሰል ተግባር ላይ የተሰማራን ሰው አሳማሚ ቅጣት እንደሚጠብቀው ዝቷል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ (ሱ.ወ) የሚያሰክርን ነገር የሚጠጣ ሰውን የመግል እንጥፍጣፊን ሊያጠጣው ቀጠሮ ዝቶበታል፡፡» (ሙስሊም 2002) ይህ መግል የጀሀነም ሰዎች ቁስል እዥ ነው፡፡
- ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ኸምርን በመጠጣት ላይ የተሳተፈም ሆነ የረዳ ሰው በዛቻው ውስጥ ይካተታል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኸምር ዙሪያ ተሳታፊና ተያያዥነት ያላቸውን አስር ሰዎች ረግመዋል፡፡ ጠማቂውን፣ አስጠማቂውን፣ ጠጪውን፣ ተሸካሚውን፣ አሸካሚውን፣ ቀጂውን፣ ሻጩን፣ ዋጋውን የሚበላውን፣ እሱን ገዝቶ ጋባዡን፣ እና የሚገዛለትን ወይም ተጋባዡን ረግመዋል፡፡ (አል ቲርሚዚ 1295)

## > አደንዛዥ እጽ

የሚበቅልም ይሁን በፋብሪካ የተመረተ አደንዛዥ እጽን በአፍንጫ በመሳብም ሆነ በመዋጥ፣ ወይም በመርፌ መልክ በመወጋት መጠቀም ወይም መውሰድ ከታላላቅ ወንጀሎችና ሃጢአቶች መካከል ነው፡፡ እሱ አዕምሮን የሚጋርድ ከመሆኑም በተጨማሪ የሰው ልጅን ነርቮች ያበላሻል፡፡ አደንዛዥ እጽን የሚያዘወትር ሰው በተለያዩ የነርቭና የመንፈስ በሽታዎች ይጠቃል፡፡ ምናልባትም ለሞቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ አላህ ለናንተ አዘኝ ነውና፡፡» (አል ኒሳእ 29)

## > የባሕር ምግቦች

የባሕር ምግቦች ሲባል የሚጠቁመው በውሃ ውስጥ እንጂ የማይኖሩትን እንስሳት ነው፡፡

ባሕር ደግሞ ብዙ ውሃ ያለው ሲሆን እንደ ሐይቅና የመሳሰሉት ብዙ ውሃ ያለባቸው የውሃ ዓይነቶችም በዚሁ ስር ይካተታሉ፡፡

እነኚህ የባሕር ምግቦች፣ እንስሳት ወይም እጽዋቶች ቢሆኑም የታደኑ ወይም ሞተው የተገኙ ሆነው በጤንነት ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ከሆነ እነሱን መመገብ የተፈቀደ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የባሕር ታዳኝና ምግቡ ለናንተም ለመንገደኞችም ተፈቀደ፡፡» (አልማኢዳ 96)

ታዳኝ ማለት ከነነፍሱ የተያዘ ማለት ነው፡፡ ምግቡ የተባለው ደግሞ ከሞተ በኋላ ባሕር የተፋው ማለት ነው፡፡



# > የየብስ እንስሳት

የየብስ እንስሳትን መብላት የሚፈቀደው ሁለት መስፈርቶች ከተሟሉ ነው፡፡

1 እነሱን መመገብ የተፈቀደ መሆናቸውና

2 አደናቸው ወይም እርዳቸው ኢስላማዊውን ሕግ በተከተለ መልኩ የተከናወነ መሆኑ ነው፡፡

### የሚፈቀዱ እንስሳት የትኞቹ ናቸው?

ሐራምነታቸው ከቁርኣንና ከሱና ማስረጃ ከተገኘላቸው ውጭ ያሉ ሁሉም እንስሳት መሰረታቸው የተፈቀደ ነው፡፡

የተከለከሉት የሚከተሉት ናቸው፡

**1** አሳማ፡

በኢስላም ውስጥ አሳማ እርም የተደረገና እርኩስ ነው፡፡ እያንዳንዱ ገላውና አካሉ ከርሱም የሚወጣ ማንኛውም ነገር እርምና ነጃሳ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «በክት፣ ፈሳሽ ደምም፣ የእሪያ (አሳማ) ስጋም ... በናንተ ላይ እርም ተደረገ፡፡»

(አል ማኢዳ 3)

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የአሳም ስጋ እሱ እርኩስ ነውና፡፡» (አል አንዓም 145) እርኩስ ማለት ነጃሳ ማለት ነው፡፡

**2** ማንኛውም አዳኝ ጥርሶች ያሉት አውሬ፡

ይህ ማለት ማንኛውም ስጋ በሊታ አውሬ ለማለት ነው፡፡ እንደ አንበሳና ነብር ያሉ ትላልቆችና ግዙፎች ቢሆኑም አለያም እንደ ድመትና የመሳሰሉ ትናንሾችም ቢሆኑ ፍርዱ ልዩነት የለውም፡፡ ውሻም በዚሁ ስር የሚካተት ነው፡፡

**3** ማደኛ ያላቸው በራሪ አዕዋፍ፡

ይህ ስጋ በሊታ የሆኑ አዕዋፍን በሙሉ የሚመለከት ነው፡፡ ቁራ፣ ንስር አሞራንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

**4** ነፍሳት፡

ማንኛውም በየብስ የሚኖሩ ነፍሳትን መብላት አይፈቀድም ምክንያቱም እነርሱ ለመታረድ አይመቹም፡፡ ከነሱ መካከል አንበጣ ለብቻው ተነጥሎ ይወጣል፡፡ እሱን መብላት ይፈቀዳል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሁለት ሙት ነገሮች ተፈቅደውልናል፤ አሳና አንበጣ፡፡» (ኢብኑ ማጀህ 3228)

**5** እባብ፣ ዘንዶና አይጥ፡

እነኚህን መብላት ክልክል ነው፡፡ እንድንገላቸው ታዘናል፡፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል፡ - «አምስት ነገሮች አጥፊዎች ናቸው፡፡ በሐጅ ትጥቅ ላይ ሆኖም፣ ተፈቶም እነሱን መግደል ይፈቀዳል፡፡ እነሱም፡ እባብ፣ ጥቁር አሞራ፣ አይጥ፣ ተናካሽ ውሻና ቀርጮ፡፡» (አል ቡኻሪ 3136 / ሙስሊም 1198)

**6** የቤት አህያ፡

ዕቃን ከቦታ ቦታ ለመጓጓዝና ለመጫን የሚገለገሉበት አህያ ነው፡፡



> በቁርኣንና በሱና ለብቻቸው ተነጥለው የተነገሩት ሲቀሩ እንስሳትን ካረዱ በኋላ መመገብ ይፈቀዳል፡፡

## የተፈቀዱ እንስሳት ዓይነት

ከነዚህ መካከል አላህ የፈቀዳቸው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

- በበረሃ የሚኖሩ፣ ከሰው ልጅ የሚሸሹ፣ ሰዎች ይዘውት ለማረድ የማይችሉትን የዱር እንስሳ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ልናድነው ይፈቀድልናል፡፡

- ሌላው ዓይነት ደግሞ ለማዳና በቀላሉ ሊያዝ የሚችል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ደግሞ በኢስላማዊ አስተራረድ ካልታረደ በስተቀር መመገቡ አይፈቀድም፡፡




> የመጽሐፍቱ ባለቤቶች፡ አይሁድና ኑሣራ፣ ኢስላማዊውን አስተራረድ ተከትለው ያረዱት ከሆነ፣ አላህ(ሱ.ወ) እርዱን እንድንበላ ፈቅዶልናል፡፡

## ኢስላማዊ አስተራረድ

ኢስላማዊ መስፈርቶችን ያሟላ እርድ ማለት ነው፡፡

የኢስላማዊው አስተራረድ መስፈርቶች

1. የሚያርደው ግለሰብ ለማረድ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡ እሱም ሙስሊም ወይም የመጽሐፍት ባለቤቶችን፣ ክርስቲያንና አይሁዳውያንን የሚያካትት ሲሆን እርዱን መምረጥ የሚችልና ስለ እርድ የሚያውቅ መሆን አለበት፡፡
2. የሚያርድበት መሳሪያ እንደ ቢላዋ ያለ የሚቆርጥ፣ ደም የሚያፈስና ለማረድ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡ እንስሳቱን በክብደቱ በሚጫን መሳሪያ፣ ወይም የእንስሳቱን ጭንቅላት በመግጨት ወይም በኤሌክትሪክ ንዝረት በማቃጠል መግደል እርም ነው፤ አይፈቀድም፡፡
3. እጁን ለማረድ በሚያንቀሳቅስ ጊዜ «ቢስሚላህ» በማለት የአላህን ስም ማውሳት፡፡
4. በእርድ ላይ መቆረጥ ያለባቸውን ክፍሎች መቁረጥ፡፡ እነርሱም የአየር ቧንቧ፣ ጉሮሮና ሁለቱ የደም ጋኖች ናቸው፡፡ እነኚህ፣ በአንገት ግራና ቀኝ ያሉ የደም ስሮች ናቸው፡፡ ከነኚህ አራት አካላት መካከል ሦስቱን ቢቆርጥ በቂ ነው፡፡

እነኚህ ጉዳዮች ከተሟሉ እርዱን መብላት ይበቃል፡፡ ነገር ግን ከእነኚህ መስፈርቶች መካከል አንዱ ከተጓደለ እርሱን መብላት አይፈቀድም፡፡

## የስጋ ዓይነቶች በምግብ ቤትና በልኳንዳዎች የሚገኝ ስጋ

1. **ሙስሊም ወይም የመጽሐፍቱ ባለቤቶች ያላረዷቸው፣** ቡዲሂስቶች፣ ሂንዶዎች፣ እንዲሁም ሃይማኖት የለሾች ያረዷቸው፣ ያልተፈቀዱና እርም የተደረጉም ናቸው፡፡ ብዙሃኑ ነዋሪዎቿ ሙስሊም ወይም የመጽሐፍ ባለቤቶች ባልሆኑቸ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ምግብ ቤቶችና ልኳንዳዎችም በዚህ ስር ይካተታሉ፡፡ ተቃራኒ የሆነ ብይን እስካልተረጋገጠለት ድረስ ይህ ዓይነቱ ሐራም ነው፡፡
2. **ሙስሊም ወይም የመጽሐፍት ባለቤት የሆነ አራጅ ኢስላማዊውን** ሕግ በተከተለ መልኩ ያረደውን መብላት በአንድ ድምፅ የሚፈቀድ ወይም ሐላል መሆኑ የጸደቀ ነው፡፡
3. **አንድ ሙስሊም ወይም የመጽሐፍት ባለቤት የሆነ ሰው** ኢስላማዊውን ሕግ ባልተከተለ መንገድ እንስሳው እራሱን ስቶ እንዲሞት፣ ወይም ውሃ ውስጥ ሰጥሞ እንዲሞት የተደረገ እንስሳ ስጋ፡፡ ይህን ዓይነቱን መብላት ክልክል ነው፡፡
4. **አንድ አስተራረድ በማያውቅ የመጽሐፍት ባለቤት በሆነ** ግለሰብ ወይም ምግብ ቤትና ልኳንዳ ውስጥ የታረደ፡፡ በመሰረቱ ይህ ዓይነቱም ከነሱ እርድ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ እናም ምንም እንኳ ሐላል መሆኑ ግልጽ የሆነን ስጋ ፈልጎ መመገቡ በላጭ ቢሆንም፣ እንዲህ ያለውን እርድ መመገብ የተፈቀደ መሆኑን የሚያጸድቅ አስተያየት ትክክል ነው፡፡ ሲመገቡት ግን የአላህን ስም ማውሳት መዘንጋት የለበትም፡፡

# > ሸሪዓዊው አደን

ሸሪዓዊው አደን የሚፈቅደው፣ ስጋቸው የሚፈቀድ፣ ነገር ግን እነርሱን በቁጥጥር ስር አውሎ መባረክና ማረድ የማይመች የሆኑ እንስሳትን ነው:: ለምሳሌ፡ ስጋ በሊታ ከሆኑት በጫካና በዱር የሚገኙ አዕዋፍ፣ እንዲሁም ሚዳቋ፣ ጥንቸልና የመሳሰሉት ይገኙበታል::

ለአደን መስፈርቶች አሉት:: ከነርሱም መካከል፡

1 አዳኙ፣ ጤናማ አዕምሮ ያለው፣ አደንን አስቦ የወጣ፣ ሙስሊም አለያም ከመጽሐፍት ባለቤት የሆነ መሆን አለበት:: ጣዖት አምላኪ ወይም አዕምሮን የሳተ ሰው ያደነው አይፈቀድም::

2 እንሰሳው በመበርገግና ከሰው በመራቁ ምክንያት ተባሮ ሊያዝና ሊታረድ የማይችል መሆን አለበት:: እንደ ዶሮ፣ ፍየልና በግ፣ እንዲሁም ከብት አይነት ከሆነ ማደን አይቻልም::

3 እንሰሳው የሚገደልበት መሳሪያ እንደ ቀስት፣ ጥይትና የመሳሰሉ መሳሪያዎች ዓይነት በስለቱ የሚገድል መሆን አለበት:: እንደ ድንጋይና መሰል በክብደቱየሚገድል ዓይነት፣ ሰውዬው  እንሰሳው ከመሞቱ በፊት ደርሶ የሚባርከውና የሚያርደው ካልሆነ በስተቀር መመገቡ አይፈቀድም::

4 ማደኛ መሳሪያውን ከመተኮሱ ወይም ከመልቀቁ በፊት፣ «ቢስሚላህ» በማለት የአላህን ስም ማውሳት አለበት::

5 እንሰሳውን ወይንም በራሪውን ካደነው በኋላ ሳይሞት በሕይወት ካገኘው በማረድ ሐላል ሊያደርገው ይገባል::

6 ለመብላት ካልሆነ በስተቀር እንስሳትን ማደን እርም ነው:: ያደኑትን ሳይበሉ፣ ለመዝናናትና ለሌላ ጥቅማ ጥቅም እንሰሳትን ማደን ክልክል ነው::



# > የመብላትና የመጠጣት ስርዓት



አላህ ለሰው ልጆች የዋለውን ጸጋ ለማስታወስ፣ ከበሽታዎች ለመጠበቅ፣ ማባከንን እና፣ ድንበር ከማለፍ መጠበቅን ይመስል ዓላማንና አምላካዊ ጥበብን ለማረጋገጥ፣ አላህ (ሱ.ወ) በምግብና መጠጥ ውስጥ ብዙ ስርዓቶችን ደንግጓል፡፡

ከነኚህ ስርዓቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1. በወርቅና ብር ዕቃዎች፣ ወይም የሁለቱ ቅብ በሆኑ ዕቃዎች ላይ መመገብ ክልክል ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት፣ በዚህ ውስጥ ብክነት፣ ድንበር ማለፍ፣ አና የድሆችን ቀልብ መሰበር ስላለበት ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በወርቅና ብር ዋንጫዎች አትጠጡ፤ በነርሱም ትሪዎች ላይ አትመገቡ፤ እርሷ በዚህች ዓለም የነርሱ (የከሃዲያን)፣ በወዲያኛው ዓለም ደግሞ የኛ ነች፡፡» (አል ቡኻሪ 5110 / ሙስሊም 2067)

2. ከምግብ በፊትና በኋላ እጅን መታጠብ፡፡ በእጅ ላይ ቆሻሻና የምግብ ቅሪት ካለበት ደግሞ መታጠቡ የጠበቀ ይሆናል፡፡

3. መብላት መጠጣት ከመጀመሩ በፊት፣ «ቢስሚላህ» ማለት፡፡ ትርጉሟ፡ በአላህ ስም በረከትን እፈልጋለሁ፣ በርሱም እታገዛለሁ፤ ማለት ነው፡፡ ከረሳና በምግቡ መሐከል ካስታወሰ፣ «ቢስሚላሂ ፊ አወሊሂ ወአኺሪሂ» (መጀመሪያውንም መጨረሻውንም በአላህ ስም) ይላል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመመገብ ስርዓትን የማያውቅና የማያስምርን አንድ ትንሽ ሕፃን ልጅ አይተው ሊያስተምሩት እንዲህ አሉት፡- «አንተ ልጅ ሆይ! የአላህን ስም አውሳ፤ በቀኝ እጅህ ብላ፤ ከአጠገብህም ብላ፡፡» ( አል ቡኻሪ 5061 / ሙስሊም 2022)

4. በቀኝ እጅ መብላትና መጠጣት፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በግራ እጃችሁ አትብሉ፤ ሸይጣን የሚበላው በግራ እጁ ነው፡፡» ( ሙስሊም 2019)

5. ቆሞ ባይበላና ባይጠጣ ይወደድለታል፡፡

6. አንድ ሰው እርሱ አጠገብ ካለ ምግብ መብላትና ሰዎች ፊት ለፊት ካለው አለመብላት ከአደብ ነው፡፡ ከሰዎች ፊት እያነሱ መብላት፣ ስርዓት ማጣት ነው፡ ፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለልጁ፣ «ከአጠገብህም ብላ፡፡» ብለውታል፡፡

7 ጉርሻ ከወደቀ ማንሳትና ያለባትን ቆሻሻ ማስወገድ እስከተቻለ ድረስ ማበስና መብላት ይወደዳል፡፡ በዚህ ውስጥ ጺጋንና ምግብን መጠበቅ አለበት፡፡

8 የምግብን ነውር አለመናገር፣ አለማዋደቅና አለመናቅ፡፡ ከተቻለ ያድንቅ፤ አለበለዚያ፣ ይተወውና ዝም ይበል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዴም ምግብን አነውረው አያውቁም፡፡ ከፈለጉት ይበሉታል፤ ከጠሉት ደግሞ ይተውታል፡፡ (አል ቡኻሪ 5093/ሙስሊም 2064)

9 ምግብን አለማብዛትና በርሱም አለመወጠር፡፡ ይህ የበሽታና የድብርት ምንጭ ነው፡፡ መሐከለኛ መሆን የነገሮች ሁሉ ያማረው ገጽታ ነው፡፡ ጉዳዩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት ነው፡፡ ‹‹የሰው ልጅ ከሆድ የከፋን ዕቃ አልሞላም፡፡ ለኣደም ልጅ፣ ወገቡን ቀና የሚያደርግበት ጥቂት ጉርሳዎች ይበቁታል፡፡ መብላት የግድ ከሆነ ግን፣ አንድ ሦስተኛውን ለምግቡ፣ ሌላ አንድ ሦስተኛውን ለመጠጡ፣ ሌላ አንድ ሦስተኛውን ደግሞ ለአየር ያድርገው፡፡›› (አትቲርሚዚ 2380/ ኢብኑ ማጃህ 3349)

10 ሲያበቃ « አልሐምዱሊላህ » በማለት ከሰዎች ብዙዎችን ሳያካትት እርሱን በመመገብ ያበለጸገውን አላህን ያመሰግናል፡፡ በዚህም ላይ አክሎ፣ ((አልሐምዱ ሊላሂ አለዚ አጥዐመኒ ሓዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሐውሊን ሚኒ ወላ ቁዋህ)) -‹‹የኔ ብልሃትና ኃይል ሳይኖርበት ይህንን የመገበኝና የሰጠን አላህ ይመስገን›› ማለት ይችላል፡፡

> ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አላህ ለአንድ ባሪያ፣ ትንሽ ምግብን በልቶ ሊያመሰግነው፣ ትንሽ መጠጥንም ጠጥቶ ሊያመሰግነው ይወድለታል፡፡›› (ሙስሊም 2734)





# ልብስህ



# 9

ልብስ ለሰው ልጅ ከተሰጡ የአላህ ጸጋዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹የአደም ልጆች ሆይ ሃፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ፣ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፤ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው፡፡ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው ይገሰፁ ዘንድ (አወረደላቸው)፡፡›› (አል አዕራፍ 26)

## የምዕራፉ ማውጫ

ልብስ በኢስላም

የተከለከሉ ልብሶች

- ሀፍረተ ገላን የሚያጋልጥ
- በሁለቱ ጾታዎች መካከል መመሳሰልን የሚፈጥር
- ከካሃዲያን ጋር የሚያመሳስል
- ኩራትንና መኮፈስን የሚያንጸባርቅ
- ሐርነት ወይም ወርቅነት ያለው ከሆነ
- ብክነት ወይም አላስፈላጊነት የሚታይበት

# ልብስ በኢስላም

አንድ ሙእሚን ከሰዎች ጋር ለመደባለቅና ሠላትን ለመስገድ የሚለብሰው ልብስ፣ የሚያምርና ንጹህ መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «የአደም ልጆች ሆይ (ሃፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡» (አል አዕራፍ 31)

አላህ (ሱ.ወ)፣ የሰው ልጅ በአለባበሱና በይፋዊ መገለጫው እንዲቆነጃጅ የሚያዘው ሕግን ደንግጓል፡፡ ይህ በራሱ የአላህን ጸጋ ይፋ ማድረግ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የአላህን ጌጥ ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማን ነው? በላቸው እርሷ በትንሳኤ ቀን ለነዚያ ላመኑት ብቻ ስትኾን በቅርቢቱ ሕይወት ተገቢያቸው ናት፡፡ በላቸው እንደዚሁ ለሚያውቁ ሕዝቦቹ አንቀጾችን እናብራራለን፡፡» (አል አዕራፍ 32)

ልብስ ብዙ ጉዳዮች ይፈጸሙበታል፡

1 የተወሰኑ የሰውነት ክፍሎችን ከእይታ ይሸፍናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የአደም ልጆች ሆይ ሃፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፡፡» (አል አዕራፍ 26)

2 ገላን ከሙቀትና ከውርጭ፣ እንዲሁም ከጎጂ ነገሮች ይጠብቃል፡፡

ብርድና ሙቀት ተለዋዋጭ የአየር ንብረቶች ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፣ የልብስን ገጽታ በማስመልከት እንዲህ ብሏል፡- «ሐሩርንም (ብርድንም) የሚጠብቋችሁን ልብሶች፣ የጦራችሁንም አደጋ የሚጠብቋችሁን ጥሩሮች ለናንተ አደረገላችሁ፡፡እንደዚሁ ትሰልሙ ዘንድ ጸጋውን በናንተ ላይ ይሞላል፡፡» (አል ነሕል 81)



## > በልብስ ዙሪያ



> ኢስላም ልብስን በተመለከተ፣ መለበስ አለበት ብሎ የገደበው ወይም የወሰነው ልብስ የለም፡ ፡ በላጩና የተሻለው፣ በኢስላም የተፈቀደና የሀገሬው ነዋሪዎች የሚለብሱት የልብስ ዓይነት ነው፡፡

ኢስላም ተፈጥሯዊ ሃይማኖት ነው፡፡ በመሆኑም የሰዎችን አኗኗር አስመልክቶ የተደነገጉት ሕጎች በሙሉ ከተፈጥሮ ጋር የሚስማሙና ከጤናማ አዕምሮ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡

የሙስሊም አለባበስና የተፈቀዱ መቆነጃጃዎች

ኢስላም የሰው ልጅን አለባበስ የተገደበ አላደረገውም፡፡ ድንበር ማለፍ የሌለባቸው ከሆነና ለተፈለጉበት ዓላማ መዋል የሚችሉ እስከሆኑ ድረስ፣ ሁሉም የልብስ ዓይነቶች ሕጋዊ መሆናቸውን ያጸድቃል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ በዘመኑ የነበሩ አልባሳትን ለብሰዋል፡፡ ሰዎች የተወሰኑ ልብሶች ብቻ እንዲለበሱ አላዘዙም፡፡ እንዳይለበሱ የከለከሉት ውስን ልብስም የለም፡፡ የከለከሉት በአለባበስ ዙሪያ ያሉ የተወሰኑ ገጽታዎችን ነው፡፡

በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ የሁሉም ነገር መሰረቱ የተፈቀደ ነው፡፡ በማስረጃ ካልሆነ በስተቀር እርም ነው ማለት አይቻልም፡፡ ልብስ ደግሞ ከነዚህ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ አምልኮ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ማንኛውም ዓይነት አምልኮ መሰረቱ የተከለከለ ነው፡፡ በማስረጃ ካልሆነ በስተቀር የተፈቀደ ወይም ሕጋዊ አይሆንም፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ያለማባከንና ያለኩራት ብሉ፣ መጽውቱ፣ ልበሱ፡፡» (አል ነሳኢ 2559)

### የተከለከሉ አልባሳት

1 አንድ ሙስሊም ሀፍረተ ገላውን በልብስ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡ - «ሀፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፡፡» (አል አዕራፍ 26)

ኢስላም ለወንዶችም ለሴቶችም የሀፍረተ ገላን ገደብ አስቀምጧል፡፡ የወንድ ልጅ ሀፍረተ ገላ ከእንብርቱ እስከ ጉልበቱ ሲሆን፣ ትልቁ ሀፍረተ ገላው ሁለት ብልቶቹ ናቸው፡፡ እነኚህ ሁለት ብልቶች፣ ለሚስት ወይም እንደ ሕክምና እና መሰል ጉዳዮች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ማሳየት አይፈቀድም፡፡ አንድ ሠሐቢይ፣ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ሀፍረተ ገላ በጠየቃቸው ጊዜ እንዲህ ብለውታል፡- «ሀፍረተ ገላህን፣ ለባለቤትህ ወይም በቁጥጥርህ ስር ላሉ ባሮች ካልሆነ በስተቀር ከማጋለጥ ጠብቅ፡፡»

ሠሐቢዩም፡ «አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ፣ ሰዎች ከፊሉ ከከፊሉ ጋር ተደበላልቀውና ተቀላቅለው የሚኖሩ ከሆነስ?» አላቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉት፡- «አንድም ሰው እንዳያይብህ ማድረግ እስከቻልክ አይይብህ፡፡» አሉት

ሠሐቢዩም በማስከተል፡- «እሺ አንዳችን ብቻውን ከሆነስ?(እርቃኑን ቢሆንስ)» በማለት ጠየቀ፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አላህ ከሰዎች የበለጠ ሊታፈር ይገባል፡፡» አሉት (አቡ ዳውድ 4017)

ሴት ልጅ፣ ለወንዶች እይታ በምትጋለጥበት ወይም ወንዶች ፊት ለፊት ስትሆን፣ ከመዳፎቿና ከፊቷ በስተቀር ሰውነቷ በጠቅላላ ሀፍረተ ገላዋ ነው፡፡ ይህ ሴቶችን ከማናቸውም ክብራቸውን ከሚያጎድፍና በነርሱ ላይ አደጋን ከሚጋርጥ ነገር የሚጠብቅ ነው፡፡

ኢስላም፣ በፈቀደበት አጋጣሚ ላይ ካልሆነ በስተቀር ለባዕድ (አጅነቢ) ወንዶች ምንም ዓይነት የገላዋን ክፍል መግለጥና ለእይታ ማጋለጥ አይፈቀድላትም፡፡ ነገር ግን የቅርብ ተጠሪዎቿ (መሓሪሞቿ) ፊት ለፊት በተለምዶ መግለጥ ወይም መታየት ያለበት የሆነን ገላዋን ተገልጣ መታየት ትችላለች፡፡ ባሏ ግን ለርሱም ሆነ ለርሷ የፈለጉትን መመልከትና በሱም መርካትና መደሰት ይችላሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው፤ እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ፡፡» (አል በቀራ 187)

የገላን ቅርጽ የሚያወጣ የተወጣጠረ ልብስም ሆነ ከስሩ ያለን ገላ ገልጦ በሚያሳይ ስስ ልብስ መሸፈን አይቻልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፣ ሀፍረተ ገላውን የሚያሳይ ስስ ልብስ በሚለብስ ሰው ላይ የዛተው ለዚህ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ሁለት ዓይነት ሰዎች የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡» ካሉ በኋላ «ለብሰው የተራቆቱ ሴቶች፡፡» በማለት አንደኛውን ጠቅሰዋል፡፡

### 2 በሁለቱ ጾታዎች መሐል መመሳሰልን የሚፈጥር

ይህህ ሴቶች ብቻ የሚለብሷቸውን አልባሳት በመልበስ ወንዶች ከሴቶች ጋር መመሳሰላቸውንና እንዲሁም ሴቶች በወንዶች መመሳሰላቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ ይህ ከከባባድ ወንጀሎች ውስጥ የሚፈረጅ እርም ወይም ክልክል ነው፡፡ በአካሄድ፣ በንግግርና በመሳሰሉት መመሳሰልም በዚሁ ስር የሚካተት ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሴቶችን ልብስ የሚለብስን ወንድ እንዲሁም የወንዶችን ልብስ የምትለብስ ሴትን ተራግመዋል፡፡ (አቡ ዳውድ 4098)

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከወንዶች መካከል በሴቶች የሚመመሳሰሉትን፣ ከሴቶች መካከልም በወንዶች የሚመሳሰሉትን ተራግመዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 5546)

እርግማን ማለት ከአላህ እዝነት መባረርና መራቅ ነው፡፡ ኢስላም የወንድ ባህሪና ውጫዊ መገለጫዎቹ፣ የርሱ ብቻና ከሴቶች የሚለዩት እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ ሴቶችም እንዲሁ፡፡ ካልተበረዘ ተፈጥሯዊ ስርዓትና ጤናማ አዕምሯዊ እይታ ጋር የሚስማማውም ይሄው ነው፡፡

### 3 ከካሃዲያን ልዩ መገለጫ ጋር የሚመሳሰለል ልብስ

እንደ ባሕታውያንና ካህናት ልብሶች ዓይነት የተወሰነ ሃይማኖት መገለጫ ወይም አርማ የተደረጉ አልባሳትና የመሳሰሉት የተከለከሉ ናቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከሕዝቦች ጋር የተመሳሰለ እርሱ ከነርሱ ነው፡፡» (አቡ ዳውድ 4031) የሃይማኖት ማንጸባረቂያ አርማ ያለባቸው አልባሳትም በዚሁ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ መመሳሰል፡ የአቋም ድክመት፣ በራስ አለመተማመንና እርሱ በእምነት እርግጠኛ አለመሆንን የሚያስረዳ ነው፡፡

አንድ ሙስሊም፣ ከከሃዲያን መካከል አብዛኞቹ የሚለብሱትና የሚያዘወትሩት ቢሆንም፣ በሀገሩ ላይ በሰፊው ሕዝብ የሚለበስን ልብስ መልበሱ መመሳሰል አይባልም፡፡ ምክንያቱም፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኢስላማዊው ድንጋጌ ከተከለከለው ውጭ የቁረይሽ አጋሪያን ይለብሱት የነበረውን የልብስ ዓይነት ይለብሱ ነበር፡፡



> ከካሃዲያን ጋር የሚያመሳስልን ወይም ከኢስላም ውጭ ያሉ ሃይማኖቶችን አርማ በላዩ ላይ ያዘለን ልብስ መልበስ ክልክል ነው፡፡

## 4 ኩራትና መኮፈስን የሚያንጸባርቅ አለባበስ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በቀልቡ ውስጥ የቅንጣትን ክብደት ያክል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡» (ሙስሊም 91)

ኢስላም ኩራትና መኮፈስን የሚፈጥር ከሆነ ወንዶች ልብሳቸውን ከቁርጭምጭሚታቸው በታች በመልቀቅ እንዳይጎትቱ ከልክሏል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በትዕቢት ተሞልቶ ልብሱን የጎተተ ሰው የትንሳኤ ቀን አላህ አይመለከተውም፡፡» (አል ቡኻሪ 3465 ሙስሊም 2085)

ለታዋቂነት የሚጋብዝ ልብስም ተከልክሏል፡፡

አንድ ሰው በመልበሱ ሰዎች የሚገረሙበትና የሚደነቁበት፣ ስለሱ የሚያወሩለት ፣በይዘቱ ወይም በመልኩ ወይም እሱን የለበሰ ሰው በሚያሳየው የኩራትና የትዕቢት ስሜት ምክንያት የሚሸማቀቁበት የአለባበስ ዓይነት ወይም ልብስ የተከለከለ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በዱንያ ላይ የታዋቂነት ልብስን የለበሰ ሰው፣ አላህ (ሱ.ወ) በትንሳኤ ቀን የውርደት ልብስን ያለብሰዋል፡፡» (አህመድ 5664 ኢብኑ ማጃህ 3607)

## 5 ሐርነት ወይም ወርቅነት ያለው ከሆነ ለወንዶች የተከለከለ ነው፡፡

ኢስላም ሁለቱንም በወንዶች ላይ እርም አድርጓል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እነኚህ ሁለቱ በወንድ ሕዝቦቼ ላይ እርሞች ናቸው፤ ለሴቶቻቸው ደግሞ የተፈቀዱ ናቸው፡፡» (ኢብኑ ማጃህ 3595 / አቡ ዳውድ 4057)

በወንዶች ላይ እርም የተደረገው፣ በሐር ትል የሚመረተው የተፈጥሮ ሐር ነው፡፡

## 6 ማባከንና ማዝረክረክ ያለበት፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማባከንና ኩራት በሌለበት ሁኔታ ብሉ መጽውቱ ልበሱ፡፡» (አል ነሳኢ 2559)

ይህ እንደሁኔታው ይለያያል፡፡ ባለሃብት፣ ድሃ ሊገዛው የማይገባውንና የማይችለውን የልብስ ዓይነት የመግዛት መብት አለው፡፡ ይህም ካለው ሃብትና ገቢ፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ደረጃ አንጻር የሚታይ ይሆናል፡፡ አንድ ልብስ ለድሃ ሰው ማባከን ተብሎ ለሃብታም ግን ማባከን ላይባል ይችላል፡፡



> ማባከን በአለባበስም የተከለከለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደየግለሰቡ የቀን ገቢና የተገቢነት ደረጃ ይለያያል፡፡



# ቤተሰብህ



# 10

ኢስላም ቤተሰባዊ ሕይወት እንዲጸናና እንዲረጋ፣ እንዲሁም ቤተሰብን ከሚያበላሹና ከሚያፈርሱ ነገሮች በመጠበቅና በመከላከል ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ባጠቃላይ፣ አንድ ቤተሰብ ካማረና ከተስተካከለ የተቀናጀ ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ዋስትናዎችን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## የምዕራፉ ማውጫ

ቤተሰብ በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ

ሴት በኢስላም ውስጥ ያላት ክብርና ደረጃ

- ኢስላም ልዩ ትኩረት የሰጣቸው ሴቶች
- በሁለቱ ፆታዎች መሐከል መጣረስ የለም
- ከወንድ አንጻር የሴት ዓይነቶች
- በባዕድ ወንዶችና ሴቶች መሐከል ለሚኖር ግንኙነት የተቀመጠ መመሪያ
- የሂጃብ -የሴቶችኢስላማዊ አለባበስ- ገደብ

ጋብቻ በኢስላም

የባልና የሚስት መብቶች

ከአንድ በላይ ሚስቶች ማግባት

ፍቺ

የወላጆች መብት

የልጆች መብት

## > ቤተሰብ በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ

የሚከተሉት ጉዳዮች ኢስላም ለቤተሰብ ልዩ እንክብካቤና እገዛ ማድረጉን በግልጽ ያሳያሉ፡-

**1** ኢስላም በጋብቻ ጅማሬና በቤተሰብ ምስረታ ላይ ልዩ እይታ አለው፡፡ በመሆኑም ከስራዎች ሁሉ የላቀ ተግባር ከመሆኑም ባሻገር፣ የመልክተኞች ፈለግ እንዲሆንም አድርጎታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነገር ግን እኔ እጾማለሁ እፈታለሁም፤ እሰግዳለሁ አሸልባለሁም፤ ሴትም አገባለሁ፡፡ ከኔ ፈለግ የወጣ ከኔ አይደለም፡፡»
(አል ቡኻሪ 4776 /ሙስሊም 1401)

- ቁርኣን ከታላላቅ ተዓምራትና ጸጋዎች ጎራ ከቆጠራቸው ነገሮች አንዱ አላህ (ሱ.ወ) በባልና ሚስት መሐከል ፍቅርን እዝነትንና እርካታን ማድረጉን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ለናንተም ከነፍሶቻችሁ ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉሉ፡፡» (አል ሩም 21)
- ጋብቻን ገር ማድረግ፣ ለማግባት የሚፈልግም ሰው ነፍሱን ከዝሙት እንዲጠብቅ መረዳትና መታገዝ እንዳለበት ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ሦስት ዓይነት ሰዎችን ለመርዳትና ለማገዝ በራሱ ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡» አሉና ከነሱ መካከል፣ «ጥብቅነትን ፈልጎ ጋብቻን የፈፀመን ሰው» ጠቅሰዋል፡፡ (አል ቲርሚዚ 1655)
- ወጣቶችን ገና በአፍላ ዕድሜያቸውና ባልተነካ ጉልበታቸው ላይ ሳሉ ጋብቻን እንዲፈፅሙ አዟል፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ ለነሱ መርጊያቸውና መርኪያቸው ስለሆነ ነው፡፡ ለፍቶት ስሜታቸውና ፍላጎታቸው ትክክለኛ መፍትሄም ነው፡፡



> ቁርኣን በባልና በሚስት መሐከል ያለን እርካታ፣ ፍቅርና መተዛዘን ከታላላቅ ጸጋዎች መድቦታል፡፡

**2** ኢስላም ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ወንድም ሆነ ሴት ልዩ ክብር ሰጥቷል፡፡

ኢስላም ልጆችን የመንከባከብና በማሳዳግ ጉዳይ በእናትና በአባት ላይ ከባድ ኃላፊነት ጥሏል፡፡ ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ማለታቸው ተላልፏል፡- «ሁላችሁም እረኞች ናችሁ፤ ማናችሁም ከሚጠብቀው ይጠየቃል፡፡ አንድ መሪ እረኛ ነው፤ በጥበቃው ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡ አባወራ በቤተሰቡ ላይ እረኛ ነው፤ በርሱ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡ ሴትም በባሏ ቤት ውስጥ እረኛ ነች፤ በርሷ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነች፡፡ ባሪያ በአሳዳሪው ንብረት ላይ እረኛ ነው፡፡ በርሱ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 853 /ሙስሊም 1829)

**3** ኢስላም ለአባቶችና ለእናቶች ክብር በመስጠትና ደረጃቸውን በመጠበቅ፣ እንዲሁም እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ድረስ እነርሱን መንከባከብና ትዕዛዛቸውን መፈፀምን አስመልክቶ ልዩ ትኩረት ቸሯል፡፡

ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣ ምንም ያህል ትልቅ ሰው ቢሆኑም ለወላጆቻቸው ታዛዥ የመሆንና ለነሱ በጎ የመዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ጉዳይ ከርሱ አምልኮ ጋር አቆራኝቶ ጠቅሶታል፡፡ እነርሱ ላይ በንግግርና በተግባር ድንበር ማለፍን ከልክሏል፡፡ በነሱ መናደዱን የሚመለክትን ቃል ወይም ድምፅ ማሰማትንም ሳይቀር ከልክሏል፡፡ «ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፤ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ በወላጆቻችሁም መልካምን ስሩ፤ በአንተ ዘንድ ኾነው

አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፤ አትገላምጣቸውም፤ ለነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው።» (አል ኢስራእ 23)

4 ኢስላም የወንድም ሆነ የሴት ልጆችን መብት እንድንጠብቅ አዟል። በመካከላቸው በወጪም ሆነ በይፋ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ፍትሃዊ መሆንም ግዴታ ነው።

5 ኢስላም በአንድ ሙስሊም ላይ ዘመድናን የመቀጠል ግዴታ ጥሎበታል። ይህ ማለት በእናቱም ሆነ በአባቱ በኩል ያሉትን ዘመዶቹን ዝምድና በመቀጠልና ለነርሱ በጎ በመዋል ይገለፃል።

ወንድሞቹ፣ እህቶቹ፣ አጎቶቹ፣ አክስቶቹና ልጆቻቸው እዚህ ውስጥ የሚገቡ ሲሆን ለነርሱ መልካም መስራት፣ ከታላላቅ ወደ አላህ መቃረቢያዎችና ታዛዥነትን መግለጫ መንገዶች መካከል ቆጥሮታል። ዝምድናቸውን ከመቁረጥ፣ ወይም ክፉ ነገር በነርሱ ላይ ከመፈፀም እንድንርቅ አስጠንቅቋል። ይህን ማድረግን ከከባባድ ወንጀሎች ፈርጆታል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ዝምድናን ቆራጭ ጀነት አይገባም።» (አል ቡኻሪ 5638 /ሙስሊም 2556)



> ኢስላም ለእናትና ለአባት ክብር የመስጠትን መሰረት ጥሏል።

## > ሴት በኢስላም ውስጥ ያላት ስፍራ

ኢስላም ሴት ልጅን እጅግ በጣም አክብሯታል። ለወንዶች ባሪያ ከመሆንም ነፃ አውጥቷል። ክብርና ደረጃ የሌላት ውዳቂና ርካሽ ከመሆንም አድኗታል። ከሴት ልጅ ክብር ጋር ተያያዥነት ካላቸው ኢስላማዊ ድንጋጌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ኢስላም ለሴት ልጅ ፍትሃዊ በሆነ ክፍፍሎሽ የውርስ ድርሻዋን ሰጥቷል። በአንዳንድ ስፍራ ከወንድ ጋር እኩል ታገኛለች። በአንዳንድ ስፍራ ደግሞ ድርሻዋ ከወንዱ ይለያል። ይኸውም ለሟች ባላት ቅርበት፣ እንዲሁም ካለባት ኃላፊነትና ወጪ አንጻር የሚወሰን ነው።

- በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ወንድና ሴትን እኩል አድርጓቸዋል። ከነዚህም መካከል ማንኛውም ገንዘብ ነክ እንቅስቃሴ አንዱ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሴቶች የወንዶች ክፋይ ናቸው።» (አቡ ዳውድ 236)

- ኢስላም ለሴት ልጅ ባሏን የመምረጥ ነፃነት ሰጥቷል። ልጆችን የማሳደግ ትልቅ ኃላፊነት ደግሞ ጥሎባታል፡ ፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሴት ልጅ በባሏ ቤት ውስጥ ጠባቂ ነች፤ ከምትጠብቀው ነገር ተጠያቂ ነች።» (አል ቡኻሪ 853 / ሙስሊም 1829)

- ስሟና በአባት የመጠራት ክብሯ እንዲቆይ አድርጎላታል። ከጋብቻ በኋላም በአባት መጠራቷ ይቀጥላል። ምን ጊዜም በአባቷና በቤተሰቦቿ መጠራቷም ይዘልቃል።

- ወጪያቸውን መሸፈን ከሚኖርበት ሴቶች መካከል ከሆነች ማለትም ሚስቱ እናቱ ወይም ሴት ልጁ ከሆነች፣ ኢስላም በወንዱ ላይ እሷን የመጠበቅና ወጪዋን የመሸፈን ግዴታ ጥሎበታል።

- የቅርብ ዘመድ ባትሆንም፣ ረዳት የሌላትን ደካማ ሴት መርዳትና ማገዝ ልዩ ክብርና ደረጃ የሚሰጠው መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶታል። እሷን ለመርዳትና ለማገዝ መሯሯጥ አላህ ዘንድ ትልቅ ክብር ያለው ተግባር መሆኑን በመግለጽ አነሳስቷል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶችና የችግረኞችን ጉዳይ ለመፈፀም የሚሯሯጥ ሰው፣ ልክ በአላህ መንገድ ላይ ትግል እንደሚያደርግ፣ ሌሊት ተነስቶ ሳይታክት እንደሚሰግድና፤ ጾሞ እንደማያፈጥር ሰው ነው።» (አልቡኻሪ 5661 / ሙስሊም 2982)

## ኢስላም ልዩ ትኩረት እንዲቸራቸው ያደረጋቸው ሴቶች

**እናት፡** አቡ ሁረይራ(ረ.ዐ) የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡፡ አንድ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፣ አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ ከሰዎች ሁሉ በበለጠ ጓደኝነቱን ወይም ግንኙነቱን ልጠብቅለት የሚገባ ማን ነው? አላቸው፡፡ እሳቸውም፡ ‹‹እናትህ›› አሉት፤ ከዚያስ? አላቸው፤ ‹‹ከዚያም እናትህ›› አሉት፤ ከዚያስ? አላቸው፤ ‹‹አሁንም እናትህ›› አሉት፡፡ ለአራተኛ ጊዜ፡ ከዚያስ? አላቸው፣ ‹‹ከዚያማ አባትህ ነው፡፡›› አሉት፡፡ (አል ቡኻሪ 5626 / ሙስሊም 2548)

**ሴት ልጅ፡** ዑቅበቱ ኢብኑ ዓሚር(ረ.ዐ) ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል፡ ‹‹ሦስት ሴት ልጆች ኖረውት፤ ስለነርሱ ትዕግስት አድርጎ፣ ጥሮ ግሮ ከላቡ ውጤት ያበላቸው፣ ያጠጣቸውና፣ ያለበሳቸው ሰው፣ የትንሳኤ ቀን ከእሳት ግርዶሽ ይሆኑለታል፡፡›› (ኢብኑ ማጃህ 3669)

**ሚስት፡** እመት ዓኢሻ(ረ.ዐ)፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፡- ‹‹በላጫችሁ ለቤተሰቦቹ መልካም የሆነው ነው፡፡ እኔ ለቤተሰቦቼ መልካማችሁ ነኝ፡፡›› (አል ቲርሚዚ 3895)

> በኢስላም የወንድና የሴት ግንኙነት የመደጋገፊያ ግንኙነት ነው፡፡ እያንዳንዳቸው ሙስሊም ማህበረሰብን በመገንባት ላይ የሚዘጉት ክፍተት ወይም ቀዳዳ አላቸው፡፡

## በሁለቱ ፆታዎች መካከል ሽኩቻ የሚፈጥር ነገር የለም፡፡

**በአንዳንድ ያልሰለጠኑ ማህበረሰቡች ውስጥ እንደታየው፣** በወንድና በሴት መካከል የተደረጉት ሽኩቻዎች፣ በወንዱ በሴት ላይ ፈላጭ ቆራጭ መሆን፣ አለያም ደግሞ በሴቷ ከተፈጥሯዊ ባህሪ ማፈንገጥና ከአላህ ሕግጋት ውጭ መሆን ይጠናቀቃል፡፡

ይህ ደግሞ ከአላህ ሕግጋት ፍፁም በመራቅ እንጂ ሊከሰት አይችልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹አላህም ከፊላችሁን በከፊላችሁ ላይ በርሱ ያበለጠበትን ጸጋ አትመኙ፤ ለወንዶች ከሰሩት ስራ ዕድል አላቸው፤ ለሴቶችም ከሰሩት ስራ ዕድል አላቸው፤ አላህንም ከችሮታው ለምኑት አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነውና፡፡›› (አል ኒሳእ 32)

በኢስላም ሁለቱም ፆታዎች እራሱን የቻለ ልዩ ተሰጥኦ፣ ኃላፊነትና ክብር አላቸው፡፡ ሁሉም የአላህን ችሮታና ውዴታ ለማግኘት ይጥራል፡፡ ኢስላማዊው ድንጋጌ፣ ለሙስሊም ማህበረሰብ ብሎም ለሰው ዘር በሙሉ እንጂ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ሲባል የተደነገገ አይደለም፡፡

**በኢስላም እይታ መሰረት፣** በሁለቱ ፆታዎች መሐከል ያ ለሽኩቻ ቦታ የለውም፡፡ በዓለማዊ ጥቅም መፎካከር ትርጉም አልባ ነው፡፡ በሴቶች ላይ ማሴር ወይም በወንዶች ላይ ማመጽ የሚባል ነገር ጣዕም ወይም ስሜት አይኖረውም፡ ፡ አንዱ ሌላኛውን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ፣ ድክመቱን ችግሩንና ጉድለቱን ለማጋለጥ የሚካሄድ ሙከራ በኢስላም ቦታ የለውም፡፡

ይህ ሁሉ በአንድ በኩል ስንመለከተው ጫወታ ነው፡ ፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኢስላምንና የሁለቱን ፆታዎች ትክክለኛ የስራ ዘርፍ አላግባብ ከመረዳት የመነጨም ነው፡፡ ሁላቸውም አላህን ከችሮታው ሊለምኑት ይገባል፡፡



## ከወንድ አንጻር ሴቶች ያላቸው ስፍራ

ሴት ለወንድ ከምትሆንለት አንጻር በብዙ ክፍል ትመደባለች፡


### 1 ሴቷ ለወንዱ ሚስት መሆኗ

አንድ ወንድ ሚስቱን በፈለገው መልኩ ማየትና በሷ መርካት ይፈቀድለታል፡፡ ሴትም ከባሏ ጋር እንዲሁው ይፈቀድላታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የመንፈስ ትስስራቸውን፣ የስሜት ውህደታቸውንና የአካል ቅርርባቸውን ሲገልጽ፣ ባልን የሚስት ልብስ ሚስትንም የባል ልብስ በማለት ይገልጻቸዋል፡፡ ‹‹እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው፤ እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ፡፡›› (አል በቀራ 187) (ገጽ፣ 204 ተመልከት)

## 2 የቅርብ ዘመዱ (መሕረም) ከሆነች

ከሴቶች መሕረም የሚባሉት፣ አንድ ወንድ ፈፅሞ ሊያገባቸው የማይችሉ የሆኑ ሴቶች ናቸው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡

| | |
|---|---|
| 1 | ወላጅ እናትና አያት፤ አያትነቱ ቢረዝምም ቢያጥርም አንድ ነው፡፡ |
| 2 | የራሱን ሴት ልጅ፣ የወንድ ልጁ ሴት ልጅ፣ የሴት ልጁ ሴት ልጅ፤ የልጅ ልጅነታቸው ምንም ያክል ቢወርድም እርምነቱ ያው ነው፡፡ |
| 3 | የእናት አባቱ ልጅ እህቱ፣ በአባት የሚገናኙ እህቱ፣ ወይም በእናት የሚገናኙ እህቱ፤ |
| 4 | የአባቱ እህት አክስቱ፤ ለአባቱ እህትነቷ በአባትም በእናትም ቢሆንም በአባት ብቻ ወይም በእናት ብቻም ቢሆንም ልዩነት የለውም፡፡ የአባት አክስትና የእናት አክስትም በዚሁ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ |
| 5 | የእናቱ እህት የሹሜው፤ ለእናቱ እህትነቷ በአባትም ሆነ በእናትም ቢሆን፣ በአባት ወይም በእናት ብቻም ቢሆን ልዩነት የለውም፡፡ የአባት አክስትና የእናት አክስትም በዚሁ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ |
| 6 | የወንድሙ ሴት ልጅ፤ ወንድምነቱ በእናትም በአባትም፣ ወይም በእናት ብቻ፣ ወይም በአባት ብቻ ቢሆንም ልዩነት የለውም፡፡ |
| 7 | የወንድም ወንድ ልጅ ሴት ልጅን ይመስል የልጅነት ሐረጓ ቢወርድም ፍርዱ ያው ነው፡፡ |
| 8 | የሚስቱ እናት፡ ሚስቱ አብራው ብትሆንም ወይም ቢፈታትም እናቷ እስከመጨረሻው መሕረምነቷ ይቆያል፡፡ ልክ እንዲሁ የሚስት እናት እናት ወይም የሚስት አያትም ከዚሁ ትመደባለች፡፡ |
| 9 | ከርሱ የማትወለድ የሚስቱ ሴት ልጅ |
| 10 | የልጅ ሚስት ወደ ታች የሚወለድ ቢሆንም ለምሳሌ እንደ ልጅ ልጅ ሚስት |
| 11 | ወደ ላይ ከፍ ቢልም የአባት ሚስት ወይም ልክ እንደ የልጅ ሚስት በአባት በኩል |
| 12 | የጡት እናቱ፡ የጡት እናት ማለት በሁለቱ የመጀመሪያ የአራስነት ዓመታት ወቅት ውስጥ አምስት ጊዜ ጠግቦ የጠባት ሴት ናት፡፡ እርሱን በማጥባቷ ምክንያት ኢስላም ለርሷ በርሱ ላይ መብት ደንግጎላታል፡፡ |
| 13 | የጡት እህቱ፡ ይህች ደግሞ እርሱን ያጠባችው ሴት ልጅ ናት፡፡ በዚሁ መልክ፣የጡት አክስት የጡት ወንድም ልጅ የጡት እህት ልጅና የመሳሰሉት ሁሉም የጡት ዘመዶች ልክ የደም ትስስር እንዳላቸው ዘመዶች እርም ይሆናሉ፡፡ |




በእነዚህ ክልክል በሆኑ ወንዶች ፊት እንደ ባህሉ መሠረት መውጣት ይችላሉ። ነገር ግን ድንበሩን ማለፍ የለበትም እጅች፣ ትከሻ፣ፀጉር፣ የመሳሰሉት ግልፅ መሆን ይችላሉ።

ቤተሰብህ

## 3 ሴቷ ለርሱ ባዕድ ከሆነች

ባዕድ ሴት የምትባለው ከተጠቀሱት መሐሪሞች ውጭ ያለች ሴት ሁሉ ነች፡፡ ከርሱ ጋር ዝምድና ያላቸው ቢሆኑም፣ እንደ አጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ የወንድሙ ሚስት፣ ወይም ከርሱ ጋር ዝምድና የሌላቸው ቢሆንም ከርሱ ጋር የሚያስተሳስራቸው የዘር ሐረግ ወይም የአማችነት ትስስር ባይኖርም በኢስላም እይታ አጅነቢ ወይም ባዕድ ናቸው፡፡

በእርግጥ ኢስላም አንድ ሙስሊም ከባዕድ ሴት ጋር ሊኖረው የሚገባን ግንኙነት ሥርዓትና መመሪያ አድርጎለታል፡፡ ይህ ደግሞ ክብርን የሚጠብቅና የሰይጣን በሮችን የሚዘጋ ነው፡፡ የሰው ልጅን የፈጠረው አላህ(ሱ.ወ)፣ ለርሱ የሚበጀውን ከማንም በላይ ያውቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲኾን (ሚስጥርን ሁሉ) አያውቅምን?» (አል ሙልክ 14)

በየዕለቱ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከእምነት አስተምህሮ በራቁ ቤተሰቦችና ማህበረሰብ ውስጥ የአስገድዶ መድፈርና ፀያፍ የወንጀል ስራዎች በሰፊው ተስፋፍተዋል፡፡

## በወንድና በባዕድ ሴት መካከል የሚኖር ግንኙነት ስርዓት

### 1 ዓይንን መስበር

አንድ ሙስሊም የሌላ ሰውን ሀፍረተ ገላ ማየት አይፈቀድለትም፡፡ የፍትወት ስሜቱን የሚቀሰቅሱ ነገሮችንም መመልከትም የተከለከለ ነው፡፡ ያለ ጉዳይ አንዲትን ሴት አተኩሮ ማየት የለበትም፡፡

አላህ ሱ.ወ) ሁለቱንም ጾታዎች ዓይናቸውን ሰበር እንዲያደርጉ አዟቸዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ የጥብቅነትና የጨዋነት ጎዳና በመሆኑ ነው፡፡ ዓይንን ያለ ገደብ እንደፈለጉ መልቀቅ የዝሙትና የወንጀል መንገድ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ለምዕመናን ንገራቸው ዓይኖቻቸውን ያልተፈቀደን ከማየት ይከልክሉ፤ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ ይህ ለነሱ የተሻለ ነው፤ አላህ በሚሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡ ለምእመናትም ንገራቸው ዓይኖቻቸውን ይከልክሉ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ፡፡» (አል ኑር 30-31)

በድንገት የተከለከለን ነገር ለማየት የተጋለጠ ሰው ወዲያው ከዚያ እይታ ዓይኑን ሰበር ማድረግ አለበት፡፡ ዓይንን መስበር በተለያዩ መገናኛ ብዙሃንና በኢንተርኔት ከሚሰራጩ የተከለከሉ ነገሮችንም ያካትታል፤ የፍትወት ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ ነገሮችን መመልከት ክልክል ነው፡፡

### 2 በስርዓትና በመልካም ስነምግባር አብሮ መኖር

ስርዓትን በጠበቀና መልካም ስነ ምግባርን በተላበሰ መልክ፣ ከማንኛውም ስሜት ቀስቃሽ ነገሮች ርቀው አንዲት ባዕድ ሴትን ቢያናግር፣ እሷም ብታናግረው፣ ማሕበራዊ ሕይወታቸውን ቢመሩ አይከለከልም፡፡



> ኢስላም በሴቶችና በወንዶች መካከል የሚኖርን ግንኙነት ስርዓት የሚያሲዝ ደንብና መመሪያ አስቀምጧል፡፡



> አላህ ከከለከላቸው ነገሮች ዓይንን ሰበር ማድረግ ጨዋነትንና ክብርን ማስጠበቂያ መንገድ ነው፡፡

- አላህ(ሰ.ወ) ሴቶች ባዕድ ወንዶችን ሲያናግሩ ድምፃቸውን እንዳያስለመልሙ ከልክሏል፡፡ ግልጽ የሆነ ንግግርን እንዲናገሩም አዟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- ‹‹ያ በልቡ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል በንግግር አትለስልሱም መልካምንም ንግግር ተናገሩ፡፡›› (አል አሕዛብ 32)
- ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ አረማመዶች፣ እንቅስቃሴዎችና ከጌጦችም ከፊሎቹን ግልጽ ማድረግ የተከለከሉ ናቸው፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) ሴቶችን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ከጌጦቻቸው የሚሸፍኑት ይታወቅ ዘንድ በእግሮቻቸው አይምቱ፡፡›› (አል ኑር 31)

### 3 የኸልዋ (ለብቻ መነጠል) እርምነት

ኸልዋ ማለት አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ማንም በማያያቸው ስፍራ ላይ ለብቻቸው መገኘት ሲሆን ይህንን ኢስላም እርም አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም፣ ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ፣ ዝሙትና ፀያፍ ተግባራት እንዲፈፀሙ የሚያደርግበት የሸይጣን መግቢያ በር በመሆኑ ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አድምጡ! ከእይታ በራቀ ቦታ ላይ አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር አይነጠልም ሦስተኛቸው ሰይጣን ቢሆን እንጂ፡፡›› (አል ቲርሚዚ 2165)

### 4 አል ሒጃብ (የሴቶች ኢስላማዊ አለባበስ)

አላህ (ሱ.ወ) በሴቶች ላይ ሂጃብን ግዳጅ ያደረገው ማራኪ ውበትና አታላይ ተክለ ሰውነት ያላበሳቸው በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ተፈጥሯቸው ደግሞ ለወንዶች ፈታኝነቱ፣ ወንዶች ለሴቶች ካላቸው ተፈጥሯዊ ፈታኝ ገጽታ በእጅጉ የላቀ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ሂጃብን የደነገገው ለብዙ ዓላማ ነው፡

- ሴት የተፈጠረችለትን ዓላማና የተጣለባትን ማህበረሰባዊ ኃላፊነት፣ በዕውቀትም በተግባርም በብቃትና በጥራት እንድትወጣ እንዲሁም ክብሯንና ጨዋነቷን ጠብቃ እንድትኖር ለማድረግ ነው፡፡
- የዋልጌነትና የጋጠወጥነት መንስኤዎችን በመቀነስና በማዳከም በአንድ በኩል የማህበረሰቡን ጽዱዕነት በሌላም በኩል የሴትን ክብር ለማስጠበቅ ነው፡፡
- ወደሴቶች ለሚመለከቱ ወንዶች በጥብቅነትና ስሜትን በመቆጣጠር ላይ ማገዝ፤ ይኸውም እንደማገኛውም የእድገትና የልማት አጋር ከሴቶች ጋር እንዲረዳዱና እንዲተጋገዙ ያደርጋል፡፡ የቅጽበታዊ ስሜት ማርኪያ የፍቶት ስሜት ቀስቃሽ ብቻ አድርገው እንዳይመለከቷት ለማድረግ ያስችላል፡፡

## የሂጃብ ይዘት

አላህ (ሱ.ወ) ሴት ልጅ በባዕድ ወንዶች ፊት ከፊቷና ከመዳፎቿ በስተቀር ሰውነቷን በሙሉ እንድትሸፍን ግዴታ አድርጓል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡ - ‹‹ጌጣቸውንም ከርሷ ግልጽ የኾነውን በስተቀር አይግለጡ፡፡›› (አል ኑር 31)

ግለጽ የኾነ የሚባለው ፊትና መዳፍን ነው፤ እሱም ቢሆን፣ ፊትና መዳፍን በመገለጥ የሚከሰት ፈተና ወይም ችግር ካለ መሸፈናቸው ግድ ይሆናል፡፡

## የሒጃብ ስርዓተ ደንብ

አንዲት ሴት የሚከተሉትን ቅድመ መስፈርቶች በጠበቀ መልክ የፈለገችውን ዓይነት መልክና ይዘት ያለው ሒጃብ ወይም ልብስ መልበስ ይፈቀድላታል፡፡

1. ሒጃቡ የግድ መሸፈን ያለበትን የሰውነት ክፍል በጠቅላላ የሚሸፍን መሆን አለበት
2. ሰፊ መሆን አለበት፤ የሚያጣብቅ፣ ጠባብ፣ የሰውነትን ቅርጽ የሚያወጣና የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡
3. ወፍራም መሆን አለበት፡፡ ስስነቱ በስሩ ያለን የሰውነት ክፍል የሚያጋልጥና የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡



> ሒጃብ ሴት ልጅን በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖራት የሚገባውን ሚና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከሚታወቁት ስርዓቶች ሁሉ በጥራትና በብቃት እንድትወጣ አመቻችቷታል፡፡

# > ጋብቻ በኢስላም

ጋብቻ ኢስላም ልዩ ትኩረት ከቸራቸውና ካበረታታቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ የነብያት ፈለግም ነው፡፡ (ገጽ፣ 196 ተመልከት)

ኢስላም ለጋብቻ ዝርዝር ድንጋጌና ስርዓትን በመዘርጋት ትኩረት ሰጥቶታል፡፡ የባለ ትዳሮች መብት መከበር የጋብቻው ግንኙነት እንዲጎለብትና እንዲረጋ ያደርጋል፡፡ በመንፈስ የተረጋጋ፣ በእምነቱ የጸና፣ በሁሉም የማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ የመጠቀ፣ ሕፃናት በውስጡ የሚያድጉበት የሆነን ስኬታማ ቤተሰብ ለመመስረት ያስችላል፡፡



> ጋብቻ ኢስላም ልዩ ትኩረት ከቸራቸው ማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ ነው

### ከነኚህ ኢስላማዊ ድንጋጌዎች መካከል፡

ኢስላም ለአንድ ጋብቻ ትክክለኛነት በባልም ሆነ በሚስት በኩል የግድ ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶችን አስቀምጧል፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

## ኢስላም ለሚስትነት ያስቀመጣቸው መስፈርቶች፡

1 **ሙስሊም፣ ወይም የመጽሐፍት ባለቤት ማለትም አይሁድ ወይም ክርስቲያን መሆን አለባት፡፡** ይሁን እንጂ ኢስላም ከሙስሊሟም ቢሆን በሃይማኖቷ ጠንካራዋን እንድንመርጥ ይመክራል፡፡ ምክንያቱም ወደፊት ለልጆችህ እናትና ተንከባካቢ፣ ለአንተ ደግሞ በመልካም ነገር ላይ የምታግዝህና የምታጸናህ እሷ በመሆኗ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ባለ ሃይማኖቷን ምረጥ አለያ እጅህ አመድ አፋሽ ትሆናለች» (አል ቡኻሪ 4802 / ሙስሊም 1466)

2 **ጥብቅና ጨዋ መሆን አለባት፡፡** በዝሙትና በእንዝላልነት የምትታወቅ ሴትን ማግባት ክልክል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ከምእመናት ጥብቆቹም ከነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም (ተፈቀዱላችሁ)» (አል ማኢዳ 5)

3 **ለዘላለሙ ሊያገባቸው እርም ከተደረጉ መሐሪሞቹ መካከል መሆን የለባትም፡፡** የዚህን ዝርዝር ማብራሪያ ከዚህ በፊት አሳልፈናል፡፡ በጋብቻው አንዲት ሴትን ከእህቷ ወይም ከአክስቶቿ ማለትም ከአባቷ እህት ወይም ከእናቷ እህት ጋር በአንድ ላይ ማግባት አይፈቀድለትም፡፡ (ገጽ፣ 200 ተመልከት)

## ኢስላም ለባልነት ያስቀመጣቸው መስፈርቶች፡

ባል ሙስሊም መሆን አለበት፡፡ በኢስላም፣ ሙስሊም ሴትን ሃይማኖቱ የመጽሐፍ ተከታይ (አህለል ኪታብ) ወይም መጽሐፍ የለሽ ቢሆንም ለካሃዲ መዳር የተከለከለ ነው፡፡ ኢስላም አንድን ወንድ በባልነት ለመቀበል ወንዱ ሁለት ባህሪዎችን የተላበሰ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

- በሃይማኖቱ ጽኑ መሆኑና
- መልካም ስነ ምግባር የተላበሰ በሆኑ ናቸው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሃይማኖቱንና ስነምግባሩን የምትወዱለት ልጃችሁን ከጠያቃችሁ አጋቡት፡፡» (አል ቲርሚዚ 1084 / ኢብኑ ማጃህ 1967)

# > የባልና የሚስት መብቶች

አላህ (ሱ.ወ) በባልም በሚስትም ላይ ሊጠብቁት የሚገባ የሆነ መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም የጋብቻን ሕይወት የሚያሳምሩና የሚጠብቁ ነገሮችን በሙሉ እንዲፈፅሙ አነሳስቷል፡፡ እነኚህን ጉዳዮች የመጠበቅ ኃላፊነት በሁለቱም ወገን ላይ የተጣለ ነው፡፡ ባልም ሆነ ሚስት አንዳቸው ከሌላኛው የማይቻልን ነገር እንዲፈፅም መጠየቅ የለባቸውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ለነርሱም (ለሴቶች) የዚያ በነርሱ ላይ ያለባቸው (ግዳጅ) ብጤ በመልካም አኗኗር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው፡፡» (አል በቀራ 228)

የሕይወት ጉዞ ቀጣይነት እንዲኖረው እና የተከበረው ቤተሰብ እንዲጸና ነገርን ማግራራትና ጉድለትን ማለፍ እንዲሁም መለገስ ያስፈልጋል፡፡



> አንድ ሰው በአካባቢው ተለምዶ መሰረት የባለቤቱንና የልጆቹን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

## የሚስት መብቶች

### 1 ቀለብና መጠለያ

- ሚስት ባለ ሃብት ብትሆንም እንኳ፣ ባል ለሚስቱ የምግቧን፣ የመጠጧን፣ የልብሷንና የአስፈላጊ ጉዳዮች ወጪዋን የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም ለሰረሷ ተመጣጣኝ የሆነን መኖሪያ ወይም ማረፊያም ሊያዘጋጅላት ይገባል፡፡
- የወጪ መጠን፡ ወጪ የሚለካው እንደ ባለየው የገቢ መጠንና እንደየ አገሩ የአኗኗር ዘይቤ ሲሆን፣ ማባከንም ሆነ መጨናነቅ የሌለበት ሊሆን ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ፤ በርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበት ሰው፣ አላህ ነፍስን የሰጣትን እንጅ አያስገድዳትም፡፡» (አል ጠላቅ 7)
- ይህን ወጪ ሲሸፍን መመጻደቅ፣ እንዲሁም በመጨናነቅ እሷንም ሆነ እራሱን ማዋረድ የለበትም፡፡ ገንዘብ ሲያወጣ፣ አላህ (ሱ.ወ) በገለጸው መልኩ በመልካም እሳቤ ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሚስት በባሏ ላይ ያላት መብት እንጂ እርሱ በቸርነቱ የለገሳት አይደለም፤ እናም መብቷን በአግባቡ ሊጠብቅላትና ሊሰጣት ይገባል፡፡
- በኢስላም፣ በሚስትና በቤተሰብ ላይ የሚወጣ ወጪ ከባድ ምንዳን ያጎናጽፋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሙስሊም ከአላህ እመነዳበታለሁ በሚል እሳቤ በሚስቱ ላይ ወጪ ሲያወጣ ለርሱ ምጽዋት ይሆንለታል፡፡» (አል ቡኻሪ 5036 / ሙስሊም 1002)

በሌላም ዘገባ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በርሷ ብትመነዳባት እንጂ አንተ የአላህን ፊት ከጃይ ሆነህ አንድም ወጪን አታወጣም፤ በሚስት አፍ ውስጥ የምታስቀምጣት ጉርሻ እንኳን ብትሆን፡፡» (አል ቡኻሪ 56 /ሙስሊም 1628)

ወጪ አልሰጥም ያለ ሰው፣ ወይም እየቻለ ማውጣት ካለበት የቀነሰ ሰው፣ በርግጥ ከባድ ወንጀል ውስጥ ተዘፍቋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ለአንድ ሰው ወንጀለኛነት፣ የሚያስተዳድረውን ሰው ማንገላታቱ ይበቃዋል፡፡» (አቡ ዳውድ 1692)

### 2 መልካም አኗኗር ወይም ግንኙነት

መልካም አኗኗር በሚለው የተፈለገው መልዕክት መልካም ስነ ምግባር የሚለው ነው፡፡ ልበ ለስላሳነት፤ ለብ ያለ ንግግርን መናገር፤ አንድም የሰው ልጅ ሊርቃቸው የማይችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን ችሎ ማለፍና የመሳሰሉትን ነው፡፡ አላህ ሱ.ወ እንዲህ ብሏል፡- «በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፤ ብትጠሉዋቸውም (ታገሱ)፤ አንዳችን ነገር ልትጠሉ፣ አላህም በርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይቻላልና፡፡» (አል ኒሳእ 19)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከሙእሚኖች መካከል የተሟላው ሙእሚን በስነ ምግባሩ በላጭ የሆነው ነው፤ በላጮቻችሁ ለሚስቶቻቸው በስነ ምግባራቸው ጥሩዎቹ ናቸው፡፡» (አል ቲርሚዚ 1162)

ቤተሰብ

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህም ብለዋል፡- «ከሙእሚኖች መካከል የተሟላው ሙእሚን በስነ ምግባሩ ጥሯቸውና ለሚስቱ ገራገር የሆነው ነው፡፡»

(አል ቲርሙዚ 2612 / አህመድ 24677)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በላጫችሁ ለቤተቡ ጥሩዋችሁ ነው፤ እኔ ለቤተሰቤ ጥሩዋችሁ ነኝ፡፡» (አል ቲርሚዚ 3895)

አንድ ሡሐቢይ፣ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ የአንዳችን ሚስት በሱ ላይ ያላት መብት ምንድን ነው?» በማለት ጠየቃቸው፤ እሳቸውም፡ «ስትበላ ልታበላት፤ ስትለብስም ልታለብሳት፤ ፊቷን ላትመታት፤ ላታዋርዳት፤ በቤትህ ውስጥ እንጂ ላታኮርፋት ነው፡፡» አሉት፡፡ (አቡ ዳውድ 2142)

3 መቻቻል

የሴቶች ተፈጥሯዊ ባህሪ ከወንዶች ጋር ይለያያል፤ በመሆኑም ይህን የሚለዩባቸውን ባህሪያት ወንዱ ሊላመደውና አቅልሎ ሊመለከተው ይገባል፡ ፡ የጋብቻን ሕይወት ከብዙ አቅጣጫ ለማየት ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ማንም ከስህተት ነፃ አይደለም፤ እናም ስህተት ሲከሰት ትዕግስት ማድረግና ከስህተቱ ባሻገር ያሉትን መልካም ጎኖች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፣ ባልንም ሚስትንም፣ አንዱ የሌላኛውን መልካም ወይም ጠንካራ ጎን እንዲመለከቱ ያሳስባል፡፡ እንዲህ ይላል፡- «በመካከላችሁም ችሮታን አትርሱ፡፡» (አል በቀራ 237)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሙእሚን አንዲትን ሙእሚን አይጥላት፤ አንድ ባህሪዋን ቢጠላባት ሌላ ባህሪዋን ይወዳልና፡፡» (ሙስሊም 1469)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ለሴቶች ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸውና ወንዶች በመልካም እንዲኗኗሯቸው አሳስበዋል፡፡ አያይዘውም የሴቶች መንፈሳዊና ስጋዊ ባህሪያቸው ከወንዶች ጋር እንደሚለያይ ተናግረዋል፡፡ ይህ የባህሪ ልዩነት ለአንድ ቤተሰብ መደጋገፊያና ውበት መሆኑንም አስተምረዋል፡፡ እናም ይህ የባህሪ ልዩነት የመለያየትና የፍቺ መንስኤ ሊሆን አይገባም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሴት የተፈጠረችው ከጎን አጥንት ነው፤ በምንም ጉዳይ ላይ ላንተ አትስተካከልልህም፤ በሷ ልትጠቀም ከፈለግህ ከነጉብጠቷ ልትጠቀምባት ትችላለህ፤ ለማቃናት ከሞከርክ ግን ትሰብራታለህ፤ ስብራቷም መፈታቷ ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 3153 / ሙስሊም 1468)



> ባል በጋብቻ ውል ላይ የተጠቀሱ ቅድመ መስፈርቶችን የመጠበቅና የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡

## 4 አብሮ ማደር ወይም መተኛት

አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር ግብረ ስጋ መተኛት አለበት፡፡ ቢያንስ በአራት ቀናት አንዴ ይህንን ሊፈፅም ይገባል፡፡ ከአንድ በላይ ያገባ ከሆነም የሳምንቱ ቀናቶችን በእኩልነት በሚስቶቹ መካከል ሊከፋፍል ይገባል፡፡

## 5 ክብርህና ሞገስህ ስለሆነች ልትከላከላት ይገባል፡፡

አንድ ሰው ሲያገባ፣ ያገባት ሴት የእርሱ ክብሩ ነች፡፡ ስለሆነም ለሞት የሚዳርገው ቢሆንም እንኳን ይህን ክብሩን ሊከላከልና ሊሚገትለት ይገባል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ስለ ሚስቱ የተገደለ ሰው ሰማዕት ነው፡፡» (አል ቲርሚዚ 1421/ አቡ ዳውድ 4772)

## 6 የሚስትን ሚስጥር አለማባከን

አንድ ሙስሊም፣ የሚስቱን ልዩ ባህሪያትና፣ በርሱና በርሷ መካከል ስለ ተፈፀመ የአልጋ ላይ ሚስጥር ለሰዎች ሊያወራ አይፈቀድለትም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «የትንሳኤ ቀን ከሰዎች ሁሉ ከደረጃ በኩል የከፋ ሰው ማለት፣ እርሱ ለሚስቱ ተገላልጦ፣ ሚስቱም ለርሱ ከተገላለጠች በኋላ የሷን ሚስጥር አውጥቶ የሚበትን ሰው ነው፡፡» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 1437)

## 7 በሴት ላይ ድንበር ማለፍ አይፈቀድም

ኢስላም ለሚፈጠሩ ችግሮች በርካታ መፍትሄዎችን አስቀምጧል፡፡ ከነዚህም መካከል፡

- ስህተቶች በመወያየት፣ በመመካከርና በተግሳጽ ሊታረሙ ይገባል፡፡
- ከሦስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ አለማናገር ወይም ማኩረፍ ከዚያም ከቤት ሳይወጣ በመኝታና በግብረ ስጋ ግንኙነት ማኩረፍ ይፈቀድለታል፡፡

- እመት ዓኢሻ እንዲህ ብለዋል፡- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአላህ መንገድ ላይ ሲዋጉ ካልሆነ በስተቀር አንዲትንም ሴት ሆነ ባሪያ መራቅ አያውቁም፡፡

## 8 ማስተማርና መምከር

ሰውየው ሚስቱን በመልካም ሊያዛትና ከመጥፎ ሊከለክላት ይገባል፡፡ ወደ ጀነት ጸጋ የሚያዳርሳቸውን፣ ከእሳት ቅጣት የሚያርቃቸውን ነገሮች በማመቻቸትና በሱም ላይ በማበረታታት፣ እንዲሁም እርም ነገሮችን በመከልከልና እንዲጠሉ በማድረግ ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሚስትም ባሏን በመምከር፣ ወደ መልካም ነገር በመገፋፋትና በመጠቆም፣ ልጆችን በጥሩ ስነ ምግባር ኮትኩቶ በማሳደግ ላይ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን ከእሳት ጠብቁ፡፡» (አል ተህሪም 6)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሰውየው በሚስቱ ላይ ጠባቂ ነው፣ ስለጠበቀው ነገር ይጠየቃል፡፡» (አል ቡኻሪ 2416 /ሙስሊም 1829)

## 9 ሚስቱ ያስገባችውን ቃል መጠበቅ

ጋብቻው በሚፈፀምበት ጊዜ፣ ሚስት ለምሳሌ፣ ይዘቱ ለየት ያለ ቤትን ሊገዛላት ወይም ሊሰራላት ዓይነት የተፈቀዱ ነገሮችን እንዲፈፅምላት ቃል ካስገባችው፣ ቃሉን የመጠበቅና የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡ ምክንያቱም የጋብቻ ውል ከቃልኪዳኖች ሁሉ ትልቁና ከባዱ በመሆኑ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከመስፈርቶች ሁሉ እጅግ በርሱ ልትሞሉ የሚገባው ብልትን የተፈቀደ ያደረጋችሁበት ቃል ኪዳን ወይም መስፈርት ነው፡፡» (አል ቡኻሪ 4856 / ሙስሊም 1418)



## የባል መብቶች

### 1 በመልካም ነገር ላይ እሱን የመታዘዝ ግዴታ አለባት

አላህ (ሱ.ወ) ወንድን በሴት ላይ የበላይ አስተዳዳሪ አድርጎታል፡፡ ይኸውም ልክ የአገር መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ለሕዝብ እንደሚያገለግሉት፣ ጉዳይዋን የሚያስፈፅምላት፣ መስመር የሚያስይዝላትና የሚከታተልላት እሱ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው አላህ (ሱ.ወ) ለወንድ ልዩ መገላጫዎችን የሰጠው በመሆኑና በንብረት የማስተዳደር ኃላፊነት በሱ ላይ የተጣለ በመሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፤ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘባቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡» (አል ኒሳእ 34)

### 2 ባሏ እንዲረካባት መዘገጃጀት ወይም መመቻቸት

ባል በሚስቱ ላይ ካለው መብቶች አንዱ፣ እርሱ ግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈፅም እራሷን ማመቻቸትና እንዲረካባት ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ሆን ብላ ለርሱ መቆነጃጀትና መዘገጃጀት ይወደድላታል፡፡ የወር አበባ ደም ላይ መሆን፣ ወይም የግዳጅ ጾም ላይ መሆን፣ ወይም በህመምና በመሳሰሉት ሸሪዓዊ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር፣ ሚስት ባሏ ሊገናኛት እየፈለገ ወይም ሲጠራት ፈቃደኛ ካልሆነች እጅግ በጣም ትወገዛለች፤ ከባድ ወንጀልንም ትሸከማለች፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው ሚስቱን ወደ ፍራሹ ሲጠራት እንቢተኛ ከሆነችና ተቆጥቶባት ወይም ተከፍቶባት ካደረች እስኪነጋ ድረስ መላእክት ይረግሟታል፡፡» (አል ቡኻሪ 3065 /ሙስሊም 1436)

### 3 ባል ወደቤቱ እንዲገቡ የማይፈልጋቸውን ሰዎች እንዲገቡ አለመፍቀድ

ባል በሚስቱ ላይ ካለው መብቶች መካከል ሚስት እርሱ ከሚጠላቸው ሰዎች አንዱንም አለማስገባት ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዲት ሴት በርሱ ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር ባሏ እያለ ልትጾም አይፈቀድላትም፤ በሱ ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር በቤቱ ውስጥ ሰው እንዲገባ መፍቀድ የለባትም፡፡» (አል ቡኻሪ 4899)

### 4 በባል ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ከቤት አለመውጣት

ባል በሚስት ላይ ካሉት መብቶች አንዱ ያለርሱ ፍቃድ ከቤት አለመውጣት ነው፡፡ ልዩ ቦታ ለመሄድ መውጣቷም ይሁን ለስራ ጉዳይ መውጣቷ ሁለቱም አንድ ነው፡፡ ያለ ባል ፈቃድ አይሆንም፡፡

### 5 ሚስት ባሏን መንከባከብ

ሚስት ባሏን በሀገሬው ተለምዶ መሰረት ምግብ በማዘጋጀትና መሰል በሆኑ በቤት ውስጥ ጉዳዮች ልትንከባከበው ይገባል፡፡



# > ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት

በኢስላም የጋብቻ መሰረት የሚጠነሰሰው አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ጋር የሚዋደዱ፣ የሚተሳሰቡና የሚደጋገፉ ኾነው በሚመሰርቱት ቤተሰብ ነው፡፡ ከመሆኑም ጋር፣ ኢስላም ለወንዱ ከአንድ በላይ ሚስት እንዲያገባ ፈቅዶለታል፡፡ ይህ ደግሞ በቀደምት መለኮታዊ ድንጋጌዎችም ጭምር ሲሰራበት የነበረ ነው፡፡ ይህንን የፈቀደበት ዓላማ የግለሰቦችንና የማሕበረሰቡን ጥቅም ለመጠበቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን ስርዓት የለሽና ደንብ አልባ አድርጎ አልተወውም፡፡ እንደውም ሴቶች እንዳይበደሉና እንዳይገፉ የሚያደርጉ መብታቸውን የሚያስከብሩ የሆኑ ቅድመ መስፈርቶችንና በደልን ከልካይ ነጥቦችን አስቀምጧል፡፡

## 1 ፍትሃዊነት

በቤት ወጪ፣ በመኖሪያ ቤትና በመሳሰሉት ግልጽ በሆኑ ቁሳዊ ጉዳዮች በሚስቶች መካከል ፍትሃዊ መሆን ግዴታ ነው፡፡ በመካከላቸው ፍትሃዊ መሆን የማይችል ከአንድ በላይ ማግባት በርሱ እርም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «አለማስተካከልንም ብትፈሩ አንዲትን ብቻ...ያዙ» (አል ኒሳእ 3)

ፍትሃዊ አለመሆን እጅግ በጣም አደገኛና አስከፊ ወንጀል ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሁለት ሚስቶች ኖረውት ወደ አንደኛዋ ያዘነበለ ሰው የትንሳኤ ቀን በአንድ ጎኑ ተጣሞ ይቀሰቀሳል፡፡» (አቡ ዳውድ 2133)
የማይቻል ጉዳይ ነውና በልባዊ ፍቅር ፍትሃዊ መሆን ግዴታ አይደለም፡፡ በሚከተለው አንቀጽ ላይ የተጠቀሰውም ይኸው ነው፡፡ «በሴቶችም መካከል ምንም እንኳ ብትጓጉ (በፍቅር) ለማስተካከል አትችሉም፡፡» (አል ኒሳእ 129)

## 2 የሚስቶችን ወጪ መሸፈን መቻል

የሚስቶቹን ጠቅላላ ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያውን ጋብቻ ሲፈፅም ይህ ጉዳይ የጋብቻ መስፈርት እንደሆነው ሁሉ በሁለተኛው ላይ ደግሞ የበለጠ ወሳኝ የሆነ መስፈርት ይሆናል፡፡

## 3 ከአራት ሚስቶች በላይ አለመጨመር

በኢስላም ከአንድ በላይ የማግባት ገደቡ ይህ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ለናንተ ከሴቶች የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ፡፡» (አል ኒሳእ 3)

ከአራት በላይ ሚስቶች ኖረውት ኢስላምን የተቀበለ ሰው፣ ከነርሱ መካከል አራቱን ብቻ መርጦ በማስቀረት ሌሎቹን ሊፈታ ይገባል፡፡

## 4 ቤተሰባዊ ግንኙነትን ለመጠበቅና ዝምድናን ላለማበላሸት አንዳንድ ሴቶችን በአንድነት በአንድ ጊዜ ማግባትም አይፈቀድም፡፡

- አንዲትን ሴት፣ ከእህቷ ጋር በአንድ ወቅት ማግባት አይፈቀድም፡፡
- አንዲትን ሴት፣ ከእናቷ እህት ከየሹሜዋ ጋር በአንድ ወቅት ማግባት አይፈቀድም፡፡
- አንዲትን ሴት፣ ከአባቷ እህት፣ ከአክስቷ ጋር በአንድ ወቅት ማግባት አይፈቀድም፡፡



> ኢስላም ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን አስመልክቶ ሕግጋትና ቅድመ -ዝግጅቶች አስቀምጧል።

ቤተሰብህ

## > ፍቺ

> ኢስላም የባልና የሚስት ግንኙነት ቀጣይነት ያለው መሆን እንዳለበት ያስተምራል፡፡ ለጉዳዩም ትኩረት ይሰጣል፡፡ ግና የግድ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ፍቺንም ይፈቅዳል፡፡




ኢስላም የጋብቻ ውል ዘላቂና ዘውታሪ መሆን እንዳለበት ይመክራል፡፡ ጋብቻው ሁለቱም ወገኖች ሞት እስኪለያያቸው ድረስ የሚቆይ መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ጋብቻን የጠበቀ ውል ሲል ጠርቶታል፡፡ በኢስላም፣ ጋብቻን ለተወሰነ የጊዜ ገደብ በሚል መፈፀም ጨርሶ አይፈቀድም፡፡

ኢስላም በጋብቻ ላይ ሰዎችን ሲያበረታታ ድንጋጌው የወጣው በምድር ላይ ለሚኖር ሰብዓዊ ፍጡራን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እነርሱ ደግሞ የራሳቸው የሆነ ልዩ መገለጫ ባህሪያትና ስጋዊ ፍላጎቶች አሏቸው፡፡ በመሆኑም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና መንገዶች ሁሉ ሲዘጋጉ፣ የማስተካከያና የማሻሻያ ዘዴዎች ሁሉ ፍሬ አልባ ሲሆኑ፣ ከዚህ ውል እራሳቸውን እንዴት ነፃ ሊያደርጉ ወይም ሊያላቅቁ እንደሚችሉ ስርዓትን ደንግጎላቸዋል፡፡ በዚህም ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ፍትሃዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚበጃቸውን መስመር ይዘረጋል፡፡ ብዙ ጊዜ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ፍቺን ብቸኛ የችግራቸው መፍትሄ የሚያደርጉበት አጋጣሚ አለ፡፡ በቤተሰቡም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር የሚያደርግበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ምክንያቱም በባልና ሚስት መሐከል የተመሰረተው ትዳር የተፈለገበትን ግብ ሊመታ ባለመቻሉ አብረው ከመቆየታቸው ይልቅ ፍቺ የተሻለ ይሆናል፡፡

ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ለመውጣት ሲባል ፍቺ የተፈቀደው ለዚህ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው ሌላ የትዳር አጋር መቀየር አለባቸው፡፡ ምናልባት ሁላቸውም ከመጀመሪያው የትዳር አጋራቸው ያጡትን ከዚህኛው ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ቢለያዩም አላህ ሁሉንም በችሮታው ያብቃቃቸዋል፡፡ አላህም ችሮታው ሰፊ ጥበበኛ ነው፡፡» (አል ኒሳእ 130)

### ፍቺ እራሱን የቻለ ስርዓት አለው፡

- ፍቺ በወንዱ እጅ እንጂ በሴቷ እጅ አይደለም፡፡
- አንዲት ሴት ከባሏ ጋር መኖር ካልቻለች፣ እሱ ደግሞ ሊፈታት ፍቃደኛ ካልሆነ፣ ዳኛ ዘንድ በመሄድ እራሷን ማስፈታት ትችላለች፡፡ ዳኛውም ያቀረበችው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ሊያፋታት ይገባል፡፡
- አንዲት ሴት ከተፈታች በኋላ፣ ሁለት ጊዜ መመለስ ትችላለች፡፡ ነገር ግን ለሦስተኛ ጊዜ ከፈታት ሌላ ትክክለኛ ጋብቻ ፈፅማ እስካልተፈታች ድረስ ወደ መጀመሪያው ትዳሯ መመለስ አትችልም፡፡

## > የወላጆች መብት

ለወላጆች በጎ መዋል ከመልካም ስራዎች መካከል ከባዱና አላህ ዘንድ ብዙ ምንዳን ከሚያስገኙ ተግባሮች ሲሆን፣ አላህ (ሱ.ወ) እርሱን ከመገዛትና በአሃዳዊነቱ ከማመን ጋር አቆራኝቶታል፡፡

ለነርሱ በጎ መዋልና ጥሩ መሆን ጀነት ለመግባት የሚያስችል ወሳኝ ምክንያት አድርጎታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ - ‹‹ወላጅ የጀነት የመሐለኛው በር ነው፤ ይህን በር ብትፈልግ ቸል በለው ወይንም ጠብቀው፡፡ ›› (አል ቲርሚዚ 1900)



### ❈ በወላጆች ላይ የማመፅና ለነርሱ ክፉ የመሆን አደገኝነት

መለኮታዊ መመሪያዎች በሙሉ በአደገኝነቱና በከባድ ወንጀልነቱ የተስማሙበትና ከርሱም ያስጠነቀቁት ነገር ቢኖር ለወላጆች ክፉ መሆን ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሠሓቦቻቸው፡ ‹‹አይከብዱ የከበዱ ወንጀሎችን አልነግራችሁምን?›› አሉ፡፡ ሠሐቦችም፡ ‹‹እንዴታ ይንገሩን እንጂ አንቱ የአላህ መልክተኛ›› አሉ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ)፡ ‹‹በአላህ ማጋራትና በወላጆች ላይ ማመፅ ናቸው፡፡›› አሉ፡፡ (አል ቡኻሪ 5918)

### ❈ በአላህ ላይ ከማመፅ ውጭ ባለ ጉዳይ እነርሱን መታዘዝ

አላህ(ሰ.ወ) ላይ በማመፅ ወይም የአላህን ሕግ በመጣስ እስካላዘዙ ድረስ ወላጆች በሚያዙት ነገር ሁሉ ለነርሱ ፍጹም ታዛዥ መሆን ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም በፈጣሪ ላይ እያመፁ ለፍጡራን መታዘዝ አይፈቀድም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ሰውንም በወላጆቹ መልካም አድራጎትን አዘዝነው፤ ላንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን (ጣዖት) በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህ አትታዘዛቸው፡፡›› (አል አንከቡት 8)

### ❈ ለነርሱ በጎ መዋል በተለይም ሲሸመግሉ

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፤ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ በወላጆቻችሁም መልካምን ስሩ፤ በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፤ አትገላምጣቸውም፤ ለነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው፡፡›› (አል ኢስራእ 23)
አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅ ለወላጆቹ በተለይም ከሸመገሉና ከደከሙ በኋላ ታዛዥ እንዲሆንና እንዳይገላምጣቸው ወይም እንዳይቆጣቸው አዟል፡፡ ኡፍ በማለት ቢሆንም ቃል ባይተነፍስም እንኳ በእነርሱ ላይ መበሳጨትና መቆጣት የለበትም፡፡

### ❈ ከሃዲያን ወላጆች

አንድ ሙስሊም ወላጆቹ ከሃዲያን ቢሆኑም እንኳን ለነርሱ ፍፁም ታዛዥና በጎ የሚውልላቸው ሊሆን ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ለአንተ በርሱ እውቀት የሌለህን ነገር በኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው፤ በቅርቢቱም ዓለም በመልካም ስራ ተወዳጃቸው›› (አል ሉቅማን 15)

ለነርሱ በጎ ከመዋል ሁሉ እጅግ ታላቁና ጠቃሚው እነርሱን በጥሩ ስነምግባርና በጥበብ በተሞላ መልኩ ወደ ኢስላም መጥራት ነው፡፡

# > የልጆች መብት



❖ ጥሩ እናት ልትሆን የምትችል መልካም ሚስት ለጋብቻ መምረጡ አባት ለልጆቹ ከሚያቀርብላቸው ስጦታዎች ሁሉ በላጩ ነው፡፡

❖ ስም ከነርሱ የማይለይ የሆነ መገለጫቸው በመሆኑ፣ ልጆችን በሚያማምሩ ስሞች መሰየም ልጆች በወላጆች ላይ ካላቸው መብት መካከል ነው፡፡

❖ በመልካም ስነ ምግባር አንጾ ማሳደግ፣ መሰረታዊ የሃማኖት ጉዳዮችን ማስተማርና ሃይማኖታቸውን እንዲወዱ ማድረግ፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እያንዳንዳችሁ እረኞች ናችሁ፤ ከጠበቃችሁት ነገርም ተጠያቂዎች ናችሁ፤ በሰዎች ላይ የተሾመ ሹም እረኛ ነው፤ ስለነርሱ ተጠያቂ ነው፤ አባወራ በቤተሰቡ ላይ እረኛ ነው፤ ስለነርሱ ተጠያቂ ነው፤ ሴት በባሏ ቤትና በልጆቹ ላይ እረኛ ነች፤ ስለነርሱ ተጠያቂ ነች፤ ባሪያም በአሳዳሪው ንብረት ላይ እረኛ ነው፤ ስለርሱ ተጠያቂ ነው፤ አዋጅ! ሁላችሁም እረኞቸች ናችሁ፤ ሁላችሁም ስለጠበቃችሁት ነገር ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡» (አል ቡኻሪ 2416 / ሙስሊም 1829)

ወላጆች እንደየአስፈላጊነቱና አንገብጋቢነቱ ቅደም ተከተል በማስያዝ ልጆቻቸውን ማነጽ ይኖርባቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ከማጋራትና ከፈጠራ አመለካከት የጸዱ ማድረግ፣ ትክክለኛውን የእምነት መሰረት እንዲይዙና ከዚያም አምልኮዎችን፣ በተለይም ሠላትን እንዲሰግዱ ማድረግና ብሎም ጥሩ ስነምግባርንና ስርዓቶችን ሊያስተምሯቸው ይገባል፡፡ ክብርና በጎ የሆነን ሁሉ ሊያሳዩዋቸው ይገባል፡፡ ይህ አላህ ዘንድ ትልቅ ከሚባሉ ስራዎች ነው፡፡

❖ ወጪ፡ ወላጅ አባት የወንድም ሆነ የሴት ልጆቹን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ችላ ማለትም ሆነ መሳነፍ አይገባውም፡፡ እንደውም እንደችሎታውና አቅሙ በተሟላ መልኩ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት መጣር ይኖርበታል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው የሚያስተዳድረውን መጣሉ ብቻ ከወንጀል በኩል ይበቃዋል፡፡» (አቡ ዳውድ 1692)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ሴት ልጆችን በመጠበቅና ለነርሱ ወጪ ማድረግን በተመለከተ እንዲህ ብለዋል፡- «የነዚህን ሴት ልጆች ጉዳይ የተሸከመና ለነርሱም በጎ የዋለላቸው፣ እነርሱ ለርሱ ከእሳት ግርዶ ይሆኑለታል፡፡» (አል ቡኻሪ 5649/ ሙስሊም 2629)

❖ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በሁሉም ልጆች መካከል ፍትሃዊ መሆን፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህን ፍሩ በልጆቻችሁ መካከል ፍትሃዊ ሁኑ፡፡» (አል ቡኻሪ 2447 / ሙስሊም 1623)

ሴቶችን ከወንዶቹ ማስበለጥ እንደማይፈቀድ ሁሉ ወንዶችንም ከሴቶች ማስበለጥም አይፈቀድም፡፡ ይህን ማድረግ አደገኛ ችግርን ይፈጥራል፡፡



# ስነ-ምግባርህ በኢስላም



# 11

በኢስላም፣ ስነ-ምግባር ማሟያ ወይምትርፍ ነገርአይደለም፤ ይልቁንም፣ በሁሉም ዘርፍ የጠበቀና ጥልቅ ትስስር ያለው የሃማኖት ክፍል ነው፡፡ ስነ ምግባር በኢስላም የላቀና ከፍተኛ ስፍራ አለው፡፡ ይህ ደግሞ በኢስላም ድንጋጌዎችና ህገ ደንቦች ውስጥ በይፋ የሚታይ እውነታ ነው፤ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላኩትም መልካም ስነ ምግባሮችን ሊያሟሉ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማውጫ

### ስነ-ምግባር በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ

- ስነ-ምግባር የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መላክ ዋነኛው ዓላማ ወይም ምክንያት መሆኑ
- ሥነ-ምግባር ዋና የእምነት ክፍል ነው
- ስነ-ምግባር ከሁሉም የአምልኮ ዘርፎች ጋር የተሳሰረ መሆኑ
- አላህ (ሱ.ወ) ለጥሩ ስነ-ምግባር ባለቤቶች ያዘጋጀው የላቀ ችሮታና ታላቅ ምንዳ

### ስነ-ምግባር በኢስላም ውስጥ ያለው ልዩ መገለጫ

- የላቀ ስነ-ምግባር በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተለየ አይደለም
- የላቀ ስነ-ምግባር በሰው ልጅ ላይ ብቻ የተገደበ አለመሆኑ
- በህይወት ዘርፎች በጠቅላላ ውስጥ የሚኖሩ የላቁ ስነ-ምግባሮች
- በተለያዩ አጋጣሚዎች ውስጥ የሚንጸባረቁ የላቁ ስነ-ምግባሮች

### ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕይወት ተምሳሌትነት

- መተናነስ
- እዝነት
- ፍትሃዊነት
- በጎ መዋልና ለጋስነት

# ስነ-ምግባር በኢስላም ውስጥ ያለው ስፍራ

**1** ስነ-ምግባር፣ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰው ዘር ከተላኩበት ዓላማዎች መካከል ዋነኛው ነው፡፡
አላህ (ሱ.ወ) ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡- «እርሱ ያ በመሃይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን) በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣ (ከማጋራት) የሚያጠራቸውም... የኾነን መልክተኛ የላከ ነው፡፡» (ጁምዓ 2 ) በአአንቀጹ ላይ፣ አላህ (ሱ.ወ) ለምእመናን ቁርአንን እንዲያስተምራቸውና ከእኩይ ስነ-ምግባር እንዲያጠራቸው መልክተኛውን በመላኩ የዋለውን ውለታ አውስቷል፡ ፡ እራስን ማጥራት ወይም ተዝኪያ፡- ቀልብን በአላህ ከማጋራት እንዲሁም እንደ ቂምና ምቀኝነት ካሉ እኩይ ስነ-ምግባሮች፣ ንግግርና ተግባርን ደግሞ ከተወገዙ ልማዶች ማጥራትን ያካትታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሻሚ ባልሆነ ግልጽ ቃላቸው እንዲህ ብለዋል፡- «እነሆ እኔ የተላኩት መልካም ስነ-ምግባሮችን ላሟላ ዘንድ ነው፡፡» (አል በይሃቂ 21301) ለነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) መላክ ምክንያት ከሆኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ግላዊና ማህበራዊ ስነ-ምግባሮችን ማሳደግና ማረቅ ነው፡፡

**2** ስነ-ምግባር ዋነኛ የእምነት ክፍል ነው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኢማኑ በላጩ አማኝ የትኛው ነው? ተብሎ በተጠየቁ ጊዜ፡ «በስነምግባሩ በላጫችሁ ነው ብለዋል፡፡» (አል ቲርሚዚ 1162 /አቡ ዳውድ 4682)
አላህ (ሱ.ወ) ኢማንን በጎ ነገር በሚል አውስቶታል፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «መልካም ስራ፣ ፊቶቻችሁን ወደ ምስራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ስራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነብያትም ያመነ ሰው....(ስራ) ነው፡፡» (አል በቀራ 177)
መልካም ነገር (ቢር)፡ በጎ ነገሮችን ከስነ-ምግባር፣ ከንግግርና ከተግባር ጋር የሚያቆራኝ ጥቅላዊ ስያሜ ወይም መጠሪያ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «መልካም ነገር ጥሩ ስነ ምግባር ነው፡፡» ያሉት ለዚህ ነው፡፡ (ሙስሊም 2553)
ይህ ጉዳይ በይበልጥ ግልጽ የሚሆነው በሚከተለው የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ውስጥ ነው፡- «ኢማን ከስልሳ ሦስት እስከ ስልሳ ዘጠኝ ደረጃዎች አሉት፤ ከፍተኛው ላኢላሃኢለላህ የሚለው ቃል ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ ከመንገድ ላይ ቆሻሻን ማስወገድ ነው፤ ህፍረትም ከኢማን ክፍል ነው፡፡» (ሙስሊም 35)




> ስነ ምግባርን ማሟላት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተልዕኮ ዓላማዎች ዋነኛው ነው

**3** ስነ-ምግባር ከእያንዳንዱ የአምልኮ ዘርፍ ጋር የተሳሰረና የተቆራኘ ነው አላህ (ሱ.ወ) አንድንም የአምልኮ ዓይነት ሲያዝ ስነምግባራዊ ዓላማውን ወይም በግለሰብና በማህበረሰብ ላይ የሚያስገኘውን ለውጥ ወይንም የሚጥለውን ፋና አብሮ ያሳስባል ወይም ይገልጻል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮች አሉ፤ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

**ሠላት፡**

«ሠላትንም (ደንቡን ጠብቀህ) ስገድ፤ ሠላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡» (አል አንከቡት 45)

**ዘካ፡**

«ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ፡፡» (አል ተውባ 103)
በመሰረቱ፣ ዘካ ለሰዎች በጎ መዋል፣ እነርሱን መደገፍና መርዳት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ፣ የሰጪውን ክፍል ነፍስ ከመጥፎ ስነ-ምግባሮች ያጠራለታል፡፡

**ጾም፡**

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡» (አል በቀራ183)
የጾም ዓላማው፣ ትዕዛዙን በመፈፀምና የተከለከለውን በመራቅ አላህን መፍራት ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «የውሸት ንግግርና በርሱ መስራትን ያልተወ ሰው፣ ምግብና መጠጡን ከመተው አላህ ጉዳይ የለውም፡፡» ብለው የተናገሩት ለዚህ ነው፡፡ (አል ቡኻሪ 1804)
መጾሙ ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ስነ-ምግባራዊ ለውጥ ያላመጣለት ሰው በርሱ ላይ የጾም ዓላማ አልተረጋገጠበትም፡፡

4 አላህ (ሱ.ወ) ለጥሩ ስነ-ምግባር ያዘጋጀው የላቀ ደረጃና ከባድ ምንዳ

በዚህ ዙሪያ በርካታ የቁርኣንና የሐዲስ ማስረጃዎች ተላልፈዋል፡፡ ከነሱም መካከል፡

- በትንሳኤ ቀን በሚዛን ላይ እጅግ በጣም ክብደት ከሚያነሱ ወይም ከሚደፉ መልካም ስራዎች መካከል ነው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በሚዛን ላይ ተደርጎ ከጥሩ ስነ- ምግባር የበለጠ የሚከብድ ነገር የለም፤ የጥሩ ስነ-ምግባር ባለቤት የጾመኛና የሰጋጅ ደረጃን በርሱ ይደርሳል፡፡» (አል ቲርሚዚ 2003)

- ጀነት ለመግባት ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሰው ልጅን በብዛት ጀነት የሚያስገባው፣ አላህን መፍራትና ሰናይ ስነ-ምግባር ነው፡፡»

(አል ቲርሚዚ 2004 /ኢብኒ ማጃህ 4246)

- የጥሩ ስነ ምግባር ባለቤት የትንሳኤ ቀን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጅግ የቀረበ ይሆናል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በትንሳኤው ቀን እኔ ዘንድ እጅግ ተወዳጃችሁና በስፍራም ለኔ የበለጠ ቅርባችሁ፣ ከናንተ መካከል በስነ ምግባሩ በላጫችሁ ነው፡፡» (አል ቲርሚዚ 2018)

- በጀነት ከፍተኛውን ማዕረግ እንደሚያገኝ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዋስትና ሰጥተውታል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እውነቱ እርሱ ዘንድ ቢሆንም ሙግትን ለተወ ሰው፣ በጀነት ዳርቻ የሆነ ቤትን፣ ለቀልድ ቢሆንም ውሸትን ለተወ ሰው ደግሞ በጀነት መሐል የሆነ ቤትን፤ ስነ-ምግባሩ ላማረ ሰው ደግሞ በጀነት የላይኛው ክፍል የሚገኝ ቤትን ዋስትና እሰጠዋለሁ፡፡» (አቡ ዳውድ 4800)



> ሰናይ ስነ ምግባር አላህ ዘንድ ከታላላቅ ተግባራት መካከል የሚመደብ ሲሆን ለሰው ልጅም እረፍትና ደስታን ይሰጠዋል፡፡

# በኢስላም ውስጥ የስነ ምግባር ልዩ መገለጫዎች

በኢስላም፣ ስነ ምግባር በርካታ የሆኑ ልዩ መገለጫዎች አሉት፡፡ ያ ደግሞ ይህን ታላቅ ሃይማኖት ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል ነው፡

## 1. የላቀ ስነ-ምግባርን ማሳየት በሰው ልጅ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅን ሲፈጥር በተለያየ ቅርጽ፣ ቀለምና ቋንቋ ላይ አድርጎ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአላህ ሚዛን ሁሉም እኩል ናቸው፡፡ በኢማናቸው፣ አላህን በመፍራታቸውና በጥሩነታቸው ልክ እንጂ፣ አንዳቸው በሌላኛው ላይ ምንም ዓይነት ብልጫ የለውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡» (አል ሑጁራት 13)

መልካም ስነ ምግባር፣ አንድ ሙስሊም ከማንኛውም ሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ልዩ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም፣ በሃብታምና በድሃ፤ ደረጃው በተለቀና ባነሰ፣ በጥቁርና በነጭ፣ በዐረቡና ዐጀሙ መካከል ልዩነት ስለማይፈጥር ነው፡፡

ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር የሚኖር ስነምግባር

አላህ (ሱ.ወ) ስነ ምግባራችን ከሁሉም ጋር ያማረ እንዲሆን አዞናል፡፡ ፍትሃዊነት፣ በጎነት፣ እዝነት፣ ትክክለኛ ሙስሊም ከሙስሊሞችም ሆነ ከካሃዲያን ጋር በሚኖረው ግንኙነት የሚታወቅበት መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሙስሊም ይህ መልካም ስነ ምግባሩ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ወደዚህ ታላቅ ሃይማኖት የሚጠራበት ዋነኛ መንገዱ እንዲሆን ይጥራል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከነዚያ በሃይማኖት ካለተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካለወጡዋችሁ (ከሃዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፤ አላህ ትክክለኞቹን ይወዳልና፡፡» (አል ሙምተሒና 8)

አላህ የከለከለው ከካሃዲያን ጋር መጎዳኘትንና እነርሱ ያሉበትን ክህደትና ማጋራትን መውደድ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «አላህ የሚከለክላችሁ ከነዚያ በሃይማኖት ከተጋደሉዋችሁ ከቤቶቻችሁም ካወጡዋችሁ እናንተንም በማውጣት ላይ ከረዱት (ከሃዲዎች) እንዳትወዳጁዋቸው ብቻ ነው፤ ወዳጅ የሚያደርጓቸውም ሰዎች እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡» (አል ሙምተሒና 9)



>የዘር ሃረጋቸውም ሆነ ሃይማኖታቸው ከርሱ ጋር የሚለያይ ቢሆንም፣ አንድ ሙስሊም ከሁሉም ሰው ጋር የሚኖረው ግንኙነት በመልካም ስነ ምግባር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

## 2. የላቁ ስነ ምግባሮች በሰዎች ብቻ የተገደቡ አይደሉም፡፡

ስነ ምግባር ከእንሰሳት ጋር

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ አንዷት ሴት ድመትን አስራ በረሃብ በመግደሏ ምክንያት ጀሃነም እንደገባች, ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ አንድ ሰው የተጠማ ውሻን በማጠጣቱ ምክንያት አላህ ወንጀሎቹን እንደማረው ነግረውናል።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዲት ሴት ባሰረቻት ድመት ምክንያት እሳት ገባች፤ ወይ አላበላቻት ወይ ከመሬት ነፍሳቶች እንድትበላ አልተወቻት፡፡» (አል ቡኻሪ 3140/ ሙስሊም 2619)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አንድ ሰውዬ በመንገድ እየተጓዘ ሳለ ውሃ ጥም ጠናበት፤ የጉድጓድ ውሃ አገኘ፤ ወደ ጉድጓዱ ወርዶ ጠጣ፤ ከዚያም ሲወጣ ከመጠማቱ የተነሳ አፈር የሚልስ፣ ምላሱን ጎልጉሎ የሚያለከልክ ውሻ አገኘ፤ እንዲህም አለ፡- «ይህ ውሻ ልክ እኔ ተጠምቼ እንደነበርኩት ዓይነት ተጠምቷል» አለና በድጋሚ ወደ ጉርጓዱ ወርዶ፣ በጫማው ውሃ ሞልቶ፣ በአፉ ነክሶ ይዞ በመውጣት ውሻውን አጠጣው፤ በዚህም አላህ ስራውን ወዶለት ወንጀሉን ማረው፡፡» ብለው ተናገሩ፡፡ ሠሓቦቹም፣ «የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኮ እኛ በነዚህ እንስሳትም ምንዳ እናገኛለን?» በማለት ጠየቁ፤ እሳቸውም፡ «ነፍስ ባለው ነገር ሁሉ ውስጥ ምንዳ አለ፡፡» አሉ፡፡ (አል ቡኻሪ 5663 / ሙስሊም 2244)

ስነ ምግባርና የአካባቢ ጥበቃ

ኢስላም፣ በመመራመርና ስልጣኔን በማሳደግ፣ በመስራት፣ በማልማት፣ ምድርን እንድናስውባት አዞናል፡፡ ይህም፣ ምድር ላይ ያለውን ጸጋ በመጠበቅ እንዲሁም ከሚያበላሹትና ከሚያባክኑት ነገሮች በመካለከልና በሚገባው ስፍራ ላይ ግልጋሎት እንዲሰጥ በማድረግ ይረጋገጣል፡፡ የአካባቢ ብልሽትና ብክለት ሰዎችን፣ እንሰሳትንም ሆነ እጽዋትን መጉዳቱ ሁሉም በአንድ ዓይን የሚታይ ነው፡፡ ጉዳቱ በየትኛውም አካል ላይ ቢሆን፣ ኢስላም አጥብቆ የሚያወግዘውና የሚጠላው ተግባር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በማንኛውም የሕይወት ዘርፍ ማበላሸትን አይወድም፡፡ እንዲህም ይላል፡- «አላህም ማበላሸትን አይወድም፡፡» (አል በቀራ 205)

ይህ ኢስላማዊ እሴት፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊሞች በአስቸጋሪና አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ቢሆኑ፣ መልካምን እንዲሰሩና ምድርን ያለሙ ዘንድ ትእዛዝን እንዲያስተላልፉ አድርጓል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዳችሁ በእጅ ችግኝ ይዞ ሰዓቲቷ ብትከሰት፤ ሳትከሰት ሊተክላት የቻለ ሁሉ ይትከላት፡፡» (አህመድ 12981)



> ኢስላም አካባቢን በመጠበቅ ላይ ያበረታታል፡፡

## 3. መልካም ስነ ምግባር በሕይወት ዘርፎች ሁሉ

### በቤተሰብ ውስጥ፡

ኢስላም፣ በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል ስነ ምግባር ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው እንደሆነ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ «በላጫችሁ ለቤተሰቡ መልካም የሆነው ነው፤ እኔ ለቤተሰቦቼ መልካማችሁ ነኝ፡፡» (አል ቲርሚዚ 3895)

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰው ዘር በጠቅላላ ምርጡ ሰው ናቸው፡፡ እንዲህ ከመሆናቸውም ጋር በትንሽ በትልቁ፣ በቤት ውስጥ ጉዳይ ባለቤታቸውን ይረዱና ያግዙ ነበር፡፡ ባለቤታቸው፣ እመት ዓኢሻ(ረ.ዐ) የሚከተለውን ብለዋል፡- «እሳቸው በቤተሰባቸው ጉዳይ የተጠመዱ ነበሩ፡፡» (አል ቡኻሪ 5048) የህ ይረዷቸው ነበር፤ በቤት ውስጥ በሚሰሩት ስራ ከቤተሰባቸው ጋር ይሳተፉ ነበር ማለት ነው፡፡

- ከሚስቶቻቸው ጋር ይቃለዱና ይጫወቱም ነበር፤ ባለቤታቸው እመት ዓኢሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- «በአንድ ወቅት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በሆነ ጉዟቸው ላይ አብሪያቸው ተጉዤ ነበር፤ በወቅቱ እኔ ልጅ ነበርኩ፡፡ አልወፈርኩም አልከበድም ነበር፤ ነብዩ ለሰዎች እንዲህ አሉ፡ «ቅደሙን ከፊት ከፊት ሂዱ፡፡» ሰዎቹም ከፊት ከፊት ሄዱ፡፡ ከዚያም «ነይ እስኪ እንሽቀዳደም» አሉኝ ተሽቀዳደምንና እኔ ቀደምኳቸው፤ ዝም አሉኝ፤ ከወፈርኩ፣ ክብደት ከጨመርኩ እና ተሽቀዳድመን እንደነበረ ከረሳሁት በኋላ አሁንም በሆነ አጋጣሚ በአንድ ጉዟቸው ላይ አብሬያቸው ተጓዝኩ፡፡ አብረውን የነበሩ ሰዎችን «ወደፊት ቅደሙ» አሏቸውና ሰዎቹም ከፊት ከፊታችን ተጓዙ፤ እስቸውም «እስኪ ነይ እንሽቀዳደም» አሉኝ፤ ተሽቀዳደምንና ቀደሙኝ፤ ከዚያም እየሳቁ፡ «ይህች የዚያች መካሻ ናት፡፡» አሉኝ « (አሕመድ 26277)



### በንግድ ውስጥ፡

ምናልባት የሰው ልጅ ለገንዘብ ካለው ፍቅር የተነሳ ድንበር በማለፍ እርም የተደረጉ ነገሮች ውስጥ ሊዘፈቅ ይችላል፡ ፡ በመሆኑም ኢስላም ይህን የገንዘብ ውዴታውን በላቀ ስነ ምግባር ሥርዓት ማስያዝ እጅጉን አስፈላጊ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቶ ያስተምራል፡፡ ለምሳሌ፡

- ኢስላም በሚዛን ድንበር ማለፍንና መበደልን ይከለክላል፡፡ ይህን የሚሠራ ሰውንም ብርቱ የሆነ ቅጣት እንደሚጠብቀው ይነግራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ለሰላቢዎች ወዮላቸው፤ ለነዚያ ከሰዎች ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ፤ ለነሱም (ለሰዎቹ) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለኾኑት)» (አል ሙጠፊፊን 1-3)
- በግብይት ላይ ገራገር መሆንን ያበረታታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሲሸጥ፤ ሲገዛና፤ ሲፋረድ ገር የሆነን ሰው አላህ ይዘንለት፡፡» (አል ቡኻሪ 1970)

### በሥራ ውስጥ:

ኢስላም፣ የፈጠራ ባለቤቶችን በርካታ ስነ ምግባሮችና ስርዓቶችን ሊላበሱ እንደሚገባ ያስተምራል፡፡

- ሥራን በብቃትና በጥራት መስራትን፤ ምርትን በሚያምር ሁኔታ ማምረትን ያዛል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ:- «አላህ (ሱ.ወ)፣ አንዳችሁ በሚሠራ ጊዜ ሥራውን በብቃትና በጥራት እንዲሰራው ይፈልጋል፡፡» (አቡ ያዕላ 4386/ አል በይሃቂ ፊ ሺዓቢል ኢማን 5313)
- ከሰዎች ጋር የተደረገን ስምምነትና ውል መጠበቅ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ «የመናፍቅነት መገለጫ ምልክቶች ሦስት ናቸው፤» ካሉ በኋላ ከነሱ መካከል «ቃል ከገባ በኀዋላ ቃሉን ማፍረስ» በማለት ጠቅሰዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 33)



### 4. የላቀ ስነ ምግባር በማንኛውም ሁኔታ አስፈላጊ ስለመሆኑ

በኢስላም፣ ስነ ምግባር እዚህ ውስጥ አይገባም የሚባልለት ነገር የለም፡፡ ሙስሊም፣ ጦርነትን ጨምሮ እጅግ አዳጋች በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ የአላህን ሕግ በመፈፀም ረገድ የመልካም ስነ ምግባርን መርሆዎች ይከተላል፡፡ የአንድ ነገር ዓላማና መድረሻ መልካምነት የመዳረሻ መንገዶቹን መጥፎ ገጽታ አያጸዳውም፤ ስህተትነቱንና ጥመቱንም አይሸፍነውም፡፡

ስለሆነም ኢስላም ሙስሊሙን፣ ከጠላት ጋር በሚኖረው ግንኙነት እና በጦርነት ወቅት በሚኖረው ሁኔታ ላይ ሳይቀር፣ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው የሚገዛውና በስርዓት የሚመራው የሆነ ጠቅላይ መመሪያ አስቀምጧል፡፡ ይህ መመሪያ፣ የአንድ ሙስሊም የሕይወት ገጠመኝ፣ የንዴትና የጭፍንነት ግላዊ ስሜቶች ተገቢና እንዲሁም ለቂም ለችክተኝነትና ለማን አለበኝነት መፈንጪያ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

### በጦርነት ላይ ያለው የኢስላም ስነ ምግባራዊ መመሪያ

1- ኢስላም ከጠላት ጋር ፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት እንዲኖር አዟል፤ በደልንና በነርሱ ላይ ድንበር ማለፍን ከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤ አስተካክሉ፤ እርሱ (ማስተካከል)ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው፡፡ » (አል ማኢዳ 8)

ለጠላቶቻችሁ ያላችሁ ጥላቻ ድንበር እንድታልፉና በደል እንድትፈጽሙ ሊያደርጋችሁ አይገባም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም በንግግራችሁም ሆነ በተግባራችሁ ፍትሃዊ ሁኑ እያለ ነው፡፡

2- ኢስላም፣ ከጠላት ጋር በሚደረግ ውልና ስምምነት መክዳትንና ማታለልን ይከለክላል፡፡

ጠላትንም ቢሆን መክዳትና ማታለል ክልክል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «አላህ ከዳተኞችን አይወድምና፡፡» (አል አንፋል 58)

3- ኢስላም የጠላትን ሬሳ ማንገላታትና መቆራረጥን ይከለክላል፡፡

የሙታንን ገላ መቆራረጥ ሐራም ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-«ሬሳን አትቆራርጡ» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 1731)

4- በጦርነት ላይ የማይሳተፉ አካባቢን በማበላሸት የማይታወቁ የሆኑ ሰላማዊ ነዋሪዎችን መግደል ይከለክላል

ታላቁ ሦሐቢይ፣ የሙስሊሞች ኸሊፋ፣ አቡበከር(ረ.ዐ)፣ ኡሳማ ቢን ዘይድን(ረ.ዐ) ወደ ሻም ሀገር የጦር መሪ አድርገው በላኩ ጊዜ:- «ታዳጊ ሕፃንን፣ ያረጀ ሽማግሌንም፣ ሴትንም አትግደሉ፡፡ የተምር ዛፍን አትቁረጡ አታቃጥሉም፡፡ የሚያፈራ ዛፍንም አትቁረጡ፡፡ ልትመገቡ ካልሆነ በስተቀር በበቀል የሕዝቦችን ፍየሎች፣ ላምና ግመሎች አትረዱ፡፡ እራሳቸውን ለአምልኮ ያገለሉ፣ በገዳማት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችም ያጋጥሟችኋል፤ እራሳቸውን አሳልፈው በሰጡለት ነገር ላይ ተዋቸው፡፡» ብለዋል፡፡ (ኢብኑ ዓሳኪር 2/ 50)

# ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ታሪክ ስነ ምግባራዊ አስተምህሮት መካከል፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ እጅግ የላቀ ለሆነው የሰው ልጅ መልካም ስነ ምግባር ዓይነተኛ ተምሳሌት ነበሩ፡፡ ቁርኣን የሳቸውን ስነ ምግባር ታላቅ በማለት የገለጸው ለዚህ ነው፡፡ ባለቤታቸው እመት ዓኢሻም(ረ.ዐ) ስለርሳቸው ስነ ምግባር ሲናገሩ፡- «ስነ ምግባራቸው ቁርኣን ነበር፡፡» ከማለት ሌላ የተሻለ የረቀቀ አገላለጽ አላገኙለትም፡፡ እርሳቸው፣ ለቁርኣን ስነ ምግባራዊ አስተምሮት ተግባራዊ ተምሳሌት ነበሩ፡፡



> ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በስነ ምግባራቸው ከሰዎች ሁሉ የላቁ ነበሩ

## መተናነስ፡

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸውን በማክበርና በማላቅ አንድም ሰው እንዲቆምላቸው አይፈልጉም ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ ሠሐቦቻቸውን እንዲህ ማድረግን ከልክለዋል፡፡ በመሆኑም ሠሐቦች ለርሳቸው ያላቸው ክብርና ውዴታ እጅግ ጠንካራ ከመሆኑ ጋር የእርሳቸውን መምጣት እያዩ አይቆሙላቸውም፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው፣ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር እርሳቸው እንደሚጠሉ ስላወቁ ነው፡፡ (አህመድ 12345 /አል በዛር 6637)
- ዐዲይ ቢን ሓቲም(ረ.ዐ) ኢስላምን ሲቀበል፣ ወደርሳቸው ዘንድ መጣ፡፡ ዐዲይ፣ ከዐረብ መኳንንት አንዱ ነበር፡፡ የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ጥሪ እውነታ ለማወቅ ፈለገ፡፡ ዐዲይ(ረ.ዐ) ይህንን ገጠመኝ ሲናገር፡- «እርሳቸው ዘንድ ስደርስ አንዲት ሴትና አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሕፃናት አብረዋቸው ነበሩ፤ - ከነብዩ ጋር ያላቸውን የዝምድና ቅርበትም ጠቅሷል - በዚህን ጊዜ እነሆ እርሱ የኪስራም ሆነ የቀይሠር ንግስና ዓይነት እንዳልሆነ ተረዳሁኝ፡፡» ይላል፡፡ (አህመድ 19381)

መተናነስ የነብያት ሁሉ መገለጫ ባህሪ ነው፡፡

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ሲቀመጡ፣ ከነርሱ መካከል እንደሆነ አንድ ተራ ሰው ነበር፡፡ ከነሱ የሚለዩበት ምንም ነገር አይታይባቸውም፡፡ በዙሪያቸው ከሚቀመጡት የሚለያቸው የሆነ ስፍራም አይቀመጡም፡፡ የማያቃቸው እንግዳ ሰው በተቀመጡበት ቦታ በድንገት በሚገባ ጊዜ፣ እርሳቸውን ከባልደረቦቻቸው ለይቶ ማወቅ አይችልም፡፡ እናም «ከመካከላችሁ ሙሐመድ የትኛችሁ ነው? « በማለት ይጠይቅ ነበር፡፡ (አል ቡኻሪ 63)
- አነስ ቢን ማሊክ እንዲህ ብለዋል፡- «ከመዲና ባሮች መካከል የሆነች አንዲት ባሪያ፣ ጉዳይዋን እንዲያስፈፅሙላት የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እጅ ይዛ የፈለገችበት ቦታ ትሄድ ነበር፡፡» (አል ቡኻሪ 5724)

«እጃቸውን ይዛ» የሚለው ሐረግ፣ ለትንሹም ለደካማውም የነበራቸውን እሺታና ገራገርነት ለመግለፅ የተጠቀሙበት ነው፡፡ ይህ፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመተናነስ ላይ የነበራቸውን ባህሪ ድካ በደረሰ መልኩ ይገልፃል፡፡ ምክንያቱም በታሪኩ ላይ የተጠቀሰው ወንድ ሳይሆን ሴት፤ ነፃ ሳትሆን ባሪያ ነች፡፡ ከመሆኑም ጋር ጉዳይዋን እንዲያስፈፅሙላት የፈለገችበት ስፍራ ይዛቸው ትሄድ ነበር፡፡

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በልቡ ውስጥ የቅንጣት ክብደት ያህል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡» (ሙስሊም 91)

## እዝነት፡

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «አዛኞች አርረህማን ያዝንላቸዋል፤ በምድር ውስጥ ላለ እዘኑ፤ ከሰማይ በላይ ያለው ያዝንላችኋልና፡፡» ብለዋል (አል ቲርሚዚ 1924 / አቡ ዳውድ 4941)

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አዛኝነት በበርካታ ስፍራዎች ላይ ይንጸባረቃል፤ ከነዚህም መካከል፡

## ለሕፃናት የነበራቸው እዝነት፡

- አንድ ገጠሬ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፡ «ልጆቻችሁን ትስማላችሁን? እኛ ግን አንስማቸውም፡፡» አላቸው፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ)፣ «ታዲያ አላህ ከቀልብህ ውስጥ እዝነትን የነጠቀ ከሆነ እኔ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?» በማለት መልስ ሰጡት፡

(አል ቡኻሪ 5652 ሙስሊም 2317)

ሌላ ገጠሬ ደግሞ የዓሊይን ልጅ ሐሰንን ሲስሙ ተመለከታቸውና፣ «እኔ አስር ልጆች አሉኝ ነገር ግን አንዱንም ስሜው አላውቅም፡፡» አለ፡፡ በዚህን ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «እነሆ የማያዝን አይታዘንለትም፡፡» አሉት፡ (ሙስሊም 2318)

- አንድ ጊዜ የልጃቸውን ሴት ልጅ፣ ኡማማ ቢንት ዘይነብን ይዘው ሰግደዋል፡፡ ሱጁድ ሲያደርጉ ቁጭ ያደርጓታል፤ ሲቆሙም ይሸከሟት ነበር፡፡ (አል ቡኻሪ 494/ ሙስሊም 543)

- ሠላት ውስጥ ሆነው የሕፃን ልጅ ለቅሶ ከሰሙ፣ ሠላቱን አጠርና ፈጠን አድርገው ይሰግዱ ነበር፡፡ አቡ ቀታዳ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን አስተላልፈዋል፡ «ሠላት ስሰግድ በውስጧ ማስረዘምን እፈልጋለሁ፤ ከዚያም የሕፃን ልጅ ለቅሶ እሰማለሁ፤ እናም እናትየዋን እንዳላስጨንቃት በማሰብ ሠላቴን አሳጥራለሁ፡፡» (አል ቡኻሪ 675/ ሙስሊም 470)

## ለሴቶች የነበራቸው እዝነት

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሴት ልጆችን በመንከባከብ ለነርሱ በጎ በመዋል ላይ አነሳስተዋል፡፡ «በነዚህ ሴት ልጆች የሆነ ፈተናን የተፈተነ ለነርሱም በጎን የዋለ ሰው ለርሱ ከእሳት ግርዶ ይሆኑለታል፡፡» ይሉም ነበር፡፡

(አል ቡኻሪ 5649 / ሙስሊም 2629)

የሚስትን መብት በተመለከተ ጠበቅ አድርገዋል፡፡ የሷን ጉዳይ ልዩ ትኩረት ቸረውታል፡፡ የተለየ እንክብካቤም ሰጥተውታል፡፡ ሙስሊሞችም በዚሁ ዙሪያ ከፊላቸው ለከፊሉ አደራን እንዲያስተላልፍ አዘዋል፡፡ « ስለ ሴቶች መልካም ነገርን ተናዘዙ፡፡» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 4890)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቤተሰባቸው ጋር ገራገር በመሆን ዓይተኛ ተምሳሌት ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ በአንድ ወቅት ግመላቸው አጠገብ ቁጭ ባሉበት ባለቤታቸው ሠፊያ(ረ.ዐ) እግሯን በጉልበታቸው ላይ በማድረግ ተንጠላጥላ ግመሉ ላይ ወጥታለች፡፡ (አል ቡኻሪ 2120)

ልጃቸው ፋጢማ እሳቸው ዘንድ በምትመጣ ጊዜ እጇን ይዘው ይስሟታል፤ እርሳቸው በሚቀመጡበት ቦታም ያስቀምጧታል፡፡ (አቡ ዳውድ 5217)




## ለደካሞች የነበራቸው እዝነት

◈ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ሰዎች ወላጅ አልባ ሕፃናትን የመንከባከብ ኃላፊነትን እንዲወስዱ ያነሳሱ ነበር፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- አመልካች ጣታቸውንና የመሐል ጣታቸውን በማቆራኘት፣ - «እኔና ወላጅ አልባ ሕፃንን (የቲምን) የሚንከባከብ ሰው፣ በጀነት ውስጥ እንዲህና እንዲህ ነን» ብለዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 4998)

◈ ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች እና ለችግረኞች ጉዳይ የሚሯሯጥና የሚለፋን ሰው፣ ቀኑን በጾም፣ ሌሊቱን ደግሞ በመስገድ ከሚያሳልፍ፣ በአላህ መንገድ ላይ ከሚታገል ታጋይ ጋር እኩል አድርገውታል፡፡ (አል ቡኻሪ 5661/ ሙስሊም 2982)

◈ ለደካሞች መራራትና መደንገጥ፣ ሙብታቸውን መጠበቅ ወይም መስጠት፣ ለሲሳይ መጨመርና በጠላት ላይ ድልን የመጎናጸፊያ ሰበብም እንደሆነ አስተምረዋል፡ ፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ደካሞችን ፈልጉልኝ፤ ድልን የምታገኙትም ሆነ ሲሳይን የምታገኙት በደካሞቻችሁ ነው፡፡» ይላሉ፡፡ (አቡ ዳውድ 2594)



> ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶችና ለችግረኞች በጎ የሚውልን ሰው፣ በአላህ መንገድ ላይ ከሚታገል ሰው ጋር እኩል አድርገውታል፡፡



> ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዲት ሰሃባዎች ጫጨቶቿን የወሰዱባትን ወፍ ስትሯሯጥ በተመለከቱ ጊዜ እንዲህ ብለው ነበር፡ ማንነው ይህችን ልጆቿን በመውሰድ ያስደነገጣት? ልጆቿን መልሱላት፡፡

## ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለእንስሳት የነበራቸው እዝነት

◈ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ሰዎች ለእንስሳት እንዲራሩ ያሳስቡ ነበር፡፡ የማይችሉትን ነገር እንዳያሸክሟቸውና እንዳያንገላቷቸው አስጠንቅቀዋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ (ሱ.ወ) በነገሮች ሁሉ አሳምሮ መስራትን ደንግጓል፤ እናም ስትገድሉ አገዳደላችሁን አሳምሩ፤ ስታርዱም አስተራረዳችሁን አሳምሩ፤ አንዳችሁ ቢላዋውን ይሳለው፤ እርዱንም በቶሎ ያሳርፈው ፡፡» (ሙስሊም 1955)

◈ አንድ ሠሐብይ እንዲህ ብሏል፡- በአንድ ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያቃጠልነውን የጉንዳን መንደር ተመለከቱና፣ «ይሄን ያቃጠለው ማን ነው?» በማለት ጠየቁ፤ እኛ ነን አልናቸው፤ እሳቸውም፡ «የእሳት ጌታ እንጂ በእሳት ማንም ማንንም ሊቀጣ አይገባም፡፡» አሉን፡፡ (አቡ ዳውድ 2675)

### ፍትሃዊነት፡

◈ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቅርብ ዘመዳቸው ላይም ቢሆን ፍትሃዊውን የአላህ ፍርድ ተፈፃሚ ከማድረግ ወደ ኋላ የሚሉ አልነበሩም፡፡ አላህም እንዲህ ሲል አዟል፡ - «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (በፍትሕ) ቋሚዎች፣ በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢኾንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ኹኑ፡፡» (አል ኒሳእ 135)



> ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቅርብ ዘመዶቻቸውም ሆነ ከጠላት ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ እጅግ ሚዛናዊና ፍትሃዊ ነበሩ፡፡

- የተወሰኑ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች፣ ጎሳዋ ውስጥ ክብር የነበራት፣ ሰርቃ የተያዘች አንዲት ሴት ላይ ኢስላማዊው ቅጣት ተፈፃሚ እንዳይሆንባት ለማማለድ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመጡ ጊዜ፣ «የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፤ የሙሐመድ ልጅ ፋጢማ ብትሰርቅ እንኳን እጇን እቆርጠዋለሁ፡፡» ብለው መልሰዋቸዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 4053 / ሙስሊም 1688)

- በሰዎች ላይ ወለድ ወይም አራጣ እርም በተደረገ ጊዜ መጀመሪያ የጀመሩት ለርሳቸው እጅግ ቅርብ የሆነውን ሰው በመከልከል ነበር፡፡ ያም አጎታቸው ዐባስ(ረ.ዐ) ነው፡፡ በወቅቱ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «መጀመሪያ ውድቅ የማደርገው የኛን ወለድ ነው፤ የዐባስ ቢን ዐብዱልሙጠሊብን ወለድ (የወለድ ውል ሰርዣለሁ)፤ እነሆ ሁሉም የአራጣ ገንዘብ ውድቅ ሆኗል፡፡» አሉ፡፡ (ሙስሊም 1218)

- የአንድ ማኅበረሰብ ዕድገትና ስልጣኔ የሚለካው፣ ደካሞች ምንም ሳይፈሩና ሳያመነቱ ከጉልበተኞች መብታቸውን መውሰድ በመቻላቸው እንደሆነ አስተምረዋል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ - «በውስጧ ያሉ ደካሞች ያለ ምንም ፍርሃት መብታቸውን የማይወስዱበት ወይም የማያገኙበት ሕዝብ አይበለጽግም(አይድንም)፡፡» (ኢብኑ ማጃህ 2426)

## በጎ መዋልና ለጋስነት፡

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመልካም ነገር ላይ ለጋስ ሰው ነበሩ፡፡ እጅግ በጣም ለጋስ የሚሆኑት ደግሞ በረመዳን ወር፣ ጅብሪል(ዐ.ሰ) በሚገናኛቸው ጊዜ ነው፡፡ በረመዳን ውስጥ፣ ረመዳን እስከሚያልቅ ድረስ በየሌሊቱ ጅብሪል(ዐ.ሰ) ይገናኛቸው ነበር፡፡ በዚህም ጉብኝቱ ቁርኣንን ያናብባቸዋል፡፡ እናም ጅብሪል(ዐ.ሰ) በሚገናኛቸው ጊዜ ለመልካም ነገር ያላቸው ለጋስነት ወይም ፈጣንነት ከተላከ ንፋስ የፈጠነ ነበር፡፡ (አል ቡኻሪ 1803 / ሙስሊም 2308)

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተጠይቀው ያልሰጡት ነገር የለም፡፡ አንድ ጊዜ፣ የሆነ ሰው ሊጠይቃቸው መጥቶ፣ በሁለት ተራሮች መሐል ያለን ሸለቆ የሚሞሉ ፍየሎችን ሰጡት፤ እናም ሰውየው ወደ ጎሳዎቹ በመመለስ፣ «ሕዝቦቼ ሆይ ስለሙ፤ ሙሐመድ ድህነትን የማይፈራ የሆነን ስጦታን ይሰጣል፡፡» አለ፡፡ (ሙስሊም 2312)

- በአንድ ወቅትም ሰማንያ ሺህ ዲርሃም መጣላቸውና በከረጢት አስቀመጡት፤ ከዚያም ተመልሰው መጡና አከፋፈሉት፤ አንድንም ለማኝ ሳይመልሱ ሁሉንም አከፋፍለው ጨረሱ፡፡ (አል ሃኪም 5423)

- አንድ ሰው ወደሳቸው በመምጣት ጠየቃቸውና፡ «ምንም የምሰጥህ ነገር የለኝም፤ ቢሆንም በኔ ስም ግዛና የሆነ ነገር ከመጣልኝ እከፍለዋለሁ፡፡» ሲሉት፣ ዑመር(ረ.ዐ) «አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ፣ አላህ የማይችሉትን ነገር አላስገደደዎትም»- ለምን እራሶዎን ያስጨንቃሉ- ሲላቸው፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዑመር(ረ.ዐ) አስተያየት አላስደሰታቸውም ነበር፤ ሰውየውም እንዲህ አለ፡ «ስጥ የዙፋኑ ባለቤት እንደሆነ ያሳንስብኛል ብለህ አትፈራ፡፡» አላቸው፤ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) በሰውየው ንግግር ፈገግ አሉ፡፡ የደስታ ስሜት በፊታቸው ላይ ይንጸባረቅ ነበር፡፡ (አል አሓዲሱል ሙኽታራ 88)

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሑነይን ዘመቻ በተመለሱ ጊዜ የገጠር ሰዎችና አዲስ ሙስሊሞች ከተገኘው ምርኮ ስጦታ ከጅለው ወደሳቸው መጡ፤ በጣም አጨናነቋቸውም፤ በጣም ከማጨናነቃቸው የተነሳ ወደ ዛፍ ስር አስጠጓቸው፤ የዛፉ ቅርንጫፍ ልብሳቸውን ገፈፋቸው፤ በዚህን ጊዜ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- «ልብሴን ስጡኝ፤ በነዚህ ዛፎች ቅርንጫፍ ልክ ገንዘብ ቢኖረኝ እንኳን በመካከላችሁ አከፋፍዬው፣ ከዚያም ስስታምም ሆነ ውሸታም፣ እንዲሁም ድህነትን ፈሪ እንዳልሆንኩኝ ታውቁ ነበር፡፡» አሉ፡፡ (አል ቡኻሪ 2979)



# አዲሱ ሕይወትህ



# 12

የሰው ልጅ ወደ ኢስላም የገባበት ቅጽበት በሕይወቱ ውስጥ ከባድ ቦታ የሚሰጠው አጋጣሚ ነው፡፡ እውነተኛው ልደቱ ያ ነው፡፡ የመፈጠሩን ሚስጥር የሚረዳው ከዚያ በኋላ ነው፡፡ ገር በሆነው የኢስላም ሕግ መሰረት ሊኖርና ሕያው ሊሆን እንደሚችልም የሚገነዘበው ከዚያች ቅጽበት በኋላ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማውጫ

አንድ ሰው ወደ ኢስላም እንዴት ሊገባ ይችላል?

ንሠሐ (ተውባ)

ምስጋና የሚሹ ጸጋዎች

ወደ ኢስላም መጣራት

- ወደ አላህ መንገድ የመጣራት ትሩፋት
- የትክክለኛ ጥሪ መገለጫዎች
- ቤተሰብን መጣራት

አካባቢህና ቤተሰብህ

ወደ ኢስላም ከገቡ በኋላ ያለው ቤተሰባዊ ሕይወት


- ባልና ሚስት በአንድነት ኢስላምን ከተቀበሉ
- ባል ብቻዉን ከሰለመ
- ሚስት ብቻዋን ከሰለመች
- የሕጻናት መስለም

ከሰለሙ በኋላ ስም መቀየር

ተፈጥሯዊ ፈለጎች

# > አንድ ሰው ወደ ኢስላም እንዴት ሊገባ ይችላል?

አንድ ሰው ሁለቱን የእምነት የምስክርነት ቃል ትርጉማቸውን አውቆ፣ በልቦናውም እርግጠኛ ሆኖ፣ በምላሱ በመናዘዝ ወደ ኢስላም ይገባል፡፡ እነኚህ ሁለት የእምነት የምስክርነት ቃሎች የሚከተሉት ናቸው፡



1 «ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ» ይላል፡፡ ከአላህ ባሻገር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ በልቦናዬ አምኜ በምላሴ እመሰክራለሁ፤ እርሱን በብቸኝነት አመልካለሁ፤ ለርሱ አጋር የለውም ማለት ነው፡፡

2 «ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ናቸው ብዬ እመሰክራለሁ» ይላል፡፡ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ወደ ሰው ልጆች ሁሉ የተላኩ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን በልቦናዬ አምኜ በምላሴ እመሰክራለሁ፤ ላዘዘው ነገር ታዛዥ፣ ለከለከለውም ተከልካይ እሆናለሁ፤ አላህንም ከርሱ ድንጋጌና ፈለግ ጋር በሚገጥም መልኩ እገዛለሁ፤ ማለት ነው፡፡ (ገጽ፣ 40-48 ተመልከት)

## አዲስ ሙስሊም ገላውን ይታጠባል

የሰው ልጅ፣ ወደ ኢስላም የገባበት ቅጽበት በሕይወቱ ውስጥ ከባድ ቦታ ያለው አጋጣሚ ነው፡፡ እውነተኛው ልደቱ ያ ነው፡፡ በሕይወት የመገኘቱን ሚስጥር የሚረዳው ከዚያ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ሃይማኖት ውስጥ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ሰውነቱን በጠቅላላ በውሃ መታጠብ ይኖርበታል፡፡ ውስጡን ከማጋራትና ከወንጀሎች እንዳጠራና እንዳጸዳ ሁሉ ላዩንም በውሃ በመታጠብ ቢያጸዳ ይወደድለታል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ከዐረብ መኳንንት መካከል የነበረን ሠሐብይ ወደ ኢስላም ለመግባት በፈለገ ጊዜ ሰውነቱን እንዲታጠብ አዘውት ነበር፡፡ (አል በይሃቂ 837)

# > ንሠሐ

ንሠሐ፣ ወደ አላህ መመለስ ማለት ነው:: ማንም ሰው ከነበረበት አመጸኝነትና ከሃዲነት ከልቡ በትክክል ወደ አላህ ከተመለሰ ያ ተክክለኛ ንሠሐ ይባላል::

ሙስሊም በእያንዳንዱ የሕይወት እርከን ወደ አላህ መመለስ ወይም ተውባና ምህረትን መለመን ያስፈልገዋል:: የሰው ልጅ በተፈጥሮው ተሳሳች ነው፤ ስለሆነም በተሳሳተ ቁጥር አላህን ምሕረት መለመንና ወደርሱ ንሠሐ መግባት ይኖርበታል::

## የትክክለኛ ንሠሐ መስፈርት ምንድነው?

አንድ ሰው፣ ከክህደት፣ በአላህ ከማጋራትና ከሌሎችም ወንጀሎች በሙሉ ተውበት(ንሠሐ) ሲያደርግ፣ ንሠሐው ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የተወሰኑ ቅድመ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው:: ከነዚህ ከቅድመ መስፈርቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል::

### 1 ወንጀሉን ማቆም

ወንጀል እየሰራ ንሠሐ ገብቻለሁ ቢል ንሠሐው ትክክለኛ አይሆንም:: ከትክክለኛ ንሠሐ በኋላ ወደ ወንጀል ቢመለስ፣ ከዚህ በፊት ያሳለፈው ንሠሐ አይበላሽበትም ግን ለሰራው ወንጀል አዲስ ንሠሐ መግባት ያስፈልገዋል::

### 2 ላሳለፈው ወንጀል መጸጸትና መቆጨት

ንሠሐ(ተውበት)፣ ከአንድበፈፀመው ወንጀል ከማይጸጸትና በሰራው ሃጢኣት ከማይቆጭ ሰው ተቀባይነት አይኖረውም:: ያሳለፋቸውን ወንጀሎች የሚያወራን፣ በዚያም ኩራት የሚሰማውንና የሚኮፈስን ሰው ከተጸጻቾች መመደብ አይቻልም:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ንሠሐ ማለት መጸጸት ነው::» ( ኢብኑ ማጀህ 4252)

### 3 ዳግም ወደ ወንጀሉ ላለመለስ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ

ከንሠሐ በኋላ ወደ ነበረበት ወንጀል ለመመለስ የሚያስብ ሰው ንሠሐው ተቀባይነት አይኖረውም::

## ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዱ እርምጃዎች:

- ነፍሱ የትኛውንም ያክል ከባድ ችግር ወይም እንቅፋት ቢገጥማትም ወደ ነበረበት ወንጀል ላለመመለስ ከነፍሱ ጋር ቃል ኪዳን ይገባል:: ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ)፡- «ሦስት ነገሮች በውስጡ የተገኙለት ሰው የኢማንን ጣዕም አግኝቷል::» ባሉት ንግግራቸው ውስጥ፣ «አላህ ወደ ኢስላም ከመራው በኋላ ወደ ክህደት መመለስን ልክ እሳት ውስጥ መወርወርን እንደሚጠላው መጥላቱ ነው::» የሚለውን ጠቅሰዋል:: (አል ቡኻሪ 21/ ሙስሊም 43)
- ኢማናቸው ከዘቀጠና ወንጀልን ከሚያዘወትሩ ግለሰቦችና ወንጀል ከሚተገበርበት ቦታ መራቅ
- በገራለት አኳኋንና ቋንቋ አላህን እስከሚሞት ድረስ በሃይማኖቱ ላይ እንዲያጸናው መለመንን ማብዛት አበበት:: ከነዚህም ዱዓዎች መካከል በቁርአንና በሐዲስ የተጠቀሱ አሉ፡-
  - «ጌታችን ሆይ ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኃላ ልቦቻችንን አታዘምብልብን፤» (አል ዒምራን ፡ ለ)
  - «አንተ ልቦችን ገለባባጭ የሆንክ ጌታ ሆይ ልቤን በእምነት ላይ አጽናው፥» (አል ቲርሚዚ 2140)



## ከንሠሐ በኋላስ?

አንድ ሰው በትክክል ንሠሐ ከገባና ወደ አላህ ከተመለሰ፣ ወንጀሎቹ ምን የከበዱና የበዙ ቢሆኑም አላህ ወንጀሎቹን በጠቅላላ ይምርለታል፡፡ የአላህ(ሱ.ወ) እዝነት ሁሉን ነገር ያካበበች ነች፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «በላቸው፡ እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ሃጢአትን በሙሉ ይምራልና፤ እነሆ እርሱ መሃሪው አዛኙ ነውና፡፡» (አል ዙመር 53)

አንድ ሙስሊም ትክክለኛ ንሠሐ ከገባ በኋላ ወንጀል የሌለበት ንጹሕ ይሆናል፡፡ ከዚህም አልፎ፣ አላህ (ሱ.ወ) እውነተኛ ተጸጻች የሆነን፣ በትክክል መቆጨትን የተቆጨን ንሠሐ አድራጊ ለየት ባለ ታላቅ ካሳ ይክሰዋል፡፡ መጥፎ ሥራዎቹን በበጎ ይቀይርለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ መልካምም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር፤ እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል፤ አላህም እጅግ መሐሪ አዛኝ ነው፡፡» (አል ፉርቃን 70)

በዚህ መልክ የተገለፀ ሰው፣ ይህችን ንሠሐውን በመጠበቅ ላይ ከፍተኛ ጉጉት ሊያድርበት ይገባል፡፡ በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባና ወደ ኋላ እንዳያፈገፍግም የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ንሠሐውን መጠበቅ አለበት፡፡

## የኢማን ጣዕም ወይም ጥፍጥና

ውዴታው ከማንም በላይ ለአላህና ለመልክተኛው የሆነለት ሰው፣ ሌሎችን የሚወደው ለአላህና ለሃይማኖታቸው ለኢስላም ባላቸው ቀረቤታ ልክ የሆነ፤ ወደነበረበት የክህደትና የማጋራት እንዲሁም የጥመት መንገድ መመለስን ልክ በእሳት መቃጠልን እንደሚጠላ ያክል የጠላ፤ በዚህን ጊዜ በልቡ ውስጥ የኢማንን ጣዕምና ጥፍጥና ያገኛል፡፡ ይህም ከአላህ በሚያገኘው ማበረታቻና እርጋታ፣ በአላህ ድንጋጌዎች በመርካትና በመደሰት፣ እንዲሁም ለቀጥተኛው ጎዳና መመራት ጺጋ ይረጋገጣል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሦስት ነገሮችን በውስጡ ያገኘ ሰው፣ በነርሱ ሰበብ የኢማንን ጣዕም ያገኛል፤ አላህና መልክተኛው ከነርሱ ሌላ ካለ አካል ሁሉ እርሱ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ መሆናቸውን፤ አንድን ሰው ለአላህ ብሎ እንጂ ለሌላ ነገር አለመውደድን፤ አላህ ከርሱ ከገላገለው በኋላ ወደ ክህደት መመለስን ልክ እሳት ውስጥ መወርወርን እንደሚጠላ መጥላትን (በልቡ ውስጥ ያገኘ ሰው፡፡) » (አል ቡኻሪ 21 / ሙስሊም 43)



> አንድ ሙስሊም ወደ ክህደት መመለስን ልክ በእሳት ውስጥ መወርወርን እንደሚጠላ በሚጠላ ጊዜ የኢማንን ጣዕምና ጥፍጥና ያገኛል፡፡

## > ወደ ቀጥተኛው ጎዳና የመመራትንና የንሠሐን ጸጋ ማመስገን



አንድ ሙስሊም አላህ(ሱ.ወ) በርሱ ላይ ከዋላቸው ጸጋዎች ታላቁ የሆነውን፣ ወደ ቀጥተኛው ጎዳና የመመራትንና የንሠሐን ጸጋ ከሚያመሰግንባቸው መንገዶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

### 1 ሃይማኖትን አጥብቆ መያዝና ለሚያጋጥሙ ችግሮች ታጋሽ መሆን

የድልብ ባለቤት የሆነ ሰው፣ ንብረቱ የወሮበሎችና የዘራፊዎች እጅ እንዳያገኘው ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ያደርግለታል፡፡ ለጉዳት ከሚዳርጉት ነገሮች ሁሉ ይከላከለዋል፡፡ ኢስላም ለሰው ዘር በጠቅላላ የተበረከተ ታላቅ ስጦታ ነው፡፡ የአመለካከት አቅጣጫ ብቻ አይደለም፡፡ ወይም ሰዎች ባሻቸው ጊዜ የሚፈፅሙት ስሜትም አይደለም፡፡ እያንዳንዱን የሕይወት ገጠመኝና እንቅስቃሴ የሚቆጣጠርና የሚያስተዳድር ሃይማኖት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ኢሳላምን፣ የቁርኣንን መመሪያ አጥብቀው እንዲይዙ ያዘዛቸውና በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት ማፈግፈግ ሊኖር እንደማይገባ የገለጸላቸው ለዚህ ነው፡፡ ይህም ኢስላም ትክክለኛውና ቀጥተኛው ጎዳና በመሆኑ ነው፡፡

«ያንንም ወዳንተ የተወረደልህን አጥበቀህ ያዝ አንተ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነህና፡፡» ይላል፡፡ (አል ዙኽሩፍ 43)

አንድ ሙስሊም ኢስላምን ከተቀበለ በኋላ በሚያጋጥመው ችግርና መከራ ማዘን የለበትም፡፡ ለችግርና ለመከራ መጋለጥ የአላህ ተፈጥሯዊ ሕግ ነው፡፡ ከኛ በላጭና ታላቅ የነበሩት መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ብርቱ ችግርና መከራ ደርሶባቸው ታግሰዋል፤ ታግለዋል፡፡ የአላህን ነብያት ብንመለከት፣ አላህ ታሪካቸውን ተርኮልናል፤ በምን መልኩ እንደተንገላቱና እንደተሰቃዩ ነግሮናል፤ ከጠላት በፊት የዘመድና የጓደኛ ጥቃት እንደደረሰባቸው ገልጸልናል፤ ሆኖም በአላህ መንገድ ላይ በገጠማቸው ነገር ምንም አልተዳከሙም፤ የነበራቸውን አቋምና እምነት አልቀየሩም አልለወጡም፡፡ ስለዚህ ይህ በአንተም ላይ የደረሰብህ ችግር፣ እምነትህ እውነተኛ፣ እርግጠኛነትህም ጠንካራ በመሆኑ ከአላህ የሆነ ፈተና ነው፡፡ እናም በፈተናው ልክ አንተም በርታ! ይህን ሃይማኖትህን አጥብቀህ ያዝ፤ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዱዓቸው ላይ በብዛት ይደጋግሙ እንደነበረው አንተም አላህን ለምነው፡ «አንተ ልብን ገለባባጭ የሆንክ ጌታ ሆይ! ልቤን በእምነትህ ላይ አጽናልኝ፡፡» በል፡፡ (አል ቲርሚዚ 2140)

ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ሰዎች አምነናል በማለታቸው ብቻ እነሱ ሳይፈተኑ የሚተዉ መኾናቸውን ጠረጠሩን? እነዚያንም ከነሱ በፊት የነበሩትን በእርግጥ ፈትነናል፤ እነዚያንም እውነት የተናገሩትን አላህ በእርግጥ ያውቃል፤ ውሸታሞቹንም ያውቃል፡፡» (አል አንከቡት 2-3)

### 2 በጥበብና በመልካም ግሳፄ ወደ ኢስላም በመጣራት ላይ መታገል

ይህ የሰው ልጅ ለተጎናጸፈው የኢስላም ጸጋ ምስጋና ከሚገለፅባቸው መንገዶች መካከል ትልቁ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአላህ ሃይማኖት ላይ ጽናት እንዲኖር ከሚያደርጉ ምክንያቶችም ዋነኛው ነው፡፡ አንድ ከአደገኛ በሽታ ነፃ የሆነ፣ ሌት ተቀን ሲያንገላታውና ሲያሰቃየው ከነበረው ደዌ ሰውነቱ ጤናማ የሆነለት ሰው፣ እንዲሁም በምን መልኩ ከዚህ በሽታ መገላገያውንና ፍቱን መድሃኒቱን ያወቀ ሰው፣ በሰዎች መሐል ይህን ዕውቀቱን ለማሰራጨት ከፍተኛ ጉጉትና ፍላጎት ያድርበታል፡፡ በተለይም ለቤተሰቦቹ፣ ለቅርብ ዘመዶቹና ለሚወዳቸው ሰዎች ይህን ማስተማሩ ጥርጥር የለውም፡፡ እንግዲህ በሚከተለው መልኩ የሚብራራው ይህ ነው፡፡

# > ወደ ኢስላም መጣራት

### ወደ አላህ መጣራት ያለው ትሩፋት

ወደ አላህ መጣራት ትልቅ ችሮታ ካላቸው ስራዎችና ወደ አላህ ከሚያቃርቡ ነገሮች ላቅ ያለው ነው:: ይህንኑ የሚያደንቁና የሚያበረታቱ የቁርአን አንቀጾችና የሐዲስ ዘገባዎች አሉ:: ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል::

1 ወደ አላህ መጣራት በቅርቢቱ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የመዳኛና የስኬት መንገድ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:- «ከናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ፣ በመልካም ስራም የሚያዙ፣ ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ህዝቦች ይኑሩ፤ እነዚያም እነሱ የሚድኑ ናቸው::» (አል ዒምራን 104)

2 የአንድ ወደ ኢስላም ጥሪ አድራጊ ሰው ንግግር አላህ ዘንድ በላጭና ተወዳጅ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) የአንድን ተጣሪ ንግግር ሲያደንቅ እንዲህ ብሏል:-«ወደ አላህ ከጠራና መልካምንም ከሰራ፤ እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለም ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው?» (አል ፉሲለት 43) ከርሱ ንግግር የበለጠ ያማረ ንግግር የለም:: ይህ ዓይነቱ ሰው፣ ሰዎች ጌታቸውን፣ ፈጣሪያቸውን፣ እንዲሁም ከማጋራት ጭለማዎች ወደ ኢማን ብርሃን ያወጣቸውን ጌታቸውን እንዲያመልኩ የሚያመለክትና የሚመራ ሰው ነው::

3 ጥሪ ማድረግ(ዳዕዋ)፣ የአላህን ትዕዛዝ መፈፀምም ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:- «ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ::» (አል ነሕል 125) ስለሆነም አንድ ተጣሪ ወይም ዳዒ ወደ ኢስላም ሲጣራ በብልሃት ሊሆን ይገባል:: ሁሉንም ነገር በቦታው ማኖር አለበት:: ይኸውም ለሚጠራቸው ወገኖች የሚስማሙና አንገብጋቢ የሆኑ ነገሮችን በመምረጥና በማዘጋጀት እንደየደረጃቸው ምክርና ጣፋጭ የሆነ ተግሳጽን መስጠት ነው:: ለዘብ ባለና ገር በሆነ መልኩ ከነርሱ ጋር መወያየትና ለነርሱ መመራት ቅርብ የሆነውን አካሄድ መጠቀም አለበት::

4 ወደ አላህ መጣራት የመልክተኞች ሁሉ፣ በተለይ የነቢያችን የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባር ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እሳቸውን በሰው ልጆች ላይ መስካሪ አድርጓቸዋል:: ለምእመናን በጀነት አብሳሪ፤ ለካሃዲያንና ለአመጸኞች ከእሳት አስጠንቃቂ አድርጎ ልኳቸዋል:: ወደ አላህ የሚጣሩ በሰው ዘር ውስጥ መለኮታዊ ብርሃንን የሚያሰራጩም ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:- «አንተ ነብይ ሆይ እኛ መስካሪ አብሳሪና አስፈራሪም አድርገን ላክንህ፤ ወደ አላህም በፈቃዱ ጠሪ አብሪ ብርሃንም (አድርገን ላክንህ) አማኞችንም ከአላህ ዘንድ ለነርሱ ታላቅ ችሮታ ያላቸው መኾኑን አብስራቸው::» (አል አሕዛብ 45-47)

5 ጥሪ ማድረግ ወይም ዳዕዋ የማይዘጋ የመልካም ነገር በር ነው:: ጥሪህን የተቀበለና በአንተ እጅ የተመራ ሰው ካለ ወይም ከገጠመህ ላንተም የእርሱ ዓይነት ምንዳ አለልህ:: በሠላቱ፣ በአምልኮው፣ ሰዎችን ባስተማረ ቁጥር ላንተም ምንዳው ይጻፍልሃል:: እንዲህ ያለው ተጣሪ የሚያገኘው ጸጋ ምንኛ የላቀ የአላህ ጸጋ ነው:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «ወደ ቀጥተኛው ጎዳና የተጣራ ሰው፣ እርሱን ከነርሱ ምንዳ ምንም ነገር ሳይጎድል የተከተሉት ሰዎች ምንዳ ይጻፍለታል::» (ሙስሊም 2674)

6 የአንድ ዳዒ ምንዳ ከዱንያና በውስጧ ካሉ መጣቀሚያ ነገሮች ሁሉ የተሻለና የበለጠ ነው::

አንድ ዳዒ ምንዳውን የሚያገኘው ከአላህ ዘንድ ነው:: ከሰዎች የሚጠብቀው ምንም ዓይነት ምንዳ የለም:: ምንዳው ትልቅ የሚሆነውም ለዚህ ነው::

ሊጋሱ አላህ ደግሞ ለሚወደው ትልቅን ነገር እንጂ አይሰጥም:: አላህ (ሱ.ወ) በነቢዩላህ ዩኑስ (ዐ.ሰ) አንደበት እንዲህ ይላል:- «ብትሸሹም (አትጎዱኝም) ከምንዳ ምንንም አልለምናችሁምና:: ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፤ ከሙስሊሞች እንድኾንም ታዝዣለሁ::» (ዩኑስ 72) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «አንድን ሰው አላህ በአንተ ሰበብ ቢመራልህ፣ ቀያይ ግመሎች ላንተ ከሚኖሩህ ይሻላል::» (አል ቡኻሪ 2847 / ሙስሊም 2406)

## የትክክለኛ ዳዕዋ(ጥሪ) መገለጫዎች

አላህ(ሱ.ወ)፣ ትክክለኛ ጥሪ ከሌላ የጥሪ ዓይነት የሚለይበትን ባህሪ አብራርቷል፡፡ ትክክለኛ ጥሪ የሚከተሉት መገለጫዎች አሉት፡፡

### 1 መረጃና ዕውቀት

አንድ ተጣሪ ወይም ዳዒ ወደርሱ በሚጠራበት ነገር ዕውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚናገረውን ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላቸዋል፡- «በል፤ይህች መንገዴ ናት፤ ወደ አላህ እጠራለሁ፤ እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን፡፡» (ዩሱፍ 108)

አንተ ነብይ ሆይ! መንገዴ፣ መመሪያዬ ይህ ነው፤ በዕውቀትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ወደ አላህ መጣራት ነው፤ ይህ ደግሞ እኔን የተከተሉ ተጣሪዎችም መንገድ ነው ብለህ ግለጽ እያላቸው ነው፡፡

አንድ ተጣሪ ወደ አላህ መንገድ ለማጣራት የግድ በርካታ ነገሮችን ማወቅ አይጠበቅበትም፡፡ አንድን ሸሪዓዊ ሕግ ካወቀ ወደዚያ ነገር የመጣራት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ አላህን በብቸኝነት መገዛትን (ተውሒድን) ከተማረ፣ ይህንኑ ለሰዎች የማድረስ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ የኢስላምን መልካምነት ካወቀ ያወቀውን ያክል ለሰዎች ማስተላለፍ አለበት፡፡ የሚያውቀው አንዲትን የቁርአን አንቀጽ ቢሆንም እንኳን ለሰዎች የማድረስ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«አንዲት አንቀጽ ብትሆንም ከኔ የሰማችሁትን አስተላልፉ፡» (አል ቡኻሪ 3274)

ሠሓቦችም እንዲሁ ነበሩ፡፡ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት ኢስላምን ይቀበሉና በትንሽ ቀናት ውስጥ የሃይማኖቱን መሰረታዊ መርሆችንና መመሪያዎችን ይማራሉ፤ ከዚያም ወደ ጎሳዎቻቸው በመመለስ ወደ ኢስላም ጥሪ ያደርጋሉ፤ እንዲሰልሙ ያነሳሱዋቸዋል፡፡ ባህሪያቸው፣ ሰዎች ኢስላምን እንዲወዱና እንዲቀበሉ የሚጋብዝና የሚያበረታታ ነበር፡፡

### 2 በዳዕዋ ውስጥ ብልሃትን መጠቀም

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- «ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ፤ በዚያችም እርሷ መልካም በኾነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው፡፡» (አል ነሕል 125)

ብልሃት ማለት፡ መስራት የሚገባን ነገር በሚጣጣም መልኩ መስራትና ከሚሰራው ስራ ጋር የሚስማማ የሆነን ጊዜና ቦታን መምረጥ ነው፡፡

የሰዎች ዝንባሌና ወደ ልባቸው የመግቢያ መንገድ የተለያየ ነው፡፡ ነገርን የመረዳትና የመገንዘብ ችሎታቸውም አንድ ዓይነት አይደለም፡፡ ስለሆነም ዳዕዋ አድራጊ ሰው ለእያንዳንዱ ሰው የሚስማማ የሆነን ዘዴ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ እጅግ በጣም ጫና ሊያሳድሩ የሚችሉ የሕይወት ገጠመኞችን ሊጠባበቅና ለዳዕዋ አመቺ በሆነ መልኩ ሊጠቀምባቸው ይገባል፡፡

ዳዕዋ ለሚያደርግላቸው ሰዎች ምንጊዜም ገርነትን፣ መልካም ግሳጼንና እዝነትን ማንጸባረቅ ይኖርበታል፡፡ እልህና ንትርክ ውስጥ የማይከት የሆነ ረጋ ያለ ውይይት ማካሄድም አስፈላጊ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች ጋር የነበራቸውን ገርነትና ይቅር ባይነት በአድናቆት ያወሳው ሲሆን፣ ልበ ደረቅ፣ ጨካኛ ቢሆኑ ኖሮ በዙሪያቸው የነበሩት ትተዋቸው ይበተኑ እንደነበረም አስጠንቅቋል፡፡ እንዲህም ይላል፡-

«ከአላህም በሆነ ችሮታ ለዘብክላቸው፤ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡» (አል ዒምራን 159)



## ቤተሰብን መጣራት

አላህ ኢ.ስላምን እንዲቀበል የቻረው ሰው፣ ቤተሰቦቹንና የቅርብ ዘመዶቹን ወደ ኢ.ስላም የመጥራት ከፍተኛ ጉጉት ሊያድርበት ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ከማንም በላይ ለርሱ ቅርቦቹና ወዳጆቹም በመሆናቸው ነው፡፡ ለዚህም ከነርሱ የሚደርስበትን ስቃይና እንግልት በትግስት ማሳለፍ አለበት፡፡ የተለያዩ በብልሃት የተሞሉ መንገዶችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

«ቤተሰብህንም በስግደት እዘዝ፤ በርሷም ላይ ዘውትር፡፡» (ጧሃ 132)

አንዳንድ ሰዎች በሚያደርጉት ዳዕዋ ባዕድ ሲቀበላቸው ቤተሰባቸውና የቅርብ ዘመዳቸው ግን እንቢተኛ ሲሆን እንመለከታለን፡፡ በዚህም እጅግ ይበሳጫሉ፤ ተስፋም ይቆርጣሉ፡፡ ነገር ግን ስኬታማ ዳዕዋ አድራጊ፣ የዳዕዋ ስልቶችንና አካሄዶችን በመቀያየር በተለያየ መንገድ ዳዕዋ በማድረግ የሚታገልና ዳዕዋ ለሚያደርግላቸው ሰዎች አላህ(ሱ.ወ) እንዲመራቸው የሚማጸንላቸው የሆነ ሰው ነው፡፡ እልህ አስጨራሽ በሆኑ አጋጣሚዎች ላይም ተስፋ አይቆርጥም፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአጎታቸው አቡ ጣሊብ ጋር የነበራቸውን ታሪክ ብንመለከት፣ አጎታቸው ይረዳቸው፣ ይደግፋቸው፣ ከቁረይሾችም ጥቃት ይከላከልላቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢ.ስላምን አልተቀበለም፤ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እርሱን ወደ ኢ.ስላም በመጥራት የሚያደርጉትን ሙከራ እስከመጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ አላቋረጡም፡ ፡ በዚያ ቅጽበት ላይ ሆኖ፡- «አጎቴ ሆይ ላኢ.ላሃ ኢ.ለላህ በል፤ አላህ ዘንድ የምሞግትልህ የሆነችን ቃል በል፡፡» አሉት፡፡ (አል ቡኻሪ 3671/ ሙስሊም 24)

ነገር ግን ለርሳቸው ጥሪ ምላሽ ሳይሰጥ በክህደት ላይ ሞተ፤ አላህም የሚከተለውን አንቀጽ አወረደ፤ «አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም፤ ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል፤ እርሱም ቅኖቹን ዐዋቂ ነው፡፡» (አል ቀሦሦ 56 )

አንድ ዳዕዋ የሚያደርግ ሰው የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ሃይማኖቱን የማስራጨትና ሰዎችን ወደ መልካም ነገር የመምራት ግዴታ አለበት፡፡ ልቦች በአላህ እጅ ናቸው፤ የሻውን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል፡፡



## > አካባቢህና ቤተሰብህ

አንድ አዲስ ሙስሊም ወደ ኢስላም ከገባበት ጊዜ አንስቶ ከሚያውቃቸው ሰዎች እንዲሁም ከሙስሊም ወይም ሙስሊም ካልሆኑ ዘመዶቹ ጋር ያለውን ግንኙነትና ቅርርብ ይበልጥ ማጠናከር አለበት፡፡ ኢስላም እራስን ወደ ማግለልና ወደ ባይተዋርነት የሚጣራ ሃይማኖት አይደለም፡፡

ለሰዎች በጎ መዋልና ከነርሱ ጋር በመልካም ስነ ምግባር መኗኗር፣ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) መልካም ስነ ምግባሮችን ለማሟላት የተላኩበት የሆነውን ሃይማኖት ለሌሎች ከሚያስተዋውቁ መንገዶች ሁሉ በላጩና ውጤታማው ነው፡፡



የላቁ ስነ ምግባሮች በተግባር የሚተረጎምባቸውና የተከበሩ መልካም ግንኙነቶች የሚንጸባረቅባቸው እርምጃዎች የመጀመሪያው ከቤተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት ነው፡፡ (ገጽ፣ 213 ተመልከት)

የሚከተሉት መርሆች አንድ አዲስ ሙስሊም ከቤተሰቡ ጋር በሚኖረው ትስስር ሊያውቃቸው የሚገቡ ናቸው፡

## > ወደ ኢስላም ከተገባ በኋላ ያው ቤተሰባዊ ሕይወት

### ባልና ሚስት በአንድነት ከሰለሙ

- ባልና ሚስት አብረው ከሰለሙ የነበራቸው የጋብቻ ውል ወይም ኒካሕ በኢስላምም ይጸናል፤ የጋብቻውን ውል እንደ አዲስ ማደስ አያስፈልጋቸውም፡፡

ግን ይህ የማያካትታቸው ተንጠለው የሚወጡ ሁኔታዎች አሉ፡

1. ጋብቻውን የፈፀመው በሸሪዓው ማግባት ከማይፈቀድለት(መሓሪሞች) መካከል ከአንዷ ጋር ከሆነ፡ ለምሳሌ ከእናቱ ወይም ከእህቱ ወይም ከአክስቱ ጋር ጋብቻ ፈፅሞ የነበረ ከሆነ፣ ከሰለሙ ጊዜ ጀምሮ እንዲፋቱ ማድረግ የግድ ነው፡፡ (ገጽ፣ 200 ተመልከት)

2. ሁለት እህትማማቾችን ወይም ሴቷን ከአክስቷ ጋር ወይም ሴቷን ከየሹሜዋ ጋር በአንድነት አግብቶ ከሆነም አንዳቸውን የመፍታት ግዴታ ይኖርበታል፡፡

3. እሱና ሚስቶቹ በአንድ ላይ ቢሰልሙና የሚስቶቹ ብዛት ከአራት በላይ ቢሆን፣ ከአራት ሴቶች በላይ ስለማይፈቀድለት ከነርሱ መካከል አራቱን መርጦ በማስቀረት የተቀረቱን ይፈታቸዋል፡፡

## እርሱ ሰልሞ ሚስቱ ባትሰልም የሚኖረው ድንጋጌስ ምንድነው?

በዚህ ጊዜ የሴቷ ሃይማኖት ግምት ውስጥ ይገባል፤ የመጽሐፍት ባለቤት፣ ማለትም አይሁድ ወይም ክርስቲያን ልትሆን ትችላለች፤ አለያም እንደ ቡድሂዝም ሂንዱዊዝምና ጣዖት አምላኪያን መጽሐፍት የለሽ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ልትሆን ትችላለች፤ ወይም በሃይማኖት የማታምን ሃይማኖት አልባ ልትሆንም ትችላለች፡፡ እና ፍርዱ ምንድን ነው?

### 1 የመጽሐፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ የሆነች ሚስት

አንድ ሰው ቢሰልምና ሚስቱ ግን ባትሰልም፣ የመጽሀፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ ብትሆን፣ የጋብቻው ውል በነበረበት ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሙስሊም አንዲትን የመጽሐፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ ሴትን ቢያገባ አይከለከልም፡፡ ስለሆነም ይህም የሰለመ ሰው ከሚስቱ ጋር የጋብቻ ሕይወቱን መቀጠሉና በሚስትነት እሷን ይዞ መቆየቱ የተሻለ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ዛሬም መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፤ የነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለናንተ የተፈቀደ ነው፤ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፤ ከምእመናት ጥብቆቹም ከነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፉን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፡ ፡» (አል ማኢዳ 5)

ነገር ግን ባገኘው አጋጣሚና ብልሃት በመጠቀም እሷን ወደ እስልምና በመጥራቱ ላይ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

### 2 የመጽሐፍት ባለቤት ሃይማኖት ተከታይ ያልሆነች ሚስት

ሰውየው ሰልሞ ሚስቱ ኢስላምን ለመቀበል ባትሆንና በሃይማኖቷ የመጽሐፍቱ ባለቤት ተከታይ -አይሁድ ወይም ክርስቲያን- ባትሆንና ቡድሂስት ወይም ሂንዱዊስት ወይም ጣዖት አምላኪ ወይም የሌላ እምነት ተከታይ ከሆነች፡-

አንዲት ፍች ሴት የምትጠብቀውን ወቅት ያክል ይጠብቃል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል ሰንጠረዥ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

- በዚህ ቆይታ ውስጥ ከሰለመች ሚስትነቷ ይቀጥላል፡፡ የጋብቻውን ውል በአዲስ መልክ መፈፀም አያስፈልግም፡፡

- ወቅቱ እስከሚያልቅ ድረስ ተጠብቃም ኢስላምን ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነች ግን ጋብቻው ይፈርሳል፡፡

ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሰለመችና ሊያገባት ከፈለገ እንደ አዲስ ለጋብቻ ያጫትና ያገባታል፡፡ አላህ ሱ.ወ እንዲህ ይላል፡- «የከሃዲዎቹንም ሴቶች የጋብቻ ቃል ኪዳኖች አትያዙ፡፡» (አል ሙምተሒናህ 10)

ከሰለማችሁ በኋላ ከመጽሐፍት ባለቤት ሌላ የካሃዲያንን ሴቶች በጋብቻ ቃል ኪዳኖች አትያዙ ማለት ነው፡፡



## የተፈታች ሴት ዒዳ (ፍች የሚፀናበት ጊዜ)

| | |
|---|---|
| 1 | የጋብቻ ውል ፈፅሞ፣ ይዟት ያልገባት- ግብረ ስጋ ግንኙነት አብሯት ያልፈፀመ- ወይም አብሯት ኑሮ ያልጀመረ ሰው ከፈታት፣ ፍቺውን በመፈፀሙ ብቻ ከርሱ ትለያለች፡፡ በያዝነው ርዕስ መሰረት ደግሞ እሱ ብቻውን በመስለሙ ብቻ ከርሱ ትለያለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-<br><br>«እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ምእመናትን ባገባችሁና ከዚያም ሳትነኩዋቸው በፊት በፈታችኋቸው ጊዜ ለናንተ በነሱ ላይ የምትቆጥሩዋት ዒዳ ምንም የላችሁም፡፡» (አል አህዛብ 49) |
| 2 | የእርጉዝ ሴት ዒዳ፣ ያረገዘችውን በመውለዷ ያበቃል፡፡ ጊዜው ቢረዝምም ቢያጥርም ልዩነት የለውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-<br><br>«የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው፡፡» (አል ጠላቅ 4) |
| 3 | እርጉዝ ያልሆነችና የወር አበባ የምታይ ሴት ዒዳዋ ከተፈታች በኋላ ወይም ባል ከሰለመ በኋላ ሦስት ሙሉ የወር አበባ ማየት ነው፡፡ የወር አበባ ደም መጥቶባት ትጸዳለች፤ ከዚያም በድጋሚ ይመጣባትና ትጸዳለች፤ ከዚያም ለሦስተኛ ጊዜ ይመጣባትና ትጸዳለች፤ ሦስት ሙሉእ የወር አበባ ጊዜ የሚባለው ይህ ነው ፡፡ በወር አበባዎቹ መሐከል ያለው ጊዜ ቢረዝምም ባይረዝምም ልዩነት አይኖረውም፡፡ ይህች ሴት ከሦስተኛው የወር አበባ መጽዳት በኋላ ከታጠበች ዒዳዋ ያበቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-<br><br>«የተፈቱ ሴቶችም ነፍሶቻቸውን (ከማግባት) ሦስትን ቁሩእ (ሦስትን አደፍ ወይም ሦስትን የአደፍ ጥራት) ይጠብቁ፡፡» (አል በቀራ 228) |
| 4 | ያልደረሰች ሕፃን በመሆኗ፣ ወይም ዕድሜዋ በመግፋቱ፣ ወይም ባለባት ዘውታሪ በሽታ ምክንያት የወር አበባ የማታይ ሴት፣ ከተፈታችበት ጊዜ፣ ወይም ባሏ ከሰለመበት ጊዜ አንስቶ ሦስት ወራቶችን ትጠብቃለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- «ከሴቶቻችሁ ከአደፍ ያቋረጡት (በዒዳቸውሕህግ) ብትጠራጠሩ ዒዳቸው ሦስት ወር ነው፤ እኒያም ገና አደፍን ያላዩት (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው፡፡)» (አል ጠላቅ 4) |



## ሚስት ካልሰለመች

የመጽሐፍት ባለቤት -አይሁድ ወይም ክርስቲያን- ነች?

- አይቻልም(በፍፁም)
- አዎን → ጋብቻው በነበረበት ይቀጥላል፤ ማደስ አይፈልግም፤ ወንድየው ለሚስቱ ተስማሚ በሆኑ መንገዶች ሁሉ በመጠቀም ጥሪ ሊያደርግላት ይገባል።

አይደለችም፡ የመጽሀፍት ባለቤት ካልሆነች በመጀመሪያ ወደ ኢስላም ጥሪ ያደርግላታል፤ ከዚያም በዒዳ ወቅት ኢስላምን ተቀብላለች ወይስ አልተቀበለችም ማለትን እናያለን።

- አይቻልም(በፍፁም) → የዒዳዋ ወቅት እስከሚያበቃ ድረስ ኢስላምን ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነች፣ የጋብቻው ውል ይፈርሳል፤ በሰለመች ጊዜ በአዲስ የጋብቻ ውል ሊጋቡ ወይም ሊማለሱ ይችላሉ።
- አዎን → እሷ በኢስላም ውስጥም ሕጋዊ ባለቤቱ ናት የጋብቻቸውን ውል ማደስ አያስፈልግም።

## ሴቷ ሰልማ ባሏ ባይሰልም ፍርዱ ምንድን ነው?

ሁለት ባልና ሚስቶች አብረው ከሰለሙ፣ እንደ ወንድምና እኅት በኢስላም ሊጋቡ የማይፈቀድላቸው ካልሆኑ በስተቀር የጋብቻቸው ውል ባለበት ይጸናል። (ገጽ፣ 199 ተመልከት)



ሴቷ ሰልማ ባልየው ኢስላምን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

በመስለሟ ብቻ የጋብቻው ውል ወደ ምርጫ ይቀየራል፤ ማለት ሚስት የመምረጥ መብት ይሰጣታል።

- የባሏን መስለም በትዕግስት መጠበቅ። የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ለባለቤቷ የኢስላምን እውነታ ማብራራትና መግለጽ አለባት። አላህ ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንዲመራው መማጸን ይኖርባታል። ከረዥም ጊዜ በኋላ ቢሆንም በዚህ ጥረቷ ከሰለመ መስለሙን እየተጠባበቀች እስከሆነ ድረስ በመጀመሪያው የጋብቻ ውል መሰረት በሚስትነቷ ከሱ ጋር መኖር ትጀምራለች። ከመስለሙ በፊት ግን ከእሷ ጋር እንዲተኛ ልትመቻችለት ወይም ልትፈቅድለት አይገባትም።

- ይሰልማል የሚል ተስፋ የማይጣልበት ነው በምትልበት ጊዜ ፍቺ የመጠየቅና የጋብቻውን ውል የማፍረስ መብት አላት።

ከሰለመች ጊዜ አንስቶ በሁለቱም ሁኔታዎች ለካሃዲ ባሏ እራሷን ለግንኙነት ማመቻቸት አይፈቀድላትም። እራሷን ማመቻቸቷ እርም ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡ - ‹‹አማኞችም መኾናቸውን ብታውቁ ወደ ከሃዲዎቹ አትመልሱዋቸው እነርሱ (ሴቶቹ) ለነርሱ የተፈቀዱ አይደሉም፤ እነርሱም (ወንዶቹ) ለነርሱ አይፈቀዱምና።›› (አል ሙምተሒና 10)

ሀዲስ ህይወትህ

በዚህ መመሪያ መሰረት አንዲት ሴት ከሰለመችበት ጊዜ አንስቶ የሚከተለውን መፈፀም ይኖርባታል፡

1. ከሰለመችበት ጊዜ አንስቶ የምታገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅማ በብልሃትና በመልካም ተግሳጽ ባሏን ወደ ኢስላም መጥራት አለባት፡፡

2. ባል ኢስላምን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ፣ እርሱን ለማሳመን ካልቻለች፣ ካልተሳካላት፣ ወይም በርካታ ሙከራዎችን አድርጋ ተስፋ የመቁረጥ ደረጃ ላይ ከደረሰች፤ በፍጥነት ከርሱ ጋር የምትፋታበትንና የምትለያይበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርባታል፡፡

3. ለመፈታትና ከሱ ጋር ለመለያየት የሚወስድባት ጊዜ የሚረዝም ከሆነ በመካከላቸው ያለው የጋብቻ ውል ሕጋዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባል በዚህ መሐከል ከሰለመ የዒዳ ወቅት ቢጠናቀቅም በመጀመሪያው የጋብቻ ውል ትዳራቸው መቀጠል ይችላል፡፡ አስፈላጊው ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ባል ካልሰለመና ዒዳው ካለቀ ግን የጋብቻው ውል ይፈርሳል፡፡

4. የፍቺው ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ሚስት ትዳር በመሰረተችበት ቤት ውስጥ መቆየት ትችላለች፤ ይሁን እንጂ ከሰለመችበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ቆይታ ውስጥ ለግብረ ስጋ ግንኙነት እራሷን ለባሏ ማመቻቸት አይፈቀድላትም፤ እርም ነው፡፡

### የሕፃናት መስለም

ሰዎች በሙሉ የሚወለዱት በተፈጥሯዊው እምነት በኢስላም ላይ ነው፡፡ ሌሎች ሃይማኖቶች ወላጆቻቸው በሚያስተምሯቸው ትምህርት ምክንያት በደባልነት የሚገቡባቸው ናቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ልጅ ሁሉ የሚወለደው በተፈጥሯዊ እምነት- በኢስላም- ላይ ነው፡፡ ወላጆቹ ግን አይሁድ ወይም ክርስቲያን ወይም እሳት አምላኪ ያደርጉታል፡፡» (አል ቡኻሪ 1292 / ሙስሊም 2658)

ከካሃዲያን ቤተሰብ ተወልደው በሕፃንነታቸው የሞቱ ልጆች፣ በዚህ ዓለም ከነሱ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ልክ ከካሃዲያን ጋር የምናደርገው ዓይነት ነው፡፡ አላህ ሚስጥርንና ከዚያም በላይ የተደበቀን ነገር ዓዋቂ ነው፤ እርሱ ዘንድ አንድም ሰው አይበደለም፡፡ እነኚህ ልጆች በትንሳኤው ቀን ፈተና ያቀርብላቸዋል፤ ይፈተናሉ፤ በዚያ ፈተና ታዛዥ የሆነ ጀነት ይገባል፤ አመጸኛ የሆነ ደግሞ እሳት ይገባል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ አጋሪያን ልጆች በተጠየቁ ጊዜ፡- «አላህ ገና ሲፈጥራቸው ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ ያውቃል፡፡» በማለት መልሰዋል፡፡ (አል ቡኻሪ 1317)

## በዱንያ ላይ የካሃዲያን ልጆች ሰልመዋል የምንለው መች ነው?

የሕፃናትን መስለም ለማጽደቅ የተለያዩ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ። እነሱም፡

1. ወላጆች ከሰለሙ፤ ወይም አንዳቸው ከሰለመ፤ ልጅ ከወላጆቹ መካከል በሃይማኖት የተሻለ የሆነውን ይከተላል።

2. ለሃላፊነት ያልበቃ ወይም ያልጎረመሰ፣ ነገር ግን ክፉና ደጉን የለየ ታዳጊ ሕፃን ከሰለመና ወላጆቹ ካልሰለሙስ?

   አንድ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲያገለግል የነበረ አይሁድ ታዳጊ ልጅ ከዕለታት አንድ ቀን ታሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሊጠይቁት መጡና ከራሱ አጠገብ ቁጭ ብለው «ስለም» አሉት፤ የልጁ አባት አጠገቡ ነበርና ልጁ ወደ አባቱ ተመለከተ፤ አባቱም «የቃሲምን አባት ታዘዛቸው» አለው፤ ልጁም ሰለመ

   ከዚያን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከልጁ ዘንድ ሲወጡ፣ «ይህን ልጅ ከእሳት ነፃ ያወጣው አላህ የተመሰገነ ይሁን» አሉ። (አል ቡኻሪ 1290)

ወላጆቹ በአንድነት ነው የሰለሙት ወይስ አንዳቸው ብቻ ነው የሰለመው?

- አዎን → አንድ ላይ ነው የሰለሙት፡ እስልምናው ይጸድቃል፤ በሙስሊሞች ሕግና ደንብ መሰረት ይኗኗራል።
- አይቻልም(በፍፁም) ↓

ከቤተሰቡ ተነጥሎ ለብቻው ነው የሰለመው?

- አዎን → አዎ፡ የሚናገረውን የሚገነዘብና ክፉና ደጉን የሚለይ ከሆነ በዱንያ ላይ መስለሙ ይጸድቅለታል። ይህ የኢስላም ሊቃውንት ስምምነት ነው። በአኼራም ይጠቀመዋል፤ ያድነዋል፤ በሚል ሙስሊሞች በሙሉ በአንድ ድምፅ አጽድቀውታል።
- አይቻልም(በፍፁም) ↓

የከሃዲያን ልጆች ሲሞቱ፣ እነሱን በተመለከተ በዱንያ ላይ ያለው ግንኙነታችን የሚከናወነው ከከሃዲያን እንዳለን ግንኙነት ዓይነት ነው። አላህ ሚስጥርና ከርሱም በላይ የተደበቀን ነገር ዐዋቂ ነው፤ «ጌታህ አንድንም ሰው አይበድልም»፤ እናም የትንሳኤ ቀን ይፈትናቸዋል፤ በፈተናው ለርሱ ታዛዥ የሆነ ወደ ጀነት ይገባል፤ ያመፀ ደግሞ ወደ እሳት ይገባል።

## > ከሰለሙ በኋላ ስም መቀየር የተወደደ ተግባር ነውን?

በመሰረቱ አንድ ሰው ሲሰልም የነበረውን ስም ሳይቀይር በነበረው ስሙ መጠራት አለበት፤ በሡሐባ ዘመን ስምን መለወጥ ወይም መቀየር በሰፊው የሚታወቅ ጉዳይ አልነበረም፤ ብዙ ሰዎች ሰልመዋል፤ ግን በነበራቸው ዐረብኛ ባልሆነ ስማቸው ሲጠሩ ነበር፡፡ ነገር ግን መጥፎ መልዕክትን ያዘለ ከሆነ ባዘለው መጥፎ መልክት ምክንያት ስሙ ይቀየራል፡፡




በሚከተሉት ሁኔታዎች ስምን መቀየር ግዴታ ይሆናል፡

1 ከአላህ ሌላ ላለ አካል ተገዢነትን የሚያመለክት ከሆነ ወይም ከኢማን ጋር የሚፃረር የሆነ መልክትን የያዘ ከሆነ ይቀየራል፡፡

ለምሳሌ፡ ስሙ ገብረ እገሌ፣ መሲሕ፣ ወይም ገብረ ነብይ፣ ወይም የዚህ ዓይነት ከሆነ ወይም የስሙ ትርጉምና መልዕክት ከኢማን ጋር የሚቃረንና የሚጋጭ ከሆነ ይቀየራል፡፡ ለምሳሌ ሹኑዳ «የአላህ ልጅ» ማለት ነው፤ አላህ ከእንዲህ ዓይነቱ ፍፁም የላቀና የጠራ ነው፡፡

ወይም በአላህ ልዩ ባህሪያቶችና መጠሪያዎች መሰየም

ለምሳሌ፣ ንጉሠ ነሥትና የመሳሰሉት የማዕረግ መጠሪያዎች፣ አላህን ብቻ ገላጭ የሆነን ነገር ወደ ባሪያው የሚያስጠጋ የሆነ ስያሜ ይቀየራል፡፡

2 መጥፎ መልዕክትን ያዘለ ወይም በተፈጥሮ ማንኛውም ጤናማ ነፍስ የሚጠላውና የሚያወግዘው የሆነ መጠሪያ ከሆነ ይቀየራል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ከምግብና ከመጠጥ፣ እንዲሁም በሕይወታችን ውስጥ ከሚያጋጥሙን ጉዳዮች መጥፎና ጎጂ የሆኑትን እርም አድርጎብናል፡፡ ስለሆነም ከኢስላ በኋላ መጥፎ ትርጓሜ ባላቸው ስያሜዎች መጠራት አይፈቀድም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡ - «በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፤ከእምነት በኋላ የማመጥ ስም ከፉ፡፡» (አል ሁጁራት 11)

3 ስያሜው ሙስሊም ባልሆኑ ሕዝቦች ዘንድ ሃይማኖታዊ መልዕክት ያዘለ ከሆነ ወይም ሙስሊም ባልሆኑ ሃይማኖተኞች ዘንድ የሃይማኖታቸው መገለጫ ተደርጎ በሰፊው የሚታወቅ ከሆነ ይቀየራል፡፡

ለምሳሌ፡ ጴጥሮስ፣ ጊዮርጊስ፣ ዮሐንስ፣ ጳውሎስ እና የመሳሰሉት ክርስቲያኖች ዘንድ በሰፊው የሚታወቁ ስሞች ይቀየራሉ፡፡

ይህን ዓይነቱን ስያሜ ምንም ዓይነት መሰል መልዕክትን ያላዘለ ወደ ሆነ ስያሜ መቀየር አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በኢስላማዊ ሕግ መሰረት፣ እራስን ለጥራጣሬ የሚያጋልጡ ነገሮችን መራቅ ግዴታ ስለሆነና በዚህ ዓይነቱ ስሞች መጠራት ከካሃዲያን ጋር ስለሚያመሳስል ነው፡፡

አዲሱ ሕይወትህ

ለሚከተሉት ነገሮች ስምን መቀየር የተወደደ ተግባር ነው፡፡

አዲሱ ስያሜ አላህ ዘንድ ተወዳጅ ከሆነ፤ ለምሳሌ ይጠራበት የነበረን ስም ወደ ዐብደላህ ወይም ዐብዱረህማን እንዲሁም ለአላህ ባርነትን ገላጭ ወደሆነ ስም ከሆነ፣ እነኚህ ስሞች የሚወደዱ ስያሜዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ይህ ወደ ኢስላም ከመግባት ጋር ምንም ዓይነት ትስስር የለውም፡፡

- ያለ ምንም ምክንያት ስምን መቀየርም ይቻላል፡ ፡ ለምሳሌ ዐረብኛ ያልሆነ ስሙን ወደ ዐረብኛ መቀየር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ የሚወደድ ተግባር ነው አይሰኝም፡፡ ወደ ኢስላ ከመግባት ጋርም ግንኙነት የለውም፤

የአንድ መጠሪያ ስም ትርጓሜ ከሃይማኖትና እምነት ጋር ይቃረናልን?

- አይቻልም(በፍፁም) ↓
- አዎን → አዎን፡ ይህ ዓይነቱ ትርጓሜ ያለውን ስም መቀየር ግዴታ ነው፤

ከሙስሊሞች ሌላ ባሉ ማህበረሰቦች ስሙ ሃይማኖታዊ መልዕክት አለውን? ወይም ሙስሊም ባልሆኑ ሃይማኖተኞች ዘንድ ይዘወተራልን?

- አይቻልም(በፍፁም) ↓
- አዎን → አዎን፡ አደጋን ለመከላከል ሲባል መቀየሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ከመመሳሰል ለመራቅ ሲባልም መቀየሩ አስፈላጊ ነው፡፡

ነፍሶች የሚጠሉት የሆነ ትርጓሜን የያዘ ነውን?

- አይቻልም(በፍፁም) → የተጠቀሱትን ዓይነት ትርጓሜ የያዘ ካልሆነ መቀየሩ ግዴታ አይደለም፤ ኢስላም በተስፋፋባቸው በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት ውስጥ የነበሩ በርካታ ሙስሊሞች ዐረብ ያልሆኑ ስሞቻቸውን አይቀይሩም ነበር፡፡ ያለ ምክንያትም ቢሆንም አንድ ሰው ስሙን መቀየር ይችላል፡፡ በተለይ ደግሞ ወደ አላህ የሚያስወድዱና ዐብደላህና ዐብዱረሕማን ወደ ሚባሉ ስሞች ለመቀየር አስበ ከሆነ ስሙን መቀየሩ ተወዳጅ ነው፡፡
- አዎን → ሰውየው ወደ ኢስላም ከመግባቱ ጋር የሚስማማ በሆነ ጥሩ ትርጓሜ ባለው ስም መቀየሩ ይወደዳል፡፡

# > ተፈጥሯዊ ፈለጎች



> ኢስላም አንድ ሙስሊም ባማረ ግርማ ሞገስ ላይ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

## ተፈጥሯዊ ፈለግ ምን ማለት ነው?

ተፈጥሯዊ ፈለግ ማለት አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅን የፈጠረበት መገለጫዎች ማለት ነው፡፡ አንድ ሙስሊም እነኚህን ነገሮች በመፈፀሙ ሙሉዕ የሚሆንባቸው ናቸው፡፡ ይህን በማድረጉ ያማረ ገጽታና የተዋበ ግርማ ሞገስ ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም ኢስላም እነኚህን የውበትና የቁንጅና መሰረት የሆኑ ጉዳዮችን ልዩ ትኩረት በመስጠት አንድ ሙስሊም ውጫዊና ውስጣዊ ማንነቱም ያማረ እንዲያደርግ አዟል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አምስት ነገሮች ተፈጥሯዊ መዋቢያዎች ናቸው፤ መገረዝ፣ በብልት ዙሪያ የሚበቅልን ጸጉር መላጨት፣ ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ እና በብብት ስር ያለን ጸጉር መንጨት፡፡» (አል ቡኻሪ 5552/ ሙስሊም 257)

**ግርዛት፡** ይህ በብልት ጫፍ ላይ የሚገኝ ቆዳን ማስወገድ ወይም መቁረጥ ነው፡፡ በተለምዶ ይህ ቆዳ እንዲወገድ የሚደረገው በመጀመሪያዎቹ የአራስነት ቀናት ነው፡፡

ግርዛት ለወንዶች ተወዳጅና ከተፈጥሯዊ ፈለጎች መካካል ነው፡፡ ከጤናም አንጻር በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ነገር ግን ወደ ኢስላም ለመግባት መስፈርት አይደለም፡፡ አንድ ሙስሊም ፈርቶ ወይም በሌላ ምክንያት ባይገረዝ ወንጀለኛ አይሆንም፡፡

**ኢስቲሕዳድ፡** ይህ በብልት ዙሪያ ያለን ጸጉር መላጨት ወይም በፈለገው መንገድ ማስወገድ ነው፡፡

**ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር፡** ቀድሞ ቀመስን ባለበት መተው የተፈቀደ ቢሆንም የተወደደ ግን አይደለም፡፡ ነገር ግን አንድ ሙስሊም ቀድሞ ቀመሱን ከተወው እጅግ በጣም እስኪረዝም ድረስ መተው የለበትም ሊከረክመውና ሊያሳጥረው ይገባል፡፡

**ጺምን ማሳደግ፡** ኢስላም ጺም ማሳደግን ያበረታታል፡፡ ጺም የሚባለው በአገጭና በጉንጮች ላይ የሚበቅል ጸጉር ነው፡፡

ጺምን ማሳደግ ማለት ባለበት መተውና አለመላጨት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ መከተል ነው፡፡

**ጥፍርን ማስተካከል፡** አንድ ሙስሊም የጥፍሩን እድገትና ንጽህና ሊከታተል ይገባዋል፡፡ የቆሻሻ መከማቺያ እንዳይሆን በየጊዜው በማሳጠር ማስተካከል አለበት፡፡

**የብብትን ጸጉር መንጨት፡** አንድ ሙስሊም፣ በብብት ስር ያለውን ጸጉር በመንጨት ወይም በሌላ ማሰወገጃ ዘዴ በመጠቀም ማስወገድ አለበት፡፡ ይህም ከርሱ መጥፎ ጠረን እንዳይወጣ ለመከላከል ይረዳዋል፡፡



# የመጽሐፍ ማጠቃለያ




## ሁለተኛው እቅድህ እንዴት ነው ሚሆነው?

ይህን መጽሐፍ በማጠናቀቅህ ስለ ሃይማኖትህ ማወቅ የሚገበባህን የነገሮች የመጀመሪያ ምዕራፍ አጠናቀሃል ተማርከውንም በተግባር መተርጐምና በሕይወትህ ውስጥ አንድ አብይ ክስተት ማድረግ ይቀርሃል። በእርግጥ ተግባር ያልታከለበት እውቀት በትንሳኤው ቀን በባለቤቱ ላይ ክስረት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ያላገኘሽውን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዋቢነት ከተጠቀሱት መጽሐፍት ፈልገህ ማግኘትና ማወቅ አለብህ ።

ማንኛውም ሙስሊም በኢማን የሚፈልግበት ደረጃ ቢደርስ እንኳ ተጨማሪ መመራትን ይፈልጋል። ስሊዚህ ማንኛውም ሙስሊም በየቀኑ በሚሰግዷቸው ሰላቶች በሚደጋግማት የፋቲሃ ምዕራፍ ውስጥ የሚከተለው ተቀምጧል።«ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።»(አል- ፋቲሃ፡6)

## አላህንም የቻላችሁትን ያህል ፍሩት

በዚህ በጽሐፍም ሆነ በሌላ መጽሐፍት በሕይወትህ ስለሚያጋጥሙህ ክስተቶች በስፋት የሚያብራራ ምላሽ አታገኝም ስለዚህ የእውቀት ባለቤቶችን በመጠየቅ በተቻለህ አቅም በየአጋጣሚዎችና ሰፋ ባሉ እለታዊ ግንኙነቶች አላህን ለመፍራት በር ለሚከተለው የተከበረ አንቀጽ ተምሳሌት ለመሆን«አላህንም የቻላችሁትን ያህል ፍሩት።»

## ሙስሊም ወንድሞች ፈልግ ደወ ነርሱም ቅረብ።

ለሙስሊም ወንድሞችህ ቅርብ ሁን ኢስላማዊ ማዕከላትን መጐብኘትን አብዛ ከእርሱም ጋር ደስታም ሀዘንንም ተካፈል ከሰዎች ታላቁ የሆኑትን ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) መልካም ሰዎችን በመጐዳኘት ትዕግስት ያደርጉ ዘንድ አዝዟቸዋል።« ነፍስህንም እነዚያ ጌታቸውን ፊቱን(ውዴታውን) የሚሹ ኾነው በጧትም በማታም ከሚገዙት ጋር አስታግስ።» (አል፡ ካህፍ-28)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሙስሊሞች የመራቅን ተግባር አስጠንቅቀዋል።ምክያቱም የህ መሰሉ ተግባር ለጥመት ምክንያት ነው። ከመንጋ የተለች ለቀበሮ የመጋለጧ እድል ከፍተኛ እንደ ሆነ ነው።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡ በህብረት ግዴታ ይሆንባችሁ ከመንጋ የወጣችን (ፍየል)ቀበሮ እንደሚበላት ነው።(አል-ሙስተድሪክ 567)

ስለዚህ በአጠቃላይ  ወደ ሙስሊሞች ቅረብ ተጎዳኝ ምክንያቱም የመልካም ነገር የመመራትና የጽናት  ምክንያት ነው።

በጅምር መንገድ ላይ ያለና እጁን ይዞ ሊያጫውተው የሚፈልግ  ሰውስ ታዲያ እንዴት ሊሆን ነው።

አላህ ይስጥህ በሃይማኖቱ ላይም ያጽናህ ድብቆቹንና ግልጾቹን ፀጋዎች ያሟላልህ።



دليل المسلم الجديد

The New Muslim **Guide**

**Guide** du converti musulman

ለአዲስ ሰለምቴዎች መመሪያ

**Ang Gabay** Para sa Bagong Muslim

**Vodič** novom muslimanu

新改宗者のためのガイドブック

**La guida del nuovo musulmano**

**새내기 무슬림을 위한 지침서**

**Handbuch für den neuen Muslim**

नव मुस्लिम मार्गदर्शिका

**Guia para o novo muçulmano**

新穆斯林指南

**Руководство** для принявшего ислам

**Guía para el Nuevo Musulmán**


U.K -Birmingham
B11 1AR
Tel : +441214399144

K.S.A-Riyadh
Tel : +966112922240
Fax: +966112922205

www.newmuslimguide.com
www.guide-muslim.com
info@modern-guide.com

Amharic

እምነትህ



ንፅህናህ



ሠላትህ



ጾምህ



ምጽዋትህ (ዘካህ)



ሐጅህ



የንግድ ግንኙነትህ



ምግብህና መጠጥህ



ልብስህ



ቤተሰብህ



ስነ-ምግባርህ በኢስላም



አዲሱ ሕይወትህ



9 660000 012062
ISBN. 978-603-00-9103-4

## ለአዲስ ሰለምቴዎች መመሪያ

ይህ በስዕል የተደገፈው መመሪያ፥ መፅሐፍ አዲስ ለሰለምከው ወገን፥ ለሰዎች የተቸረ ፀጋ ስለሆነው ስለታላቁ ሃይማኖት እስልምና መግቢያና የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ዕውቀት ያስጨብጥሃል፡፡ ዘወትር በምትኗኗረውና አስፈላጊ በሆኑ የህይወት ጉዳዮችም ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

ለተለያዩ ጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጥሃል፡፡ በዙሪያህ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዴት መኗኗር እንዳለብህም ግልፅና ቀለል ባለ አኳኋን ያብራራልሃል፡፡ መፅሐፉ የሚያቀርብልህ መረጃዎች ውሱን፣ የሰነድ ማስረጃ ያላቸው ሲሆኑ መሠረታቸውም ቁርዓንና የነብዩ /ሰ.ዐ.ወ./ ሐዲሶች ናቸው፡፡

ይህ መፅሐፍ ዝርዝር የሆኑ ማብራሪያዎችን በማቅረቡ ረገድ ለንባብ ቀላል በሆነ አኳኋን ከመዘጋጀቱ ጎን ለጎን አንዳንድ በዕለቱ የሚገጥሙህ የህይወት ጉዳዮች ሸሪዓዊ ብይናቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለግህም በቂ የሆነ ማመሳከሪያ እንዲሆን ተደርጎም ተዘጋጅቷል፡፡

www.newmuslimguide.com

MODERN GUIDE
NEW MUSLIM GUIDE
Tel: +441214399144 uk@modern-guide.com